# የህይወት ታሪክ:
# ፍልሰት እና ፍቅር



ዮናስ ታደሰ

# የህይወት ታሪክ: ፍልሰት እና ፍቅር

## ዮናስ ታደሰ

መጋቢት 2015

# መግቢያ

ፋና ገብረሰንበት፣ ሜሮን  ዘለቀ እና ደረጀ ፈይሳ

## የሰዎች ከቦታ ቦታ ዝውውር በኢትዮጵያ ያለው ገጽታ

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ካሉና በርካታ ሰዎችን ወደ ሌላ ሀገር ከሚልኩ ሀገራት መካከል አንዷ ናት (RMMS 2014)[1]። አንዳንድ ሰዎች መነሻቸውን ከኢትዮጵያ ያደርጋሉ፤ ለሌሎች ደግሞ እንደመሸጋገሪያ እና መዳረሻ ሀገር ናት። በተለይ ደግሞ በእርስበርስ ግጭቶች ምክንያት ሀገራቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ለሚገደዱ የምስራቅ አፍሪካ ቀንድ እና የታላላቅ ሃይቆች (Great Lakes) ዙሪያ ሰዎቸ ኢትዮጵያ ዋነኛ መዳረሻ ሀገር ናት:: ኢትዮጵያ ለስድተኞች ጥበቃ ማድረግ የሚያስችል አሰራር ስላላት፣ ከ800 ሺ በላይ ስደተኞች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎቸ በተቋቋሙ 24 መጠለያ ስፍራዎች ይኖራሉ። ነገር ግን የተሻለ ህይወት ፍለጋ ሀገሪቱን ለቀው የሚወጡ ዜጎችን በተመለከተ የተቀናጀ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ መረጃ የለም፤ ትክክለኛው የኢትዮጵያውያን ዳያስፖራ ቁጥርም አይታወቅም። ሆኖም ከሁለት ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያዊያን በመካከለኛው ምስራቅ እስያ፣ በሰሜን አሜሪካና አውሮፓ እንደሚኖሩ ይገመታል። በዩናይትድ ስቴትስ ከሚኖሩና ከታችኛው ሰሃራ አካባቢ ከመጡ ሰዎች ጋር ሲነጻጸር ኢትዮጵያውያን ከናይጄሪያውያን ቀጥለው በብዛት የሁለተኛነት ደረጃን ይይዛሉ፤ በአውሮፓም በአምስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ (AFTCD-AFTQK, 2007)[2]።

የአለም ባንክ መረጃ እንደሚያሳየው በየጊዜው ሀገራቸውን ለቀው የሚወጡ ኢትዮጵያን መጠን በመቶኛ 0.7% ሲሆን ከሌሎች የታችኛው ሰሃራ አካባቢ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው። የተባበሩት መንግስታት ግምት የሚያሳየውም በሌሎች ሀገራት የሚወለዱ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በእጥፍ እያደገ መሆኑንና ሀገራቸውን ለቀው የሚወጡ ፍልሰተኞች ቁጥርም በፈረንጆቸ 2000 ዓ.ም. ከነበረው 443,926 በአስራ ሰባት አመታት ውስጥ ማለትመ በ2017 ዓ.ም. ወደ 800,879 አድጓል (UNDESA, 2017)[3]።

ባለፈው ግማሽ ምዕተ አመት ኢትዮጵያ የተለያዩ የፍልሰት ማዕበሎችን አስተናግዳለች። በንጉሰ ነገስቱ ጊዜም ከ1937 እስከ 1966 ዓ.ም. በነበሩት አመታት ውስን ቁጥር

1 RMMS. (2014). Blinded by Hope: Knowledge, Attitudes and Practices of Ethiopian migrants. Nairobi: Regional Mixed Migration Secretariat.

2 FTDC-AFTQK (2007) “Concept Note: Mobilizing the African Diaspora for Development”. *Capacity Development Action Plan Unit (AFTDC) and Operational Quality and Knowledge Service Department (AFTQK)*. Washington DC: African Diaspora Program, The World Bank.

3 UNDESA. (2017). Trends in International Migrant Stock: The 2017 Revision (United Nations database, POP/DB/MIG/Stock/Rev.2017). United Nations, Department of Economic and Social Affairs, Population Division.

ያላቸውና ለቤተመንግስቱ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ለከፍተኛ ትምህርት ከሀገር የወጡበት ጊዜ ነበር (Bariagaber 1997)[4]። እነዚህ በመንግስት ድጋፍ ለትምህርት የሚላኩ ሰዎች ራሳቸውን በእውቀት አበልጽገው ወደ ሀገራቸው በመመለስ ለኢትዮጵያ ወደ ዘመናዊነት በሚደረገው ጉዞ ላይ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸው ነበር። የንጉሱ አገዛዝ ከወደቀበት ከ1966 ዓ.ም. በኋላ ደግሞ በርካታ ኢትዮጵያውያን የአፍሪካ ቀንድ ጎረቤት ሀገራትን ተሻግረው ወደ ተለያዩ ሀገራት ተሰደዱ (Getachew 1991)[5]። ይህ ወቅት የወታደራዊውን የደርግ መንግስት ፖለቲካዊ ግድያና እስር ፈርተው ብዙዎች የተሰደዱበት ነው። ከ1966 እስከ 1983 ዓ.ም. በዘለቀው የደርግ አገዛዝ ህጋዊ በሆነ መንገድ ለተሻለ የስራ እድል ፍለጋ ወደ ሌላ ሀገራት መሔድ አይፈቀድም ነበር።

የደርግ አገዛዝ መውደቅ የሀገሪቱ ከቦታ ቦታ ዝውውር ህግ እና አተገባበር እንዲሻሻል እድል ፈጠረ። የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ደሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አዋጅ በአንቀጽ 32 ቁጥር 1 እንዲህ ይላል፤

> “ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነጻነት አለው።”

ሰዎች ሀገራቸውን ጥለው የሚወጡት በተለያዩ ግላዊ፣ ቤተሰባዊ፣ ማህብረሰባዊና መዋቅራዊ በሆኑ ምክንያቶች ነው። አብዛኛውን ጊዜ ኢትዮጵያውያን ከሀገር ለመውጣታቸው እንደምክንያት የሚያቀርቡት ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶችን ነው። ምንም እንኳን ኢትዮጲያ ከ1995 እስከ 2011 ዓ.ም. በአማካይ 10.5 በመቶ ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ብታስመዘግብም፤ በአለም አቀፉ የሰብዓዊ ልማት አመላካች መረጃ መሰረት አሁንም ከአለማችን 189 ደሃ ሀገሮች ተርታ ተመድባ በ163ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች (UNDP 2018)[6]። ይሔው አመላካች መረጃ 22 ሚሊዮን የሚሆኑ ኢትዮጵያዊያን በከፋ ድህነት ውስጥ እንደሚኖሩ ያሳያል። በዚያ ላይ የህዝብ ቁጥር እድገቱ መፋጠን በየአመቱ የስራ ሃይሉን ለሚቀላቀሉ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ሰዎች ስራ የመፍጠር ሂደቱን ፈታኝ አድርጎታል። ከዚህም ሌላ ተደራራቢ መዋቅራዊ ችግሮችን ያስከትላል፤ ለምሳሌ ጠንካራ የሆነ ፍልሰትን የሚያበረታታ ባህል፣ የትምህርት ጥራት መዳደል፣ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች፣ ደካማ ህዝባዊ አግልግሎቶች፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ አለመረጋጋቶችና አስተዳድራዊ ችግሮች ይጠቀሳሉ። በማህበረሰብ ውስጥ ከሚታዩት ምክንያቶች መካከል ደግሞ

4 Bariagaber, A. 1997. Political Violence and the Uprooted in the Horn of Africa: A Study of Refugee Flows from Ethiopia. Journal of Black Studies 28 (1): 26–42.

5 Getachew, M. 1991. The Ethiopian Revolution of 1974 and the Exodus of Ethiopia’s Trained Human Resources. New York: Edwin Mellen Press.

6 UNDP 2018a Ethiopia: Briefing note for countries on the 2018 Statistical Update. Retrieved from http://hdr.undp.org/sites/all/themes/hdr_theme/country-notes/ETH.pdf. 2018b Ethiopia: National Human Development Report 2018.

በተለይ ወጣቱ ለገጠር ኑሮ ፍላጎት ማጣቱና በከተሜ ብልጭልጭ ህይወት መማለሉ አንደኛው ነው። በዚያም ላይ ሰዎችን በህገወጥ መንገድ ከሀገር የሚያስኮበልሉ ደላሎች በአቅራቢያ መኖራቸውና ይህንን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ወይም በድብቅ ግንኙነት ለመመስረት የሚያስችሉ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች መኖሩ ሌላኛው ፈተና ነው።

የተሻለ ህይወት ፍለጋ በህጋዊ መንገድ ከሀገር ለመውጣት ፈጽሞ አማራጭ ሲጠፋ ወይም እድሉ ሲመናመን ኢትዮጵያውያን ኢ-መደበኛ የሆነውንና አደገኛውን መንገድ ይመርጣሉ። ይህ መንገድ ለህገወጥ አዘዋዋሪዎች ስለሚያጋልጣቸው፤ በሀገር ውስጥም ሆነ የሌሎችን ሀገራት ድንበር ለመሻገር ሲሉ ህይወታቸውን አደጋ ላይ ይጥላሉ። ኢትዮጵያውያን ፍልሰተኞች በዋናነት ሶስት ከሀገር የመውጫ በሮችን ይጠቀማሉ። አንድኛው በስተምስራቅ በኩል ያለውና በየመን አድርጎ ወደ መካከለኛው ምስራቅና ከዚያም ባሻገር ወዳሉ ሀገራት የሚመራው ነው። ሁለተኛው ደግሞ በስተሰሜን በኩል በሱዳን ወይም በሊቢያ አድርጎ የማዕከላዊ ሜዲትራኒያን መውጫ መንገድን ተከትሎ ወደ አውሮፓ የሚያመራው ሲሆን፤ በዚሁ መስመር በግብጽ፣ ሲናይ በረሃ አድርገው ወደ እስራኢል ለመግባት ይሔዱበታል። ሶስትኛው የደቡብ መውጫ በር ሲሆን መተላለፊያው በኬንያ በኩል ወደ ታንዛኒያ በማቅናት ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመግባት የሚሔዱበት መንገድ ነው። ከነዚህ መውጫ አቅጣጫዎች ጎን ለጎን አብዛኛው ዝውውር የሚደረገው በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ነው።

ሰዎች የተሻለ የስራ እድል ፍለጋ ወደ ምስራቅ አቅጣጫ የሚያደርጉትን ዝውውር በተመለከተ በርካታ ጥናቶች ተደርገዋል። በዚህ በምስራቁ አቅጣጫ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሴቶች ስራ ፍለጋ ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚያደርጉት ጉዞ ረጅም ጊዜያትን ያስቆጠረ ሲሆን በሶስት አይነት መንገድ ከሀገር እንደሚወጡ ጥናቶች ያሳያሉ። የመጀመሪያው ኢትዮጵያ ውስጥ የግል ስራና ሰራተኛ አገናኝ ደርጅት ወይም ኤጀንሲ ሆነው በተመዘገቡና ፈቃድ ባላቸው ደርጆቶች በኩል በህጋዊ መንገድ የሚደረገው የጉዞ ዝግጅት ነው። የቀጣሪ አስቀጣሪ ኤጀንሲዎች ስራና ሰራተኛን ከማገናኘት ባሻገር፣ ቀጣሪዎች ለሰራተኞቻቸው የመመለሻ የአውሮፕላን ቲኬት፣ ቪዛ፣ ኢንሹራንስ፣ የስራ ፈቃድ እና ህጋዊ የቅጥር ኮንትራት ማመቻቸታቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። ተቀጣሪ ተጓዦች ደግሞ በበኩላቸው ፓስፖርት ማውጣትና ሙሉ የጤና ምርመራ ማድርግ አለባቸው። ሁለተኛው መንገድ በግላቸው ጥረት የስራ እድል የሚያገኙ ሰዎችን የሚመለከት ሲሆን እነዚህ ሰዎች የስራ ቅጥርውላቸውን በሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስመዝግብ ይኖርባቸዋል። ሶስተኛውና ብዙዎች የሚጠቀሙበት መንገድ በደላሎች የሚመቻቸው ጉዞ ነው። በ2006 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መንግስት ወደ መካከለኛው ምስራቅ በሚደረግ ጉዞ ላይ ጊዜያዊ እገዳ በመጣሉ የተነሳ በርካቶች ደላሎችን ተጠቅመው መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከሀገር ወጥተዋል።

ሁለተኛውና ኢትዮጵያውያን በስተሰሜን በኩል ወደ አውሮፓ የሚያደርጉት ጉዞ ረጅሙና አደገኛው ጉዞ ነው። ከምስራቁ አቅጣጫ በተለየ መልኩ ይሔኛው በስተሰሜን ያለው መንገድ በወንድ ስደተኞች ይዘወተራል። ስደተኞቹ ሊቢያ ለመድረስ ከዚያም ጉዞውን ወደ አውሮፓ ለማቅናት ተከታታይ የመሸጋገሪያ ቦታዎችን ማለፍ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ መንገድ ለሚያልፉ ስደተኞች ዋነኛዋ መሸጋገሪያ ሀገር ሱዳን ናት። ከኢትዮጵያ የሚነሱ ሰዎች ሱዳን፣ ካርቱም ለመድረስ ሶስት የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማሉ። አንዳንዶች ከአዲስ አበባ ወደ መተማ አድርገው ሱዳን ድንበር ሲጓዙ፤ ሌሎች ደግሞ በሁለተኛው መንገድ ከአዲስ አበባ ወደ ሁመራ ከዛም በሱዳንና ኤርትራ ድንበር በኩል ያመራሉ፤ ወይም ደግሞ በቀጥታ ከአዲስ አበባ ወደ ካርቱም በአውሮፕላን ይበራሉ።

ሱዳን ከደረሱ በኋዋላ ወደ ሊቢያ ለማቋረጥ በዳርፉር በኩል፣ ወይም በሰሜን ሱዳን ዶንጎላ በኩል፣ አለዚያም ወደ ቻድ በሚያመራው መውጫ ጉዞዋቸውን ይቀጥላሉ። ካርቱም በሱዳን ዋነኛዋ የስደተኞች መተላለፊያ ቦታ ናት። አብዛኛውን ጊዜ ከጎረቤት ሀገር የሚመጡ ተጓዦች በከተማዋ ቆይተው አነስተኛ ስራዎችን በመስራት ገንዝብ ለመቆጠብና ቀጣዩን የጉዟቸውን ወጪ ለመክፈል ይዘጋጁባታል። ቀጣዩን ወደ ሊቢያ የሚደረገውን ጉዞ የሚያመቻቹላቸው ደላሎችን የሚያገኙትም እዚሁ ካርቱም ውስጥ ነው። ሊቢያ ከደረሱ በኋላ ደግሞ ማልታ ወይም ወደ ላምፔዱሳ ጣልያን ለመድርስ ለጀልባ ጉዞ ይከፍላሉ። ስደተኞቹ ጣልያንን መዳረሻ ማድረግ ይመርጣሉ፤ ምክንያቱም ጣልያን በውል የተቀናጀ ህገወጥ ስደተኞችን በእስር የምታቆይበት ፖሊሲ ስለሌላት እና ጣልያን ምድር ላይ ካረፉ ወደ ሌሎች አውሮፓ ሀገራት መጓዝ ቀላል ስለሚሆንላቸው ነው።

ወደ ደቡብ የሚደረገው ጉዞ ገና ከሀገር ሳይወጣ ጀምሮ የተለያዩ መሸጋገሪያ ቦታዎች አሉት። ተጓዦች የኬንያን ድንበር ከማቋረጣቸው በፊት በዲላ እና ሞያሌ ከተሞች ያርፋሉ። ከዚያም የኬንያን ድንበር አቋርጠው ወደ ታንዛኒያ እና ማላዊ ያቀናሉ:: እንደየሁኔታውና የአሸጋጋሪ ደላሎች ምርጫ በሞዛምቢክ አለዚያም በዚምባብዌ አድርገው ወደ ደቡብ አፍሪካ ይገሰግሳሉ። ይህ መጽሃፍ ይህንን ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚወስደውን መንገድ ተከትሎ የተሻለ ህይወት ፍለጋ ከቤቱ የወጣ ወጣት የሚያደርገውን ፈታኝ ጉዞ ፍንትው አድርጎ ያሳያል።

## በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት መካከል የሚደረግ ፍልሰት

የህዝብ እንቅስቃሴ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የነበረ እና ወደፊትም የሚኖር ነው:: የ2019 የተባበሩት መንግስታት ጥናት እንደሚያሳየው የፍልሰተኞች ቁጥር 272 ሚሊየን ደርሷል:: ይህ ደግሞ ከ2010 ዓ.ም ጋር በንጽጽር ሲታይ የ51 ሚሊየን ብልጫ አሳይቷል::

በአሁኑ ወቅት የፍልሰተኞች ቁጥር በመቶኛ ሲሰላ ከአጠቃላይ የዓለምን ህዝብ ቀጥር 3.5 በመቶ ይደርሳል።

በሰው ልጅ ታሪክ ፍልሰት ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ሲካሄድ ኖሯል። የፍልሰት ቀጠና አከፋፈሉ ውስብስብነት እንደተጠበቀ ሆኖ 4 አይነት የፍልሰት ቀጠናዎች አሉ:- 1ኛ ካደጉት ሀገራት በማደግ ላይ ወዳሉት ሀገራት የሚደረግ ፍልሰት (በእንግሊዘኛው North-South Migration)፤ 2ተኛ በማደግ ላይ ካሉት ሀገራት ወደ አደጉት ሀገራት የሚደረግ ፍልሰት (በእንግሊዘኛው South-North Migration)፤ 3ተኛ በአንፃራዊ ልዩነት ባላቸው በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት መካከል የሚረግ ፍልሰት (በእንግሊዘኛው South-South Migration)፤ እና 4ተኛ ባደጉ ሀገራት መካከል የሚደረገው (በእንግሊዘኛው North-North Migration) ናቸው።

እስከ 2ተኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በዓለም ላይ የነበረው ፍልሰት በአብዛኛው ከአደጉት ወደ ማደግ ላይ ወዳሉት ሀገራት ነበር የሚደረገው። ታሪካዊ ዳራው የቀኝ ግዛት ተንሰራፍቶ የነበረት ሲሆን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍል አባላት ከቅኝ ገዥ ሀገራት ወደ ቅኝ ተገዥ በአፍሪካ እስያ ላቲን አሜሪካ ወደሚገኙ ሀገራት በተለያየ ምክንያት ተሰደዋል። ገሚሱ አዲስ የተቋቋሙት ቅኝ ግዛቶች ለማስተዳደር ሲሆን ሌላው ደግሞ ምቹ በታዎችን ፈልገው ለመስፈር ነበር። በአፍሪካ ይህ አይነት ፍልሰት ወደ በደቡብ አፍሪካ እና ኬኒያ በስፋት ታይቷል። በተለምዶ የበርሊን ስምምነት ከሚባለው እ.ኤ.አ 1889 ከመፈረሙ በፊት ፍልሰት በስፋት የሚዘወተረው በአውሮፓውያን ሲሆን ጉዞውም በአብዛኛው ወደ አሜሪካ፣ ካናዳ አውስትራሊያ እና ኒውዚላንድ ነበር። በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው የእነዚህ ሀገራት ነዋሪ እንግሊዚኛ ተናገሪ የሆነበት ምክንያት ከዚህ ከእንግሊዞች የቅኝ ግዛት ታሪክ ጋር ይያያዛል። ከዛም አስከትሎ በስፋት ከቅኝ ግዛት ጋር የተያያዘ ስደት ወደ አፍሪካ እና እስያ ቀጠለ።

የፀረ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ በጊዜ ሒደት አዳዲስ ነፃ ሀገራትን ወለደ። በአፍሪካ የድህረ ቅኝ ግዛት መንግስታት በአብዛኛው እንደፈረንጆቹ አቆጣር በ1960ዎቹ እውን የሆኑ ሲሆን የቀድሞ ቅኝ ግዛቶች ገሚሱ በህዝባዊ ትግል ተገልብጦ ሌላው ደግሞ የነፃነት አይቀሪነትን በመገንዘብ የግዳቸውን ለነዚህ መንግስታት እውቅና ሰጡ። ብዙም ሳይቆዩ አዲስ የቅኝ ግዛት የግንኙነት መስክ ዘርግተው (neo-colonialism) የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቻቸውን በተጽዕኖ ስር አስገቧቸው። ይህንንም ተከትሎ አዲስ ፍልሰት እንቅስቃሴ በማደግ ላይ ካሉት ወደ አደጉት ሀገራት በስፋት ተሰራጨ። ነፃነትን ተከትሎ የተከሰተው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እና ግጭት ተጨማሪ ገፊ ምክንያት ሆኖ ፍልሰቱን አስፋፋው። ባደጉ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት መካከል ያለው ስር የሰደደ መበላለጥ እና ይህን ተከትሎ ህይወትን ለመቀየር ሰዎች በተለይ ወጣቶች በስፋት ወደ አደጉ ሀገራት

ለመፍለስ ምክንያት ሆኗል። ይህ የፍልሰት አይነት ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚደረግ ፍልሰት በመባል የሚታወቅ ሲሆን በብዛት ዓለም አቀፋዊ የጥናት፣ የሚዲያ እና የፖሊሲ ሽፋን ያገኘው ይኸው (South North Migration or SNM) ተብሎ የሚጠራው የፍልሰት ዓይነት ነው። መጠኑ ያነሰ ይሁን እንጂ ባደጉት ሀገራት መካከልም የሚደረግ ፍልሰት አለ። ይህ በአብዛኛው ባለሙያተኞችን (skilled labour migration) ያካተተ ሲሆን የካፒታሊዝምን እድገት እና ግሎባላይዜሽንን ተከትሎ የተከሰተ የፍልሰት አይነት ነው። በተወሰነ ደረጃ በተመሳሳይ ሁኔታ ብዙ ሙያተኞች ካደጉት ሀገራት ወደ በማደግ ላይ ወዳሉት ፈልሰው ይሰራሉ።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ትኩረት ያገኘው የፍልሰት አይነት በማደግ ላይ ባሉት ሀገራት መካከል የሚደረግ ነው። ይህ የፍልሰት አይነት በእንግሊዘኛ ምህፃረ ቃል SSM ወይም South-South Migration ተብሎ ይጠራል። ደቡብ የሚለው ቃል በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ያመለክታል፣ የሰሜን ሀገራት ወይም ያደጉ ሀገራት የሚለው ቃል ተቃራኒ ቃል ነው። በዚህም ምክንያት የፍልሰት ሂደቱ ከደቡብ ወደ ደቡብ የሚደረግ ፍልሰት ይባላል። ከደቡብ ወደ ደቡብ የሚደረግ ፍልሰት (SSM) እስከ 82 ሚሊየን ያህል ሰው የሚሳተፍበት ሲሆን ይህም ከአጠቃላይ የፍልሰት መጠኑ 36 በመቶውን ይይዛል።[7] የመጠኑ መብዛት ብቻ ሳይሆን የደቡብ ደቡብ ፍልሰተኞች የመጡበትንም ሆነ የሚሄዱበትን ሀገራት ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በእጅጉ የማሻሻል ሀይል አላቸው። ይሁን እንጂ እንደመጠኑ መብዛት እና እንደፈርጀ ብዙ ተጽዕኖ ፈጣሪነቱ የደቡብ ደቡብ ፍልሰት ተገቢውን ትኩረት ተነፍጎ ቆይቷል። ዓለም አቀፍ የመገናኛ ብዙሀን እና የልማት ድርጅቶች በስፋት እና በጥልቀት የሚከታተሉት ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚደረገውን የፍልሰት ዓይነት ነው።

ዘወትር በቴሌቪዥን መስኮቶቻችን ምን ያህል ፍልሰተኞች አውሮፓን እና አሜሪካን እንዳጥለቀለቁ ይነገረናል። በተለይ ከ2015 እ.ኤ.አ ጀምሮ የፍልሰት ቀውስ (migration crisis) በአውሮፓ የሚል ትርክት በስፋት ይነገራል። ይህ ግን ከእውነታው በእጅጉ የራቀ ነው።[8] ከላይ እንደተጠቀሰው የ1/3 ተኛውን ድርሻ የሚይዘው የፍልሰት አይነት SSM ነው። ይህ ማለት አብዛኛው የህዝብ እንቅስቃሴ የሚደገው በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት መካከል ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች ቁጥሩ በእጅጉ ይጨምራል። አፍሪካን እንደአብነት ብንወስድ ከአህጉሩ የሚነሱ 50 በመቶ ፍልሰተኞች በአፍሪካ ውስጥ ይዘዋወራሉ።[9]

7 https://www.oecd.org/development/migration-development/south-south-migration.htm
8 https://www.theglobeandmail.com/news/world/europes-migrant-crisis-eight-reasons-its-not-what-youthink/article26194675/
9 https://www.friendsofeurope.org/wp/wp-content/uploads/2022/01/AEF_Summit_African-Migrations.pdf

በአንዳንድ ንዑስ አካባቢዎች ለምሳሌ በምዕራብ አፍሪካ 64 በመቶ ፍልሰተኞች በዛው ምዕራብ አፍሪካ ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። ይህ ቁጥር በ1990ዎቹ ወደ 80 በመቶ ደርሶ ነበር። ቁጥሩ የቀነሰው ወደ አደጉ ሀገራት የሚረግ ፍልሰት ጨምሮ ሳይሆን በአፍሪካ ውስጥ አዳዲስ መዳረሻዎች፣ እንደጋቦን እና ኢኳቶሪያል ጊኒ አይነት፣ መከፈታቸው ነው። ምናልባትም ብቸኛው የአፍሪካ አካባቢ በስፋት ከአፍሪካ ውጪ ፍልሰት የሚደረግበት ሰሜን አፍሪካ ሲሆን ይህም ቢሆን ወደ አውሮፓ ወይም ወደ አሜሪካ ሳይሆን ወደ መካከለኛው ምስራቅ የሚደረግ ፍልሰት ነው። ይህ ደግሞ በSSM ውስጥ ይካተታል።

የፍልሰት ጥናት/ታሪክ በአብዛኛው የሚያጠነጥነው በአንድ አይነት ማለትም ከደቡብ ወደ ሰሜን በሚደረገው ፍለሰት ላይ በመሆኑ የደቡብ ደቡብ ፍልሰት ትኩረት እንዳያገኝ አድርጎታል። አብዛኛው በፍልሰት ላይ የሚደረጉ ጥናቶች ከሰሜን ሀገራት እና በሰሜን ሙሁራን መሆኑ በፍልሰት ሂደት ላይ የተዛባ መረጃ እና መረዳትን እንዲያኖሩ አድርጓል። ይህ ደግሞ የፖሊሲ እንድምታ አለው። 1ኛው ከአፍሪካ ውጭ የሚደረጉት ፍልሰቶች ህገወጥ እና ኢ-መደበኛ የሚል ስያሜ እንዲያገኙ አድርጓቸዋል። የሰሜን ሀገራት የፖሊሲ ማጠንጠኛው በዚሁ ብየና ዙሪያ ነው። ይህ አካሄድ በተለይ በአውሮፓ ህብረት ዘንድ ጎልቶ የሚታይ ሲሆን የልማት አጋርነታቸው ስደተኞች በብዛት የሚመጡባቸውን ሀገራት በመደገፍ ፍልሰትን ማስቀረት ይቻላል የሚለው መሰረታዊ እሳቤ ላይ የተመሰረተ ነው። እንደፖሊሲ እና የራስን ብሄራዊ ጥቅም ከማስፈጸም/ከማስጠበቅ አኳያ እንዲህ ያለው እሳቤና አካሄድ በራሱ ችግር የለውም። ችግር የሚሆነው ከዚህ ባለፈ መልኩ መተላለፊያ ናቸው በሚባሉት የአፍሪካ ሀገራት ላይ ተጽዕኖ በማድረግ አጠቃላዩን በአፍሪካ ውስጥ የሚደረገውን የአፍሪካ ህብረት እና የአካባቢ ስብሰቦች የሚደግፉትን የህዝብ እንቅስቃሴ ያውካል። ለዚህም ዓላማ ማስፈጸሚያ ለምሳሌ አውሮፓ ህብረት ኒጀርን ከምዕራብ አፍሪካ እና ሱዳንን ከምስራቅ አፍሪካ መርጠው ስደት ከነዚህ ሀገራት አልፎ እንዳይሄድ የተለያዩ ዳረጎቶችን በመጠቀም በሀገራቱ መንግስታት ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋሉ።

ሌላው በደቡብ ሰሜን ላይ የሚደረገው ትኩረት በዚሁ የፍልሰት አይነት ላይ ብቻ ተገድቦ እንዲቀር አድርጎታል። ፍልሰተኞች ሰርተው ወደ መጡበት ሀገራት የሚልኩትን ገንዘብ በተመለከተ ለምሳሌ ከልማት ጋር ያለው ትስስር ትኩረት ያገኘው በሰሜን ሀገራት ባሉ ፍልሰተኞች ነው። የደቡብ ደቡብ ፍልሰት ያለው የልማት አቅም እና ለተባበሩት መንግስታት ቀጣይ የልማት ግቦች (Sustainable Development Goals, SDGs) ያለው ፋይዳ እውቅና የተሰጠው ቢሆንም ግን ሙሉ አቅሙን እስከ አሁን መጠቀም አልተቻለም። ይህም የሆነበት ምክንያት ይህ የፍልሰት ቀጠና ተገቢውን ትኩረት አለማግኘቱ ነው። ይህንን ክፍተት ለመሙላት የደቡብ ደቡብ ስደት (SSM) ላይ ትኩረት ያደረጉ አዳዲስ ጥናቶች እየተደረጉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ፍልሰት ለልማት እና እኩልነት

(Migration for Development and Equality, MIDEQ) የተሰኘው አለማቀፋዊ ጥናት SSM ላይ ትኩረት በማድረግ ትልቁ የጥናት ፕሮጀክት ነው።

በ12 ሀገራት እና በ6 የፍልሰት ኮሪደሮች ሲሆን እነዚህም ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ፣ ከቡርኪና ፋሶ ወደ ኮትዲቫር፣ ከቻይና ወደ ጋና፣ ከግብጽ ወደ ጆርዳን፣ ከኔፓል ወደ ማሌዥያ እና ከሄይቲ ወደ ብራዚል የሚደረጉ የፍልሰት እንቅስቃሴዎች ናቸው።[10] MIDEQን የተለየ የSSM ጥናት የሚያደርገው ጆግራፊያዊ ትኩረቱ ፍልሰት በደቡብ ሀገራት መሀከል ላይ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጥናቱን በሃላፊነት እና በብዛት የሚያካሄዱት ምሁራን ከደቡብ ሀገራት የተገኙ መሆናቸው ነው። ይህ ደግሞ በፍልሰት ዙሪያ የሚደረገውን የእውቀት ምርት ይበልጥ ደቡባዊ ቃና እንዲኖረው ያደርጋል። ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ አፍሪካ በሚደረገው የፍልሰት ጥናት ደግሞ የእውቀት አምራቾችን አድማስ በማስፋት ፍልሰተኞቹ እራሳቸው በቀጥታ የእውቀት አምራች እንዲሆን ያበረታታል፣ ያመቻቻል። የዚህ መጽሀፍ ጥንስስ እና ዓላማ ከዚህ አዲስ የእውቀት ምርት ዘይቤ ጋር ይያያዛል።

## ስለ ማስታወሻው ጥንስስ

የእዚህን መፅሀፍ ደራሲ ያገኘነው በሐምሌ 2013 በሆሳዕና ከተማ ነበር። ከኢትዮጰያ [በተለይ ከሀድያ] ወደ ደቡብ አፍሪካ ያለውን የፍልሰት ሁኔታ ማጥናት የጀመርነው በታህሳስ 2012 ነበር። ሐሳባችን ተከታታይ የሆኑ የመስክ ጥናቶችን ማድረግ ቢሆንም መጋቢት 2012 ዓ.ም. ላይ ከተደረገው አጭር የመስክ ቆይታ በኋላ የ COVID-19 ወረርሽኝ መከሰት እና ተያያዥ ክልከላዎች እና የምርምር ሰነ ምግባር እሳቤዎች ስራችንን ቀዝቀዝ እንድናደርግ አስገድደውን ነበር። ስለዚህ በ2013 ዓ.ም ረዘም ያለ የመስክ ስራ ስናከናውን በደስታ እና ያመለጠንን ጊዜ ለማካካስ በማለም ነበር።

በሆሳዕና እና ሌሎች የሀድያ ዞን ከተሞች/በኖሻ፣ ጃጁራ እና ፎንቆ/ በዛ ያሉ ሰዎችን በግልም ሆነ በጋራ ለማነጋገር ዕድሉን አግኝተን ነበር። የፍልሰት መጥፎ ጎኖች ቢኖሩም [ለምሳሌ ሞት፣ አካል መጉደል፣ የትዳር መፍረስ፣ የቤተሰብ መበተን] ጥናቱን በጀመርንበት ወቅት በብዛት ያገኘናቸው የፍልሰትን መልካም ጎኖች የሚያሳዩ ነበሩ። አብዛኞቹ እንዳሰቡት ደቡብ አፍሪካ ደርሰው፣ የተለያዩ ስራዎችን ሰርተው ገንዘብ አጠራቅመው ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው በተለያዩ መስኮች መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስሰው ነበር።

ከተወሰነ ቆይታ በኋላ የፍልሰት ሙከራቸው ያለተሳካላቸውን ሰዎች ማፈላለግ ጀመርን። በዚህም ጊዜ የምናገኛቸው አብዛኞቹ ሰዎች በኢትዮጵያ እና ደቡብ አፍሪካ መካከል ባሉ ሃገሮች ተይዘው የተወሰነ ጊዜ በእስር አሳልፈው ወደ ሀገር ቤት የተመለሱ ነበሩ። በዚህ የምልሰት ጉዞ የአለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (IOM) የሙያ ስልጠና፣ የገንዘብ እና

10 https://www.mideq.org/en/

የመስሪያ ዕቃ ድጋፍ ሲያደርግ ፣ የመንግስት አካላት ደግሞ የመታወቂያ እና ሌሎች ፍቃዶችና በማመቻቸት በረራው እንዲሳካ ያደርጋሉ።

በዚህ ሙከራችን ያገኘናቸው አብዛኞቹ ተመላሾች ተመልሶ መቋቋም ያልቻሉ እና ከባድ የኑሮ ሁኔታ እያሳለፉ ያሉ ናቸው። በአንድ እድለኛ ቀን አንድ የጥናት ተሳታፊ ስለ አንድ ተመላሽ የተለየ ታሪክ ነገረን። ግለሰቡ በፍልሰት ሙከራው ወቅት በታንዛኒያ ታስሮ ወደ 3 ዓመት አሳልፎ ሲመለስ ደግሞ የተሳካለት የfurniture [እንጨት ስራ] ላይ እንዳለ ተነገረን። እኛም ያለበትን አፈላልገን ቀጥሎ ባለው ቅዳሜ ጠዋት ላይ በመስሪያ እና መሸጫ በታው አገኘው። እንደነገረን አምስት ለሚሆኑ ወጣቶች የስራ እድል ፈጥሮ እና በመቶ ሺዎች ብር ሊያወጡ የሚችሉ የተለያዩ ስራ ማሽኖች፣ የስራ ግብዓቶች እና ያለቁ/ ለባለቤት ለመስጠት ወይም ለሽያጭ የቀረቡ/ ዕቃዎችን አይተን በስራው ጥራት እና በትትርናው ተደሰትን።

ወዲያውኑ ቀላ ብሎ ቸምቸም ያለ ፂም ያሳደገው እና ፊቱ ምቾት የተላበሰ ወጣት ከእነ ስራ ቱታው የጀመረውን ስራ አቋርጦ ወደ እኛ መጣ። የመጣንበትን ጉዳይ ስንነግረውም የተባለው ከፍልሰት ተመላሽ እሱ መሆኑን ነግሮን፣ ስሙ ጆኒ (Johny) እንደሆነ ተዋውቆን ሰለ ስራው እና ስለ ፍልሰት እና እስር አጋጣሚው በሰፊው አጫወተን። ለዛ ያለውን ገለፃውን እና ጨዋታውን እያጣጣምን ሳለን ነው በእስር ላይ የፃፈው ማስታወሻ እንዳለው ጣል ያደረገልን።

ወደ ማረፊያችን ተመልሰን ስለነበረን ውሎ ስንወያይ የቀመረው የፍልሰት እና እስር ቤት ቆይታ ማስታወሻ ምናልባትም ብቸኛው ሊሆን እንደሚችል ገመትን። እንደአለመታደል ሆኖ በሀገራችን ማስታወሻ መያዝ እና በስነስርዓቱ ሰንዶ ለመጪው ትውልድ መማሪያ ለማድረግ ማስቀመጥ በታላላቅ ሰዎቹም የተለመደ አይደለም፤ እንኳን በአማካይ ኢትዮጰያዊው። በዚህ ላይ ደግሞ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲኮን እና ያለው የትምህርት ቆይታ አነስ ያለ ሲሆን ተጠባቂነቱ ይቀንሳል። ስለዚህ የጆኒ ማስታወሻ በራሱ አንድ ጎላ ያለ አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል የሚል ሃሳብ ጫረብን።

በተጨማሪም የጆኒ ማስታወሻ በፍልሰት ጥናት ላይ የሚኖረው አስተዋጽዎ ይኖራል ብለን አሰብን። በፍልሰት ጥናት፣ በሌሎችም ማህበረዊ ሳይንስ መስኮች እንደሚሆነው ሁሉ፣ ዋነኛው የመረጃ ምንጭ በፍልሰት የተሳተፉ ግለሰቦች፣ የፍልሰት አመቻቾች እና በመንግስት በኩል ሆኖ የመቆጣጠር እና የመከታተል ስራ የሚሰሩ ናቸው። አጥኚው የእነዚህን ከዋኞች ልምድ፣ ዕውቀት እና ሀሳብ በተለያዩ የጥናት ዘዴዎች በመሰብሰብ እና ከዚህ በፊት ከተቀመሩ የዘርፉ ዕውቀቶች እና ንዑስ ሃሳቦች ጋር አሰናድቶ የጥናቱን ውጤት ያቀርባል። በዚህ ሂደት አጥኚው የጥናቱ ውጤት ባለቤት ሆኖ የጥናቱ መረጃ ምንጮች ወደ ግርጌ ይደበቃሉ።

የጆኒ ማስታወሻ ይህንን የሃይል ሚዛን መዛባት በማስተካከል የመረጃው እና የልምዱ ባለቤት፣ በእኛ ሁኔታ የፍልሰት ተሳታፊው ዕራሱ፣ የዕውቀት ምንጬ ይሆናል። ይህም ዕውቀት እና የዕውቀት ማመንጨት/ ማጎልበት ሂደት ላይ ያሉ መስተጓጎሎችን በመቀነስ ዕውቀትን የበለጠ በሰሪው የሚመረት እና የሚደረስ ለማድረግ ያግዛል።

ሌላው የማስታወሻው ጠቃሚ ነጥብ ሆኖ ያገኘነው የፍልሰት ተሳታፊ ሰዎችን ስሜት በፍልሰት ሁኔታ ላይ እንዳለ ይዞ መገኘቱ ነው። በቃለመጠይቅ ወይም በሌላ የጥናት ዘዴ ሰዎች ሲጠየቁ የሚያጋሩን እውነታቸው በትውስታ ላይ የተመሰረተ ነው። በትውስታ ደግሞ መርጦ ለማስታወስ ወይም ለመርሳት ብሎም የተመረጡ ሁነቶችን እና ስሜቶችን ማጉላት ይኖራል። የጆኒ ማስታወሻ በጽሁፍ ካሰፈራቸው ነጥቦች በተጨማሪም በስዕል አስደግፎ ያጋጠመውን ገጠመኞች እና የተሰማውን ስሜቶች ለማስፈር መሞከር ደግሞ ሌላው ተጨማሪ በኋላ ነበር።

በመጨረሻም መንግስት፣ ሀገር በቀልም ሆነ አለም አቀፍ ተቋማት ፍልሰትን ለማስቀረት፣ ለመቀነስ እና አዲስ ፈላሾችን ለመቀነስ ከሚጠቀሙባቸው ዋነኛ መንገዶች አንዱ የግንዛቤ ማስጨበጥ ነው። የግንዛቤ ማስጨበጥ ክንውኖችም አብዛኛውን ጊዜ በባለሙያዎች [ከአካባቢው የመንግስት ቢሮ ወይም መንግስታዊ ካልሆኑ ቢሮዎች ወይንም ከአዲስ አበባ] በመጡ ባለሙያዎች የሚሰጥ ነው:: ይህም ወደፊት ሊፈልሱ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡትን ወጣቶችን እንደተቀባይ እና አላዊቂ ነው የሚወስደው:: በእኛ እሳቤ እንደጆኒ አይነት ማስታወሻዎች በብዛት ቢታተሙ ወደፊት ወደ ደቡብ አፍሪካ በመደበኛ ባልሆነ መንገድ ለመፍለስ የሚያሰቡ ወጣቶች የጉዞውን ሁኔታ ከአቻቸው እና ያንኑ ሁኔታ ካለፈው ለመማር ያግዛቸዋል።

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ነጥቦች ላይ በጥልቀት ከተወያየን በኋላ፣ የጆኒን ማስታወሻ በስነ ስርዓቱ አሁን በምታዩት መልክ ማሳተም እንዳለብን ወሰንን። ውሳኔውን ወደ ተግባር ለመቀየር በመጀመሪያ የጆኒን ፍቃደኝነት አገኘን። በተጨማሪም የMIDEQ projectን በሃላፊነት ከሚያስተዳድረውን Coventry University ይሁንታ አገኘን:: ብሎም መፃሐፉን ለማሳታም የወጣው ወጪ ሙሉ በሙሉ የ MIDEQ project ሸፍኖታል::

ጆኒን ባገኘነው በሁለት ወር ውስጥ የማስታወሻውን ኮፒ አግኝተን በኮምፒውተር አስፅፈን አንብበን የመጀመሪያ ዙር አስተያየት ሰጥተን ነበር። በተወሰነ መልኩ የተከለሰውን የማስታወሻ ቅፅ ይህንን የመግቢያ ክፍል አክለን በ2014 ዓም. መጀመሪያ መንፈቅ ለማሳተም አስበን እየተንቀሳቀስን ሳለ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በእንግሊዝ ኢኮኖሚ ላይ አደረሰ በተባለው ጫና ምክንያት የMIDEQ ፕሮጀክት የምርምር ድጋፍ ከሚያገኝበት

ከፍተኛ የሆነ የበጀት መቀነስ አጋጠመን። ስለዚህም የማሳተሙን ሃሳብ በእንጥልጥል ማቆየት ነበረብን። አሁን ጊዜው ደርሶ ለህትመት ደርሷል።

ማስታወሻውን ወደ መፅሀፍ በመቀየር ሂደት በቻልነው መጠን ጣልቃ ገብነታችንን ለመመጠን እና የፀሃፊውን ሃሳብ በፃፈበተ ጊዜ እንደፃፈው እንዲተላለፍ የቻልነውን ጥረት አድርገናል። ለፀሃፊው የሰጠነው ይዘትን በጉልህ መልኩ የመቀየር እድል የነበረው የመጨረሻዎቹ ገፆች ላይ ያሉትን ከተመለሰ በኋላ ያለውን የህይወቱ ክፍል ጋር የተያያዙትን ነው። ከዛም መለስ ያሉ የተደረጉ ለውጦች ለአንባቢው የማያስፈልጉ ዝርዝር ነገሮችን በተለይም በግልፅ ቢቀመጡ ሰዎችን ወይም የተቋማትን ስም ጨምሮ ሊጎዱ ይችላሉ ያልናቸውን በማጥቆር እንዳይነበቡ ማድረግ ነው። በተጨማሪም ትንንሽ እንግሊዝኛ መነሻ ያላቸውን ቃላት ወደ አማርኛ እንዲቀየሩ አድርገናል። ለምሳሌ ቸርች ወደ ቤተክርስቲያን፣ ሴሚስተር ወደ መንፈቀ አመት፣ text ወደ የፁሁፍ መልክት፣ ሃይ ስኩል ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት። መጠነኛ የአርትኦት ስራም ሰርተናል፣ በዋነኝነት የፅህፉን ተነባቢነት እና የንባብ ፍሰት ቀና ለማድረግ።

## ጥቂት ስለማስታወሻው

ጀኒ ማስታወሻውን የሰጠው ርዕስ “የህይወት ታሪክ: ፍልሰት እና ፍቅር” የሚል ነው። በእርግጥም በ37 ክፍሎች አደራጅቶ ከውልደት አንስቶ አሁን እስካለበት የእንጨት ስራ እና ተስፋዎች ድረስ ያስነብበናል። ከመጨረሻዎቹ ጥቂት ክፍሎች በቀር ሌላው በታንዛኒያ ዕስር ቤት የፃፋቸው ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ክፍሎች ስለውልደት፣ የቤተሰብ ሁኔታ እና ጥሩ የሆነ የትምህርት ውጤት የሚያሳዩ ናቸው። በዚህ መሃከል እናቱን በልጅነት ማጣቱ እንደወሰኝ የህይወት ክስተት ያቀርብልናል። ክፍል 5 ላይ ጀኒ ሀደሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል ከወንድሙ ጋር ወደ ሀደሮ ከተማ በሄደበት ጊዜ ያገኛትን፣ ወደፊት የፍቅር ጓደኛው ስለምትሆነው ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ ያነሳል።

አብዛኛው የማስታወሻው ክፍል ከእሷ ጋረ የነበረውን ጥሩ ጊዜ፣ መቀያየም፣ መታረቅ እና መነፋፈቅ ይዳስሳል። ይህም በአንድ በኩል ለስዋ ያለውን ፍቅር ሲያሳይ በሌላ በኩል ደግሞ በዕስር ቤት ቆይታው ዋናው ሃሳቡ እና ትዝታው እርሷ እንደነበረች በግልፅ ይነግረናል። ለመሄድ ያለውን ሃሳብ ሲያነሳባት በሕጋዊ/መደበኛ መንገድ እንዲጠቀም ያለችውን ባይቀበልም ብሎም በስነ ስርዓቱ ሳይሰናበታት መንገዱን ቢጀምርም ልክ ድንበር ተሻግሮ ኬኒያ እንደገባ እርሷ በአጋጣሚ ልደቷ ስለሆነ ሊደውል ይሞክራል። የመጀመሪያ ስልክ ጥሪውን ወደ እሷ ያደርጋል። ታንዛኒያ በፖሊሶች ከተያዘ በኋላ የስልክ እና ኢንተርኔት የመጠቀም አጋጣሚ ሲኖረው ሙከራው እርሷን ለማግኘት ነበር።

የፍልሰት አንዱ ብዙ የማይነገር ህመም እና ጉዳትም ይሄ ነው፣ የተጀመሩ ግንኙነቶችን መላላት እና መበጣጠስ የተለመዱ ገጠመኞች ናቸው። ማስታወሻው ሌሎች ስቃዮችም በዝርዝር ይነግረናል። የምግብ እና ውሃ ማጣት ቋሚ ችግር ነበረ። ይህ ችግር በጉዞ ላይም ሆነ በዕስር ቤት ይደጋገማል። ገፅ 59 ላይ “ምግብ ከተረፈበት ከአባቴ ቤት ወጥቼ ከመሬት የተደፋ ዕለቃቅማለሁ” ብሎ ያዝናል። በታንዛኒያ የኢትዮጵያ አምባሳደር አቶ ደግሞ በገፅ 71 “ክትፎ ከሞላበት ሀድያ እና ከምባታ ምን ልታደርጉ መጣችሁ” ብለው እስረኞችን ይወቅሳሉ። በጉዞ ላይ ንፅህና መጠበቅ የማይታሰብ ቢሆንም በእስር ቤት ያለው ደግሞ የባሰ ነበር። ለገላ መታጠቢያ እና ልብስ ማጠቢያ ውሃ አለመኖር ቅያሬ ልብስ አለመኖር ጋር ተደምሮ ልብሳችን ቀምሎ ጠዋት 4 ሰዓት ላይ ሸሚዝ አገልድመን መቅመል ስራችን ሆኖ ነበር ይለናል።

ይሄ ሁሉ ደግሞ ሲሆን የጉልበት ስራ መስራት ግድ ነበር፣ አድካሚ የእርሻ ስራ በጠራራ ፀሃይ ረጅም ርቀት በእግር ተጉዞ ሰርቶ ለመመለስ መመገብ ግድ ነበር። ምግቡ ይዘቱና ጣዕሙ የማይጋብዝ ቢሆንም በ24 ሰዓት አንዴ ስለሚመጣ የተገኘውን መብላት ግድ ነበር:: የእርሻ ስራው ላይ ቀስ ሲባል ለገመ፣ ሲፈጠን ደግሞ ለማምለጥ ነው ብሎ መሰደብ፣ መገረፍ የተለመደ ነበር። ይህ በማይቀር መልኩ ከፍተኛ የሰውነት ክብደት መቀነስ፣ የጉልበት መድከም እና ለህመም መጋለጥ አምጥቷል።

ከዚህ ሁሉ ሕጋዊ እና መንፈሳዊ ጫና ላይ የሀገር ስም አበላሸን የሚል ስሜት ይጨመርበታል። በገፅ 57 የስደት አመቻቾች ጫካ ውስጥ ጥለውን ሄደው የሚቀጥለው ተቀባይ ሲመጣ “አትዮጵያ” “ኢትዮጵያ” እያለ ተጣራ ይለናል። በምግብ ስንሻማ ሰው ተሰብስቦ ሲያየን፣ በቴሌቪዥን ሲቀረፅ የሀገር ስም አጠፋን ብሎ ይጨነቃል። ዕስር ቤት እያሉ አዲስ ታሳሪ ሲመጣ በድካም፣ በረሃብ፣ በውሃ ጥማት ከስቶ ገርጥቶ ሁለመናው ቆሸሾ ሲመጣ ሌሎች ታንዛኒያዊያን እስረኞች ሀገራችሁ ምግብ፣ በቆሎ ስለሌለ ነው የምትመጡት ሲሉ ተደባድበን ይለናል። ሀገርን በጥሩ ማስጠራት ባይቻልም ማሰደቡ በጣም አሞት የነበር ይመስላል።

ማስታወሻውን ስታነቡት እንደምትታዘቡት ጆኒ ከሀገር የመውጣቱን ውሳኔውን እንደተጠራጠረ እና ለምን ተሰቃየሁ፣ባልመጣሁ ኖሮ ብሎ የሚያስብ ይመስላል። ይህ በዕርግጥም በጊዜው ያሰበው ይሁን፤ ወይም በእስር ቤት ቆይታው እና ተስፋ መቁረጥ የተከለሰ አመለካከት መሆኑን ማወቅ አሰቸጋሪ ነው። አንድ ወሳኝ ጥያቄ ግን እንደዚህ አድካሚ እና ፈታኝ ጉዞ ምን ያክል ታስቦበት እና ከቤተሰብ ጋር ተወያይቶ የተወሰነ ነው የሚለው ነው።

ስለ ደቡብ አፍሪካ መዳዝ/መፍለስ ሃሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚነግረን በድንገት ነው። ይኸውም በተለይም በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ጥሩ ውጤት አመጣለሁ ብሎ ሲነገረን

ቆይቶ፣ 10ኛ ክፍል ውጤት ሲመጣ በሴት ጓደኛው ጥሩ ውጤት ማምጣት ተደስቶ ቀጥሎ ደግሞ በራሱ መውደቅ ሲደሰት ነው። ለዚህም የሚያስቀምጠው ምክንያት ደቡብ አፍሪካ ያሉት ወንድሞቹ ትምህርት ካልሆነለት እንደሚወስዱት ቃል ስለገቡለት ነበር። ይህ በጣም የተለመደ ክስተት ነው። እኛም ባደረግነው የመስክ ጥናት በተደጋጋሚ የሰማነው ነገር ይሄው ነው። አንዳንድ ጊዜ አውቆ ያለማጥናት እና መውደቅ ጭምር እንዳለ ነው ያረጋገጥነው። ሌላኛው በጥናታችን ያስተዋልነው በአካባቢው ህፃናት እና ወጣቶች የኑሮ ህልማቸው በአብዛኛው በፍልሰት ዙሪያ እንደሆነ እና ፍልሰት አዋጭ የህይወት መንገድ ተደርጎ እንደሚታሰበው ነው። ቀጥሎም ያሉትን ዓመታት ሞተር በመንዳት [እንደታክሲ] እና ዕንጨት ቤት ተቀጥሮ በመስራት አሳልፏል። ይህን በማስታወሻው ለይ ባይነግረንም በቃል መጠይቅ ላይ ተቀጥሮ የተወሰነ ሙያ ይዞ እንደነበረ እና በአለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ለሚደረግ ድጋፍ ዘርፍ ምረጡ ሲባልም ወደ ዕንጨት ስራ የገባው በዚያ መነሻ እንደነበር ነግሮናል።

በክፍል 21 እንደሚነግረን ወንድሙ ደውሎ ደቡብ አፍሪካ በእግር ለመምጣት ነገ፣ በአውሮኘላን ደግሞ በ6 ወር ውስጥ ብሎ ሲያስመርጠው ነገ እነሳለሁ ብሎ የወሰነው ቀላል አድርጎት ይመስላል። ቤተሰቡ፣ ዘመዱ እና የሴት ጓደኛው ቢለምኑትም ወይ ፍንክች ብሎ በማግስቱ ወደ ሐዋሳ፣ ዲላ ሞያሌ .... ብሎ ጉዞውን ይጀምራል። ይህም የሚነግረን ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረግ ፍልሰት በጣም ከመብዛቱ የተነሳ መደበኛ ምርጫ ተደርጎ ያለብዙ ዝግጅት እና ምክክር የሚደረግ እንደሆነ ነው። ይህም ፍልሰቱን ለመቀነስ እና ለማስቀረት ያሉትን ጥረት የሃሳቡ ስር መስደድ በቀላሉ ከንቱ እንደሚያስቀሩት ያሳያል።

በሌላ መልኩ ደግሞ ስቃዩን [በተለይም በታንዛኒያ] ከባድ ያደረገው በሀገሪቱ የኢትዮጵያ ኢምባሲ እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ አለመኖሩ ነበር። ይህም ስራዬ ብሎ ለታሳሪ ኡትዮጵያውያን መብት የሚከራከር እንዳይኖር አድርጓል። ይህም ታሳሪዎች ተስፋ ወደ መቁረጥ እና የሱስ ተገዥ ወደ መሆን አድርሷቸዋል። ከኢምባሲው መከፈት በኋላ ደግሞ የበጀት ዕጥረት ታሳሪዎቹን ወደ ሀገር ቤት የመመለስ ስራ ቀርፋፋ አድርጎ የእስረኞቹ መንፈስ በድጋሚ የሚያሽ ይሆናል።

ጀኒን ለየት የሚያደርገው በዚህ ጊዜ ውስጥ ከዕድሜው በላይ በማሰብ የመሪነት ሚና መጫወት መጀመሩ ነው። የሌሎች እስረኞችን መንፈስ ለመጠበቅ መጽሃፍ ቅዱስ ተሰብስቦ ማንበብ እና መወያየት መርሃ ግብር ያስጀምራል። በጊዜ ሂደትም የሃገሩን ቋንቋ ስዋህሊ በመማር ባለው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ያገለግል የነበረውን በእስር ቤት እና በኢትዮጵያዊያን ታሳሪዎች አገናኝነት ሚናውን ያጠናክራል። ከሌሎች እስረኞች ጋርም ያለውን መስተጋብር የስዋሂሊ ቋንቋ መቻሉ አጠናክሮታል። ስለዚህም የቻለውን ያክል ያሉትን እስረኞች በማገልግል ለእራሱም ሻል ያለ ጥቅም አግኝቷል። ከማረሚያ

ቤቱ አስተዳደር ጋር ያለው ግንኙነት በመጠቀም ያሉትን ችግሮች ከማስረዳት [መሞት ነው የቀረን ግደሉን እስከማለት] እስከ ኢምባሲ ጋር ያሉ ግንኙነቶችን ለማሳለጥ እሰከመሞከር ድረስ ይደርሳሉ። በዚህ አይነት ግንኙነት ነው ከአንድ ታንዛኒያዊ ታሳሪ ጋር ባለው የስራ ግንኙነት [ልብስ አጥቦ ክፍያ ማግኘት] ይሄንን ማስታወሻ የተፃፈበት ደብተር የተገዛለት።

ወደ ሀገር ቤት ተመልሶ ቦሌ አውሮኘላን ማረፊያ ሲደርስ የሁሉንም ደስታ ማንበብ፣ መሬት መሳምና ያለውን ስሜት ሲታይ ያስደስታል። በጥቂት ወራት ውስጥ ደግሞ በቢሮክራሲ ተሰፋ ቆርጦ የሚሰራ ነገር በማጣት እና ብሩህ ተስፋ ባለማግኘት ተመልሶ ወደ ደቡብ አፍሪካ [አሁን በአውሮኘላን ቢሆንም] ለመሄድ መነሳቱን ስናነብ መልሶ ለአንባቢ ግራ ያጋባል። በመጨረሻ ግን የዕንጨት ሰራ ጀምሮ ሰዎች ቀጥሮ እየሰራ እና ባገኘው አጋጣሚ ሌሎች ፍልሰትን እንዳይሞክሩት እየመከረ የደስታ ኑሮ እየመራ ይገኛል።

መልካም ንባብ።

# ክፍል አንድ

ከተወለድኩበት እስከ ዛሬ ድረስ ያደረሰኝ እግዚአብሔር ይመስገን። ከፈጣሪ በታች ያሳደጉኝ እናቴን እና አባቴን በጣም አመሰግናለሁ። የተወለድኩት በሀድያ ዞን በሆሳዕና ከተማ በአለላ ቀበሌ ነው። የተወለድኩት በ1987 ዓመተ ምህረት በ5ተኛው ወር በቀን 17 ነው። ከተወለድኩ በኋላ ዕድሜዬ ለትምህርት ሲደርስ ወላጅ አባቴ ወደ ትምህርት ቤት ወስዶ በመዋዕለ ሕፃናት፣ በቤተክርስቲያን አስገቡኝ። ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ቤት እንደገባሁ የሰፈሬ ልጅ በጣም ያስቸግረኝ ጀመር። ከዚያ ልጅ ጋርም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተደባደብን። ሌላ በጣም የምንዋደድ የሰፈሬ ልጅ ብዕር ሲያቀብለኝ በዚያው ብዕር አንገቱ ላይ ወጋሁት። ከልጁም ብዙ ደም ፈሰሰ። እንደወጋሁት አላወቅኩም ነበር እና አዘንኩኝ። በኋላ ላይ አስማሪያችን ብዕር በጣቶቼ ላይ አድርጋ በጣም ቀጣችኝ፣ እኔም በጣም አለቀስኩኝ። በኋላ ላይም ከልጁ ጋር አስታረቀችን። አስተማሪያችን ትባላለች። በመጀመሪያ ዓመት በትምህርቴ በጣም ደካማ ነበርኩኝ። ለአባቴ አስተማሪያችን "ሰላሳ አራተኛ ወጥተሃል፤ ስለዚህ በሁለተኛው መንፈቀ-አመት ጥሩ ውጤት ለማምጣት ጠንክር" ብላኛለች አልኩት። አባቴም "ጥሩ ውጤት ስላላመጣህ እኮ ነው" አለኝ። እኔ ግን "ከፍተኛ ቁጥር አምጥቼ እንዴት?" አልኩት። አንደኛ የወጣው አንድ ቁጥር ያለው ብቻ ስለሆነ እርሱ ደካማ ይመስለኝ ነበር። ነገር ግን በኋላ ሲያስረዳኝ አንደኛ መውጣት ሽልማት ለማስገኘት የሚያስችል መሆኑን ተረዳሁ።

የሁለተኛው መንፈቀ-አመት ትምህርት ከተጀመረ በኋላ ትምህርቴን በጥሩ ሁኔታ መቀጠል ጀመርኩኝ። ታላላቆቼ ሲያስጠኑኝ እና ሲያስረዱኝ በቻልኩት መጠን በጥሩ ሁኔታ ትምህርቴን ለመከታተል ሞከርኩኝ። እናቴ ለትምህርት በጣም ትኩረት ትሰጣለች። በዚያ ምክንያት ከትምህርት እንድቀር በፍፁም አትወድም ነበር። እኔ ግን የጠዋት እንቅልፍ ስለምወድ አንድ አንዴ መቅረትን እፈልግ ነበር። እርሷ ግን ከእንቅልፌ በግድም ቢሆን አስነስታኝ ወደ ትምህርት ቤት እንድሄድ ታደርገኛለች። በሆነ ሰሞን ጭራሹኑ እንቅልፌን መውደድ ጀመርኩ። ከዚያም በጣም ተቆጣችኝ፤ ወደ ትምህርት ቤት እንድሄድም አስገደደችኝ። እኔ ግን ከመንገድ ተመልሼ ሰፈር ላይ ከልጆች ጋር መጫወት ላይ ብቻ ትኩረቴን ሰጠሁ። ይህንን ነገርም በተደጋጋሚ ማድረግ ጀመርኩኝ። ጠዋት ተነስቼ ቁርሴን እበላና ወደ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ ብያቸው እወጣለሁ። ነገር ግን ከመንገድ ላይ ተመልሼ ከልጆች ጋር ስጫወት ውዬ ወደቤቴ እመለሳለሁ። ይህ የማደርገው ነገር ከትንሽ ሳምንታት በኋላ ለቤተሰቦቼ ደረሰ። እኔን ምን ይዋጠኝ? ይህንን ነገር ከሰሙማ ይገድሉኛል ብዬ በጣም ፈራሁ። በኋላ ላይ ከኔ ታላቅ የሚባለውን እርሱ ወደ ትምህርት ቤት እኔን አድርሶ እንዲመለስ አደረጉት። አንድ

አንዴ እንቅልፍ ቢሸውደኝ እንኳን ከእንቅልፌ አስነስቶኝ በአርጩሜ እየጠቀጠቀኝ እሰከ ትምህርት ቤት ያደርሰኛል። በዚህ ሁኔታም የመዋዕለ-ሕጻናት ትምህርቴን ጨረስኩ።

## ክፍል ሁለት

አንደኛ ከፍል የተማርኩበት ሃይሌ በቡሞ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም በልዩ ስሙ ቁጥር አንድ ትምህርት ቤት ተብሎ ይጠራል። በዚህ ትምህርት ቤት ተመዝግቤ መማር ጀመርኩ። በጥሩ ሁኔታም ቀጠልኩኝ፣ የትምህርት ፍላጎቴም ከድሮ በጣም ጨመረ። ቀን የተማርኩትን ማታ ማታ ወንድሜ ያስረዳኝ ነበር። በቤታችን በጣም ጎበዝ ልጅ አለ፣ ስሙ ይበላል። በትምህርት ቤት ሁሌም የደረጃ ተማሪ ነበር። በዚህ ልጅ ሁሌም እቀና ነበር። እኔም አርሱን በማየት ለትምህርቴ በጣም ትኩረት መስጠት ጀመርኩኝ።

አንደኛ ከፍል የአንደኛ መንፈቀ-አመት ትምህርት ማለቂያ ደረሰ። አንድ ቀን ሁላችንም ወደ ትምህርት ቤት ተጠራን፣ በዚህ የፈተና ድምር ውጤት በሚነገርበት ቀን ያልጠበቅኩት ነገር በእኔ ላይ ሆነ። ስም ጠሪያችን የስም ዝርዝሩን ይዛ ወደ ክፍል መጣችና በቅደም ተከተል መጥራት ጀመረች። በቅደም ተከተሉ መሰረት የስሜ [ዮናስ] መነሻ ፊደል የሆነው ዮ መጨረሻ አካባቢ ስለሆነ የልጆቹ ስም ሁሉ ተጠራ። በመጨረሻ ላይም ስም ጠሪያችን ጠራችኝ እና ውጤቴን ሁሉ ነገረችኝ። ያላሰብኩት ውጤት ነበር የመጣልኝ፤ ያመጣሁት ውጤት አማካኝ 98.1 ከመቶ ነበር። በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከ1ኛ ክፍል A እስከ C የእኔን ውጤት ያመጣ አልተገኘም ነበር።

በኋላ ላይ በሁለተኛ መንፈቀ-አመት ትምህርት መክፈቻ ላይ የሽልማት ኘሮግራም ነበር። በዚህ ኘሮግራም ላይ እኔም እንደታላቁ ሽልማት ይዤ ወደ ቤት መጣሁ። ቤተሰቦቼም በዚህ በጣም ደስተኛ ሆኑ፤ እኔም ምኞቴን አሳካሁኝ። በሚቀጥለው መንፈቀ-አመትም በጣም በማንበብ በጥሩ ሁኔታ ትምህርቴን መከታተል ቀጠልኩኝ። በዚህ በሁለተኛው መንፈቀ-አመት አንድ ነገር ተፈጠረ። በሰፈራችን ውስጥ የሚባል ልክ እንደእኔ በጣም ጎበዝ ልጅ ነበረ። ከዚህ ልጅ ጋር በክፍል ውስጥ በጣም እንፎካከራለን። ለጥያቄ መልስ ስንሰጥ እራሱ በፉክክር ነበር የምንመልሰው።

ይህ ልጅ በሁለተኛው መንፈቀ-አመት ትምህርት ከእኔ በትንሽ ነጥብ በልጦ አንደኛ ሆኖ ሲሸለም በጣም ተናደድኩኝ። እኔ ሁለተኛ ሆኜ ሽልማት ተቀበልኩ፤ ነገር ግን ሽልማቱን መቀበል እራሱ በጣም አስጠላኝ። ለዚህም ምክንያቱ ለምን ተሸነፍኩ ብዬ ተቆጭቼ ስለነበር ነው። ሆኖም ምንም ማድረግ ባለመቻሌ ወደ ቤቴ እያዘንኩ ተመለስኩ፤ ቤተሰቦቼም አፅናኑኝ። ሁለተኛ ክፍልም ከደረጃ ተማሪነት ሳልወጣ ሁለተኛ ደረጃን በማግኘት በጥሩ ሁኔታ ጨረስኩኝ።

ሦስተኛ ክፍል ደግሞ በሁለቱም የመንፈቀ-አመት ትምህርቶች በተመሳሳይ ውጤት፣ በአንደኝነት ደረጃ አለፍኩኝ። ቀጥሎም አራተኛ ክፍል ተመዝግቤ ትምህርቴን ቀጠልኩኝ:: በአንደኛው የመንፈቀ-አመት ትምህርት ጥሩ ውጤት ይዤ ከደረጃ ሳልወርድ አለፍኩ:: በክፍል ውስጥ ልጆች በክብር ነበር የሚያዩኝ፤ በክፍል ውስጥም የቡድን ስራ ሲሰጠን ልጆች ከእኔ ጋራ መስራት በጣም ይፈልጋሉ። ደግሞም በጣም ተጫዋች እና ቀላጅ ነበርኩ። በዚህ ምክንያትም ልጆች በጣም ይወዱኝ ነበር። በዚህ መልኩ አንደኛ መንፈቀ-አመት አለፈ። እኔም እንደልማዴ ሽልማቴን ይዤ በመሰናበቻ ዝግጅቱ ላይ ከልጆች ጋር ተለያየሁኝ። ሁላችንም “ቻው! ቻው! በሁለተኛ መንፈቀ-አመት እንገናኝ” ተባብለን ተለያየን። ከእረፍት በኋላ ሁለተኛው የመንፈቀ-አመት ትምህርት ተከፈተ። ይገርማል! በጣም ተነፋፍቀን ስንገናኝ እጅግ ደስተኞች ሆነን ትምህርታችንን ቀጠልን።

ትምህርቴን በትኩረት እና ትልቅ ቦታ ሰጥቼ መከታተል በጀመርኩበት በዚህ በሁለተኛው መንፈቀ-አመት መሀል እናቴን በጣም አመማት። እርሷን ለማስታመም ስል አልፎ አልፎ ከትምህርት ቤት መቅረት ጀመርኩኝ። በኋላ ላይ በሽታው እየባሰባት ሄዶ በጽኑ መታመም ጀመረች። በሆሳዕና ከተማ ሆስፒታል እና በከተማው ከሚገኙ የግል ክሊኒኮች ውስጥ ያልገባችበት ቦታ አልነበረም። ከሆሳዕና ይልቅ ሀዋሳ ብትሆን ይሻላታል ብለን ወደ እህቷ ጋር ሀዋሳ ሄደች። በኋላም ምንም ለውጥ አልተገኘላትም ነበር። ከጊዜያት ቆይታ በኋላ ተመልሳ ከሀዋሳ ወደ ሆሳዕና መጣች። ትንሽ ከቆየች በኋላም ህመሟ ክፋኛ እየጨመረ መጣ። የምናደርገው ነገር አጣን፤ ቀጥሎም ተመልሳ ወደ ሆሳዕና ሆስፒታል ገባች። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ሲመቸኝ ወደ ትምህርት ቤት እየሄድኩ የሁለተኛ መንፈቀ-አመት ትምህርት ትንሽ ገፋሁ። ከቤት ወደ ትምህርት ቤት መመላለስ ተረሳኝ፤ ምክንያቱም ዘውትር ከሆስፒታል ነበር ወደ ትምህርት ቤት የምመላለሰው። በዚህ ሁኔታ ውስጥም ሆኜ ሆስፒታል ውስጥ አልፎ አልፎ አነባለሁኝ። ከጊዜ ወደ ጊዜ ይሻላታል ብለን ስንጠብቅ ጭራሽ እየባሰባት ስለሄደ ከትምህርቴ መቅረት ጀመርኩ።

በጣም ስለምወዳት ከአጠገቧ መለየት በጣም ነው የሚከብደኝ፤ ሌሎች ልጆች ቢኖሩም እርሷን ጥያት ወደ ቤት መሄድ በጣም ይከብደኛል። በዚህ ሁኔታ ትምህርት ማለቂያ ደረሰ። ትምህርቴን ምንም ሳልከታተል ወራቶች አለፉ። በቃ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩኝ። የዘንድሮ ትምህርቴ ቀረ አልኩ። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ እናቴም በሽታዋ በጣም ጠናባት:: የካቲት አስራ አምስት አካባቢ የባሰ እየደከመች መጣች፤ በጣም ፈራን:: ከዚያም በቃ ተስፋ ቆርጠን ወደ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሄደን እንድትታከም ሪፈራል ለማጻፍ የሚያስፈልጉትን ሂደቶች ወንድሜ አዲስ አበባ በሚኖር ልጅ በኩል አስጀመረ:: እናቴ ወደ አዲስ አበባ ለህክምና ልትሄድ ጥቂት ቀናቶች በቀሩበት ሰዓት እንዲህ ብላ ማውራት ጀመረች። “ ሴት ናት ለእርሷ አልጨነቅም፤ ዮኒን አደራ” ብላ ለወንድሜ

ተናገረች። እኔም ከሆስፒታል ወደ ሰፈር ሂድ ብለው በጣም ሲያስገድዱኝ ወደ ሰፈር ሄደኩኝ። በዚህ መሃል እናቴ በጣም እጅ መስጠት ጀመረች። የካቲት 22 ቀን 2002 ዓ.ም፤ ቀኑም ቅዳሜ ቀን በዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች።

እኔ ሰፈር ውስጥ ነበርኩኝ። በመኪና አስክሬንዋን ይዘው ቤት እስከሚደርሱ ድረስ ምንም ነገር አልሰማሁም ነበር። በድንገት በመኪና በራችን ላይ ደረሱ። እህቴ እራሷን አታውቅም ነበር። ወንድሞቼን ሰው በግራ እና በቀኝ ይዟቸዋል። ምን ልሁን እንዴት ልሁን ሳላውቀው እራሴን ሳትኩኝ። የምሆነው ነገር አጣሁኝ፤ በቃ ሁሉ ነገሬ ተበላሸ። እናቴን አጥቻት እንዴት እኖራለሁ ብዬ መሞትን ተመኘሁ። የሚያፅናናኝ ጠፋ። ጭራሽ ጭንቅላቴ ተበጠበጠ። ከእንግዲህ እምኖር አይመስለኝም ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። እንደገና ሳስበው በህይወት ሳለች የምታወራልኝ፣ የምታስደስተኝ፣ የምትመርቀኝ፣ የምትመክረኝ፣ የምታስተምረኝ እና የምታጫውተኝ ነገር ሁሉ እየመጣብኝ ጭራሽ መፅናናት አልቻልኩም ነበር።

## ክፍል ሦስት

ምንም ማድረግ ስለማልችል ሁሉን ነገር መርሳት ጀመርኩ። አክስቶቼ በጣም መከሩኝ። አጎቴ የሀገር ሽማግሌ ነው። እርሱም በጣም መከረኝ። ከተቀበረች በኋላ በሰባተኛው ቀን አጎቴ በሀገሩ ሰዎች ፊት አቁሞን ከኔ አንስቶ እስከ አንጋፋው ልጅ ድረስ አስመረቀን። የሃገር ሽማግሌዎች "ከዚህ በኋላ ሀዘን ሳይሆን፣ ለቅሶ ሳይሆን የደስታ ቀን ከፊት ለፊታችሁ ይጠብቃችሁ" ብለው ብዙ ነገር መረቁን። ከትንሽ ቀናቶች በኋላም የክፍሌ ልጆች ሊያጽናኑኝ ወደ እኔ መጡ። አጽናንተውኝም ተመልሰው ሄዱ።

ነገር ግን ምንም ነገር ቢደረግልኝ የእኔ ሃሳብ ከእርሷ ጋር ብቻ ሆነብኝ። ተደብቄ ሄጄ ቀብር ቦታ ላይ አንዳንዴ አለቅሳለሁኝ። ይህ የማደርገው ነገር ደግሞ ለቤተሰቦቼ ደረሰ። ታላቄ በጣም መከረኝ "ሁለተኛ እንደዚህ ካደረግህ ነግሬሃለሁ እማ ዳግመኛ አትመጣም፤ እኛ ነን ወደ እርሷ የምንሄደው" ብሎ በጣም አስጠነቀቀኝ። "የሚያስፈልግህን ሁሉ እኔን ጠይቀኝ አንተን መከባከብ ለእኔ አያቅተኝም" ብሎ በጣም መከረኝ። እኔም "ሁለተኛ አላደርግም" ብዬ ቃል ገባሁለት፣ ነገር ግን ቆይቼ ቆይቼ በጣም ሳስባት፣ በጣም ስትናፍቀኝ ወደ ቀብር ቦታዋ እሄድ ነበር። በዚህ ሁኔታ አራተኛ ክፍል ማጠቃለያ ፈተና ደረሰ። አባታችን ደግሞ "ከዚህ በኋላ መጠንከር ነው እንጂ ማናችሁም በትምህርት ወደ ኋላ እንድትቀሩ አልፈቅድላችሁም" ብሎ ሁላችንንም መከረን።

እኔ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ። እህቴ ትባላለች፤ እርስዋ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ነበረች። ታላቅ ወንድሜ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪ ነበረ፤ ስሙም

ይባላል። ሌሎቹ ሁሉም ትምህርት ጨርሰዋል። በቤታችን ትልቅ የነበረው በአዲስ አበባ ከተማ የግል ስራ ብረታ ብረት ነው የሚሰራው፤ ስሙም ይባላል። ሌላኛው በኤሌክትሪክሲቲ [electricity] ተመርቆ በሆሳዕና የግል ሥራ ነው የሚሰራው። አንዱ 2001 ዓመተ-ምህረት ላይ ወደ ደቡብ-አፍሪካ ሄዶ ሥራ ይሰራል። በትምህርት መስክ ላይ ያለነው ሦስታችን ማለትም እኔ፣ ብቻ ነን። አባታችንን እና አጎታችንን፤ በተለይም ደግሞ አጎታችንን በጣም ስለምንፈራው የማጠቃለያ ፈተና እንድንፈተን አስገደደን። እኛ ከትዕዛዛቸው መውጣት ስለማንችል ትምህርት ለመቀጠል ወሰንን።

ሁላችንም ትምህርት ጀመርን። እኔ የአራተኛ ክፍል የማጠቃለያ ፈተና ተፈተንኩኝ፤ እህቴም የዘጠነኛ ክፍል የማጠቃለያ ፈተና ተፈተነች፤ ወንድሜም የአስራ ሁለተኛ ክፍል የመልቀቂያ ፈተና [ማትሪክ] ተፈተነ። ሁላችንም በዚያ በችግር ውስጥም ቢሆን ትምህርታችንን ጨረስን።

። እህቴም ወደ አስረኛ ክፍል ተዘዋወረች። ወንድሜም ጥሩ የማለፊያ ውጤት አግኝቶ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ደረሰው። ወደ መቀሌ ሄዶም የአካውንቲንግ ትምህርቱን ጀመረ። ወደ 10ኛ ክፍል ገብታ ትምህርቷን ቀጠለች፤ እኔም አምስተኛ ክፍል መማሬን ቀጠልኩኝ። በጭንቀትም በደስታም ቢሆን ህይወቴን ቀጠልኩኝ። አምስተኛ ክፍል በሁለተኛው የትምህርት መንፈቀ-አመት መጨረሻ አካባቢ ላይ አስተማሪያችን፤ ማለትም የስፖርት መምህር ከመቶ የሚያዝ ፈተና ሊፈትነን ከትምህርት ክፍለ ጊዜ ውጪ የጠዋት ክፍለ ጊዜያችንን ጨርሰን ከሰዓት በኋላ ለመገናኘት ቀጠረን።

ሻወር ገብቼ የስፖርት ትጥቅ ለብሼ በተነሳሁ ሰዓት የአጎቴ ልጅ ማለትም ስሙ ይባላል፣ በፈጣሪ ሳር ጎዝጉዝና እስቲ ያን ጣፋጩን ያንተን ቡና አፍላ ብሎ በጣም ለመነኝ። ልጁ በእናቴ በኩል የአጎቴ ልጅ ነው። ከዚያም አልፎ የበለጠ እንደወንድሜ ነው። ብዙ ጊዜም ከእኛ ጋር ነው ያሳለፈው። ይሄ ልጅ በዚያን እለት ቤታችን ውስጥ ጓደኛውን ቀጥሮት ነበር። እኔ ግን ትምህርት ቤት ለስፖርት ፈተና በስምንት ሰዓት ቀጠሮ እንዳለብኝ ነገርኩት። ይሁንና "ትደርሳለህ ችግር የለም፤ አሁን ሰባት ሰዓት ከምናምን ነው" ብሎ በጣም ለመነኝ። እኔም እጅግ ስለምወደው እምቢ ማለት አልቻልኩም ነበር።

ቡና አፍልቼ ጠጥተን ስናበቃ ወደ ትምህርት ቤት እየሮጥኩ ሄድኩኝ፣ ነገር ግን ልደርስ አልቻልኩም ነበር። ከመቶ የሚያዘው ፈተና አመለጠኝ። አስተማሪውን አጥብቄ ብለምንም እምቢ አለኝ። ይህ እንደአንድ የትምህርት አይነት ያልተሟላ ውጤት ሆነ። ግን ይህ ሆኖም በክፍል ውስጥ ሦስተኛ ደረጃ ለመውጣት ቻልኩ። ያን ስፖርት ፈተና ተፈትኜ ቢሆን ኖሮ እሸለም ነበር። በጣም ተናድጄ ሽልማቱን መውሰድ እምቢ

አልኩኝ፤ እስከ ዛሬም ሽልማቴ በርዕሰ-መምህሩ ቢሮ ይገኛል። በዚህ ሁኔታ አምስተኛ ክፍልን ጨረስኩ፣ ስድስተኛ እና ሰባተኛ ክፍልንም በጥሩ ውጤት አለፍኩኝ። ቀጥሎም ስምንተኛ ክፍል ገባሁ፤ በመጀመሪያው የትምህርት መንፈቀ-አመት በክፍል ውስጥ አምስተኛ ደረጃን በማግኘት ጥሩ ውጤት አመጣሁ። ቀጥሎም ዋናው ሃገር አቀፍ ፈተና ማለትም ሚኒስትሪ ደረሰ። ፈተናውንም ተፈተንን።

በዚህ መሃከል ደግሞ አንድ ነገር ተፈጠረ። ከእኔ በኋላ ለፈተና የተቀመጠው ልጅ፣ ከእኔ በጣም የሚተልቅ ነበር። ልጁ “ሰርተህ እንደጨረስክ ወዲያውኑ አቀብለኝ” ብሎ በጣም አስፈራራኝ። እኔም እጅግ ፈርቼ፣ ሕጻንም ስለነበርኩኝ ሰርቼ ስጨርስ መልሶቹን እንኳን አጥቁሬ ሳልጨርስ ማለትም ከጥያቄው ወረቀት ወደ መልስ ወረቀት ሳልገለብጥ ከእጄ ነጥቆ መውሰድ ጀመረ። እርሱ ሰርቶ ሲጨርስ ጠብቄ ደግሞ ለራሴ መልሶቹን ማጥቆር እጀምራለሁ። እንዲህ እያደረግኩ ሳለ መልሶቹን አጥቁሬ ሳልጨርስ የተሰጠው ሰዓት ያልቃል። ግማሹን ጥያቄ ሰርቼ የመልስ ወረቀት እሰጣለሁ። በዚህ ሁኔታ የስምንተኛ ክፍል ውጤቴ በጣም ተበላሸ። ቤተሰቦቼም በጣም ደነገጡ ምክንያቱም ተሸላሚ ተማሪ መሆኔን ያውቁ ስለነበር ነው።

## ክፍል አራት

2006 እና 2007 አመት በስምንተኛ ክፍል ብቻ አሳለፍኩኝ። ምንም እንኳን አዕምሮዬ ቢጎዳም በዚህ በሁለተኛው ዓመት በጥሩ ሁኔታ ትምህርቴን በመቀጠል በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ከፍተኛ ውጤት የነበረውን ውጤት 93.1 ከመቶ አገኘሁ። ቀጥሎም ወደ የካቲት 25/67 ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ገባሁ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ታሪክ በዚሁ አበቃ።

በሁለተኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት በዘጠነኛ ዩ (9-U) ተመዝግቤ ትምህርቴን ቀጠልኩኝ። በዚህ በሁለተኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት ደግሞ በጣም የምወደውን ጓደኛዬን አገኘሁት። ስሙ ይባላል፣ ቤተሰቦቹ ግን ብለው ነው የሚጠሩት። ከዚህ ልጅ ጋር በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ አብረን ነበር ሚኒስትሪ የተፈተንነው፣ በጣምም እንዋደዳለን። ይህ ጊዜ ለእኛ በጣም ጥሩ ጊዜ ሆነ። በትምህርት ቤት አንድም ቀን ተለያይተን አናውቅም ነበር። አልፎም ተርፎ አንድ አንዴ እኔ ጋር በሌላ ጊዜ ደግሞ እርሱ ጋር በፈረቃ ነበር የምናድረው። አብዛኛውን ጊዜ ግን እኔ ጋር እናድራለን። ምክንያቱም እኔ ቤት ተከራይቼ ብቻዬን ነበር የምኖረው።

ለእኔ ትምህርት ቤቱ ከሰፈሬ ትንሽ ይርቃል። እዚያ ለመድረስ ወደ 35 ደቂቃዎችን ይወስዳል፤ ሌሎች ልጆች ግን ከሰፈራቸው ነው የሚመላለሱት። ቤተሰቦቼ ግን እኔን

በጣም ስለሚወዱኝ እንድጨናነቅ አይፈልጉም ነበር፤ ለገንዘብም አልጨነቅም ምክንያቱም ወንድሜ ባንክ ውስጥ ሰራተኛ ነው። በየወሩም ለእኔ ብር ይልክልኛል። በደቡብ አፍሪቃ ሌሎች ሁለት ልጆችም ስለነበሩ እነርሱም ሁልጊዜ ገንዘብ ይልኩልኝ ነበር። በአዲስ አበባ የሚኖር ከሁላችንም ተለቅ ያለው እርሱም በጣም ይረዳኛል። የእርሱ ሚስትም ስልክ ደውላ ወደ አዲስ አበባ ትጠራኛለች፤ በጣምም ይወዱኛል። እህቴም ሆነ ባለቤትዋ በጣም ስለሚወዱኝ ጭራሽ እንድጨነቅ አይፈልጉም። ሁሌም ከባለቤትዋ ጋር በስልክ እየደወሉ የሚቸግረኝን ይጠይቁኛል፤ ከቤታችንም ከሁሉም ልጆች የመጨረሻው ስለሆንኩ በጣም ይንከባከቡኛል። ከዚህም ሁሉ በተጨማሪ ደግሞ አባቴ በየወሩ መጨረሻ ሁሌም 350 ብር ይሰጠኛል። በዚህ ቤት ውስጥ እራሱ ደስ ሲለኝ ብቻ ነበር ምግብ የምጠቀመው አብዛኛውን ጊዜ ውጭ ነበር የምመገበው።

ከሁሉም በላይ ደግሞ ወደ አዳር ስሔድ በጣም የምትረዳኝ የምትባለው የወንድሜ ሚስት ነች። ለኔ ግን እንደእናትም እንደእህትም እንደጓደኛዬም ነች፤ በጣም ስለምትወደኝ የሳምንቱን የመጨረሻ ቀናት እርሷ ጋር እንዳሳልፍ ነው የምትፈልገው:: ስመለስም በጣም ብዙ ነገር አስይዛኝ፣ መሳፈሪያ ሰጥታኝ ትሸኘኛለች። በየሳምንቱ ይህን ነገር እያደረገች ሳለች በፍጹም ሰለቸሁ ብላ አታውቅም ነበር። እንደውም በግድ ነው ወደ አዳር የምትጠራኝ። ለካ ምንም ተጨንቄ እና ተቸግሬ አላውቅም ነበር። ከዚህ ከጓደኛዬ ጋር በዚ ሁሉ ጊዜ አንድ ላይ ነው የምናሳልፈው፤ ተለያይተን አናውቅም ነበር።

እኔን እና ይህን ተለያይተን የማናውቀውን ጓደኛዬን የሚለያየን ነገር በእኔ ላይ ሆነ። ወንድሜ ወደ ሀደሮ ከተማ እንደሚወስደኝ እና በሀደሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርቴን እንደምቀጥል ነገረኝ። እኔም ይህንን ነገር ለጓደኛዬ ነገርኩት፤ በጣምም አዝኖ "ዮኒ ጥለኸኝ ልትሄድ ነው በቃ" ሲል በጣም ተከፋ። ምንም ነገር ለማድረግ ስለማልችል ለመሔድ ወሰንኩኝ፤ ያሉኝንም ነገሮች እና የትምህርት ቤት ሂደቶች ጨርሼ ለመሄድ ተዘጋጀሁ። ጓደኛዬም በጣም አዘነ፤ የክፍሌ ተማሪዎች በጣም አዘኑ ምክንያቱም የክፍሉ አለቃ ስለነበርኩኝ ነው። ልጆች ከትምህርት ሲቀሩም እንኳን ቀሪ አድርጌ መዝግቤአቸው አላውቅም ነበር። ስም ጠሪያችን የስም ዝርዝሩን ለእኔ ሰጥቶ ነበር የክፍሉ ሙሉ ስም የሚጠራው፤ ለካ በጣም ይወዱኛል። በኋላ ላይ ሁሉን ነገር ጨርሼ፣ የክፍል ጓደኞቼንም ቻው ብያቸው ጉዞዬን ወደ ሀደሮ ቀጠልኩኝ። ወንድሜ በሀደሮ ከተማ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በዘጠነኛ ኢ (9-E) ክፍል አስመዘገበኝ።

# ክፍል አምስት

በሀደሮ ከተማ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በዘጠነኛ ኢ (9-E) ክፍል ትምህርቴን ለመቀጠል ሐሙስ ቀን፣ በስድስት ሰዓት ከሰላሳ ላይ ወደ ትምህርት ቤት ገባሁ። የክፍሉን በር ያንኳኳሁት የሒሳብ ክፍለ ጊዜ ላይ ነበር። መምህሩም ወደ ውስጥ ግባ አለኝ። የክፍሉ መሀል አካባቢ አንዲት ልጅ ለብቻዋ ቁጭ ብላ ነበር። ወደ ውስጥ ገብቼም ከልጅትዋ ጋር ቁጭ ብዬ ደብተሬን አውጥቼ በሒሳብ ደብተር ላይ "ሁለተኛ ሴሚስተር" ብዬ መጻፍ ጀመርኩኝ። ከልጆቹ ጋር እንዴት ሆኜ እግባባለሁ ብዬ በጣም ተጨነቅኩ። መምህሩም ትምህርቱን ማስተማር አቋርጦ ከልጆቹ ጋር እንድተዋወቅ ጊዜ ሰጠኝ። እኔም እራሴን ማስተዋወቅ ጀመርኩኝ። እራሴን ከአስተዋወቅኳቸው በኋላ ወደ በታዬ ተመልሼ ተቀመጥኩኝ። ከዚያም ወደ ጥቁሩ ሰሌዳ እየተመለከትኩ መፃፍ ጀመርኩ። ድንገት ከፊት ለፊት ካለው ቀጥሎ ያለው በሁለተኛ ወንበር ላይ የተቀመጠች በጣም የምታምር ልጅ ሰረቅ አድርጋ ስታዬኝ፣ የእኔና የልጅቷ አይን ተገጣጠመ። በጣም ደነገጥኩ፤ እርስዋም በጣም ደነገጠች። የፍቅር ታሪኬ ከዚህ ይጀምራል።

በፍርሃት ተሞላሁ፤ መፃፉን ትቼ ሀሳብ ውስጥ ገባሁ፤ በጣም ተንገበገብኩኝ፤ የምሆነውን ነገር አጣሁኝ። ልቤ ፈሰሰ። ወደ ጥቁር ሰሌዳው እመለከታለሁ፣ አሁንም አይን ለአይን ተገጣጠምን። ይህ ለኔ ደግሞ ልዩ መልእክት ሆነብኝ። "ይህች ልጅ ወድዳኝ ይሆን?" በማለት ሀሳብ ውስጥ ገባሁኝ። ገና ሳንተዋወቅ በዚህ በአይን ብቻ አወራን፤ በፍቅር ተነደፍኩኝ። ከልጆቹ ጋር በደንብ ተዋውቄ ስለ እርሷ እስከምጠይቅ በጣም ቸኮልኩኝ። ክፍለ ጊዜው እንደምንም አበቃ። ፍቅር ፀንሼ ወደ ቤት ተመለስኩ። ቀኑም ሐሙስ ቀን ነበር። ሐሙስ የቀን ቅዱስ አልኩኝ፤ ምክንያቱም ከተወለድኩበት ቀን ጀምሮ እንደዚህ ያለ ልብን የሚያንቀጠቅጥ፣ በጣም የሚያስደነግጥ፣ ደግሞም በጣም የሚያስደስት ነገር በህይወቴ ሆኖ አያውቅም ነበር። ያ ቀን ለእኔ ብርሃን ሆኖኛል። ምን ልበል? በጣም ደስተኛ ሆንኩኝ፤ ወደ ትምህርት ቤት ሔጄ ዳግም እስከማያት በጣም ናፈቀችኝ። ቀስ በቀስ ልቤ ውስጥ ገባችብኝ። ያን ማታ እንቅልፍ የሚባል ነገር በየት መጥቶልኝ? እርሷን ብቻ በማሰብ አደርኩኝ፤ ሌሊቱ እንደምንም ነግቶ ወደ ክፍል ሔድኩኝ።

የክፍሉ አለቃ አበበ ይባላል። ይህ ልጅ በጣም ቀረበኝ፣ ስለ ራሱም ነገረኝ፣ ስለ እራሴም ነገርኩት። በጣም መቀራረብ ጀመርን። ከዚያም ስለ ልጅቷ ለመጠየቅ ምርጥ አጋጣሚ አገኘሁ። ስለ ልጅቷም ጠየቅኩት። ልጁም በጣም ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር ነገረኝ። "ልጅቷ ለፍቅር ጥያቄ ቦታ የላትም፤ ትኩረቷ በትምህርት ብቻ ላይ ነው" ብሎ ነገረኝ። በአንደኛው መንፈቀ-አመት በክፍሉ ውስጥ አንደኛ ደረጃ፤ በግቢ ውስጥ ካሉ ሴቶች ደግሞ ተሸላሚ መሆኗን ነገረኝ። በጣም አዘንኩኝ። ይህን ተስፋ የሚያስቆርጥ

ነገር ስለነገረኝ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ። በዚህ በሁለተኛ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እኔን ያላዋራኝ ሴት በጣም ጥቂት ነው። የባሰ ደግሞ በትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ መጥተው በጣም ይረብሹኛል፤ በግድ እንተዋወቅ ይሉኛል። የመጨረሻ ተስፋ ቆርጠው የሚሰድቡኝ ብዙዎች ናቸው። በዚህ ሁሉ ውጣ ውረድ ላይም ልቤ ያለው ከዚህች ልጅ ጋር ብቻ ነበር።

የኔ ጓደኛ ደግሞ በዚህ መሀል አንድ ነገር አመጣልኝ። ትባላለች፤ በመስኮት መጥታ ሁሌም ታዋራኛለች። “ሀገሩን ለምደሃል ወይ?” ትለኛለች። ይህች ልጅ ደግሞ በጓደኛዋ በኩል ለጓደኛዬ መልእክት ላከችልኝ። ጓደኛዬም መጥቶ በአንተ ፍቅር የተነሳ የማትፈልገው ነገር ልታደርግ ነው ብሎ ነገረኝ። እኔም እንዲህ ብዬው ጓደኛዬን መልሼ ላክኩት። “እኔ አማላጅ አልፈልግም፤ ከወደደችኝ መጥታ እራሷ መውደዷን ትንገረኝ” ብዬ ጓደኛዬን በጣም ተቆጣሁት። ልጁም ወስዶ ለጓደኛዋ ነገራት። ሁለተኛ ሌላ ነገር አልደገመችም፤ ነገሩ በዚያው ቆመ። ያችን መጀመሪያ ያየኋትን ልጅ ከዓይኔ ለማውጣት እምቢ አለኝ፤ እርሷን ለማየት ሳላስብ በድንገት እንኳን ስመለከታት በጣም እደነግጣለሁ።

ከትምህርት ቤት ጓደኞቼ ጋር በክፍል ውስጥ ሁሌም ለሶስት ነው የምንቀመጠው። በጣም እንዋደዳለን። አንዱ አበበ ይባላል፤ ሁለተኛው ደግሞ ። ከነዚህ ጓደኞቼ ጋር በጣም ሚስጥር የሆነ ነገር ሳይቀር እናወራለን። ሶስታችንም ምንም ሚስጥር አንደባበቅም። እኔ በልጅቷ ፍቅር እንደምሰቃይ ነገርኳቸው። እነርሱም እኔን በጣም ማደፋፈር ጀመሩ፤ እኔ ግን ድፍረት የሚባል ነገር ከየት ይምጣልኝ? ከጓደኞቼ ተለይቼ ወደ ቤት ስሄድ ስራዬ ስለ እርሷ ማሰብ ብቻ ሆነብኝ። ማታ ማታ እንቅልፍ የሚባል ነገር ከየት ይምጣልኝ? በቃ በጣም ተሰቃየሁ። ወደ ትምህርት ቤት ሄጄ አይኗን ሳያት ትንሽ እረጋጋለሁ። በዚህ ሁኔታ ትምህርቴን መከታተል እራሱ በጣም እየከበደኝ መጣ። ጓደኞቼ ደግሞ ካልነገርካት ብለው በጣም አስገደዱኝ። ነገር ግን ወደ ክፍል ስሄድ እና ዓይኗን ስመለከት ያሰብኩት ነገር ሁሉ ይጠፋብኛል። በቃ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ። እንዴት ሆኜ ፍቅሬን እንደምገልጽላት ግራ ተጋባሁ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳምንቶች አለፉ። በአይን ብቻ መተያየት ሆነ። በዛ ላይ እንዲህ ማሰብ ጀመርኩ “ወደዚህ ለምን መጣሁ? እዛው ሆሳዕና ብሆንስ?” በማለት በጣም ተጨነቅኩኝ።

ወይ ፍቅሬን አልገለጽኩላትም፤ ወይ ከአፏ አንድም ነገር አልሰማሁም፤ ዝም ብሎ የልብ መቃጠል ብቻ። ይሄ ነገር ደግሞ በጣም እየጎዳኝ መጣ። ምክንያቱም ማታ ያለ እንቅልፍ እያደርኩ ነው። በዚህ መሃል ደግሞ ጓደኞቼ በጣም ወጥረው ይዘውኛል። “እስከአሁን ለምን?” አሉ፤ ዛሬማ እነግራታለሁ ብዬ ስዘጋጅ ድፍረት አጣለሁ። ብታሳፍረኝስ እላለሁ፤

ብዙ ነገር ወደ አይምሮዬ ይመጣብኛል። እንዲህ በጨነቀኝ መሃል ደግሞ ልጅቷ በፍቅር ዓይን ትመለከተኛለች። ይህን ነገር ደግሞ ማመን አቃተኝ። አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፥ በእረፍት ሰዓት ወጥተን እስክንመለስ እርሷ ቀድማኝ ወደ ክፍል ገብታ፣ በእኔ ቦታ ላይ ቁጭ ብላ መፃፍ ጀመረች። ጓደኞቼ ደግሞ "አሪፍ አጋጣሚ ነው" ብለው አክለውም "በል አሁን ንገራት። አጠገቧ ቁጭ ብለህ እያጫወትካት፣ ከዛም ንገራት። ልጅቷ ደግሞ በጣም ነው አንተን የምትወድህ" ብለው ገፋፉኝ።

እኔ ግን "አይሆንም! አላደርገውም!" አልኳቸው። እኔ ደግሞ በእርሷ ቦታ ላይ ሔጄ ቁጭ አልኩኝ። ጓደኞቼ በጣም ተናደዱ። በተለይ    የሚባለው ጓደኛዬ በጣም ተናደደ። በክፍል ውስጥ ደግሞ ልጆች አንድ ነገር አመጡ። የክፍል ልጆች ሁሉም በተራ በተራ ተነስተው ቀልድ መናገር ጀመሩ። ለእኔም ተራ ደረሰኝ። ለእኔ ተራ ሲደርሰኝ ደግሞ እምቢ አልኳቸው። በግድም አሳምነውኝ እንድነሳ አደረጉ። ከዚያም ተነስቼ ብዙ ቀልዶችን ማውራት ጀመርኩ። ከዚያ ልጅቷ ከልጆቹ ይልቅ እኔ በማወራው ነገር በጣም ትስቃለች። ለእኔ በጣም ግራ ገባኝ። በኋላ ተራዬን ጨርሼ ቁጭ አልኩኝ። በዚህ ሁኔታ ሳምንቶች አለፉ።

## ክፍል ስድስት

ምንም ባልጠበቅኩት ሰዓት አንድ ነገር ተከሰተ። ቀኑም እሁድ ቀን ነበር። ወደ 10፡30 ሰዓት ላይ ወደ እኔ በማላውቀው፣ 0965 ብሎ በሚጀምር ስልክ ቁጥር ተደወለልኝ። "ማን ይሆን?" ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። ቀኑም እሁድ ስለነበር፤ ለወንድሜም የእረፍት ቀኑ ስለሆነ ወደ ከተማ ወጥተን በተስፋ ካፌና ሬስቶራንት ሻይ ቡና እያልን ነበርን። እኔ፣ ወንድሜ እና የወንድሜ ሚስት   ፣ ሶስታችን ብቻ ነበርን። በድጋሚ ተደወለልኝ። እኔም ስልኩን አንስቼ ማውራት ጀመርኩ። ከዚያ ድምፁ የሴት ድምጽ ሲሆንብኝ፤ ወንድሜንም ስለምፈራው ሻይ ቡና ለማለት ቁጭ ካልንበት ቦታ ቀስ ብዬ ተነስቼ ከእነርሱ ፈቀቅ ብዬ ማውራት ጀመርኩ።

"ሄሎ ዮኒ ነክ አይደል?" አለችኝ። እኔም "አዎን ዮኒ ነኝ" አልኳት። እርሷም መልሳ "እኔን አወቅኸኝ ወይ?" አለችኝ እኔም "አይ አላወኩሽም" አልኳት። እርሷም መልሳ "እስቲ ጠርጥር አለችኝ"። እኔ ግን መልሼ "አይ ላውቅሽ አልቻልኩም እባክሽን ንገሪኝ" አልኳት። እርሷም ነገረችኝ፤ "   ነኝ፣ አሁንስ አወቅኸኝ? አለችኝ" እኔ ደግሞ "   " ስትል በጣም ደነገጥኩኝ። ከዚያም በቃ ሰላምታ ተጠያይቀን እርሷም "ነገ ክፍል ትመጣለህ አይደል?" አለችኝ እኔም "እመጣለሁ" ብዬ ነገርኳት። "በል እሺ ጥሩ" ብላ ስልኩን ዘጋች። በጣም ተደሰትኩኝ፤ ደስታዬን መቆጣጠር እራሱ አቃተኝ። ትንሽ ቆይታ በስልኬ ላይ መልእክት ላከችልኝ፤ መልእክቱም እንዲህ የሚል ነበር "ዮኒ በጣም ነው የምወድህ

በጣም አፈቅርሃለው” ይላል። ማመን አቃተኝ። በጣም በደስታ ልብ እኔም መልሼ በጣም እንደምወዳትና በጣም እንደማፈቅራት ነገርኳት።

ደግሞም “መጀመሪያ ቀን ወደ ክላስ በመጣሁ ቀን ነበር በዓይኔ ላይ የገባሽብኝ። በጣም የወደድኩሽ ያንኑ ቀን ነው። ስለአንቺ ልጆቹን ስጠይቃቸው ጎበዝ ተማሪ መሆንሽን ስለነገሩኝ፣ ደግሞም ለፍቅር ጥያቄ ቦታ አይኖርሽም ብዬ በማሰብ ፍቅሬን ደበቅኩ” ብዬ ነገርኳት። እርሷም መልሳ “ይኸው እኔ ቀደምኩህ” አለችኝ። ወደ ወንድሜና ወደ ስመለስ “ዮኒ ብዙ ሰዓት እኮ ነው የቆየኸው፤ እኔ ነግሬሀለሁ! በኋላ የሀደሮ ሴቶች በፍቅር ካጠመዱ አይለቁህም። ዮኒ ያወራኸው ብቻ ከሴት ጋር እንዳይሆን” ብላኝ ሳቋን ለቀቀችው። ወንድሜም መልሶ “ዮኒ ከሴት ጋር ብቻ እንዳይሆን ይህን ሰዓት ሁሉ ያወራኸው” ብሎ ተናገረኝ። እኔ ደግሞ አይ አይደለም ከሆሳዕና ጓደኞቼ ደውለው ነው፣ ከእነርሱ ጋር ነው ያወራሁት ብዬ ዋሸኋቸው። ከዚያም ሻይ፣ ቡና ብለን በባጃጅ ወደ ቤት ሸኘተናት እኛ ደግሞ ወደ ፑል ቤት ገባን። ጨዋታ በጀመርንበት ሰዓት በስልኬ መልዕክት አደረገች። እኔም ከወንድሜ ፈቀቅ ብዬ ደወልኩላት። ከዚያ በአፏም ጭምር እንደምታፈቅረኝ ነገረችኝ። እኔም መልሼ እንደማፈቅራት ነገርኳት።

ይህ ቀን አልፎ፣ ሌሊቱ ነግቶ፣ በሁለተኛው ቀን ክፍል እስከምንገናኝ በጣም ቸኮልን። ፊት ለፊት እስከምንገናኝ በጣም ተነፋፈቅን። እርሷም በጣም ከመናፈቋ የተነሳ በዚያ ቀን ብዙ ጊዜ ደወለችልኝ። የስልክ ካርድ ሲያልቅ ብቻ ነበር የተለያየነው። ምሽቱንም የጽሁፍ መልእክት በስልክ ስንለዋወጥ አደርን፤ ሌሊቱም እንደምንም ነጋ። ወደ ክፍል ሔድኩኝ፣ ይገርማል። ብቻ በጣም ናፍቃኛለች፤ እኔ ከእርሷ ቀድሜ ነበር ክፍል ውስጥ የደረስኩት። ከቤት እንደመጣች ክላስ ውስጥ አገኘችኝ፤ እንደመጣች እቅፍ አደረገችኝ። በቃ ፍቅራችን ጦፈ። ከዛም ትምህርታችንን ቀጠልን። እስከ እረፍት ክፍለ ጊዜ ተምረን ለእረፍት ወጣን። ከዛም ለብቻችን ሆነን ከማንጎው ዛፍ ስር ሆነን ብዙ ነገር ማውራት ጀመርን፤ ብዙ የፍቅር ወሬዎችን አወራን። በጣም በደስታ ተሞላን። እርሷም ደግሞ ማፍቀሯን እስከምትነግረኝ በጣም እንደተሰቃየች፣ ቀናቶችን እንቅልፍ እንዳጣች ነገረችኝ። እኔም በጣም እንደተሰቃየሁ፣ ማታ ማታ ብቻዬን እንቅልፍ ማጣቴን፣ ብዙ ቀን ደግሞ ማፍቀሬን ልገልጽላት መሞከሬን፣ ግን ድፍረት ማጣቴን ነገርኳት። ያለፈውን ነገር እያወራን እየሳቅን እየተጨዋወትን የእረፍት ክፍለ ጊዜው አልቆ ለመግባት ተደወለ። ወደ ክፍል ገባን።

መለቀቂያ ሰዓት ደርሶ ከመማሪያ ክፍል ተለቀቅን። ሁለታችንም እያዘገምን፣ የልብ የልባችንን እያወራን፣ ከትምህርት ቤት ወጥተን ወደ እነርሱ ሰፈር ትንሽ ሸኘኋት። ከዚያ ለመጀመሪያ ጊዜ ጉንጯን ሳምኳት። በጣም ደነገጠች። አይኔንም ማየት እንኳን ፈራችና

ፊቷን ወደዝያ አዙራ “በል ቻዎ ነገ እንገናኝ” ብላ ተለየችኝ። ትንሽ ከእኔ እንደራቀችኝ ስልኩን አውጥቼ “ ነሽ ሁሌም እወድሻለሁ” ብያት ወደ እኔ ዞር ስትል በጣም ደስተኛ ሆና እጇን እያወዛወዘች ምልክት ሰጠችኝ። እኔም ወደ ሰፈሬ ተመለስኩ። ቤት እንደገባሁ ደውላልኝ “ማርዬ ቤት ገባክ?” አለችኝ፤ እኔም “ማርዬ እንደገባሁ ደወልሽ” አልኳት። ከዛም “በል እስከምትገባ አልበላም ብዬ ስጠብቅህ ነበር አለችኝ”። እኔም “እሺ! ምሳ በልተን በኋላ እንደዋወል” ብያት ስልኩን ዘጋሁ።

በኋላ ላይ ምሳ በልተን፤ ትንሽ አርፈን በስልክ አውርተን ስናበቃ፤ በኋላ እንደዋወላለን ተባብለን ተለያየን። ማታ ቤት ውስጥ ስለማይመቸኝ በጽሁፍ መልእክት ብቻ ነበር የምናወራው። እስከ 5፡30 እና 6፡30 በጽሁፍ መልእክት እያወራን እንቆያለን። በዚህ መሃል የትንሳኤ በአል ዋዜማ ደረሰ። በዚህ በዋዜማው ላይ ስጦታ ልንለዋወጥ ለመጀመሪያ ጊዜ መንገድ ላይ ተቀጣጠርን። ቦታውም ኤልፎስ ት/ቤት ፊት ለፊት ነበር። በዚህ ቦታ ተደዋውለን ተገናኘን፤ ስጦታም ተለዋወጥን። ዋዜማም ስለሆነ እረጅም ሰዓት አልቆየንም። ትንሽ ጊዜ ብቻ ቆይተን፣ የስጦታ ወረቀት (Postcard) እና ሌሎች ስጦታዎችን ተለዋውጠን፣ ተሳስመን፣ በጣም በደስታና በመነፋፈቅ ተለያየን። እንደተለያየን እርሷን ዘወር ብዬ እየተመለከትኩ ስልክ ደወልኩላት። እርሷም ዘወር ብላ እያየችኝ ስልኩን አነሳች። እኔም “ማርዬ ሁሌም አፈቅርሻለሁ፣ ገና ሳልርቅሽ በጣም ናፈቅሽኝ” አልኳት እርሷም መልሳ “ማርዬ ብቻ በቃ ከበዓል በኋላ እንገናኝ፣ በጣም ውድድድ አደርግሀለሁ” ብላ ስልኩን ዘግታ እጇን አውዛውዘችልኝ። እኔም እጄን አንስቼ ቻው አልኳት።

## ክፍል ሰባት

የትንሣኤ በዓል አለፈ። ትምህርትም ተከፈተ። ወደ ክፍል ስሔድ እርሷ ቀድማኝ ደርሳ ነበር። ይገርማል! በጣም ተነፋፍቀናል። ተገናኘንና ሰላም ተባብለን ስለ በዓሉ ማውራት ጀመርን። በዓሉን በአሪፍ ሁኔት እንዳሳለፈች ነገረችኝ። እኔም በጣም በሚገርም ሁኔታ አሪፍ ጊዜ እንዳሳለፍን ነገርኳት። አስተማሪም ወደ ክፍል ገብቶ ማስተማር ቀጠለ። እኛም ትምህርታችንን ጀመርን። ሶስቱም ክፍለ ጊዜው ካለቀ በኋላ ለእረፍት ወጣን። ከዛም በማንጎው ዛፍ ስር ሆነን የልብ የልባችንን ማውራት ጀመርን። ብዙ ነገር እያወራን በምንጨዋወትበት መሀል በድንገት ከአፍንጫዬ ነስር ወጣኝ። በጣም ደነገጠች፤ እምባዋ ከዓይኖቿ መፍሰስ ጀመረ። እኔ ደግሞ በአፍንጫዬ ላይ ሶፍት አደረኩኝና በጣም አባበልኳት። እርሷ ግን “ማርዬ ምንድን ነው የሆንክብኝ?” እያለች በጣም አለቀሰች። በኋላ ላይ ሙቀት ሲበዛ ነስር እንደሚመጣብኝ ነገርኳት። ከዚያም ተረጋጋች። ከዚያ በኋላ ውሃ ወዳለበት ወደ ቧምቧ ሔጄ ታጥቤ ወደ ክፍል ተመልሰን ገባን።

ሁሉንም ክፍለ ጊዜ ጨርሰን ወደ ቤት መለቀቅያ ሰዓት ደረሰ። ተለቀቅንና ከሰዓት በኋላ እንድንገናኝ ተቀጣጠርን። እኔም ቤት ደርሼ፣ ሻውር ገብቼ፣ ምሳ በልቼ ከጨረስኩ በኋላ ትንሽ አርፌ፣ ከዚያም ስልክ ደወልኩላት። እርሷም እንዲህ አለችኝ “ከቤት ልወጣ ነው አንተም ወጥተህ ወደ ታች ወርደህ ጠብቀኝ” አለችኝ። እኔ ከቤት ቶሎ ብዬ ወጥቼ፣ ባጃጅ ይዤ፣ ከሰፈራችን ትንሽ ወረድ ብዬ ጠበቅኳት። ይገርማል! የትምህርት ቤት የደንብ-ልብስ ቀይራ፣ በጣም የሚያምር ልብስ ለብሳ እጅግ አምሮባት ከባጃጅ ወርዳ ወደ እኔ መጣች። ምን ልበል? ውበቷ ያበራል። በቃ ልቤን አቀለጠችው።

ከዚያም “የት ሔደን ኢንጆይ እናድርግ?” አልኳት። እርሷ ደግሞ መልሳ እንዲህ አለችኝ “ሰው የሌለበት ፀጥ ያለበት” አለችኝ። እኔ ደግሞ በጣም ግራ ገባኝ። ሀገሩን በደንብ አላውቅም እና የት እንደምወስዳት ግራ ገባኝ። አንድ ሀሳብ መጣልኝ “በሀደሮ ከተማ ሁለት በጣም የታወቁ ሎጆች (Lodges) አሉ። ወደዚያ እንሂድ?” አልኳት። እርሷም “አይ አይሆንም፣ በጣም ሰው እፈራለው። ፀጥ ያለ ቦታ ብቻ ውሰደኝ” አለችኝ:: እንደገና አንድ ነገር ወደ አይምሮዬ መጣልኝ። ከዚያ በፊት ከጓደኞቼ ጋር ወደ ወንዝ ዳር ሄደን ብዙ ጊዜ እንቀመጥ ነበር። በክፍል ውስጥ በጣም የምንዋደድ ሁለት ልጆች አሉ። እነርሱም በጣም ሚስጥራችንን የማንደባበቅ ልጆች ናቸው። በዚህ በወንዝ ዳር ከክፍል መልስ ማለትም ከሰዓት በኋላ ሁሌም ወደዚህ ቦታ እንሄድ ነበር። ይህችን ልጅ ማፍቀሬንም፣ እርሷም ወደ እኔ ደውላ ፍቅራችንን መገላለፃችንን በዚህ ቦታ ነበር የነገርኳቸው። ይህን ነገር ስነግራቸው በጣም በደስታ ተሞልተው፣ በጣም ደስ ብሏቸው ነበር። በጣም ምስጢር የሆኑ ነገሮችን ሶስታችንም መጥተን በዚህ ቦታ ስለምናወራ ይህ ቦታ ትዝ አለኝ። ምክንያቱም እርሷ እንደምትፈልገው ቦታው በጣም ፀጥ ያለና በጣም ደግሞ ፍቅር የሚያስዝ ነው።

“ወደዚህ ቦታ እንሂድ” አልኳት። እርሷም እሺ ብላ ተስማማች፤ ወደዚያ ጉዞ ቀጠልን:: ከከተማው ወደ 15 ደቂቃ ይርቃል። በእግራችን እየተጓዝን ቦታውን ደረስን። እርሷም በወንዙ ዳር ባሉት የዛፍ ስሮች፣ በቦታው አቀማመጥ በጣም ተገረመች። “ይህን ቦታ እንዴት አወቅከው? አንተ ስለ ሀደሮ አታውቅም ግን ይህን ቦታ እንዴት አወቅክ? ማን አሳየህ?” ብላ በጣም ተገረመች። እኔም ብዙ ጊዜ ወደዚህ ቦታ ከጓደኞቼ ጋር እንደምመጣ ነገርኳት። በጣም ደስ አላት፤ ከዚያም ተቀምጠን ጣፋጭ የሆነ ወሬያችንን ጀመርን። እኔም በጨዋታ መሃል አንድ ነገር ልነግራት አሰብኩኝ፤ ስለ እኔ ምንም ልደብቃት አልፈለግኩም ነበር። ምክንያቱም በጣም ስለወደድኳት ስለ ማንነቴ ሁሉንም ነገር ግልጽ አርጌ ልነግራት በውስጤ ወሰንኩኝ።

በጨዋታ መሀልም “ማርዬ” አልኳት እርሷም “ወዬ ማር” አለችኝ፣ አንድ ነገር ልነግርሽ እፈልጋለሁ አልኳት። እርሷም “እሺ ንገረኝ” አለችኝ። ከዚያም “የዛሬ ስድስት ዓመት፣ ማለት ለኔ ትልቅ የሀዘን ቀን ነበር” አልኳት። በጣም ደነገጠች፤ አይኖቿም እምባ አቀረሩ። እኔም መልሼ “ምን መሆንሽ ነው ማርዬ? እንዲህ የምትሆኚ ከሆነ ከኔ ምንም ነገር መስማት አትችይም። በትዕግስት አዳምጪኝ አልኳት”። ከዚያም በ2002 ላይ እናቴ እንደሞተች ነገርኳት።

እምባዋን መቆጣጠር ሲያቅታት እኔም እምባዋን አይቼ የእኔን እምባ መቆጣጠር አቃተኝ። በኋላ ላይ ተቃቅፈን እረጅም ሰዓት በጣም አለቀስን። በቃ መጥፎ ትዝታ ስላሰብኩኝ እምባዬን ማቆም እምቢ አለኝ። እርሷም መልሳ እኔን መለመን ጀመረች። እንደምንም እምባዬ ቆመ፤ ከዚያም እንዲህ አልኳት “ማርዬ አንድ ነገር ቃል ግቢልኝ?” ብዬ ጠየቅኋት። እርሷም “ማርዬ የፈለግከውን ነገር ጠይቀኝ፣ ቃል እገባልሃለሁ” ብላ ነገረችኝ። “ከስድስት ዓመት በፊት ያጣሁትን ፍቅር፣ የእናቴን ፍቅር እተካለሁ ብለሽ ቃል ግቢልኝ” አልኳት። “ደግሞም እንደእናቴም፣ እንደእህቴም፣ እንደጓደኛዬም፣ በቃ ሁሉ ነገሬ እንድትሆኚ እፈልጋለሁ። ማርዬ ይህን ሁሉ ማድረግ ትችይዋለሽ ወይ?” ብዬ ጠየቅኳት። እርሷም መልሳ እንዲህ አለችኝ “ማርዬ ምንም ነገር ቢፈጠር መቼም ቢሆን ከጎንህ እሆናለሁ። ደግሞም ሁሌም ከልቤ አፈቅርሃለሁ። በጌታ ፊት ቃል እገባለሁ” ብላ ቃል ገባች። እኔንም “ሁሌም ከጎንህ እሆናለሁ” ብላ ቃል ገባችልኝ። “ደግሞም ምንም ቢፈጠር አልተውሽም” ብለህ በጌታ ፊት ቃል ግባልኝ አለችኝ። እኔም “ማርዬ በምንም ሁኔታ ውስጥ መቼም ቢሆን አልረሳሽም” ብዬ ቃል ገባሁ።

ከዚህም በኋላ ስለ ወደፊት እያወራን የከፍተኛ ትምህርታችንን ጨርሰን እንደምንጋባ፣ ስለ ወደፊት ጥሩ ጥሩ የሆኑ ነገሮችን እየተመኘን በዚህ በአሪፍ ጨዋታ ውስጥ ቀኑ መሸ፡ ፡ ሳናውቅ ሰዓቱ ወደ 12፡40 አካባቢ ደረሰ፤ ከዚያም ወደ ከተማ ወጣን። የእኛ ሰፈር 01 ቀበሌ ነው፤ የእነርሱ ግን ከኛ ሰፈር ትንሽ ይርቃል። በባጃጅ 10 ደቂቃ ይወስዳል። ከዚያም ወደ ዋናው አስፓልት ወጥተን ባጃጅ አገኘን። ከዚያም ኮንትራት ተስማማን። ምክንያቱም ከእኛ ወደ እነርሱ ሰፈር በባጃጅ ሰስት ፌርማታ ነው። እርሷን ወደቤቷ ካስገባኋት በኋላ እኔን ወደ ሰፈሬ እንዲመልስ ተስማማን። ከዚያም እርሷን ወደ ቤት አደረስናት፤ እኔንም ወደ ቤቴ መለሰኝ።

# ክፍል ስምንት



በቃ ፍቅራችን ጦፈ። በጣም ይገርማል ሳንደዋወል አንድ ቀን ውለን አናውቅም። ምሽት የጽሁፍ መልእክት ሳንፃፃፍ አድረን አናውቅም። በዚህ ሁኔታ ትምህርታችን መማር ቀጠልን። ይገርማል! ብቻ ጓደኞቼ ከእኔ በላይ በጣም ደስተኞች ናቸው። ሁሌም ይጠይቁኛል። ደግሞም እንዲህ ይሉኛል "ፍቅራችሁ በጣም ያስቀናል፤ በጣም ደስ ትላላችሁ" ይሉኛል። በተለይ በትምህርት ቤት ውስጥ ስለ እኔና ስለ እርሷ የማያውቅ የለም፤ በዚህም ልጆች በጣም ይቀናሉ። በተለይ በክፍል ውስጥ በጣም የሚወደኝ ልጅ፣ አንድም ቀን የማንለያይ አንድ ልጅ አለ። ሌላም ደግሞ በጣም የምንዋደድ ልጅ አለ። ስማቸውም የአንደኛው የሁለተኛው ይባላሉ:: እነዚህ ልጆች መጀመሪያ እንኳን ከሆሳዕና ወደ ሀደሮ በሄድኩ ጊዜ፣ በዚህ በሀደሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ቀደም ብዬ የተዋወቅኳቸው ልጆች ናቸው። እነኚህ ልጆች ስለ ሁለታችንም፣ ማለቴ ስለ ሳይጠይቁኝ አድረው አያውቁም። ደግሞም በጣም ያስቃሉ። ከልጅቷ ጋር ተገናኝቼ በመጣሁ ጊዜ ሁሉ እንዲህ ይሉኛል "ዛሬማ ከንፈሯን ስመሃታል። በል ኸረ አንተ ልጅ ምን ሆነሃል? ይህን ያህል ቀን ከንፈሯን ሳትስም?" እያሉ በጣም ያስቁኛል። በጣምም ደግሞ ያስጨንቁኛል። ብቻ ይገርማል። በጣም ቀልደኞች ናቸው። ክፍል ውስጥ ደግሞ በጣም ቀልድ ያወራሉ፤ ልጆችን ፈታ ያደርጋሉ።

በዚህ ደግሞ እነኛን ሁለቱንም ልጆች በጣም እወዳቸዋለሁ። ሁሌም ከትምህርት ወጥተን ወደ ወንዝ ዳር ሄደን እንጫወታለን። ከትምህርት ቤት አንደ ተመለስን ወደዚህ ቦታ ሄደን ፎቶ እንነሳለን፣ እንጫወታለን። ለነዚህ ልጆች ምንም ደብቄአቸው አላውቅም ነበር። በትምህርት ቤት ውስጥ አንድ አንድ ሴቶች በድፍረት መጥተው የፍቅር ጥያቄ ሲጠይቁኝ እንኳን ለነዚህ ለሁለቱ ልጆች ደብቄ አላውቅም። ከነዚህ ከሁለቱ ልጆች ጋር ወደ መዝናኛ ቦታ ሁሌም እንሄዳለን። በድንገት አይኔ ላይ ባያት ብዬ በሰፈራቸው ሁሌም እናልፋለን፤ በድንገት ያየኋት ቀን፣ ትንሽ አውርተን በደስታ ወደ ሰፈራችን እንመለሳለን።

ይገርማል! ብቻ ጉዳይ እንዳለው ሰው ከክፍል ወጥተን ከሰዓት በኋላ ወደ 10፡00 ሰዓት ሁሌም ወደ እርሷ ሰፈር እንሄዳለን። እነኛ ሁለቱ ልጆች ደግሞ እኔ ያልኩትን ነገር ምንም ቢሆን እምቢ ብለው አያውቁም። በጣም ስለሚወዱኝ ስለ እኔ ደስታ ሲሉ ከእኔ ጋር ሁሌም ወደ እርሷ ሰፈር ይሄዳሉ። እርሷን ካገኘኋት በደስታ እንመለሳለን። እርሷም ሳታየኝ አንድ ቀን መዋል በፍፁም አትችልም። አባቷ በጣም በጣም ይቆጣጠራታል። ከቤት ወጣ ብላ በር ላይ እንኳን ከሰፈር ወንዶች ጋር ቆማ ቢያያት ቤት ውስጥ አስሮ ይገርፋታል። እንደዚህ ቁጥጥር ውስጥ ሆናም እንኳን እንደምንም ሆና ሳታየኝ ማደር አትችልም። ከሰፈራቸው ትንሽ እራቅ ብሎ ሐዋርያት ቤተክርስትያን አለ። በዚህ ቦታ ሁሌም እንገናኛለን። በቀን በክፍል ውስጥ ብንገናኝም እንኳን በዚህ ቦታ ላይ፣ ማታ 1፡30 ላይ ተገናኝተን ትንሽም ቢሆን ሳናወራ አንድም ምሽት አድረን አናውቅም። በቀን በክፍል ውስጥ እንገናኛለን። ሆኖም ግን ማታ ምሽት ከ1 ሰዓት በኋላ በዚህ በሐዋርያት ቤተክርስትያን ፊት ለፊት ተገናኝተን ካልተያየን ማታ እንቅልፍ እሺ አይለንም። እንዲህ በቀን ውስጥ ይህን ያህል ጊዜ ብንገናኝ እንኳን ናፍቆታችን በጭራሽ ቀንሶ አያውቅም ነበር።

## ክፍል ዘጠኝ

ከእለታት አንድ ቀን እንደልማዳችን ሶስታችንም ሆነን ወደ እነርሱ ሰፈር አቋርጠን እያለፍን ነበር። እንደተለመደው ምን አልባት በድንገት ወደ መንገድ ወጥታ አገኛታለሁ በማለት የተለመደውን ነገር አደረግን። ይህ የተለመደው ነገር ደግሞ ለእኔ ሰበብ አመጣብኝ። በሰፈራቸው አልፈን ወደ መዝናኛ ቦታ እንደደረስን ስልኬ ሲጠራ ከኪሴ አወጣሁት። ይላል እኔም በደስታ ስልኩን አንስቼ “ማርዬ” አልኳት እርሷም መልሳ “ለምን ማርዬ ትለኛለህ? ምንድን ነው ያደረግኸው? ያደረግኸውን ሁሉ አይቻለሁ። በቃ ይበቃል! ከእንግዲህ አትደውልልኝ!” አለችኝና ስልኩን በጆሮዬ ላይ ዘጋች። በጣም ደነገጥኩ፤ ለኔ ያወራችው ነገር ግራ ገባኝ። በጣም በሀሳብ ውስጥ ገባሁ። ጓደኞቼም በጣም ፊቴ ሲቀየር አይተው “ምንድነው በስልክ የሰማኸው?” አሉኝ። እኔም እንደሆነች ደግሞም ያለችኝን ሁሉ ነገርኳቸው። እነርሱም መልሰው “በል አሁን ደግመህ ደውልላት” ሲሉ አስገደዱኝ። እኔም ጓደኞቼን እምቢ ለማለት ስለማልችል እሺ ብዬ መልሼ ስልኩን ደወልኩ። ስልኩንም እረጅም ሰዓት ከጠራ በኋላ አነሳች እና “ደግሞ ምንቀረብህ?” አለችኝ። በጣም ተናደድኩኝ። ምንም ባላወቅኩት ነገር ብዙ ነገር በኔ ላይ ደረደረች። በጣም ከመናደዴ የተነሳ ስልኩን ማውራት አቃተኝ።

የምለው ጓደኛዬ ስልኩን ከጆሮዬ ላይ ነጥቆ ወሰደና በትዕግስት ችግሩን ጠየቃት። ሁሉንም ነገር ነገረችው። ልጁም ስልኩን አናግሯት ከጨረሰ በኋላ በእኔ ላይ

የተቀየመችበትን ሁሉንም ነገር ነገረኝ። በሰፈራቸውም ስናልፍ በእኔ ስልክ ላይ ወደ ጫካ ሔደን የተነሳነውን ፎቶ እያዩ እየሳቁ ለካ እርሷ በድንገት አይታናለች። እርሷ ደግሞ በስልኬ ላያ ያለውን ከእርሷ ጋር ያወራሁትን ሚስጥር ያሳየኋቸው መስሏት ነበር። የእኔን ሚስጥር መልእክት እንዴት ለሰው ታሳያለህ ብላ በጣም ተቀየመችኝ። በዚህም የተነሳ በጣም እኔን የሚያናድድ ነገር አወራች። እንዴት በዚህ በትንሽ ነገር? ደግሞም ምንም ባላደረኩት ነገር ለምን? ብዬ በጣም ተፀፀትኩ። ምክንያቱም ለእኔ ብዙ ቃል ገብታልኝ እንዴት ባላረጋገጠችበት ነገር እንዲህ ሆነች? ብዬ በጣም በሀሳብ ተጎዳሁ። ጓደኞቼ ሊያጽናኑኝ ቢሞክሩም በሰዓቱ ማንም እንዲያዋራኝ ፈቃደኛ አልሆንኩም ነበር። ምክንያቱም አንድም ቀን እንኳን፤ አንድም ማታ ሳንተያይ ሳንደዋወል ማሳለፍ የማንችል ሰዎች ሆነን እንዴት እንዲህ አሰበች? ብዬ በጣም ተበሳጨሁ። በዚህ ሁኔታ ላይ በክፍል ውስጥም እንተያያለን ግን አናወራም። በዚህ ላይ ደግሞ ክፍል ውስጥ ብቻዋን ቁጭ ብላ ታለቅሳለች። በእረፍት ክፍለ ጊዜ ከልጆች ጋር ድሮ ለመጫዎት የምትወጣው ቀርቶ አሁን ግን በዚህ ጊዜ ሀዘን በሀዘን ሆነች።

ክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ መግለጫ ለማስረዳት የምትነሳው እርሷ ነበረች። በቃ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ እራሱ ማድረግ እምቢ አለች። አስተማሪዎች በእርሷ ላይ በጣም እስከሚገረሙ ተለውጣለች። በዚህ ሁኔታ አንድ አንዴ ክፍል አቋርጣ በእረፍት ወደ ቤት መሄድ ጀመረች። በዚህ መሀል እያለን  የምለው ጓደኛዬ ግማሽ ተማሪ ወደ እረፍት ወጥቶ ግማሽ ተማሪ ቀርቶ፤ ክፍል ውስጥ ተነስቶ በጥቁር ቦርድ ላይ እንዲህ የሚል ዘፈን መፃፍ ጀመረ። "ኸረ አስታራቂስ የለም ወይ? ሀይ የሚለን ሰው ገላጋይ? ቀናት አለፉ ተኮራርፈን፤ ምን ነክቷቸው ነው የሚለን አንድም ሰው አጥተን" የሚል የአብነት አጎናፍር ዘፈን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ፃፈ። በኋላ ላይ ከሳምንት በኋላ የእርሷ ጓደኛ ወደ እኔ ደወለች፤ ልጅቷ ትባለለች። ስለ ሁለታችንም በተለይም ስለ ፍቅራችን በጣም ስለምታውቅ እኔ ጋር በመደወል እንዲህ አለችኝ "ዮኒ አንድ ነገር ላስቸግርህ፣ ወደ ታች ወደ እኛ ሰፈር መምጣት ትችላለህ?" አለችኝ።

እኔም " መምጣት እችላለሁ፣ ግን ለምንድነው አልኳት?" እርሷም "ስትመጣ እነግርሃለሁ በእናትህ?" ስትለኝ እኔ ደግሞ የእናት ስም ከተነሳ ምንም ነገር ማድረግ ስለማልችል "እሺ" አልኳት። ነገር ግን ከልጅቷ ጋር በስልክ ብዙ ነገር አውርተን "ሁለተኛ አልደውልልሽም፣ ከእኔ በላይ የወደድሽውም ሰው ካላ ከእንግዲህ አላስቸግርሽም" ብዬ የጽሁፍ መልእክት በስልኳ ልኬ ሁሉን ነገር ጨርሻለሁ። ምክንያቱም ሁሉን ነገሬን ነግሬአት፣ ስለ እኔ ሚስጥሬን ሳይቀር ነግሬአት እውነት ይሁን ውሸት ባላረጋገጠችው ነገር እንዴት በቀላሉ እንዲህ ሆነች? ብዬ በጣም በእርሷ ላይ ተስፋ ቆርጬ ነበር።

ይህች ልጅ፣ ማለትም በጣም ስለለመነችኝ፤ ደግሞም በእናቴ ስም ስለለመነችኝ ወደዚያ ቀጠሮ ቦታ ለመሄድ እሺ አልኳት። ወደ ቀጠሮ ቦታ ደረስኩኝ። በቤታቸው ፊት ለፊት እራሷ የምትሰራበት ቡና ቤት አላት። በዚህ ቤት ለእኔም ቡና ቀድታልኝ ስታበቃ በጣም እንደተጎዳች ነገረችኝ። “ደግሞም አንተ እራስህ ስታያት በጣም ታዝናለህ” አለችኝ። ይህን ነገር ሁሉ ከነገረችኝ በኋላ “ልጥራት እንዴ?” አለችኝ። እኔም እሺ አልኳት። የ ቤት ከቡና ቤቱ በጣም ቅርብ ነው። ቶሎ ብላ ጠራቻት። ሁለቱም አብረው መጡ፤ ከዚያም እንደገባች ወደእኔ መጣችና ምንም አላወራችም። አቀርቅራ ሰላም አለችኝ። እኔም ምንም ሌላ ነገር ላወራ አልፈለኩም ነበር።

ሰላም ከተባባልን በኋላ እኔ “ይህን ያህል ቀን እንዴት ቻልሽ?” አልኳት። እርሷም “ማርዬ በጣም በጭንቀት ነው ያሳለፍኩት። አንድም ቀን ሳላስብህ ውዬ አድሬ አላውቅም” አለችኝ። እውነትም እንዳለችኝም በጣም ተቀይራለች፤ እኔም በጣም አዘንኩላት። በጣም ተጎድታለች። በኋላ ላይ ብዙ ነገር አወራን፤ ይቅር ተባብለን ደግሞም በስልኬ ላይ ጓደኞቼ ያዩት ነገር ሚስጥር የሆነ ነገር እንዳይደለ ነገርኳት። እርሷም “የእኔን እና ያንተን ሚስጥር ያሳየሃቸው መስሎኝ ነው” ብላ ተናገረች። በዚህ ሁሉንም ነገር ፈታነው።

## ክፍል አስር

ሁሉም ነገር አለፈ። ፍቅራችንም እንደድሮ ቀጠለ። እንደልማዳችን በተለመደው ሰዓት በአንድ ሰዓት ከሰላሳ ላይ በተለመደው ቦታ በሐዋርያት ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት እየተገናኘን ጥሩ የሆነ የፍቅር ጊዜያችንን ቀጠልን። በአንድ በኩል ትምህርታችንን በሌላ በኩል ደግሞ ፍቅራችንን እያደረግን ኑሮአችንን ቀጠልን። በዚህ ውጣ ውረድ ውስጥ ዘጠነኛ ክፍልን አጋመስን።

ዘጠነኛ ክፍል እየተማርኩ የእረፍት ሰዓት በደረሰ ጊዜ የሶስተኛ ክፍለ ጊዜ ማለቅያ አካባቢ ላይ ወደ እኔ ስልክ ተደወለ። በሀዋሳ የምትኖር የአክስቴ ልጅ እንደሞተች ተነገረኝ። ምንም ሳላወራ መምህሩን አስፈቅጄ በቀጥታ ከክፍል እንደወጣሁ ወንድሜ ጋር ደወልኩለት። ወንድሜ ስልኩን አያነሳም። ባንክ ላይ በስራ ተጠምዶ ሆኖ ይሆናል ብዬ ደጋግሜ ስደውልለት ስልኩን አነሳ። ከዚያም በሀዋሳ የአክስታችን ልጅ እንደሞተች ነገርኩት። እርሱም በጣም ደነገጠ። ወዲያው ፍቃድ አጽፎ ከባንክ ወደ ቤት መጣ። አራት ሰዓት ከ ሰላሳ ላይ ከሀደሮ ወደ ወላይታ ተሳፈርን። ወላይታ ከደረስን በኋላ ምግብ እንኳን መብላት አልፈለግንም፤ ስለዚህ ውሃ ብቻ ከሱቅ ገዝተን ጉዞአችንን ቀጠልን።

በዱቲ ላይ መኪናው ለምሳ ቆመ፤ እኛ ግን ለመብላት በጣም አስጠላን። ከዚያም ከቦዲቲ ውሃ እና ቆሎ ገዝተን ጉዞአችንን ቀጠልን። ከዚያም ጉዞውን ጨርሰን ወደ ለቅሶ

ቤት ደረስን። በጣም ስለመንዋደድ በጣም አለቀስን። ስሟም ይባላል። እኔ በተለይ ስሟን እየጠራሁ በጣም አለቀስኩ፤ አክስቴም በጣም ለመነችኝ። “ልናመጣት አሁን እኮ አንችልም በቃ እረፍ ብዙ አታልቅስ” ብላ በጣም ተቆጣችኝ። ምን ያደርጋል አንዴ የሆነ ነገር ሆኗል ብዬ፤ ደግሞም እንደዚ አይነት ነገር ለኔ የመጀመሪያ ስለአይደል በእናቴም የደረሰ ነገር ስለሆነ፤ እኛ ወደ እነርሱ እንሄዳለን እንጂ እነርሱ ወደ እኛ ስለማይመጡ፤ እኔም በግድ ነገሩን ለመርሳት ጀመርኩኝ። ከዛም ከተረጋጋን በኋላ ስልኬን ስመለከት አስራ ሶስት ጊዜ ተደውሎአል።

የስልኬን security code [የሚስጥር ቁልፍ] ከፍቼ ስገባ ይላል። በጣም ደነገጥኩኝ፤ ከዚያም ከለቅሶው ቤት ወጣ ብዬ ስደውል ስልኩን አንስታ “ማርዬ አይዞህ በቃ ብዙ እንዳታስብ፣ ብዙ እንዳትጨነቅ እራስህን ያምሃል” ብላ በጣም አባበለችኝ። በጣም ደግሞ እንደናፈቀችኝ ነገረችኝ፤ ደግሞም ወደ ሀዋሳ እመጣለሁ ብላ በጣም አስቸገረችኝ። የዚያን ሰሞን ደግሞ የትምህርት ማለቂያ አካባቢ ስለነበር ፈተና ቀርቧል። ደግሞም ለወንድሜ ከባንክ ቤት ብዙ የእረፍት ቀን ስለማይፈቅዱለት ቶሎ እንደምንመለስ ነገርኳት። በቃ ይህን ነገር ስለ ነገርኳት በጣም ደስ አላት “እንዲህ ከሆነ ጥሩ! ማርዬ ቶሎ ናልኝ?” አለችኝ።

ወደ አምስት ቀን ያህል ቆየን፤ ከዚያም በስድስተኛው ቀን ወደ መዝናኛ ቦታ ወደ ፍቅር ሐይቅ ሔድን። እዚያ ትንሽ ሰዓት ቆይተን፤ ፎቶ ተነስተን፤ ሐይቅ ላይ ትንሽ ተዝናንተን፤ እኔም ደግሞ በሐይቁ ዳር የእጅ ጌጦች ከሚሸጡት ሰዎች ለማርዬ እወድሻለሁ የሚል የእጅ ጌጥ ገዝቼላት በቦርሳዬ ላይ ደበቅኩት። ከዛም የዓሳ ስጋ በላን። የዓሳ ስጋ ደግሞ በጣም ደስ አለኝ። በሆሳዕና ዙሪያ ሐይቅ ስለሌለ ከዚያ በፊት ዓሳ በልቼ አላውቅም ነበር ዓሳውም ወዲያው የተጠመደ ትኩስ ነው። ከዚያም ከፍቅር ሐይቅ ወደ መኖሪያ በኪራይ ባጃጅ ተሳፈርን። ብዙም ስለሆንን ሁለት ባጃጅ ኮንትራት ያዝን። እኔ፣ አባቴ፣ ፣ ፣ እና የወንድሜ ሚስት እንዲሁም ሁለት የአክስቴ ልጆች በተጨማሪም አንድ አክስቴ ልጅ ታረቀኝ እና የሀዋሳዋ አክስቴ ልጅ ሆነን ወደ መኖሪያ ከደረስን በኋላ ሁላችንም በየቦታችን ተበታተንን።

አባቴ ወደ ሆሳዕና ከአክስቴ ልጅ ከ ጋር አንድ ላይ ተሳፈሩ። ከባለቤቷ ጋር ወደ አዲስ አበባ መኪና ገባች። እኔ፣ እና እህቴ ፤ ሦስታችንም ወደ ወላይታ ተሳፈርን። ሁላችንንም ሸኝቶ ወደ ሰፈሩ ተመለሰ። እኛም በመንገድ ላይ ሆነን እርስ በእራሳችን ተደዋወልን። እኔ፣ እና ወላይታ ከደረስን በኋላ፤ ወደ ምሳ ቤት ገብተን ምሳችንን በልተን ከዛም ሻይ ቡና ብለን ስናበቃ ወደ አባቴ ጋር ደወልን። አባቴ ወደ ሆሳዕና እንደደረሰ ነገረን፤ እኛም በሰላም ወደ ወላይታ እንደደረስን ነገርኩት። ወደ

ጋር ስንደውልለት ገና መንገድ ላይ መሆኑን ነገረን። ከዚያም ከወላይታ ወደ ሀደሮ ከተማ ተሳፈርን። በዚህ ሁሉ ጊዜ በድምጽ ለማውራት ስላልተመቸኝ፤ በዛ ላይ ወንድሜን ስለምፈራው ከማርዬ ጋር የምናወራው በጽሁፍ መልእክት ነበር። ከዚያም ከወላይታ ወደ ሀደሮ ትራንስፖርት መያዛችንን በመልክት ነገርኳት። በጣም ንፍቅ ብላኝ ነበርች። በየደቂቃው “የት ደረስክ?” እያለችኝ ስትጠብቀኝ ነበር።

ወደ ሀደሮ፤ ወደ ቤታችን በሰላም ደረስን። ፤ ማለትም የወንድሜ ሚስት ሀደሮ ስንደርስ ወንድሜን ሳመችው። ለ መንገድ ላይ እየመጣን እንደሆነ ነግረናት ስለነበረ ቡና አፍልታ እና ምግብ ሰርታ ተቀበለችን። ቤቱንም ፏ አድርጋ ነበር። በየደቂቃው ግን መደወሏን አላቋረጠችም ነበር። ወደ ቤት በሰላም ደረስን። ሁላችንም ገላችንን ታጠብን። ምግብ ከበላን እና ቡና ከጠጣን በኋላ፤ እኔ የወንድሜን ሚስት ወንድሜንም ጭምር ቤት ውስጥ ትቼአቸው ቀስ ብዬ ከቤት ወጥቼ በሞተር ለማግኘት ወደ ሰፈራቸው ሔድኩኝ። ወደ ሰፈራቸውም ቀረብ ብዬ ስልክ ደውዬላት “ማርዬ በሐዋርያት ቤተክርስትያን ፊት ለፊት እየጠበቅኩሽ ነው። ማርዬ ቶሎ ነይልኝ?” አልኳት። እርሷም ከናፍቆቷ ብዛት የተነሳ በጣም በእሩጫ ወደ እኔ መጣች።

ገና ከእሩቅ እዳየኋት በደስታ እራሴን መቆጣጠር አቃተኝ። ወደ እኔ ቀረበች፤ እረጅም ሰዓት ተቃቅፈን እየተሳሳምን ፍቅራችንን አጣጣምን። ከዚያም ስለ ቆይታዬ ስትጠይቀኝ ነበር። በቃ ስለአሳለፍነው ቀናቶች እያጫወትኳት ከሀዋሳ ከፍቅር ሐይቅ የገዛሁላትን የእጅ ጌጥ ሰጠኋት። ጌጡ ላይ የተጻፈው ጹሁፍ “እወድሻለሁ” ይላል። በእጇ ላይ አድርጋ አነበበችና በጣም እቅፍ አርጋኝ ሳመችኝ። ከዛም “ማርዬ እኔም ውድድድድድ አደርግሃለሁ፤ ሁሌም አፈቅርሃለሁ፤ ሁሌም ከጎኔ ላጣህ አልፈልግም” ብላ እንዳቀፈችኝ እምባዋን ማፍሰስ ጀመረች። እኔም “ማርዬ ሁሌም ከጎንሽ ነኝ፤ ለምን ታለቅሻለሽ?” ብዬ በጣም አባበልኳት። ከዚያም ወደ ሰፈራቸው ትንሽ ሸኝቻት እኔም ወደ ቤት ተመልሼ ሔድኩኝ።

## ክፍል አስራ አንድ

ከሀዋሳ ከተመለስን በኋላ በሁለተኛው ቀን ሰርኘራይዝ [ድንገተኛ አስገራሚ የምስራች ዜና] ነገረችኝ። “ዮኒ” ብላ ጠራችኝ፤ ቤት ውስጥ ደግሞ ከእኔና ከእርሷ ውጪ ሌላ ማንም አልነበረም። ደግሞ ወደ ስራ ቦታ ሔዷል። በዚያ ላይ የደበቀችን ነገር ለእኔ ነገረችኝ። “ዮኒ ፀንሻለሁ እኮ” አለችኝ። እኔም በጣም በደስታ ተሞላሁ። እርሷ ግን መልሳ “ ከሰማ ይገለኛል” አለችኝ። “ለምን?” አልኳት። እርሷም መልሳ “በዚህ ሰዓት እኔ እንድጸንስ ፍቃደኛ አይደለም፤ ደግሞ የእርግዝና መከላከያ ወስጄ ነበር፤ ግን ሆኖም

ፅንሱ ተቀመጠ" አለችኝ። እኔም "አይ ይህ የሚያስደስት ነገር ነው ምንም የሚያስፈራ ነገር የለውም" አልኳት። በኋላ ላይ ወንድሜም መጸነስዋን አወቀ። ደግሞም የምግብ እና የሽንኩርት ሽታ በጭራሽ አልተስማማትም ነበር።

አንዳንድ ጊዜ ስራ በጣም ሲከብዳት እንጀራ ከጋገረች በኋላ እኔ ደግሞ ወጥ በመስራት አግዛት ነበር። ደግሞም ወደ ገበያ እንሂድ ብላ ስትለምነኝ አብረን እንሄዳለን። ገበያ ላይ የሚያውቋት ሰዎች "እንዴ ወንድምሽ ነው? የት የሚኖረው?" ይሏታል። እርሷም ደግሞ "ወንድሜ ነው። የኔ ታናሽ ነው" ትላቸዋለች። በቃ በጣም ነው የምትወደኝ፤ እኔን አንድም ቀን አስከፍታኝ አታውቅም ነበር። አልፎ ተርፎም ከገበያ ከአስቤዛ የተረፈውን ብር "ዮኒ ስልክህ ላይ ካርድ ሙላ" ብላ የሞባይል ካርድ ትገዛልኛለች።

እኔ ደግሞ ተማሪም ስለሆንኩኝ ብር አይኖረኝም። አንድ አንድ ጊዜ ደግሞ " ፑል (Pool) ልጫወት አምስት ብር ብቻ ስጭኝ?" ብዬ እለምናታለሁ፤ አንድም ቀን አታሳፍረኝም፤ ትሰጠኛለች። ስለምናት አስር ብር ከሰጠችኝ ወደ ፑል (Pool) ቤት እሔዳለሁ። ሜዳ ብቻ ነው የምጫወተው ቁማር በፍፁም አልጫወትም። ይህችን 10 ብር ለማትረፍ ስል በጣም ተጠንቅቄ ነው የምጫወተው፤ ደግሞም በጣም ጎበዝ ነኝ። ወደ 8 ሜዳ ተጫውቼ አስሩንም ብር ይዤ እወጣለሁ፤ ከዛም 10 ብር በሞባይሌ ላይ ሞልቼ ለፍቅረኛዬ ለማርዬ እደውልላታለሁ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዘጠነኛ ክፍል ማለቅያ፤ የማጠቃለያ ፈተና ደረሰ። 2008 የዘጠነኛ ክፍል ፈተና የመጨረሻ የማጠቃለያ ፈተና ተፈተንን። ፈተናውን ጨርሰን በመጨረሻ ቀን ሁለታችንም ከፈተና መልስ ለመጀመሪያ ቀን ወደ ወሰድኳት ቦታ፤ ወደዚያ ቦታ ወደ ወንዙ ዳር ሄድን። በዚያ ቦታ ፎቶ ተነስተን፤ በጣም ደስ ብሎን እዚያው ብዙ ነገር እየተጫወትን ቀኑም መሸ።

በሁለተኛው ቀን ከክፍል ልጆች ጋር ወደ አጆራ ፏፏቴ ሔደን ለመዝናናት ሁላችንም ተቀጣጠርን። ከዚያም ከተማ ውስጥ አንድ ቦታ ተሰብስበን ወደ አጆራ ለመሄድ ተዘጋጀን። ልጆቹ ሁሉም ተሰብስበው ሳለ በልጆቹ መሀል ስፈልጋት የለችም። በጣም ደበረኝ። ጓደኞቼን ከማስቀይም ብዬ ከልጆቹ ጋር ሔድኩኝ። ልጆቹ ግን አውቀዋል። እርሷ ስለሌለች ውስጤ ደስተኛ አለመሆኑን ፊቴን በማየት አውቀዋል። ግን ሆኖም እንደምንም ቀኑን አሳለፍን። ልንለያይ ስለሆነ በፏፏቴው ዳር ላይ ብዙ ፎቶዎችን ተነስተን ወደ ሰፈራችን ተመለስን። በኋላ ላይ ወደየትም እንዳትሄድ አባቷ እንደከለከላት ነገረችኝ፤ ለእኔም ቀኑ ብዙም ደስ እንዳላሰኘኝ ነገርኳት። ደግሞም ባለመምጣቷ በጣም እንደተሰማኝ ነገርኳት። እርሷም "ዮኒዬ የኔ ማር፣ የኔ ውድ በጣም ይቅርታ፤ ከአባቴ ትዕዛዝ መውጣት ስለማልችል ነው" አለችኝ። ከክፍል ልጆች ጋር በዚህ ሁኔታ ተለያየን። ከ15 ቀን በኋላ ውጤት የምናይበት ቀን ላይ ሁላችንም ተሰብስበን ማርዬም በግቢ

ውስጥ ከሴቶች ሁሉ አንደኛ፤ ከወንዶች ደግሞ በክፍል ውስጥ አንደኛ ወጥታ ብዙ ሽልማት ተቀበለች። እኔም ስጦታ ሰጠኋት። በጣም ደስ ብሏት የሽልማት ኘሮግራም ከጨረስን በኋላ ወደ እኔ መጥታ እቅፍ አርጋኝ ሳመችኝ።

ከዚያም ከትምህርት ቤት እንደወጣን አባቷ ወደ መዝናኛ ቦታ ሊወስዷት ስለሚፈልጉ ከእኔ በግድም በውድም ተለየችና ወደ አባቷ ሄደች። ከዚያም አባቷ ጋር ተዝናንተው ሲያበቁ ወደ እኔ ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ደወለችልኝ። ወደ ተለመደው ቦታ፤ ወደ ወንዝ ዳር የልብ የልባችንን ለማውራት ስለሚመችን ሄድን። በዚህ በወንዝ ዳር ላይ የልብ የልባችንን እያወራን ብዙ ሰዓት ቆየን። በጣም ደስ ብሎኝ ቀኑም መሸ፤ ወደ ሰፈርም መጣን። እንደተለመደው በኮንትራት ባጃጅ ወደ ሰፈራቸው ሸኝቻት ወደ ቤት ተመለስኩኝ። መሸ፤ ከዚያም ማታ ማታ በድምጽ ማውራት ስለማንችል፤ ቤት ውስጥ ስለማይመችን በmessage [በጽሁፍ መልእክት] ማውራት ጀመርን። ቀን ብዙ ነገር ስንጫወት ስናወራ በብዙ ነገር ስንደሰት ነበር። ይህን ሁሉ እያወራን እረጅም ሰዓት ቆየን፡፡ በዚህ ሁኔታ በትምህርታችን ላይ ምንም የሆነ ተጽእኖ የሚፈጥር ነገር ሳይገጥመን የዘጠነኛ ክፍል ትምህርታችንን ጨረስን፤ ክረምትም ገባ።

## ክፍል አስራ ሁለት

ፍቅራችን አንድም ቀን ሳይቀዘቅዝ፤ አንድም ቀን ሳንለያይ፤ ክረምቱን ሙሉ አንድ ላይ አሳለፍን። በመሀል አባቴ ወደ ሆሳዕና እንድመጣ በጣም ሲያስቸግረኝ ወደ ሆሳዕና ሄጄ ወደ ሁለት ሳምንት ቆየሁ። ይገርማል በጣም ናፍቃኛለች። በየቀኑ እየደወለችልኝ “ለምን አትመጣም?” ብላ በጣም አስቸገረችኝ። በቃ ለእርሷ ደስታ ስል አባቴን አስፈቅጄው ከሁለት ሳምንት በኋላ ተመለስኩ። ይገርማል! ወደ ሀደሮ የደረስኩት ወደ 8፡30 ላይ ነበር፤ ቤት ገብቼ ትንሽ እንደቆየሁ በጣም አስቸገረችኝ። “ዛሬ ሳላይህ በጭራሽ ማደር አልችልም፤ ወደ ተለመደው ቦታ ወደ ሐዋርያት ቤተክርስትያን ፊት ለፊት አሁኑኑ ካልመጣህ” አለችኝ። እኔም በጣም ንፍቅ ብላኝ ነበር። ወንድሜንም እየፈራሁ ግን ናፍቆቱ አላስቻለኝም ነበር።

ከቤት ና ን ሁለታቸውንም ሸውጄ፤ ወደ አንድ ሰዓት አካባቢ በኋላ በር ወጥቼ፤ ለሞተር አምስት ብር ሰጥቼ ወደ ቦታው ደረስኩኝ። ይገርማል በጣም ተነፋፍቀናል። እርሷም ከቤቷ በሩጫ መጣች። በጣም በናፍቆት ተቃቅፈን እረጅም ሰዓት ተሳሳምን። በጣም ደብሯት እንዳሳለፈች፤ በጣም በጭንቀት እንዳሳለፈች ነገረችኝ። ደግሞም “እባክህ ከእንግዲህ አልሄድም ብለህ ቃል ግባልኝ” ብላ ለመነችኝ። እኔም

“አልሄድም” ብዬ አጽናናኋት። በቃ በጣም ደስ ብሎን ትንሽ ካወራን በኋላ “ነገ በ8፡30 ላይ በተለመደው ቦታችን እንገናኝ” ተባብለን ተለያየን። በዚህ በወንዝ ዳር ሁሌም ስለምንገናኝ ለቦታው ስም ሰየምን። ይህ ቦታ ከዛሬ በኋላ “ካምፕ” እንበለው ብለን ስም ሰየምን። ከዚህ ቀን ጀምሮ ቦታውን “ካምፕ” ብለን መጥራት ጀመርን።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ትምህርት የሚጀመርበት ጊዜው ደረሰ። ሁለት ሺህ ስምንት አለቀ። እኔንም “ማርዬ አንድ ነገር ልጠይቅህ?” ብላ በጣም አፋጠጠችኝ። እኔም ጠይቂኝ አልኳት፤ እርሷም “ከመጠየቄ በፊት አንድ ነገር ቃል ግባልኝ” አለችን። እኔ “ነገሩን ንገሪኝና ቃል ልግባልሽ” አልኳት። እርሷም “ማርዬ እባክህ አደርጋለሁ ብለህ ብቻ ቃል ግባልኝ” አለችኝ። እርሷን ማስከፋት ስለማችል “እሺ ቃል እገባልሻለሁ፤ ምንም ችግር የለም አደርገዋለሁ ነገሩን ብቻ አሁን ንገሪኝ” አልኳት። ከዚያም ነገሩን ማውራት ቀጠለች “ዮኒ 10 ኛ ክፍል የት ነው የምትማረው? የት ነው የምትቀጥለው?” ብላ ጠየቀችኝ። እኔ “ማርዬ ምን የሚባል ጥያቄ ነው የምትጠይቂኝ? በጣም አስገረምሽኝ” አልኳት። እርሷም መልሳ “ማርዬ እባክህ የት እንደምትቀጥል ብቻ ንገረኝ። እባክህ! ስወድህ!” አለችኝ። ለኔ ነገሩ ግራ እየገባኝ “እኔማ እዚሁ ነው የምቀጥለው። ለግማሽ መንፈቀ-አመት ወደዚህ ወደ ሀደሮ እንደመጣሁ ታውቂያለሽ። ስለዚህ የሚቀጥለውንም ዓመት፤ 10ኛ ክፍልን እዚሁ ነው የምቀጥለው” ብዬ ነገርኳት። እርሷም መልሳ “እባክህን እዚህ ሳይሆን ወደ ሆሳዕና አስቀይር፤ እኔን ብቻ እሺ በለኝ” አለችኝ።

ወንድሜ እሺ እንደማይለኝ ብነግራትም በጣም በጥብቅ ለመነችኝ። በዚህ ጉዳይ ወንድሜንም ላወራው ስሞክር “ምን ማለት ፈልገህ ነው?” ብሎ በጣም ተቆጣኝ። ለእኔ እራሱ አጠያየቁ በጣም ገረመኝ። ምክንያቱም ወደዚህ ወደ ሀደሮ የመጣሁት የ9ኛ ክፍል የአንደኛ መንፈቀ-አመት ትምህርቴን በሆሳዕና ጨርሼ ለሁለተኛው መንፈቀ-አመት ነበር። በቃ ለእኔም በጣም ከበደኝ። በኋላ ላይ ወንድሜን በትህትና እና በፍቅር፤ ቀስ አድርጌ እንዲህ ብዬ ጠየቅኩት “ወንድሜ በዚህ በሀደሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ብዙም የትምህርት አሰጣጡ በጣም የወረደ ነው” ብዬ አስረዳሁት። “ስለዚህ ወደ ሆሳዕና ሄጄ በግል ትምሀርት ቤት፤ ጥሩ የትምህርት አሰጣጥ ባለበት ብማር አይሻልም?” ብዬ ጠቅኩት። እርሱም “እሺ ላስብበት” ብሎ መልስ ሰጠኝ።

“በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜ እምቢ ቢለኝ ምን ይውጠኛል?” ብዬ በጣም ሀሳብ ውስጥ ገባሁ። እርሷ ግን በስልክም ቢሆን፤ በቀን በማታ ስለዚህ ጉዳይ ብቻ ነበር የምትጠይቀኝ። እኔም በጣም በጥንቃቄ “እውነቱን ግን አላውቅም፤ ማርዬ ለምንድነው ግን ይህን ከባድ ጥያቄ የጠየቅሽኝ?” አልኳት። እርሷም መልሳ “ማርዬ እኔ አባቴ ወደ አረካ ሄጄ እንድማር ወስኗል። እህቴም ደግሞ የአስራ ሁለተኛ ክፍል የሀገር-አቀፍ ፈተና ተፈታኝ ስለሆነች፤

ስለዚህ ወደ አረካ ሁለታችንም ሄደን በግል ትምህርት ቤት እንድንማር ወስኗል። ታውቃለህ ደግሞ አባቴ በጣም ቁርጠኛ መሆኑን። እርሱ ካወራው ነገር መውጣት ደግሞም እንደማልችል አንተ እራስህ በደንብ ታውቃለህ" ብላ ነገረችኝ።

ይህንንም ነገር ደውዬላት ነገርኳት። በጣም ደስ አላት፤ አላመነችኝም ነበር። ደግማ ጠየቀችኝ፤ እኔም አስረግጬ ነገርኳት። በጣም በደስታ ተሞልታ "የኔ ውድ የኔ ጣፋጭ ሁሌም አፈቅርሃለሁ" አለችኝ።

## ክፍል አስራ ሦስት

ሁለት ሺህ ዘጠኝ ገባ። ከሀደሮ ወደ ሆሳዕና ለመመለስ ከሀደሮ ትምህርት ቤት መሸኛ ጠየቅኳቸው። መሸኛውንም ሰርተው፤ ሁሉን ነገር ጨርሰው፤ በተለይ የአንደኛ መንፈቀ-ዓመት ትምህርት የዘጠነኛ ክፍል የውጤት ካርዴን (transcript) ሰርተው ከሀደሮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሸኙኝ። ወደ ሆሳዕና ተመለስኩ። በሆሳዕና በግል ትምህርት ቤቶች አንዱ ወደሆነው አባ ትምህርት ቤት ስሄድ የሚባል በሆሳዕና በኤፍ ኤ [FA] ትምህርት ቤት ዳይሬክተር የነበረ ወደ እዚያ ተቀይሮ በዚህ በካቶሊክ (Catholic) ወይም አባ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ሆኖ ተቀጥሯል። ለመመዝገብ ፈልጌ የስምንተኛ እና የዘጠነኛ ክፍል ውጤቴን ሁሉንም ሰጠሁት። እርሱ ግን አይሆንም እዚህ አልመዘግብህም፤ አንተ እዚህ በጭራሽ እዚህ አትማርም፤ ወደ ኤፍ ኤ ትምህርት ቤት ሂድ እዛ ይቀበሉሃል ብሎኝ ከዚያ ቦታ ተናድጄ ወጣሁና ወደ ኤፍ ኤ ትምህርት ቤት ሔድኩኝ። እዛም ደግሞ ከእጄ ውጤቱን ወስደው ካዩት በኋላ የውጤት ካርዴን (transcript) "ለምን ሁለት ቦታ ላይ አስደረክ? ለምን ሁለት ቦታ ሆነ?" ብለው ጠየቁኝና፤ "በል ወደ ሀደሮ ትምህርት ቤት ተመልሰህ ይህን በተለያየ ካርድ ላይ ያለውን ውጤት በአንድ ላይ አሰርተህ ይዘህ ና" አሉኝ።

እኔ ግን እሺ ችግር የለም አሰርቼው ይዤ እመጣለሁ ብዬ ሸውጃቸው ወጣሁ። ያሉኝ ነገር ውጣ ውረዱ ስለደበረኝ ተስፋ ቆርጬ ወደ መንግስት ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ሄድኩኝ። መጀመሪያ ሁለተኛ ደረጃ በጀመርኩበት ወደ የካቲት ትምህርት ቤት እዛው ተመልሼ ትምህርቴን ለመቀጠል ተመዘገብኩኝ። በዚህ በየካቲት 25/67 ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ብዙ አስተማሪዎች ስለሚያውቁኝ ብዙም አልተከራከሩኝም። እንኳን ተመለስክልን ብለው ነበር የተቀበሉኝ።

እኔም በዚህ መጀመሪያ ጥያቸው የሄድኩትን የልብ ጓደኛዬ ጋር እንደገና ተገናኘሁ። በሆሳዕና ከተማ በየካቲት 25/67 ሁለተኛ ደረጃ እና የመሰናዶ ትምህርት ቤት ትቻቸው ከሄድኳቸው ጓደኞቼ ጋር ትምህርቴን እንደገና ቀጠልኩኝ።

ም ከሀደሮ ወደ አረካ አስቀይራ ሄደች። ትምህርታችን የእኔም ሆሳዕና የእርሷም አረካ ሆኖ ሳለ ተራርቆ ፍቅር በጣም ከበደን። በሀደሮ ሳለን ሌት ቀን የምንገናኝ ሰዎች አሁን በዚህ ሁኔታ በጣም ከባድ ሆነ። ከሆሳዕና ከተማ ወደ አረካ ለመሄድ ወደ ሰማንያ ኪሎ ሜትር ያህል ነው። ትራንስፖርት ደግሞ ከሆሳዕና አረካ ወደ 40 ብር አካባቢ ነው:: ይህን ገንዘብ ደግሞ በየጊዜው እንዳናወጣ ገና ተማሪዎች ነን። በቃ በጣም ከበደን። ተራርቆ ፍቅር ይከብዳል የተባለው እውነትም በህይወቴ ሆኖብኝ አየሁ።

ሆኖም ግን አንድ ነገር አገኘን። እርሷም ከአረካ ወደ ሀደሮ እኔም ከሆሳዕና ወደ ሀደሮ እየሄድን በየአስራ አምስት ቀናቱ ለመገናኘት ወሰንን። በየአስራ አምስት ቀናት መገናኘት ጀመርን። በተለመደው በወንዝ ዳር በካምፓችን ተገናኝተን የልብ የልባችንን እያወራን የአስራ አምስት ቀኑን ናፍቆት ቢያንስ ከስምንት ሰዓት እስከ ማታ አንድ ሰዓት ያህል ቆይተን እንወጣ ነበር። ከናፍቆት ብዛት የተነሳ እስከ ማታ በጭራሽ አንለያይም ነበር። በግድ ነበር የምንለያየው። ትምህርታችንን የግድ መማር ስላለብን እና ቤተሰቦቻችንም ስለሚቆጡ ብቻ ነው የምንለያየው። እዚያ ከተገናኘን በኋላ እርሷም ወደ አረካ እኔም ወደ ሆሳዕና ለመሄድ መኪና መናኸሪያ ውስጥ አንለያያለን። ይህንንም ነገር በተደጋጋሚ ማድረግ ጀመርን። በየአስራ አምስት ቀኑ ሳንገናኝ ቀርተን አናውቅም ነበር።

አልፎም ተርፎ ይህ በየአስራ አምስት ቀን የምንገናኘው ናፍቆታችንን ሊቀንስልን አልቻለም። በዚያ ላይ በሳምንቱ ቀናትም ሳንደዋወል አንድም ማታ አሳልፈን አናውቅም። ሆኖም ግን ናፍቆታችን ጨመረ። ከዚያም የበለጠ እኔ ወደ አረካ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ እርሷ ሄድኩኝ። ከዚያም ከክፍል ወጥታ እኔን ለመቀበል ወደ ከተማ መጣች። ከሴት ጓደኛዋ ጋርም ጠበቀችኝ። እኔም ከመኪና እንደወረድኩ ለእርሷ ስደውልላት የቦታውን ምልክት ነገረችኝ። ቦታውም አረካ ሆስፒታል በልዩ ስሙ ኡቱጌ ይባላል ብላ ስለነገረችኝ ለሞተረኞቹ ቦታውን ነገርኳቸው። ወስደው በሆስፒታሉ በር ላይ አወረዱኝ፤ ይገርማል! በጣም እስከሚጋነን ድረስ በጣም ተነፋፍቀናል። ፊት ለፊቴ ላይ በድንገት መጣች፤ በጣም ደነገጥኩኝ፤ እርሷም በጣም ደነገጠች። ከዚያም ተገናኘንና ወደ መዝናኛ ቦታ ሄድን። በስልኬ ላይም ብዙ አሪፍ አሪፍ ፎቶ እየተነሳን አንዴ እየተቃቀፍን፤ ደግሞም ተራ በተራ እየተነሳን፤ አንድ ላይ ደግሞ የራስ-ምስል ፎቶግራፍ (selfie) እየተነሳን እረጅም ሰዓት ከተጫወትን በኋላ ወደ አንድ ሆቴል ምሳ ልንበላ ገባን።

ለመጀመሪያ ጊዜ ከእኔ ጋር ወደ ሆቴል ገባች። በጣም ደስ አለን። የሆቴሉም ስም ፅዮን ሆቴል ይላል። እዚያው ምሳ በልተን፤ ሻይ ቡና ብለን ቀኑም እየመሸ መጣ። ከሆቴሉ ከወጣን በኋላ በእግራችን ትንሽ እየተራመድን፣ እየተጫወትን ሳለ ሰዎች እኛን ቆመው ማየት ጀመሩ። እኔም ደግሞ ማርዬን “ለምንድነው ሰዎች በጣም የሚያዩን?” ስላት

እርሷም “የዚህ ሀገር ሰው በጣም ሰውን ትኩር ብሎ ያያል” ካለች በኋላ ከዚያም “ምን አገባቸው?” ብላ ከእኔ ጋር እየተሯሯጥን ጨዋታችንን ቀጠልን። ሲደክመን ሞተር ይዘን ወደ መኖሪያ ስፍራ ደረስን። እኔም እንዲህ አልኳት “ማርዬ በቃ ልትለይኝ ነው? በቃ ሂጂ ለእኔም በጣም መሽቶብኛል። አሁን በቃ ቻው” አልኳት። በዓይኗ ላይ እምባዋን ሞላች፤ በቃ ቻው ቻው ተባብለን መለያየት አቃተን። ከዚያም በኋላ አንድ ነገር አሰበች “በቃ ሁለታችንም ወደ ሀደሮ እንሂድ?” አለችኝ። ቀኑም አርብ ቀን ነበር። “በቃ አባዬ ከጠየቀኝ የሚያስፈልገኝን ነገር ለመውሰድ ነው እላለሁ” አለችና ከኔ ጋር ወደ ሀደሮ ለመምጣት ወሰነች። ለአባቷም ደውላ ነገረቻቸው፤ እሳቸውም “መሽቷል ነገ ነይ” ሲሏት “አይ መንገድ ላይ ወጥቻለሁ” ብላ ሸወደቻቸው።

ከዚያ ከቤቷ ቦርሳዋን ይዛ ወጣች። አንድ ላይ ወደ መናኸሪያ ሄድን። ነገር ግን መኪና አጥተን ፈተና ውስጥ ገባን። በኋላ ላይ ከወላይታ ሶዶ የሚመጣ መኪና አገኘን፤ ነገር ግን መኪናው ሞልቶ ሰው ከመኪና ተርፎ እየፈሰሰ ነው። በጣም ጭንቀት ውስጥ ገባን። አባቷ ደግሞ በየደቂቃው እየደወሉ “የት ደርሰሻል? መሽቷል” እያሉ በጣም እያስቸገሯት ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ “መኪና አግኝቼ እየመጣሁ ነው” ብላ ስላለቻቸው መቅረትም መሄድም አቃታት።

እንዲህ እያልን ጨራሽ መሸ። አንድ ነገር ወደ አይምሮዬ መጣ፤ “በቃ በሞተር እስከ ማዘሪያ እንሂድ?” ብዬ ጠየቅኳት። እርሷም “እሺ” አለችኝ። ሞተር ለሚነዱት ልጆች ስነግራቸው ደግሞ ብዙ ብር መጠየቅ ጀመሩ። የሆነ ልጅ ብዙ ብር ሲጠይቀኝ ከልጁ ጋርም ጥል ውስጥ ገባን። ማርዬም ስትለምነኝ ካልተደባደብኩ አልኩኝ። በኋላ ልጆች መሃል ገብተው ገላገሉን:: ከመሃከላቸውም አንዱ እኔን ቀርቦ ማውራት ጀመረ:: ግድ የለም እኔ እወስዳችኋለሁ ብሎ ከእኔ ጋር ተስማማን:: ከአረካም ሁለታችንንም ደርቦ ጭኖ ወደ ማዘሪያ ከተማ አደረስን። በኋላ ላይ አንድ ባጃጅ ብቻ አገኘንና ወደ ሀደሮ ሁለታችንን ብቻ ይዞን ቀጠለ። የአራት ሰው ቦታ ከፈልኩኝ፤ ወደ ሰፈራቸውም ደረስን። እዚያ ስንደርስ ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ሆኖ ነበር።

ስለምትፈራ እስከበራቸው ድረስ አደረስናት፤ ወደ ቤትዋም ገባች። እኔ ወደ ሰፈሬ በዚያው ባጃጅ ተመልሼ መጣሁና ለልጁ ብሩን ከፍዬ በጣም አመሰገንኩት። እርሱም በደስታ ብሩን ተቀብሎ ሄደ። እኔም ወደ ቤት ገባሁ:: በጣም ደነገጡ፣ “መንገድ ላይ ምን ሆነሃል ብለን በጣም ነበር የፈራነው” ብላ የወንድሜ ሚስት ተቆጣችኝ:: ከዚያም እራት አቀረቡልኝ:: እራት በልቼ ወደ መኝታ ሄድኩና ስልኬን ወደ ቻርጅ ላይ ሰካሁት። ባትሪውን ጨርሶ ዘግቶ ነበር። በኋላ ደውላ ታጣኛለች ብዬ ፈርቼ በቻርጅ ላይ እንደነበረ ትንሽ ደቂቃ ቆይቼ ስልኩን ክፍት አደረግኩ። ወዲያው ያልታሰበ ጥሪ እና ወደ ስልኬ ብዙ

የጽሁፍ መልእክት ገባ። ከዚያም የማታ ልብስ ቀይሬ ከተኛሁ በኋላ መልእክት ላኩላት፤ እርሷም መልእክቱን ወዲያው መለሰችልኝ፤ ከዚያም ወሬአችንን እስከ ማታ ስድስት ሰዓት ድረስ ቀጠልን። በማግስቱ ተደዋውለን በስምንት ሰዓት አካባቢ ተገናኘተን ወደ ካምፓችን ሄደን ወሬያችንን ጀመርን፤ አሪፍ ጊዜም አሳለፍን። በሁለተኛው ቀን እርሷም ወደ አረካ እኔም ወደ ሆሳዕና ለትምህርታችን ስንል ተለያየን።

ከአንድ ወር በኋላ ወደ ሆሳዕና መጣች። በጣም አምሮባት መጣች። ይገርማል! በጣም ተነፋፍቀናል። ወደ መናኸሪያ ሄጄ ተቀበልኳት። ከዚያ ወደ ቤት ወሰድኳት። ከዚያም ተመልሼ ወጥቼ ለሁለታችንም ቴክ አዌይ [ወደ ውጪ የሚሄድ] ምግብ አሰርቼ፣ አስጠቅልዬ ይዤ ወደ ቤት ተመለስኩ። በልተን ትንሽ ካረፍን በኋላ ወደ ከተማ ሻይ ቡና ለማለት ወጣን። ጓደኛዬንም እኛ ያለንበት ቦታ ድረስ እንዲመጣ ደውዬ ነገርኩት። እርሱም ቦታውን ሲጠይቀኝ “አደባባዩ ፊት ለፊት፣ ከአቢሲኒያ ባንክ ጎን፣ ፊቶና ካፌ እና ሬስቶራንት ነን ያለነው” ስለው ወዲያው መጣ። በጣም የምወደው የሰፈሬ ልጅ ነው፤ ስሙም ይባላል። ልጁ በጣም የገባው ልጅ ነው፤ በጣም ደግሞ ቀልደኛ ነገር ነው። እንደመጣ ከፍቅረኛዬ ከ ጋር አስተዋወኩት። ወዲያው ጨዋታ ውስጥ ገባ፤ በጣምም አሳቀን። ማርዬም ከዚያ በጣም በጨዋታው ደስ አላት። ከዚያም ወደ ሀደሮ ሸኘኋት፤ ቀኑንም በጣም ደስ ብሎን በጥሩ ሁኔታ አሳለፍን። ወደ ሀደሮ የምትሄድ መስሎኝ ነበር፤ በኋላ ወደ አረካ እንደሄደች ነገረችኝ።

## ክፍል አስራ አራት

ይህ ሁለት ሺህ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት ለእኛ በጣም ከባድ ጊዜ ሆነብን። ተራርቆ ፍቅር በጣም ከበደን፤ ነገር ግን እጅ አልሰጠንም። በየአስራ አምስት ቀኑ በሀደሮ፣ በየወሩ መጨረሻ ደግሞ በሆሳዕና ወይንም በአረካ መገናኘታችንን ቀጠልን። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የገና በዓል ደረሰ። እኔ፣ ወንድሜ እና የወንድሜ ሚስት በዓሉን ብቻቸውን ስለሚያሳልፉ አባቴን አስፈቅጄ ወደ ሀደሮ ሄድኩኝ። በዓል መሆኑ ደግሞ መልካም አጋጣሚ ሆነልኝ። ማርዬም ወደ እኔ በመደወል “በዓሉን የት ነው የምናሳልፈው?” ስትል ጠየቀችኝ። እኔም ወደ ሀደሮ እንደምመጣ ነገርኳት። ሌላ ምክንያት ደግሞ የወንድሜ ሚስት በጣም እርጉዝ ነበረች። የመውለጃዋ ወርም ቀርቦ ነበር። በዚያ ምክንያት ሆሳዕና ማሳለፍ አልፈለግኩም ነበር። ለበዓሉ ሁለት ቀን ሲቀር ለፍቅረኛዬ ለበዓሉ ስጦታና ፖስት ካርድ ይዤላት ወደ ሀደሮ ጉዞዬን ቀጠልኩኝ።

ሀደሮም እንደደረስኩኝ ወደ እነርሱ ሰፈር ሄጄ ደወልኩላት። ወዲያው መጣች። የሚገርመው ነገር ፖስት ካርድ እኔም ያመጣሁላት፣ እርሷም ለእኔ ያመጣችልኝ፣

ቀለሙ ተመሳሳይ ሆኖ በልዩ ልዩ የተፃፈው መልእክት ተመሳሳይ ነበር። በዚህ በጣም ተገረምኩኝ። ከዚያም ፖስት ካርድና ስጦታ ተለዋወጥን። ማርዬ ደግሞ ደብዳቤ ፅፋልኝ ነበር። ሁሉንም ነገር ተለዋውጠን መልካም በዓል ተባብለን ተለያየን። ለበዓሉ ዶሮ ልገዛ ወደ ሀደሮ ከተማ ወደ ገበያው ወንድሜ ብር ሰጥቶ ላከኝ። እኔ ግን ለእርሷ ደውዬላት ወደ ገበያ እንደመጣች ጠየቅኳት። እርሷም ለአስቤዛ ወደ ገበያ እንደመጣች ነገረችኝ። ለኔም በጣም ደስ አለኝ፤ እርሷንም በገበያ ውስጥ ፈልጌ አገኘኋት። በጣም በደስታ ተቃቀፍን። ከዚያም ትንሽ እንዳወራን ወንድሜ ወደ እኔ ስልክ ደውሎ "ዮኒ ጥሩ ዶሮ ገዛክ? እንዴት ነው አሪፍ ተገኘ ወይ?" አለኝ። " ገና እየፈለግኩ ነው" ብዬ ሸወድኩት። ከዚያም ከእርሷ ተለይቼ ወደ ዶሮ ተራ ገባሁ። በጣም አሪፍ አሪፍ ዶሮ መርጬ ወዲያው ገዝቼ ወደ ቤት በሞተር ሄድኩኝ። በበዓል ቀን ደግሞ በተለመደው በካምፓችን ላይ እንገናኝ ተባብለን ተቀጣጥረን በካምፓችንም ላይ ተገናኝተን አሪፍ ጊዜ አሳለፍን።

ሁለት ቀን በተደጋጋሚ በካምፓችን ላይ ተገናኝተን የልብ የልባችንን እያወራን አሪፍ ጊዜ አሳለፍን፣ በዓሉም በዚህ ሁኔታ አሳለፍነው። በጣም አሪፍ ጊዜ ነበር። በዓል ካለፈ በኋላ እኔም ለትምህርቴ ወደ ሆሳዕና እርሷም ለትምህርቷ ወደ አረካ ተለያየን። ግን ምንም ብንራራቅ፤ ምንም የቦታው እርቀት ቢለያየንም፤ ፍቅራችን ግን አንድም ቀን ቀንሶ አያውቅም። የምን መቀነስ? ይባስ ፍቅራችን እየጨመረ መጥቶ ከድሮ ይልቅ በጣም መነፋፈቅ ጀመርን። በዚህ በፍቅራችን ምክንያት በትምህርታችን ላይ አንድም እንቅፋት ተፈጥሮብን አያውቅም። እኔ ደግሞ በትምህርት ጊዜ ምንም ላዋራት በጭራሽ አልፈልግም ነበር። ምንም እንኳን በጣም ብትናፍቀኝም ትምህርቷን ትታ ወደ እኔ እንድትመጣ በጭራሽ አልፈቅድም።

በዚህ ሁኔታ የትንሳኤ በዓል ደረሰ። ለበዓሉም ከሆሳዕና ወደ ሀደሮ ብዙ ዕቃ እንደሚወስድ ወንድሜ በስልክ ነገረኝ፤ በባንክ አካውንቴ ላይም ብር ላከልኝ እና ለበዓሉ የሚያስፈልገውን ሁሉ ነገረኝ። እኔም ከሆሳዕና ለዶሮ የሚሆን፣ ከጤናዬ ባልትና፣ በርበሬ እና ሌላም ሌላም አስቤዛ ሰብስቤ ወደ ሀደሮ ጉዞዬን ቀጠልኩኝ። ብዙ ጊዜም ለወንድሜ የሀደሮ በርበሬ ስለማይፈልግ ከሆሳዕና ነበር በየጊዜው የምወስድለት። በዚህ አጋጣሚ ደግሞ ለማርዬም የፖስት ካርድ እና ሌላም ስጦታ ገዝቼላት ወደ ሀደሮ ገባሁ። ከበዓሉ ዋዜማ አንስቶ እስከ በዓሉ መጨረሻ ድረስ ከሰዓት በኋላ ሳንገናኝ ቀርተን አናውቅም ነበር።

በዚህ በዋዜማው ላይም ማርዬ "ዛሬ ከአንተ ጋር የእግር ጉዞ ማድረግ እፈልጋለሁ" አለችኝ። ከከተማው ወደ ላይ የእግር ጉዞ ማድረግ ጀመርን፤ ከዚያም ከተማውን ጨርሰን ወደ ገጠር ወጣን። ወደ ገጠር ከወጣን በኋላ መንገዱን ይዘን፣ ወደ አንድ ሰዓት የሚያክል

መንገድ ሳናውቀው በእግር ጉዞ ብቻ ከከተማው በጣም እራቅን። በዚህ የእግር ጉዞ ላይ አንድ ትልቅ ድልድይ ላይ ደረስን። ከድልድዩ በታች ደግሞ ትልቅ ፏፏቴ አገኘን። ለመዝናናትም የሚሆን አሪፍ ቦታ አገኘንና በዚህ ቦታ በፏፏቴው ላይ በስልካችን ፎቶ እየተነሳን፣ በውሃው እየታጠብን፣ ደግሞ ውሃ እየተራጨን ጫወታ ውስጥ ገባን። ይህ ቀን ለኔ በጣም ልዩ ቀን ሆኗል። ቀኑም መሸ። በማግስቱ እንደተለመደው በካምፓችን ተቀጣጥረን ፖስት ካርድ እና ስጦታ ተለዋውጠን ወደ ሰፈራችን ተመለስን። በዓሉም አሪፍ ጊዜ ሆኗል። በበዓሉም ቀን ሁለታችንም ሳንለያይ በጥሩ ሁኔታ አሳለፍን።

የወንድሜ ሚስት ከወለደች ትንሽ ወራቶች አልፏት ነበር። እርሷ ህፃኑን ይዛ ወደ ገበያ ለመውጣት ስለምትቸገር ለህፃኑ የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ የአጃ ዱቄት፣ ብዙ ለህፃኑ የሚያስፈልጉ ፓምፐርስ [ዳይፐር ወይንም የህጻናት ንጽህና መጠበቂያ] በየጊዜው ከሆሳዕና እወስዳለሁ። ይህም ከድሮ ይልቅ ለእኔ በጣም ተመቸኝ። በዚህም ምክንያት በየሳምንቱ ወደ ሀደሮ መምጣት ጀመርኩ። በዚህ ላይ ቶሎ ቶሎ እንዳገኛት አሪፍ አጋጣሚ ሆነልኝ። የሆነ ምክንያትም ፈጥሬ፣ እርሷም ወደ ሀደሮ በመምጣት በዚህ አጋጣሚ ቶሎ ቶሎ እንገናኛለን። ማርዬ ደግሞም ቶሎ ቶሎ ስንገናኝ በጣም ደስ አላት። እንዲህ እንዲህ እያልን ዋና ፈተና የምንፈተንበት ጊዜ ደረሰ።

ይህን ብሔራዊ ፈተና፣ ማትሪክ፣ እኔም ሆሳዕና ሆኜ እርሷም አረካ ሆና ተፈተንን። የፈተና ሰሞን፣ ለፈተና ደግሞ ብዙ ሰው ለእኔ ብር ልኮልኝ ነበር። ከቤይሩት የምትባል ዘመዳችን ወደ 1,000 ብር ላከችልኝ። ወንድሞቼም ደግሞ አንድ ላይ አድርገው ጥሩ ብር ከደቡብ አፍሪካ ልከውልኛል። ከአዲስ አበባም ወንድሜ ገንዘብ ልኮልኝ ነበር። የእህቴ ባልም በጣም ስለሚወደኝ መጀመሪያ በአርባ-ምንጭ በጎፋ ባንክ ሲሰራ በነበረበት ጊዜ እዚያ ጠርቶኝ በጣም ያዝናናኝ ነበር። ይህም የእህቴ ባል፣ ሌሎቹም ሁሉም ከየቦታው የላኩልኝ ብር በጣም ብዙ ብር ነበር።

ከአባቴም የፈተና ወቅት ነው ብዬ ከእርሱም አሪፍ ብር ተቀብዬው ነበር። ይህንንም ሁሉ ሰብስቤ ወደ ባንክ አድራሻዬ ላይ አስገባሁኝ። በቃ በጣም ተደሰትኩኝ። በውስጤ ሁለታችንንም ከፈተና በኋላ ወደ ሀዋሳ ለመዝናናት እንሄዳለን ብዬ ለራሴ ወሰንኩ። ለእርሷም ደውዬላት "ማርዬ ፈተና ከጨረስን በኋላ ወደ ሀዋሳ ለመዝናናት እንሄዳለን" አልኳት። እርሷም "የክፍል ልጆች ወደ ሀዋሳ ለመዝናናት እንሄዳለን ብለው እያወሩ ነው፤ እኔ ግን አባቴ ከፈቀደልኝ ከልጆቹ ጋር ሳይሆን ከአንተ ጋር እንሄዳለን" አለችኝ። የሶስቱን ቀን ፈተና ከጨረስን በኋላ "ወደ ሀዋሳ እንሒድ?" አልኳት እርሷም አባቷ እንደከለከላት ነገረችኝ።

እኔም በጣም ተሰማኝ። በጣምም ተናደድኩኝ። ከዚያ “ወደ ሆሳዕና እንድትመጪ እፈልጋለሁ፣ ለአንድ ቀን ብቻ አስፈቅደሽም ቢሆን ነይ” አልኳት። እርሷም ተስማማችና አባቷን ከክፍሏ ልጆች ጋር ወደ ሆሳዕና እንደምትሄድ ነግራ ወደ እኔ መጣች። ተመልሳ ስለምትሄድ በጠዋቱ ወደ እኔ ደረሰች፤ እኔም ልብሴን ቀይሬ እና ፈታ ብዬ ተቀበልኳት። በቤትም ትንሽ ቆይተን ፈታ ለማለት ወደ ከተማ ወጣን። ወደ አበራሽ ሎጅ ሄደን በዚያ አሪፍ ጊዜ ካሳለፍን በኋላ፤ ሻይ ቡና ብለን፣ ጁስ ጠጥተን፣ ፎቶ ለመነሳት ወደ ውጭ ወጣን። ወደ ውጪ ስንወጣ ከሀደሮ የመጡ ልጆች፤ መጀመሪያ ዘጠነኛ ክፍል ስንማር አብረን የተማርን የሀደሮ ልጆችን አገኘናቸው። በጣም ደነገጠች። “በቃ ጉዴ ፈላ፣ ለአባዬ ሄደው ይናገራሉ” ብላ በጣም ፈራች። እኔም እንዲህ አልኳት “እነርሱም ለመዝናናት ነው፣ አንቺም ለመዝናናት ነው፣ ምን የሚያስፈራ ነገር አለ?” አልኳት። እርሷም ምክሬን ሰማችና ከእኔ ጋር ፎቶ መነሳት ቀጠለች። የእነርሱንም ነገር እረሳች። ከዚያም ወጥተን ወደ ከተማ ተመለስን። ምሳም በልተን፣ ሻይ ቡናም ብለን ለማረፍ ወደ ቤት ሄድን። ቀኑም መሸ፤ ወደ ሀደሮም ሸኘኋት። የሁለት ሺህ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት የትምህርት ጊዜን በዚህ ሁኔታ ጨረስን።

## ክፍል አስራ አምስት

አስረኛ ክፍል ተጠናቀቀ። ከአረካ ወደ ቤተሰቦቿ፣ ወደ ሀደሮ ከተማ ተመለሰች። እኔም ከሆሳዕና ወደ ሀደሮ ከተማ ክረምቱን ለማሳለፍ፣ ወደ ወንድሜ እና ወደ ተመለስኩ። ክረምቱንም አንድም ቀን ሳንለያይ፣ ሁሌም በተለመደው ካምፓችን ላይ እየተገናኘን በሚገርም ሁኔታ አሳለፍን። የሁለት ሺህ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት መጨረሻ ደረሰ፤ የአዲስ ዓመት የዘመን መለወጫ ቀረበ። የሁለት ሺህ አስር ዓመተ ምህረትም ዋዜማ ተቃረበ። በይበልጥ ስጦታና ፖስት ካርድ ተለዋውጠን መልካም በዓል ተባብለን ተለያየን።

ከበዓሉ በኋላ በተለመደው ቦታ በካምፓችን ላይ ተገናኝተን፣ በዚህ አንድ ላይ በሆንንበት ጊዜ በድንገት ወደ ፌስ ቡክ (Facebook) ገብቼ ፔጁን [ገጼን] ስመለከት የአስረኛ ክፍል ውጤት ተለቋል ። ወዲያው ለ ውጤቱ ተለቋል ብዬ ነገርኳት። እርሷም የምዝገባ ቁጥር (Registration Number Code) የእኔን ሙላ ስትለኝ፣ ኮድ ሞልቼ ውጤቷን አየን። የእርሷን ውጤትም ሳይ ወደ ሶስት ነጥብ ሃምሳ ሰባት (3.57) መጥቶላታል። በውጤቱም በጣም ደስ ብሎን ተቃቅፈን በጣም ከተደሰትን በኋላ በመቀጠል የእኔን የምዝገባ ቁጥር አስገብቼ ውጤቱን አየን። ነገር ግን የእኔን ውጤት ስንደምር ወደ ሁለት ነጥብ ሰባ አንድ (2.71) አልደረሰም።

በጣም አዘነች እኔም በጣም ተሰማኝ። እርሷም “በቃ ደግመህ ትማራለህ” ብላ በጣም አባበለችኝ። እኔ ግን በደስታና በሳቅ ራሴን መቆጣጠር አቅቶኛል። እኔን በማየት በጣም ግራ ተጋባች “ማርዬ ለምን?” አለችኝ፤ እኔም “ማርዬ እኔ እንደምፈልገው ውጤቱ ስላልመጣልኝ ነው” አልኳት። ምክንያቱም ከሰስት ዓመት በፊት የእኔ ወንድም ቃል ገብቶልኝ ነበር። “አስረኛ ክፍል ውጤት ካልመጣልህ፣ ወደ እኔ ወደ ደቡብ አፍሪካ እወስድሃለሁ” ብሎ ቃል ገብቶልኝ ነበር። እኔም ወደ ውጭ ሀገር የመውጣት ፍላጎት በጣም ስላለኝ በውጤቴ ላይ ምንም አላዘንኩም ነበር። ፈተናውን በመውደቄም በጣም ተደሰትኩኝ። ይኼንንም ነገር ግልጽ አድርጌ ነገርኳት፤ ከትንሽ ጊዜ በኋላም ወደ ደቡብ አፍሪካ እንደምሄድ ነገርኳት። እርሷም መልሳ “በአየር መንገድ በረራ ነው ወይስ በእግር ጉዞ ነው?” አለችን። እኔም “አይ ማርዬ አላውቅም፣ በረራ ካሉኝ በረራ እግር ጉዞም ካሉኝ በእግር ጉዞ አልኳት”። እርሷም መልሳ “በረራ ካልሆነ እኔ የለሁበትም፤ በጭራሽ አይሆንም” አለችኝ።

እኔም “ማርዬ ማህበራዊ ሳይንስ (social science) ግቢ” አልኳት። እርሷም “ማርዬ እንዴት ማህበራዊ ሳይንስን (social science) ወደድከው?” ብላ ተገረመች። እኔ ማህበራዊ ሳይንስ ግቢ ያልኳት ምክንያት የእኔን ሕልም እንድታሳካ ነበር። ወንድሜ ማህበራዊ ሳይንስ ተምሮ ጨርሶ በባንከ ውስጥ ተቀጠረ። ወንድሜ ወደ ስራ ሲሄድ ሁልጊዜም በጣም አምሮበት ነበር የሚሄደው። ለዚያ እኔም እንደእርሱ መሆን እመኝ ነበር። ይህ ነገር በእኔ ባይሆንም እንኳን በእርሷ በኩል ይሆንልናል ብዬ ነበር ያሰብኩት። እርሷ ግን መልሳ “ዮንዬ ማህበራዊ ሳይንስ (social science) ብዙም አልችልም” አለችኝ። እኔም ላስጨናንቃት አልፈለግኩም። “እሺ በቃ ማህበራዊ ሳይንስ (social science) ካልፈለግሽ፣ የተፈጥሮ ሳይንስ (natural sciences) ትምህርት ግቢ። ግን ማርዬ የተፈጥሮ ሳይንስ (natural sciences) ከመረጥሽማ ከአምስት መቶ ነጥብ በላይ ሰርተሽ ጤና (Health) መግባት አለብሽ፣ ካልሆነ ነግሬሻለሁ! በቃ ሐኪም (doctor) እንድትሆኚ እፈልጋለሁ” አልኳት። እርሷም “ማርዬ እንዳልክ እሆናለሁ” አለችኝ፤ እኔም በዚህ በጣም ደስ አለኝ። ከአረካ መሸኛ አውጥቼ ወደ ሀደሮ ተመለስኩ። አስራ አንደኛ ክፍልን በሀደሮ ቀጠለች። እኔም ወንድሜን ሞተር አስገዛሁ። ወንድሞቼ ደቡብ አፍሪካ ወደ እነርሱ እስከሚወስዱኝ ሞተር ላይ እየሰራሁ ለመጠበቅ ወሰንኩኝ። በሆሳዕና ከተማ ሞተር ሳይክል መስራት ጀመርኩ።

ትምህርት በአረካ ስትማር ማርዬ አንድ ነገር ነግራኝ ነበር። ይኸውም በአረካ ሆስፒታል የሚሰራ ዶክተር በጣም እንደሚፈልጋት እና በጣም እንደሚከታተላት፣ በትምህርት ቤት በር ላይ እየጠበቃት እንደሚያስቸግራት ነበር። ይህንን ነገር በነገረችኝም ጊዜ ወደ አረካ ሔጄ ልጁን ልገድለው በጣም ስፈልግ እርሷ “አትምጣ፤ ፍቅረኛ አለኝ ብዬ ስነግረው

እንደድሮ መንገድ ላይ ጠብቆ ማስቸገር ትቶኛል” ብላ ወደ አረካ እንዳልሄድ ከልክላኝ ነበር። ለዛም ስትከለክለኝ ነገሩን ትቼ ነበር ግን ወደ ሀደሮ አስቀይራ ከመጣች በኋላ ሰው በመጠየቅ እስከቤታቸው ድረስ መጣ፤ አባቷንም ጠየቀ። በዚህ ነገር በጣም ተረብሻ ወደ እኔ ደወለችልኝ። በዚያን ሰዓት ደግሞ እኔ በሞተር ስራ ላይ ነበርኩ። ነገሩንም ሰምቼ በጣም ተናድጄ “ወደ ሀደሮ አሁኑኑ እመጣለሁ” ብያት ወዲያው ለጓደኞቼ ሞተሩን ሰጥቼ ወደ እርሷ ለመሄድ ተነሳሁ። እርሷም ተመልሰው ወደ አረካ መሄዳቸውን ነገረችኝ። እኔም በጣም በንዴት መንፈስ ሆኜ “እስቲ ንገሪኝ፣ ልጁ ከአንቺ ምንድን ነው የሚፈልገው?” ብዬ በንዴት ጠየቅኳት። እርሷም “አሁንማ የት ያገኘኛል? በፊት በአረካ ሳለሁ በጣም እፈራ ነበር፣ አሁን ግን የትም ስለማይደርስ ሰድቤው ነው ያባረርኩት ማርዬ፣ ምንም አትጨነቅ” ብላ በጣም አረጋጋችኝ። እኔም ወደ ሀደሮ መሄድ ያሰብኩትን ነገር ቀረሁ። ከዚያም ቀን ጀምሮ ወደ ሀደሮ ተመልሶ አያውቅም፤ እኛም ፍቅራችንን በጥሩ ሁኔታ ቀጠልን።

ስራዬ የግል ስራ ስለሆነ weekend [የሳምንቱ ማብቂያ] ሲሆን ወደ እርሷ ሁሌም እሄዳለሁ። በተለመደውም ቦታ በካምፓችን ላይ አረፍ ጊዜ እናሳልፋለን። ከናፍቆት ብዛት የተነሳ ስንገናኝ ቶሎ አንለያይም ነበር። አንድ ቀን በዚህ ቦታ አምሽታ ስትሄድ በድንገት አባቷ ቤት ውስጥ በጣም መትተዋት፣ ስልኳንም ከእጇ ወሰዱና በግርግዳ ላይ አጋጭተው፣ የስልኩም መስታወት ፈስሶ መጥራት እምቢ አለ። ከቤትም እንዳትወጣ በጣም አስጠነቀቋት። በዚህ መሀል ደግሞ ስልኳን ስሞክር፣ ስሞክር በጭራሽ አይሰራም። እኔም በምን አስቀይሜያት ይሆን ብዬ በጣም ሀሳብ ውስጥ ገባሁ። በዚህ ሁኔታ ሳምንት አለፈ፤ በጣም ተጨነኩኝ።

ከሳምንት በኋላ በሌላ ሰው ስልክ ደውላ “ማርዬ ምንም ቢፈጠር መቼም ቢሆን አልተውህም!” አለችኝ እና በጣም አለቀሰች። ነገሩንም ስጠይቃት ሁሉንም ነገር ነገረችኝ። በጣም አዘንኩ! ወዲያውም ስልኳን ከእጇ ወስጄ እስክሪኑን [መስታወቱን] አስቀይሬ አሰርቼ ሰጠኋት። ግን እንደድሮ በካምፓችን ላይ እንዳንገናኝ፣ አባቷ በጣም እንቅፋት ሆኑባት። ሆኖም የኔ ናፍቆት አላስቻላትም ነበር። ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ ብላ ከቤት ሸውዳ ወጥታ አንድ አንዴ እንገናኛለን። በካምፓችንም እንገናኝ እና አረፍ ጊዜ አሳልፈን በፍቅራችን ሰክረን እንለያያለን።

በቃ ከእርሷ እርቄ ቢያንስ ሁለት ሳምንት እንኳን ለመቆየት አልችልም። የሆነ ጊዜ ወደ አዲስ አበባ ከቤተሰቦቼ ጋር ሄድኩኝ። ከመሄዴ በፊት ሶስት ቀን ሲቀረው፣ ወንድሜ ወደ አዲስ አበባ ስሄድ እዚያ ላለው ወንድሜ የምርቃት በግ እንድገዛ ወደ ሶስት ሺህ አምስት መቶ ብር ሰጥቶኝ ነበር። በጉን በሁለት ሺህ ሰባት መቶ ብር ገዝቼ ከዶዮገና ከተማ

እንደወሰድኩና ከሶስት ቀን በኋላ ወደ አዲስ አበባ እንደምሄድ ነገርኳት። "መሄዱን ሂድ፣ ግን እንዳትቆይ" አለችኝ። ሄጄም ገና ሁለት ማታ ብቻ እንዳደርኩ ወደእኔ ደውላ "ማርዬ ነገ ካልመጣህ በቃ ሞቼ እገኛለሁ" አለችኝ። ብለምናትም መስማት እምቢ አለችኝ። በዚህ በኩል ደግሞ ወንድማችን ወደ ሆሳዕና እንዳንመለስ ከልክሎናል። ደግሞም ከሁላችንም ታላቅ ስለሆነ ሁላችንም እንፈራዋለን። ባንክ ውስጥ የሚሰራው ወንድሜም በጣም ስለሚፈራው እርሱም ወደ ባንክ ደውሎ አስፈቀደ። ሳምንት ሳይደርስ አልለቃችሁም አለን። እንደምንም ከአምስት ቀን በኋላ ወደ ሀደሮ ሸኘን። እኔ፣ ፣ እና ህፃኑ ሁላችም ተመለስን። ማርዬ ከናፍቆቷ የተነሳ በጣም ተናዳ ጠበቀችኝ። በኋላ ላይ ይቅርታ ጠይቋያት፣ ወደ ካምፓችንም ሄደን በጣም ጣፋጭ ጊዜ አሳለፍን።

## ክፍል አስራ ስድስት

የወንድሜ የ ልጅ የ አንደኛ ዓመት የልደት በዓል ደረሰ። በዚህ በህፃኑ ልደት በዓል ብዙ ሰው ተጠርቶ ነበር። የ ጓደኞቹ፤ ባንክ ላይ አብረው የሚሰሩት ሁሉም ተጠርተዋል። እኔም ማርዬን በበኩሌ ጠራኋት። እህቴ ለመውለድ ብላ ወደ እኛ መጥታለች። አባቴም ለህፃኑ ልደት ከሆሳዕና ወደ እኛ መጥቶ፣ ወደ ሀደሮ፣ ተሰብስበናል። በዚህ የልደት በዓል ላይ ፍቅረኛዬ ከቤተሰቦቼ ጋር እንድትተዋወቅ አሪፍ አጋጣሚ ሆነ። ከእህቴም ጋር አስተዋወቅኳት፤ እህቴም በጣም ወደደቻት። አባቴን እና ሌላ ሰው ላስተዋውቃት በጣም ስለፈራሁ ቤት ውስጥ አባቴን፣ የአክስቴን ልጆችንም በእሩቅ አሳየኋት። ወንድሜ ልጅቷ የኔ ፍቅረኛዬ መሆኗን በደንብ አውቋል። ግን እኔን በጣም ስለሚወደኝ እና የእኔን አዕምሮ በጣም ስለሚጠብቅ፣ "ይህች ልጅ ምንህ ነች? የት ታውቃታለህ?" ብሎ አያውቅም። ለ ሚስት ፍቅረኛዬ መሆኗን በደንብ አስተዋውቋያት ነበር።

ከልደት በዓሉ ትንሽ ወራቶች በፊት፣ ሞተር ሳይክል እየነዳሁ ከሞተር ወደቅኩኝ። በጣም አስከፊ እና በጣም ከባድ አደጋ ደረሰብኝ። በሰዓቱ ትንሽ ካፊያ ነበር። ሰዓቱም ወደ አንድ ሰዓት አካባቢ ነበር። እኔ ከጎምቦራ ሰፈር ወደ መናኸሪያ ሰፈር በሀይለኛ ፍጥነት እየመጣሁ ነበረ። በሰዓቱ ዝናብ ስለነበረ መንገድ ላይ ብዙም ሰው የለም። ለዛም ብዬ በጣም በፍጥነት በመንዳት ላይ ነኝ። በዚህ በፍጥነት ላይ ሳለሁ ከስፖርት ሆቴል በኩል የሚመጣ ሲኖትራክ መኪና በአጭሩ ታጠፈና መንገዴን ዘጋብኝ። እኔም በፍጥነት በመሄድ ላይ ስለነበርኩ ከዚህ መኪና ጋር ከምጋጭ ብዬ ቀጥታ ወደ አደባባዩ መሀል ገባሁ። በጣም ፍጥነትም ስለነበረኝ ሞተሩ ወደ ፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ትቦ ወረወረኝ። እራሴንም ሳትኩኝ። ቀኝ እግሬም በጣም ተጎዳ። ከቦታው ሰው አንስቶኝ ወደ ሆሳዕና ሆስፒታል ወሰዱኝ። አብሮኝ ከእኔ ጋር የሚሰራ ጓደኛዬ ጋር ተደወለ። ልጁም በፍጥነት

ወደ እኔ ወደ ሆስፒታል ደረሰ። ለቤተሰቦቼም ደውሎ ነገራቸው። ማታውን ሙሉ እራሴን ሳላውቅ አደርኩኝ። ከሀደሮ ከ ከፍቅረኛዬ ጋር ጠዋቱኑ ወደ እኔ ደረሱ። በጣም ደነገጥኩኝ፤ እንዴት መጣች ብዬም በጣም ተገረምኩኝ። እኔ ወደ ተኛሁበት ክፍል በሩን በርግዳ ገባች። እንደገባች እኔን በተኛሁበት አቅፋኝ በጣም አለቀሰች።

በጣም አለቀሰች። በቃ ክፍል ውስጥ ጭራሽ ለቅሶ ቤት አስመሰሉት። ጓደኛዬም በጣም ገሰፃቸው። “ለምንድነው የምታለቅሱት? ስላልሞተ ነው? በቃ ጌታ አትርፎታል። በቃ ምንም ማልቀስ አያስፈልግም!” አላቸውና ዝም አሰኛቸው። የወንድሜ ሚስት ዶክተሮቹን ጠይቃ፣ በኋላ ዶክተሮቹም ወደ ህይወት ቀዶ-ህክምና ሆስፒታል እንድዛወር አዘዙ። ወደ እዚያም በኮንትራት በባጃጅ ወሰዱኝ። እዛም ህክምና ወስጄ፣ በትልቅ ማሽን ሶኖግራፍ ተነስቼ የእግሬ አጥንት እንዳልተሰበረ ዶክተሩ ነገረኝ።

ከዚያም አውጥተው ወደ ሀደሮ ወሰዱኝ። በሀደሮም ወር ከአስራ አምስት ቀን ቆየሁ። በዚህ ወር ከአስራ አምስት ቀን ከኔ አንድም ቀን ሳትለይ፣ ከክፍል በስምንት ሰዓት ወጥታ፣ ባለ መቶውን ራኒ ጁስ፣ ደግሞም እንቁላል በቤታቸው ሰርታ ወደ እኔ ይዛ ትመጣለች። ወንድሜን ስለምትፈራው ወንድሜ ወደ ባንክ ከሄደ በኋላ፣ ወደ እኔ በስምንት ሰአት አካባቢ ትመጣለች። ደግሞም ያመጣችውን ምግብም ሆነ ጁስ እኔ በእጄ አንስቼ እንድበላ በጭራሽ አትሰጠኝም። በእጇ ታበላኛለች። ጁስ ደግሞ በአፏ ጨምራ በከንፈሮቿ ታጠጣኛለች። በቃ በህይወት ዘመኔ ልከፍላት የማልችለው ውለታ ዋለችልኝ። ደግሞም ተሽሎኝ እስክመለስ በጭራሽ እንዳልቦዝን ሁልጊዜ ወደእኔ ትመጣለች።

በሀደሮ መጀመሪያ በሁለተኛ ደረጃ ስማር ያፈራኋቸው ጓደኞቼ መጥተው በጣም ይጠይቁኝ ነበር። ከሆሳዕና አብረውኝ ስራ የሚሰሩ ጓደኞቼም ወደእኔ መጥተው ይጠይቁኝ ነበር። የ ጓደኞች ደግሞ ከባንክ በጣም ብዙ ነገር በማምጣት ይጠይቁኝ ነበር። የእንጀራ እናቴም መጥታ ከአባቴ ጋር ጠየቀችኝ፤ ወተትም አመጣችልኝ። ወተት ደግሞ በጣም ስለምወድ ከሆሳዕና ከቤት ነው ያመጣችልኝ። አንድ ቀን የምለው ጓደኛዬ እና የምለው ጓደኛዬ ወደ እኔ መጡ። ማርዬንም ከእኔ ጋር በድጋሚ አዩዋት። በጣም ተገረሙ። መጀመሪያ በሆሳዕና እኔ ጋር ማታ መጥታ አይተዋት ነበር፤ አሁን ደግሞ ከእኔ ጋር በቤታችን አይተዋት እኔንም ጠየቁኝ። “ይህቺ ልጅ ላንተ ምንህ ነች? የ ሚስት እህት ነች? ወይስ ዘመድ?” ብለው ጠየቁኝ። እኔ ግልጹን ነገርኳቸው። “ይህች ልጅ ማለት ለእኔ ህይወቴ ነች፤ ደግሞም ሁሉ ነገሬ ነች፤ ፍቅረኛዬ ነች” ብዬ ነገርኳቸው። እነርሱም በውበቷ በጣም ተደነቁ። ለእኔም “ልጅቷ በጣም ውብ ነች፤ እውነት በጣም ታስቀናላችሁ። ዮኒ በጭራሽ እንዳታስቀይማት” አሉኝ። እኔም ለልጆቹ እርሷን በጣም እንደማፈቅራት፣ ደግሞም ለቁምነገር እንደያዝኳት ነገርኳቸው። እነርሱም በጣም ተደነቁ።

ይህ በእኔ ላይ አደጋ መድረሱም፣ ከወንድሜ ሚስት ጋር እርሷን ለማስተዋወቅ ጥሩ አጋጣሚ ሆነ። ከጓደኞቼም ጋር፣ ከብዙዎቹ ጋር አስተዋወኳት። በዚህ በህጻኑ ልደት ጊዜ ደግሞ ከእህቴ ከ ጋር በደንብ ተዋወቀች። እህቴ ከትንሽ ቆይታ በኋላ ወለደች። ለመጠየቅ እንደገና መጣች። በቃ ከእህቴ ጋርም በጣም ተዋወቀች:: ከወንድሜ ሚስት፣ ከ ጋርማ በጣም ቤተሰብ ሆኑ።

# ክፍል አስራ ሰባት

አንድ ቀን ወደእኔ ደውላ “ወደ ሀደሮ አሁን ካልመጣህ፣ ማርዬ እኔን ሁለተኛ በህይወት አታገኘኝም” አለችኝ። እኔም “ማርዬ ምን ሆነሽ ነው? አባዬ አስቀይሞሽ ነው? ወይስ ማሚ?” አልኳት። እርሷ ግን ማንም አላስቀየመኝም፣ ብቻ ዛሬ ላገኝህ እፈልጋለሁ አለችኝ። በጊዜው እኔ ደግሞ በጣም በስራ ተወጥሬ ነበር። እኔም “እሺ ማርዬ በቃ ነገ እመጣለሁ፣ አሁን ሞተር ሰጥቼ እንዳልመጣ ጓደኞቼ የሉም። ለዛም ጓደኞቼ ሲመጡ ለአንዳቸው ሰጥቼ ነገ እመጣለሁ” አልኳት። እርሷም “ዛሬ ካልመጣህ በቃ ሁለተኛ በህይወት አታገኘኝም። የምትወደኝ ከሆነ ዛሬ ልክ ስምንት ተኩል፣ በካምፑ እንገናኝ” ብላ ስልኩን ጆሮዬ ላይ ዘጋችብኝ። እኔም በቃ መልሼ ስደውልላት በጭራሽ ስልክ ማንሳት እምቢ አለች። በመልእክት ጽፌ “ማርዬ እየመጣሁ ነው” ብዬ ነገርኳት። እርሷም መልዕክቱን መለሰች። ሞተሩን በለማ ኢንተርናሽናል ሆቴል ውስጥ አቁሜ፣ ለጥበቃዎቹ ብር ሰጥቼ፣ ጉዞ ወደ ሀደሮ ጀመርኩ።

በሀደሮ መኪና ልክ ስድስት ሰዓት አካባቢ ተሳፈርኩ። መንገድ ላይም ብዙ ጊዜ እየደወለችልኝ ወደ ዋዶሌ ቁልቁለት ደረስኩ። ይህ ቦታ ደግሞ ሁሌም መኪና ለአደጋ የሚጋለጥበት ቦታ ነው። በዚያች ሰዓት ደውላ “ዋዶሌን አለፍክ?” አለችኝ። እኔም መልሼ “አይ ሆዴ ይኸው ገና ዋዶሌ ላይ ነኝ” አልኳት። እርሷም “ማርዬ ዋዶሌ እስከምታልፍ ስፀልይ ነበር” አለችኝ። እኔም መልሼ “ሆዴ ምንም አትጨነቂ፤ ጌታ አለ፤ ምንም አልሆንም” አልኳት። እርሷም “ምንም እንድትሆንብኝ አልፈልግም፤ በቃ ና እየጠበቅኩህ ነው” አለችኝ።

ወደ ወንድሜ ቤት በሰባት ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ ላይ ደረስኩኝ። ወንድሜ ከስራ ለምሳ መጥቶ ቤት ውስጥ ነበር። በድንገት ቤት ገባሁ፤ በጣምም ደነገጡ። “ዮኒ በሰላም ነው?” አሉኝ። እኔም “አዎን በሰላም ነው” አልኳቸው። በኋላ ላይ ወንድሜ ተመልሶ ወደ ስራ ሄደ። ሲሄድም ለ ሚስጥሩን ነገርኳት። እርሷም “በል ቶሎ ሂድ” ብላ ነገረችኝ። ገና ቤት ውስጥ እያለሁ ስምንት ሰዓት ተኩል አለፈ። ወንድሜ ቤት ውስጥ እያለ መውጣት ስላልተመቸኝ፣ ወንድሜ የግድ እስከሚሄድ ጠብቄ ከቤት ወጣሁ። ወደ

ቀጠሮ ቦታ ለመድረስ በጣም በሀይለኛ ሩጫ ላይ ሆኜ ሳለሁ የሆነ ሞተር ከማዞሪያ ከተማ የሚመለስ አገኘሁ። ወደ ቦታው እንዲወስደኝ ሂሳብ ተስማምቼ ሄድኩኝ።

ወደ ቦታው ስደርስ እርሷ ቀድማኝ ደርሳ ነበር፤ ወደ እርሷ ተጠጋሁ። ቦታው በጣም ፍቅር የሚያስይዝ ነው፤ ከስሩ ላይ ቁጭ ብላ ነበር። ከኋላ ሳታየኝ ቀስ ብዬ አጠገቧ ደረስኩና ከኋላ እቅፍ አደረግኳት፣ በተቀመጠችበት ቦታ ጎምበስ ብላ ነበር። ከዚያም እንዳቀፍኳት "ማርዬ እንዴት አለሽልኝ? ሰሞኑን በጣም ናፍቀሽኝ ነበር" አልኳት። ጎምበስ ብላ ምንም ለማውራት እምቢ አለችኝ። በቃ ፀጥ አለች። ላዋራትም ስሞክር ጎምበስ ብላ ፀጥ አለች። ፊቷን ለማየት በግድ አቅፌያት ፊቷን ቀና አደረግኩ። ፊቷም በጣም ተቀይሯል፤ አይኖችዋ ደግሞ በጣም ቀልተዋል፤ በጣም እረጅም ሰዓት እንዳለቀሰች ተረዳኋት።

ምክንያቱን አወቅኩኝ፤ የቀጠሮ ሰዓት አሳልፌ ስለመጣሁ፤ ለዚያም ይቅርታ ጠየቅኳት። ይቅርታዬን ግን መቀበል እምቢ አለችኝ። አውቄ እርሷን ለማስማማት ብዬ በመንገድ ላይ መኪና ተበላሽቶ ነው ብላትም ጭራሽ አልሰማም አለችኝ። በቃ እኔ የቀረኝ መኪና ተገልብጦ እኔ ብቻ ተርፌ ነው የመጣሁት ማለት ብቻ ነበር። ይሄን ያህል ሳባብላት እንኳን በጭራሽ እኔን ለማዋራት ፍቃደኛ አልነበረችም። በቃ ምንም ማድረግ ስላልቻልኩኝ አጠገቧ ሆኜ እኔም ዝም አልኩኝ።

በኋላ ላይ እኔን ለማዋራት ወደ እኔ መመልከት ጀመረች፤ እኔ ግን በተራዬ ዝም አልኩኝ። ልታዋራኝ ሞከረች፣ በቃ ብዙ ሰዓት ሳባብላት ስላልሰማችኝ በጣም ተናድጄ ነበር። በኋላ ላይ በጣም በሃይለኛ እምባዋን እያፈሰሰች በጣም አለቀሰች። በቃ እኔም በጣም አዘንኩላትና ይዣት በእቅፌ ውስጥ አደረግኳት። "በቃ አታልቅሺ" ብዬ እምባዋን ከፊቷ ከለከልኩ። በኋላ ሳታውቅ ወደ ጨዋታ ገባች፤ ነገሩንም ሁሉ እረሳች። በቃ በሳቅና በደስታ ተሞላች። እኔም በጣም ደስ አለኝ። ብዙ ነገር እያወራን እራሳችንን ፈታ አደረግን። እኔም በስልኬ ላይ classical [በመሳሪያ ብቻ የተቀናበሩ] ሙዚቃዎች ከፍቼ በፍቅር ቃላቶች በጣም አጫወትኳት፤ በቃ መጀመሪያ የተቀየመችኝን ነገር እራሱ እረሳች። በሚገርም ጨዋታ ውስጥ ገባች።

በዚህ በጨዋታችንም ላይ "ማርዬ በጨዋታ እኮ የጠራሽኝን ነገር ረሳሽ" ብዬ ነገሩን ከአፌ ሳልጨርስ ማልቀስ ጀመረች። በቃ እኔ ግራ ገባኝ። "ምንድነው የሆንሽብኝ?" ብላትም በጭራሽ ለእኔ መልስ አትመልስም። ግራ ገብቶኝ በጣም ጭንቀት ውስጥ ገባሁ። ከቤተሰቦቿ ጋር እንደተጣላች ስጠይቃትም "ከማንም ጋር አልተጣላሁም" አለችኝ። እኔንም ጠራችኝ፤ "ወዬ ማር" አልኳት "ማርዬ እኔ የምነግርህን ነገር ቃል እገባለሁ ብለህ ነገሩን ከማውራቴ በፊት ቃል ግባልኝ" አለችኝ። እኔም "እሺ ነገሩን ንገሪኝና ቃል

ልግባልሽ ችግር የለም” አልኳት። እርሷም “እባክህ የምነግርህን አደርጋለሁ ብለህ ብቻ ቃል ግባልኝ፤ ማርዬ ስወድክ” አለችኝ። ምንም ባልሰማሁት ደግሞ ምንም ባላወቅኩት ነገር እንዴት ቃል ልግባ? ብዬ በሀሳብ ውስጥ ገባሁ። በቃ ብዙ ነገር ማሰብ ጀመርኩ። አውጥቼ ሳላወራ ብዙ ነገር በውስጤ ማሰላሰል ብቻ ሆነብኝ።

እንዴ ይህች ልጅ ምን ሆና ይሆን? በሰፈር ልጆች ተደፍራ ይሆን? ደግሞም ጸንሳለች እንዳልል እኛ ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ ከከንፈር ያለፈ ግንኙነት በጭራሽ አድርገን አናውቅም። በቃ ይህች ልጅ በንፋስ እንደዶሮ ፀንሳለች ማለት ብቻ ቀረኝ። በቃ በአዕምሮዬ ላይ ብዙ ነገር መምጣት ጀመረ። ብዙ ነገርም ከማሰቤ የተነሳ በጣም አመመኝ። እራስ ምታት ደግሞ ብዙ ከተጨነቅኩ ያመኛል። ይሄን ነገር ደግሞ እርሷም በጣም ታውቃለች። በቃ እራሴን መቆጣጠር አቃተኝ፤ ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ደረሰ። ጎምበስ ብዬም ጭንቅላቴን ይዤ ዝም አልኩኝ። እርሷም ባህሪዬን ስለምታውቅ “ማርዬ አመመህ አይደል?” አለችኝ። “ደግሞም ለዛ ፈርቼ ነው ነገሩን መንገር የፈራሁት” ብላ በጣም ወደ እኔ ቀርባ “ማርዬ እኔ ልታመም! እኔን ይመመኝ! እኔ ምን አይነት ሰው ነኝ?” ብላ እራሷን መስደብ ጀመረች። እኔም “ማርዬ አይ አላመመኝም” ብዬ ነገሩን እንድትነግረኝ ጠየቅኳት። “ማርዬ እነግርሃለሁ፥ ግን በእናትህ ቃል ግባልኝ እኔ የምልክን ለማድረግ” አለችኝ። በቃ በጣም ደነገጥኩኝ ሰው ምንም ሲለምነኝ በእናትህ ካለኝ በጭራሽ እምቢ ማለት ይከብደኛል።

በዚህ ምክንያት በቃ ምንም ባልሰማሁት ነገር ቃል ገባሁላት፤ ነገሩንም መናገር ጀመረች። “ማርዬ እሁድ ቀን እኔና ማሚ ቤት እያለን በሆነ ነገር ላይ ደነገጥኩና እራሴን ስቼ ወደቅኩ። ከዚያም ማሚ ወደ ክሊኒክ ወሰደችኝ። ከዚያም ዶክተሩ መርምሮኝ የልብ ድካም እንዳለብኝ ነገረኝ” ብላ ነገሩን ግልፅ አድርጋ ነገረችኝ። ጭንቅላቴ ሁለት ቦታ ተሰነጠቀ፤ ማውራት እራሱ አቃተኝ፤ በአይኖቼ ዝም ብሎ እምባ ይወርዳል። በቃ ቀኑ ለኔ ጨለመብኝ። እምባ ብቻ ከአይኔ ይወርዳል። በቃ እርሷን አቅፌአት መራራ ለቅሶ አለቀስኩ። እርሷም ደግሞ የሚያሳዝን ነገር እያወራች ልቤን ሰበረችው። “ማርዬ በቃ ልሞት ነው አይደል? በቃ ልለይህ ነው አይደል?” ብላ በጣም አስለቀሰችኝ። ተቃቅፈንም እረጅም ሰዓት አለቀስን።

እኔም እንዳትጎዳብኝ ብዬ እንዳታለቅስ ማባበል ጀመርኩ። በዛች ሰዓትም ወደ አዕምሮዬ የሆነ ነገር መጣልኝ “ማርዬ ምንም አትሆኚም፥ አይኔ እያየ አትሞቺም! ልቤን እራሱ መቀየር የሚቻል ከሆነ ልቤን እሰጥሻለሁ” አልኳት። እርሷም “ምንም እንድትሆንብኝ አልፈልግም! አንተ ጥሩ ቦታ ደርሰህ ጥሩ ህይወት እንድትኖር ነው የምፈልገው” አለችኝ። እኔም መልሼ “ማርዬ ምንም አትሆኚም! ጌታ ደግሞ ከእኔ በጭራሽ አይለይሽም”።

ደግሞም ሌላ ሀሳብ ወደ አዕምሮዬ ሲመጣ እንዲህ አልኳት “ማርዬ ወደ ሀዋሳ እወስድሻለው። ወደ ነቢይ እዩ ጩፋ ቤተክርስቲያን” አልኳት። “ደግሞም ጌታ በፍፁም ይፈውስሻል፤ ምንም አትጨነቂ!” ብዬ በብዙ ቃል አጽናናኋት። እርሷም አባቷ እንዲሁ እንዳለ ነገረችኝ። “ከአባቴ ጋር ካልሄድኩ፣ ከእናቴ ጋር እሄዳለሁ” አለችኝ።

በኋላ ላይ “ማርዬ ሁሉንም ነገር ነገርኩህ አይደል? በቃ ቃል ግባልኝ። እኔ ከእንግዲህ አልጠቅምህም። አይኔ እያየ ለሰው አሳልፌ ከምሰጥህ አንድ ነገር ብቻ ተለመነኝ” አለችኝ። እኔም “ማርዬ የፈለግሽውን ነገር ጠይቂኝ፣ ቃል እገባልሻለው” አልኳት። እርሷም “ማሬ የሆነች ጓደኛዬ አለች፤ በጣም ጥሩ ልጅ ነች፤ እንደእኔም ልትንከባከብህ ትችላለች። በጣም ጥሩ ናት። በቃ ከልጅቷ ጋር እሆናለሁ ብለህ እባክህ ቃል ግባልኝ” አለችኝ። እኔም “ማርዬ ምንም አትጨነቂ፤ ደግሞም ፈጣሪ ከእኔ በፍጹም አይነጥልሽም፤ በእውነት ትድኛለሽ። ምንም አታስቢ።” ብያት ነገሩን ማረሳሳት ጀመርኩ። ደግሞም በብዙ ቃል አጽናናኋት፤ ነገሩንም ረስተን ወደ ጨወታና ወደ ወሬአችን ገባን። ቀኑም በዚህ ሁኔታ አለፈ። በማግስቱ ወደ ሆሳዕና ሸኘችኝ። ሳምንት አለፈ፤ ከዚያም ከአባቷ ጋር ወደ ሀዋሳ ሄደች። ወደ እዩ ጩፋ ቤተክርስቲያን ገቡ። ለእኔም ደውላ ወደ ቤተክርስቲያን እንደገባች ነገረችኝ። ነብዩም ወደ መድረክ ከአባቷ ጋር ጠራት እና ወደ መድረክ ወጡ። የእግዚአብሔር እጅም ደርሶላት ከበሽታዋ ተፈወሰች። አባቷም ትንሽ ያስለውና ያመው ስለነበር እርሱንም ፀልዮለት ከበሽታው ተፈወሰ።

የሆነውን ነገር ሁሉ ነገረችኝ። እኔም ሆሳዕና ቤት ውስጥ ብቻዬን ነበርኩ። በጣም ደስተኛ ሆንኩ። በደስታም ብዛት ቤት ውስጥ ብቻዬን እየጮህኩ ያዳናትን እግዚአብሔርን ማመስገን ጀመርኩ። “ማርዬ ከሀዋሳ እየተመለስኩ ነው ምን ላምጣልህ?” አለችኝ፤ እኔም “ማሬ ስትመለሺ ልክ አንቺን የሚመስል ውብ የሆነውን አናናስ እና በእጅ የሚደረግ ጌጥ፣ በጌጡም ላይ እወድሃለሁ የሚል ፅሁፍ ያለውን” አልኳት።

## ክፍል አስራ ስምንት

ከሀዋሳ ወደ ሀደሮ ከአባቷ ጋር ተመለሰች። በሁለተኛው ቀን ወደ እኔ ወደ ሆሳዕና መጣች። ገና መንገድ ላይ ነኝ ብላ ስትደውልልኝ ለደስደስም ብዬ በጣም ፈታ ብዬ ልጠብቃት ፈለግኩና ወደ ፀጉር ቤት ገባሁ። ከፀጉር ቤት ተስተካክዬ ወጣሁና መናኸሪያ ሰፈር በሚገኘው ቃና ካፌና ሬስቶራንት ውስጥ ቁጭ ብዬ ጠበቅኳት። እርሷም ከመኪና ወርዳ ወደ እኔ መጣች። ይገርማል! ገና ከእሩቅ ሳያት እሩጫዬን ቀጠልኩ። ሄጄም እቅፍ አደረግኳት። በቃ በደስታ ብዛት ተቃቅፈን መሳሳም ብቻ ሆነ፤ ሰውን እንኳን አልፈራንም ነበር። ከዚያም ወደ ቤቴ ወሰድኳት። ሰዓቱም ወደ አምስት ሰዓት አካባቢ ነበር።

ወደ ቤት እንደደረስን ፈጣሪ እንዴት እንደረዳት እና ደግሞም ሌላ ትልቅ የሆነ መልእክት በነብዩ እንደተላለፈላት ብዙ ነገር ነገረችኝ። “በ2008 የጀመርሽው ነገር አለ፤ ያ የጀመርሽው ነገር የራስሽ ነው፣ የግልሽ ነው” የሚል መልእክት በነብዩ ተላለፈላት። እርሷም “በ2008 ዓመተ ምህረት የጀመርኩት ምንድነው?” ብላ በጣም አሰበች በኋላ ላይ ነገሩን እንደተረዳች ለኔም ግልፅ አድርጋ ነገረችኝ። “በዚያን ዓመት ምንድን ነው የጀመርኩት?” ብላ ስታስብ በዚያ በ2008 ዓመተ ምህረት ከእኔ ጋር ፍቅር የጀመረችበት ጊዜ ነበር። ይህንን ስትነግረኝ በቃ በጣም ደስ አለኝ፤ ስለሁለታችን የጌታ ፍቃድ ስላለም በጣም ደስ አለኝ። ደግሞም በነብዩ ወደፊት እርሷ ወደ ሰባት የሚሆን ብዙ ድርጅት እንደሚኖራት መልእክት ተላልፎላታል። በቃ ይህን ነገር ስትነግረኝ በጣም ደስ አለኝ።

የሀዋሳውን ወሬ ስታጫውተኝ ሰዓቱ ወደ ምሳ ሰዓት ቀረበ። ያመጣችውንም ስጦታ በእጄ ላይ አደረገችው። እኔ መጀመሪያ እንዳልኳትም በጌጡ ላይ እወድሃለሁ የሚል መልእክት ተፅፎበት ነበር። በእጄ ላይም አጠለቀችው። ሌላው ደግሞ የሀዋሳ አናናስ ነበር። ይህን ደግሞ ከምሳ በኋላ እንበላለን ተባብለን ለምሳ ወደ ከተማ ወጣን። ሁሌም የምንጠቀምበት በጣም የምወደው ሆቴል አለ፣ ወደዚያ ሄድን። በአሻም ዓለም አቀፍ ተቋም ውስጥ ከተቀመጥንበት ትንሽ እራቅ ብሎ፣ በሀደሮ ንግድ ባንክ ውስጥ የባንኩ ሃላፊ፣ ስሙም የሚባል ተደብቆ በጣም እያየን ነበር። ሁለታችንም ምሳ ሲቀርብ ወደ እጅ መታጠቢያ ሄድን። እጃችንን ታጥበን ስንመለስ እኔና ዓይን ለዓይን ተገጣጠምን። በጣም ደነገጥኩ። በቃ ለ ጓደኛው ስለሆነ ይናገራል ብዬ በጣም ፈራሁ። ለማርዬ ነገሩን ስነግራት በጣም ፈራች። እርሷም አባዬን ያውቀዋል ብላ በጣም ፈራች። የሆነው ይሁን ብለን ምሳችንን መብላት ጀመርን።

ምሳም በልተን ከጨረስን በኋላ ወደ ሌላ ቦታ፣ ወደ ፊቶና ካፌና ሬስቶራንት ገባን። እዚያም ሻይ ቡና ብለን ተመልሰን ለማረፍ ወደ ቤት ሄድን። ያን ቀን የሰጠችኝን ስጦታ፣ ያን ቀን በእጄ ላይ በእጆችዋ ያደረገችልኝን አንድም ቀን ሳላወጣ ቆየሁ። ስጦታዋ ከዚያም ቀን ጀምሮ ከእጄ በጭራሽ ወጥቶ አያቅም ነበር። ከሻይ ቡና ተመልሰን ለማረፍ ወደ ቤት ውስጥ ገባን። በደስታ ልብ ተቃቅፈን መኝታዬ ላይ ተኛን፤ በተኛንበት ቦታ ላይ በጣም መሳሳም ጀመርን። በጣም እየተሳሳምን ሳናውቅ ወዳልተፈለገ ስሜት ውስጥ ገባን። በፊት ስንሳሳም እንዲህ ትለኝ ነበር “ማርዬ እኔ መቼም ቢሆን የሴትነት ክብሬን ለአንተ ነው የምሰጠው” ትለኝ ነበር። ለዛም በዚህ ስሜት ውስጥ እያለን ያ ነገር ትዝ አለኝ። ማርዬም ከመኝታ በርግጋ ተነሳች እኔም እራሴን ማረጋጋት ጀመርኩ። ደግሞም በእርሷ ላይ እንደዚ ያለ ነገር በጭራሽ አስቤ አላውቅም፣ ምክንያቱም በጣም እወዳታለሁ በጣምም አፈቅራታለሁ። ማርዬም “ሆዴ ምንም ስሜት ውስጥ ብንገባ እንዴት በኔ ላይ እንደዚህ አሰብክ?” ብላ በቃ በኔ ላይ በጣም ተቆጣች። በፊት ከስድስት ዓመት በኋላ

ፈጣሪ ካለ እንጋባለን ብለን ቃል ተገባብተን ነበር። ደግሞም በትምህርታችን መሀል ምንም ነገር እንዳይፈጠር ጭምር። ለዛም ብላ በጣም አኮረፈች።

በዚህ ነገር ውስጥ ሆነን ሳናውቅ ቀኑም መሸ፣ ወደ አስራ ሁለት ሰዓት አልፎ ነበር። በዚህ ሰዓት ደግሞ ብቻዋን እንዳትሔድ ሳስብ፣ በሰዓቱ መናኸሪያ ተዘግቶ ሚኒባስና ሀይሩፍ መኪና ብቻ ነበር አገልግሎት የሚሰጠው። እነርሱም ደግሞ በሕገ ወጥ ነው የሚጭኑት። “ልጅቷን የሆነ ቦታ ይዘዋት ቢጠፉስ?” ብዬ ብቻዋን እንዳትሄድ ፈራሁ። “አድረሽ ነገ ትሄጃለሽ” ስላትም “አባዬ በህይወቴ ይቀብረኛል” ብላ ማደር እምቢ አለችኝ። የምሆነው ነገር አጥቼ በቃ ከእርሷ ጋር ወደ ሀደሮ ለመሄድ ወሰንኩኝ። ሕጋዊ ትራንስፖርት [መዳዳዣ] ስለሌለ፣ ሰዓቱም ስለመሸ፣ እንደምንም ቀጥታ የሚጭን የወላይታ ሀይሩፍ መኪና አገኘሁ። የወላይታ መዳዳዣ ሂሳብ ከፍለን፣ እስከ ማዘሪያ ከተማ ተሳፍረን ገባን። በሶስተኛው ወንበር ላይ ሁለታችን ብቻ ተቀመጥን። ቅድም ያደረግነውንም ስህተት እረሳችና እኔን እቅፍ አድርጋ መሳም ጀመረች። በቃ በጣም አበድን። መኪናው ውስጥም መብራት አልበራም። ጨለማም ስለሆነ ለመሳሳም በጣም ተመቸን፣ ወደ ማዘሪያ እስከምንደርስ መኪናው የት እንደደረሰ አላወቅንም ነበር። የመኪናው ረዳት “ማዘሪያ ወራጅ አላችሁ?” ሲል ከመኪናው ወረድን።

ወደ ሀደሮ ከተማ የሚወስድ መኪና ስንፈልግም አጣን ወደ ሁለት ሰዓት ተኩል ሆነ። አንድ ባጃጅ ብቻ ነበር። ኮንትራት ተስማምተን ጉዞ ቀጠልን፤ ወደ ቤታቸው ድረስም በባጃጅ ሄድን። በበራቸውም ላይ እርሷን አወረድናት። ሳመችኝና “ማርዬ መልካም ምሽት” ብላ ወደ ግቢ ገባች። እኔም ወደ ወንድሜ ቤት ተመለስኩ። ወደ ቤትም ገባሁ። በጣም ደንግጠው እንዲህ አሉኝ “ዮኒ ሰላም አይደለም? በሰላም ነው?” አሉኝ። እኔም “በሰላም ነው፤ ሲደብረኝ ጊዜ ነው ማታ መኪና ‘ሀደሮ፣ ሀደሮ’ ሲል በቃ ዝም ብዬ ስለናፈቃችሁኝ መጣሁ” አልኳቸው። ከዚያም እራት አቀረቡልኝ፣ እራትም በልቼ ጨረስኩና ወደ መኝታ ሄጄ፣ የመኝታ ልብስ ቀይሬ፣ ወደ ሽንት ቤት ሄጄ፣ ለእርሷም ደወልኩ። አባቷ ተቆጥተዋት፣ ምንአልባት መትተዋትም ይሆናል ብዬ ፈርቼ ስለ ነበር አባቷ እንደተቆጣት ጠየቅኳት። በኋላ በር ሸውዳ ገብታ ወደ ክፍሏ እንደገባች ነገረችኝ። ይህንንም ነገር ከጠየቅኳት በኋላ ወደ ክፍሌ ተመልሼ ተኛሁ። ነግቶም ከእንቅልፌ ተነስቼ ልብሴን ቀይሬ ወደ ሆሳዕና ለመመለስ ተዘጋጅቼ፤ ቻው ብያት እሄዳለሁ ብዬ ስልኬን አውጥቼ ሞከርኩ። ስልኳን ስሞክርም መስራት እምቢ አለኝ። በቃ መኪና ውስጥ ሆኜ እደውልላታለሁ ብዬ ወደ መናኸሪያ ሄጄ በሆሳዕና መኪና ተሳፈርኩ።

እንደገና ስሞክር ስልኳ ሰራልኝ፣ በጣም ተደሰትኩኝ። በደስታ ላይም ሳለሁ ግን ስልኩ ዝም ብሎ ይጠራል እንጂ ስልኩን ለማንሳት እምቢ አለችኝ። በቃ አባቷ እንደተቆጣት

ማሰብ ጀመርኩ። ደጋግሜ ስደውልላትም በጭራሽ ማንሳት እምቢ አለችኝ። ሳላገኛትም ወደ ሆሳዕና ተመለስኩ። ከዚያም በጣም ጨንቆኝ የምሆነውን አጣሁ። በሰው ስልክ ስደውል ወይ ታነሳለች ወይም አታነሳም ብዬ አስቤ በሰው ስልክ ደወልኩላት፤ ወዲያው አነሳች። ላናግራት ስጀምር ድምፄን ሰምታ ጆሮዬ ላይ ዘጋችው። በቃ ግራ ተጋባሁኝ። ነገሩም ግራ ስለገባኝ ደግሜ በራሴ ስልክ ደወልኩላት፣ ከዚያም አነሳች። ስልኩን አንስታም “ምን ፈልገህ ደወልክ? ሁለተኛ እኔ ጋር እንዳትደውል!” አለችኝ። በጣም ደነገጥኩና “ምን ተፈጥሮ ነው ማርዬ እንዲህ የምትሆኚው?” ስላት “ማርዬ አትበለኝ!” አለችኝና “ትላንትና ያደረግከውን እረሳህ እንዴ? ደግሞ ያደረግከውን አድርገህ ምን ተፈጥሮ ነው ትላለህ?” ብላ በእኔ ላይ ጮኸች። “ትላንትና ምንድነው ያደረግኩሽ?” ብዬ ስጠይቃትም “አዬ! አላወቅህም?! ያደረግከውን አድርገህ አሁን ደግሞ ምንም እንዳላወቀ ሰው ትሆናለህ?” ብላ በጣም በቁጣ ተናገረችኝ። እኔም ላስረዳት ሞከርኩ። “ማርዬ ትላንትና እኮ ምንም ነገር አልተፈጠረም” አልኳት። እርሷም ደግሞ “ምንም አልተፈጠረም ትላለህ? እስኪ ምን እንዲፈጠር ፈልገህ ነበር? እስኪ ንገረኝ?” ብላ በቁጣ መንፈስ ተናገረች። በቃ የንዴት መንፈስ ሲበርድላት እደውላለሁ ብዬ ስልኩን ዘጋሁት። ሰው ብዙም ሲጨቀጨቀኝ ደግሞም በጣም ከተናደድኩኝ እራሴን ስለሚያመኝ በቃ ክርክሩን አቆምኩት። እርሷም ደግሞ ስለኔ በጣም ታውቃለች።

ከዚያም ከቆይታ በኋላ ይሄኔ ንዴቷ በርዶ ይሆናል ብዬ ስልኳን ሞከርኩ፤ ስልኳን አንስታም እንደገና ክርክሩን ቀጠለች። በቃ ንዴቷ በጭራሽ እየባሰ ሄደ። በቃ እኔም በጣም ተናደድኩኝ፤ ምንም ባልተፈጠረ ነገር እንዲህ የሆነችው? ብዬ በጣም ተናደድኩ። በቃ ለሳምንትም ያህል ምንም የሚባል ግንኙነት በመሀከላችን ጠፋ። በቃ ተዘጋጋን። ከሳምንት በኋላ በመልእክት እንዲህ ብላ ማውራት ጀመረች። “ግን በእኔ ላይ እንደዚህ አይነት ክፉ ነገር ለምን አሰብክ?” አለችኝ። እኔም በቃ ባላደረግኩትም ጥፋት ቢሆን ስለምወዳት ብዬ “በቃ ይቅርታ!” አልኳት። እርሷ ግን ይቅርታዬንም መቀበል እምቢ አለች።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳለሁ ወንድሜ ወደ ሀደሮ፣ ከሆሳዕና የሆነ እቃ ይዘህ ና ብሎ አዘዘኝ። ያዘዘኝን እቃ ይዤም ወደ ሀደሮ ሄድኩኝ። በሀደሮም ሳለሁ የሚባል ጓደኛዬን ስለ ሁለታችንም በደንብ ስለሚያውቅ “ዮኒ ከቺክህ ጋር እንዴት ነህ?” ብሎ ጠየቀኝ። እኔም እንደተጣላን ነገርኩት፤ እርሱም ደነገጠ። ምክንያቱም ሁለታችንም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስንማር የነበረውን ፍቅራችንን ያውቃል። በዚያን ጊዜ በነበረን ፍቅር ሰው ሁሉ ይቀና ነበር። ለዚያም ብሎ በቃ ካላስታረቅኋችሁ ብሎ ለመነኝ። ልጁ በጣም ጓደኛዬ ስለሆነ፣ ደግሞም በጣም ስለምወደው፣ እምቢ ልለው አልደፈርኩም። ከዚያም የእርሷን ስልክ ከእኔ ወስዶ ደወለላት። በቃ ታረቁ ብሎ ጠየቃት። እርሷም መልሳ

ለ እኔ ያላሰብኩትን ነገር ማውራት ጀመረች። ያወራቸውን ደግሞ ከልጁ ሰማሁኝ፤ በቃ ከፋኝ፤ ይልቁን በጣም ተናደድኩኝ። "ሁለተኛ ከእርሷ ጋር በጭራሽ አልታረቅም!" ብዬ በቃ ፊት ቃል ገባሁ። ተስፋ ቆርጦ ነገሩን ተወው። እኔም ከሀደሮ ከተማ ወደ ሆሳዕና ተመለስኩ። ሳንታረቅም፣ ምንም ንግግር ሳናደርግ ሳምንቶች አለፉ።

ነገሩም በጣም ከበደኝ፤ ደግሞ ያሳለፍናቸውን የፍቅር ጊዜያቶች ሳስብ በጣም ጭንቀት ያዘኝ። ትዝታዎች እየመጡ በጣም አስቸገሩኝ፣ ደግሞም በጣም አሳመሙኝ። በቀን በቀን እራስ ምታት፣ ጭንቀት፣ መበሳጨት፣ በቃ ምን ልበል? በጣም ከበደኝ፤ ምክንያቱም ዛሬ በዛሬ ያገኘኋት ሴት አይደለችም። ከ2008 ዓመተ ምህረት ጀምሮ ያፈቀርኳት ፍቅረኛዬ ነች። ሦስት አመት ሙሉ በፍቅር አብሬአት ያሳለፍኳት ሴት ነች። በቃ ዛሬ በዛሬ እንዳገኘችኝ ቆጠረችኝ። አበቃ! ለእርሷ ያለኝ ፍቅር በጣም ቀነሰ፣ ልረሳትም ወሰንኩኝ።

## ክፍል አስራ ዘጠኝ

ሳንታረቅ ብዙ ሳምንት አለፈ። ልረሳትም ሞከርኩ፣ ሆኖም ግን አልቻልኩም ነበር። ከዚያም ስልኬ ላይ ያለውን የእርሷን እና የእኔን ፎቶዎች ሁሉንም አጠፋሁ። በቃ በስልኬ ላይ ያሉትን ስለ ፍቅር የተፃፉ ጥቅሶች፣ ዘፈኖች፣ ፊልሞች፣ ሁሉንም አጠፋሁኝ። ግን ምንም ባደርግ ከአዕምሮዬ አልጠፋ አለችኝ። በቃ የምሆነውን ነገር አጣሁ። በቃ በጭንቀት አረርኩ፣ ተቃጠልኩ። የባሰ ትዝታዎች እየመጡ ማታ ማታ በጭራሽ እንቅልፍ የሚባል ነገር አጣሁ። ከጭንቀቴ የተነሳ "ለምን መጀመሪያ አገኘሁሽ? ለምን በህይወቴ ላይ መጣሽብኝ?" እላታለሁ ብዬ ስልኬን ከኪሴ አውጥቼ ደወልኩላት። ስልኳም "ከአገልግሎት መስጫ ክልል ውጪ ነው" ይላል። ከዚያም ለእኔ የሰጠችኝን ወደ ዘጠኝ የፍቅር ደብዳቤዎች ነበሩ። እነዚህን ደብዳቤዎች መልሼላት፣ ነገሩን ጨርሼ እመጣለው ብዬ ወደ ሀደሮ ሄድኩኝ።

ከሆሳዕና በራሴ ሞተር ነበር ወደ ሀደሮ የሄድኩት። ቀጥታ ወደ ወደ ሁለተኛ ደረጃ እና መሰናዶ ትምህርት ግቢ ደረስኩኝ። እርሷም የጠዋት ፈረቃ ነበረች፣ መውጫ ሰዓትዋ ደግሞ ልክ ስድስት ሰዓት ከሰላሳ ላይ ነው። እኔ ግን የሚባል ጓደኛዬ፣ ከእርሱ ጋር ሆኜ ልክ ስድስት ሰዓት ላይ ትምህርት ቤቷ በር ላይ ጠበቅኳት። ከክፍል ወጥታ መጣች፤ እኔ ደግሞ ከእሩቅ እንደምትመጣ አይቼ ወደ እነርሱ ሰፈር መታጠፊያ ላይ ሞተር አቁሜ፣ በሞተሩ ላይ ቁጭ ብዬ ጠበቅኳት። ወደ እኔም ደረሰች። ሳታስብ በድንገት ፊቷ ላይ መጣሁ፣ በጣም ደነገጠች። ለእኔም ሰላምታ ሰጠችኝ። እኔም ሰላም ብያት ከዛም ስለ ትምህርቷ ጠየቅኳት። እንደመጣሁት አልሆንኩም። ፊቷን ሳይ ንዴቴ ቀለለ።

እርሷም “እንዴት በድንገት መጣህ?” አለችኝ። እኔም “ስልክሽን ለምን እንዳይሰራ አደረግሽው?” ስላት አባቷ የእርሱ ስልክ ተበላሽቶበት ለጊዜው የእርሷን ስልክ እንደያዘ ነገረችኝ። ከዛም “በቃ ሌላ ሰውም አፍቅረሽ ከሆነ ግልፁን ንገሪኝ፣ እኔም ቁርጤን አውቄ ልቤን ላሳርፍበት” አልኳት። እርሷም “እባክህ የማይሆን ነገር አታውራ፣ እንዴት ይህን የሞተ ነገር ታስባለህ?” አለችኝ። በቃ ከዚህ በላይ ማውራት አልፈለግኩም ነበር። ምክንያቱም ንግግር ማድረግ ከቀጠልኩኝ በንዴት የተነሳ ስለሚያመኝ ብዬ ከኪሴ በፊት የፃፈችልኝን ደብዳቤ አውጥቼ በእጇ ሰጠኋት። እርሷም “ምንድነው?” አለችኝ። እኔም “አይ በፊት ለእኔ የፃፍሽልኝ ደብዳቤ ነው። ባይሆን ስሜ ያለበትን ደምስሰሽ አጥፍተሽ ለምትወጂው ሰው መስጠት ትችያለሽ፤ ደግሞም ለቃላት አትቸገሪም” አልኳት። እርሷም “እባክህን የሞተ ነገር አታስብ” ብላ በጣም ተናደደችብኝ። “እኔን በደንብ ስሚኝ፣ ሁለተኛ አልረብሽሽም፣ አላስቸግርሽም። አንድ ነገር ብቻ አሁንም በደንብ አዳምጪኝ። ዛሬ ልክ በስምንት ሰዓት ተኩል ላይ በተለመደው በካምፕ ላይ ላገኝሽ እፈልጋለሁኝ” ብያት በሞተር ላይ ወጥቼ፣ ልጁንም በሞተር ላይ ውጣ ብዬው፣ ሞተሩን አስነሳሁት። ልጁም “ለምንድነው እንደዚህ የምትሆኑት?” ብሎ ሊጠይቀን ሞከረ። እኔ በጣም ተናድጄ ስለነበር ሁለቱንም ባሉበት ጥያቸው ሄድኩኝ።

በኋላ ላይ ተለይቷት ወደ እኔ መጣ፤ ወደ ሰፈርም ሄድን። ልክ ስምንት ሰዓት ተኩል ሲሆን ወደ ካምፕ ሄጄ እስከምትመጣ እረጅም ሰዓት ጠበቅኳት። ግን መምጣት እምቢ አለች። በቃ የእርሷን ነገር ሁሉ እረስቼ ወደ ሆሳዕና ሄድኩኝ። በቃ እርሷን ለመርሳት ስል በስልኬ ላይ ያለውንም ነገር፣ ለእኔ የፃፈቻቸውንም ደብዳቤዎች ሁሉ ሰረዝኩኝ። ግን ሆኖም በጭራሽ ከውስጤ ያሳለፍኩት ነገር ትዝታዎች አልጠፋ አለኝ። በኋላ ላይ ለተወሰነ ጊዜ ስራ አቁሜ ወደ ሀዋሳ ሄጄ ለተወሰነ ጊዜ ለመቀመጥ፣ ጭንቀቴንም ለመርሳት ወሰንኩኝ። ደግሞም እርሷም እንደረሳችኝ አወቅኩ። ምክንያቱም ለብዙ ሳምንታት በጭራሽ ልታዋራኝ አልፈለገችም። ለአንድ ቀን እንኳን ድምጼን ሳትሰማ መዋል የማትችል ሰው፣ እንዴት ለብዙ ሳምንት ሳታዋራኝ መቆየት ቻለች? ብዬ በቃ እንደረሳችኝ አወቅኩ።

ሁሉን ነገር ከፊቴ አጥፍቼ መጽናናት ጀመርኩ። ወደ ሀዋሳም ሄጄ ለመዝናናት ለጓደኞቼ ቤቴን እና ሞተር ሳይክሌን ሰጥቻቸው፣ ሁሉንም ነገር አስተካክዬ ወደ ሀዋሳ ለመሄድ ተዘጋጀሁ። በቃ ሁሉንም ነገር እረሳሁኝ፤ እራሴንም ማፅናናት ጀመርኩ። እንዲህም ብዬ ለራሴ ቃል ገባሁ። ሁለተኛ ሴት ልጅን ለፍቅር ብዬ በጭራሽ አልቀርብም ብዬ ቃል ገባሁ። ሁሉንም ነገር እረስቼ እራሴን በማፅናናበት ሰዓት አንድ ነገር ተፈጠረ፤ በስልኬ ላይም መልእክት ገባ። ምንድን ነው ብዬ ቶሎ ብዬ ስልኬን አውጥቼ መልዕክቱን ማንበብ ጀመርኩ። መልዕክቱም እንዲህ ይላል “እባክህ ትዝታዎችህ እየመጡ አሰቃዩኝ። እባክህን

ኸረ መላ በለኝ? ደግሞም ነገ ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" ብላ መልዕክቱን ላከችልኝ። እኔም በጣም ተገረምኩኝ። "ይሄን ያህል ቆይታ ዛሬ እንዴት አሰበችኝ?" ብዬ በጣም ተገረምኩኝ። "ደግሞም ነገ ምን እንደሆነ ታውቃለህ?" ብላ የጠየቀችኝ ነገር ትዝ አለኝ። ነገ ማለት ለእኔና ለእርሷ ትልቅ ቀን ነው። ከተገናኘንበት ቀን ጀምሮ ይህን ቀን ሳናከብር አልፈን አናውቅም ነበር። ይህ ቀን እርሷ እና እኔ የተገናኘንበት ቀን ነው። ዓመቱንም በመጠበቅ ቀኑን እናከብራለን። በየዓመቱ ቀኑን ጠብቀን በየካቲት 23 አሪፍ ቦታ ሄደን፣ ወይም ጥሩ ሎጅ መርጠን፣ ወደዚያም በመሄድ ነግቶ እስከሚመሽ ድረስ ተለያይተን አናውቅም ነበር። በቃ በዚህ አመት ደግሞ እንዳናከብር ተጣልተናል፤ በቃ ለእኔም በጣም ተሰማኝ።

መልእክት ፅፌ መልሼ ላኩላት። "እንዴት የተረሳውን ሰው አሰብሽ?" አልኳት። በቃ በጣም ተናድጄባት ስለነበር ይህንን መልእክት ብቻ ልኬላት ስልኩን አጠፋሁት። በኋላ ላይ ለወንድሜ ሚስት ለ[redacted] ሁሉንም ነገር ነገረቻት፤ [redacted]ም እንደተጣላን ነገሩን ሰማች። ከሰማች በኋላ ወደ እኔ ደውላ ነገሩን ጠየቀችኝ። እኔም "ምንም አልተፈጠረም" ብዬ ለ[redacted] ነገሩን ለመደበቅ ስሞክር፣[redacted] "ዮኒ አሁኑኑ ደውለህ ይቅርታ ጠይቃት፣ ጥፋቱ እንኳን የእርሷም ቢሆን አንተ ይቅርታ ጠይቃት፤ ደግሞም አንተ በጣም ጥሩ ልጅ ነህ ሰውን ማስታረቅ የምትችል ሰው እንዴት ትጣላለህ?" ብላ በጣም ተቆጣችኝ። በቃ[redacted] በጣም ስለምወዳት፣ ደግሞም እርስዋ የተናገረችኝን ነገር እምቢ ማለት በጣም ሼም [ነውር] ስለሆነ፣ በቃ እደውልላታለሁ ብዬ ቃል ገባሁኝ። ወዲያውኑም ደወልኩላት። አናገርኳት፤ ሰላምታ ጠየቅኳት፤ እርሷም ስለ ጤንነቷ ነገረችኝ። በቃ በሰላም ንግግሩን ጀመርን። ወደ ሌላ ሃሳብም አልሄድንም፣ ወደ ክርክርም ሳንገባ በሰላም ሰላምታ ተለዋወጥን። እኔም "ነገ በተለመደው ቦታ ላገኝሽ እፈልጋለሁ" ብዬ ጠየቅኳት፣ እርሷም "እውነትህን ነው? ኸረ እኔ አላምንም!" አለችኝ። እኔም "አዎን እውነቴን ነው፤ ምነው ችግር አለ?" ስላት "አይ፣ አይ በቃ እሺ ነገ እንገናኝ። ኸረ ይመቸኛል፣ ችግር የለውም" ብላ ነገረችኝ።

በማግስቱም በተለመደው ቦታ በካምፓችን ላይ ልክ በስምንት ሰዓት ተኩል ላይ ተገናኘን። በቃ በጣም ይገርማል! ፊት ለፊትም ስንገናኝ እንደተጣላ ሰው በጭራሽ አልሆንንም። በቃ በጣም ተነፋፍቀን ነበር፤ ወዲያው ተቃቅፈን እረጅም ሰዓት ቆየን። በተለመደው ቦታችን ላይ ሁለት መንትያ እንጨት አለ፤ ሁሌም በዚህ እንጨት ስር ነበር የምንቀመጠው። ከዚያም ወደ እዚህ ቦታችን ሄደን ተቀመጥን። በቃ ያሳለፍነውን ሁኔታ ማውራት ጀመርን። በጣም በስቃይ እንዳሳለፈች፣ ትዝታዎች እየመጡ በጣም እንደተሰቃየች፣ በቃ ምንም ነገር ሳትደብቀኝ በግልፅ ሁሉንም ነገር አጫወተችኝ። እኔም የእኔን ጉዳትና ስቃዬን ምንም ሳይቀር አጫወትኳት። በፊት ያሳለፍናቸው ትዝታዎች

በጣም እንዳሰቃዩኝ ነገርኳት። ደግሞም ተጣልተን ሳለን በጥላቻ መሃል በጣም እንደምናፍቃት እውነቱን ሁሉ ነገርኳት። “በቃ ማርዬ የሆነው ሆኖ አልፏል። በቃ ከዚህ በኋላ ምንም ቢፈጠር፣ ምንም አይነት ነገር በመሀላችን ቢሆን፣ በምንም ምክንያት ልተውሽ አልፈልግም!” ብዬ ቃል ገባሁላት። ደግሞም እቅፍ አድርጌያት ሳም፣ ሳም አደረግኳት። በቃ እርሷም በጣም ደስ አላት። ቀኑም መሸ። ወደ አመሻሽ አካባቢ ላይ ወደ ሰፈር ተመለስን። በውስጥ ለውስጥ መንገድም እየተራመድን ወደ እነርሱ ሰፈር ደረስን፤ “ቻው!” ብላኝም ወደ ቤት ገባች። እኔም ወደ ሰፈር ተመለስኩ።

ለ[redacted]እንደተታረቅን፣ ሁሉንም ነገር ነገርኳት። [redacted]ም በጣም ተደሰተች። በቃ በጣም ደስ አላት። [redacted]ስልክ ላይ እኔ በኮምፒውተር የሰራሁት፣ የሁለታችንም ፎቶ በተንቀሳቃሽ ምስል መልክ ያለበት መዝሙር ነበር። ያንኑ ምሽት ሁሉንም ነገር ከ[redacted]ስልክ ወደ ስልኬ ላኩት። በንዴት ከስልኬ ያጠፋሁትን ነገር ሁሉ በ[redacted] ስልክ ላይ አገኘሁት። [redacted]የሁለታችንን ፍቅር በጣም ስለምትፈልግ መጀመሪያ ከስልኬ ላይ ደብቃ ሁሉንም ነገር ወደ ራሷ ስልክ ልካው ነበር። ያጠፋሁትን ነገር ሁሉ ማግኘት ባልችልም፣ የተወሰነውን አገኘሁት። ያንን ቀን፣ ደግሞ ከዚህ በኋላ በፍቅራችን መሀል ምንም አይነት ነገር ቢፈጠር ተቻችለን ለማሳለፍ ቃል ተገባባን። ፍቅራችንን አድሰን በጥሩ ሁኔታ ማሳለፍ ጀመርን እኔም ወደ ስራ ወደ ሆሳዕና ተመለስኩ። እርሷም ትምህርቷን በጥሩ ሁኔታ ቀጠለች። ጥላቻም ከመሀላችን ጠፋ። በፍቅር በጥሩ ሁኔታ ማሳለፍ ጀመርን። በቃ አንዳችን ለአንዳችን ማሰብ፣ ችግርም ቢሆን ለመሸከም፣ ትልቅ ቃል በመሀላችን አስቀመጥን። ደግሞም የእርሷ ትልቅ ውለታ በውስጤ አለ። በእኔ ላይ የሞተር ሳይክል አደጋ በደረሰብኝ ጊዜ ያደረገችልኝን ውለታ በህይወት ዘመኔ በጭራሽ አልረሳውም። ብጣላት እራሱ ይህ ነገር ሁሌም ትዝ ይለኛል።

## ክፍል ሃያ

ጊዜአችንን በፍቅር እና በጥሩ ሁኔታ ማሳለፍ ጀመርን። ከመሀላችን ጥላቻ የሚባል ነገር ጠፋ። ወደ ሀደሮ ከተማ በየሳምንቱ እሄዳለሁ፤ የእረፍት ቀናችንን ሁሌም አንድ ላይ እናሳልፋለን። በምንም ተአምር ቅዳሜና እሁድን ተለያይተን አናሳልፍም ነበር።

ወንድሜም በየሳምንቱ ወደ ሆሳዕና ለመዝናናት ብሎ መምጣት ጀመረ። እሁድ በጠዋት ወደ እኔ ይደውላል፤ እኔም ቀደም ብዬ ጠዋቱኑ ተነስቼ እጠብቀዋለው። ወደ እኔም በጠዋት ይደርስና ከእኔ ጋር ይውላል፤ እስከ ማታም ከእኔ አይለይም። ቁርስ በልተን ከጨረስን በኋላ ወደ ፑል (pool) ቤት እንሄዳለን። እዚያም ቆይተን ብዙ ሰዓት ከተጫወትን በኋላ ወደ ካፌ እንሄዳለን። እዛም የልብ የልባችንን እያወራን ሰዓቱ

ይመሻል። እርሱ ወደ ሀደሮ ይዞ የሚሄደውን አስቤዛዎችን ከባልትና ገዝተን፣ ለህፃንዋም የሚያስፈልግ ነገር ገዝተን ወደ ሀደሮ እሸኘዋለሁ።

ይህን ነገር በየሳምንቱ ማድረግ ጀመርን፤ በዚህ ምክንያት ከእርሷ ጋር ለመገናኘት በጣም ተቸገርኩ። ወንድሜን ደግሞ ወደ ሆሳዕና አትምጣ ማለት ለእኔ በጣም ሼም [ነውር] ነው። ወንድሜ ወደ ሆሳዕና ቅዳሜ እና እሁድ ሳይመጣ ሲቀር ብቻ ወደ ሀደሮ ሄጄ አገኛታለሁ። እርሷ ግን የእኔን ችግር በጭራሽ አትረዳኝም፣ በየቀኑ ወደ ሀደሮ ካልመጣህ ትለኛለች። "በጣም ናፍቀኸኛል፣ አሁን ካልመጣህ" ትለኛለች። እኔ ግን እንደምንም ለምኛት በሳምንት አንዴ እሄዳለሁ። በዚህ ሁኔታ በሚገርም ፍቅር ነበር የምናሳልፈው። እርሷም ትምህርቷን ቀጠለች። እኔም ወደ South Africa [ደቡብ አፍሪካ] እስከምሄድ በሞተር ሳይክል ስራ እየሰራሁኝ ቆየሁ።

በድንገት በእኛ ቤት ውስጥ ህጻንዋን በጣም አመማት። ማታ ወደ ዓራት ሰዓት ወንድሜ እና ህፃንዋን ይዘው ወደ ወላይታ ሶዶ ክርስቲያን ሆስፒታል (Christian Hospital) ወስደው ደውለው ነገሩኝ። እኔም በቃ ጠዋቱኑ እመጣለሁ፣ ምንም አትጨነቁ፣ ህፃንዋ ምንም አትሆንም አልኳቸው። እነርሱም ህፃንዋን ማታውኑ አሳክመዋት ጠዋት ወደ ሀደሮ ወደ ቤት ተመለሱ። እኔም ከሆሳዕና ልክ በሁለት ሰዓት ደረስኩ። ሀፃንዋን በጣም ስለምወዳት ማታውኑ ሳልተኛ በጣም እያሰብኩ አደርኩ። ወደ ሀደሮም ስደርስ ቤት ገብቼ ሳያት ህጻንዋ ወዲያው ጤነኛ ትሆናለች፤ ደግሞም ወዲያው ራሷን ትስታለች። ሁላችንም በጣም ተጨነቅን። እኔም ሁሉንም አናገርኳቸው እና ወደ ሆሳዕና እንውሰዳት ብያቸው ወደ ሆሳዕና ጉዞ ጀመርን። የህፃንዋ እናት በጣም እያለቀሰች በጣም ተቸገርን፣ ለማጽናናትም አልቻልንም ነበር። ልጅቷ ራሷን እያሳታት በዚህ ሁኔታ ወደ ሆሳዕና ደረስን።

ወደ ህፃናት ህክምና ክሊኒክ ወደ ማርያም ሰፈር ወሰድናት፤ በዚያም ምንም ነገር መርዳት አልቻሉም። ወደ ሆሳዕና ሆስፒታልም ወሰድናት። በዚያም አልጋ ይዘን አስተኛናት። ከትንሽ ቀናቶች በኋላ ህጻኗ በጣም ተሻላት። ወደ ሁለት ሳምንት ደረስን። በዚህ አስራ አምስት ቀን ውስጥ በጣም ለውጥ ተገኘ። ሆስፒታል ውስጥ በጣም አዋቂ ባለሙያዎች ነበሩ፤ የህጻኗ ትክክለኛው በሽታም አግኝተውላት ነበር። በህፃንዋ ላይ ነጭ ደም ሴል [ህዋስ] በጣም በዝቷል፤ ከመጠን በላይ ወደ አስራ ዘጠኝ ሺህ ሆኗል፤ ስለዚህ ወደ ስድስት ሺህ መውረድ አለበት አሉ። በዚህ በሁለት ሳምንት ውስጥ ግን በጣም ለውጥ ተገኘ። በዚህ ጉዳይ በጣም ተወጥሬ ነበር። ስራም መስራት አቁሜ ነበር። ለ ደውዬ ነገርኳት፣ ልንገናኝም አልተመቸንም ነበር። ከሁለት ሳምንት በኋላ ከሆስፒታል ወደ ቤት ወሰድናት፤ በዚህ አጋጣሚም በተለመደው በካምፓችን ተገናኘን። ወደ ሶስት ቀን እዛው ሀደሮ ከቆየሁ በኋላ ወደ ሆሳዕና ተመለስኩ፣ ስራም ጀመርኩ።

ከእለታት አንድ ቀን ወደ እኔ ማታ ላይ፣ ወደ ሁለት ሰዓት አካባቢ ትደውላለች። በሰአቱ ከጓደኞቼ ጋር ነበርኩ። ሳላውቅ ስልኬን አንስቼ ከጓደኞቼ ጋር ማውራቴን ቀጠልኩ። እረጅም ደቂቃ ከቆጠረ በኋላ ስልኩን ዘጋች። በቃ በዚህ ጉዳይ በጣም ተናደደች። ይህ ከመሆኑ በፊት ደግሞ በሞተር ላይ ሆኜ "በኋላ ልደውልልሽ? አሁን አልተመቸኝም" ብያት ስልኩን ዘግቼባት ነበር። ይህን ሁሉ ቆጠረችና "በቃ ሁለተኛ ወደ እኔ እንዳትደውል፤ ከዛሬ በኋላ አልፈልግህም! አትፈልገኝ!" አለችኝ። እኔም "ማርዬ በጣም ይቅርታ! ብያት ስለምናት እኔን ንቀኸኛል አልፈለከኝም" ብላ ስልኬን ከዚያ ቀን ጀምሮ ማንሳት እምቢ አለችኝ። በጣም ግራ ገባኝ። ለምንድነው በትንሽ ነገር የምትጣላኝ ብዬ በጣም ጭንቀት ውስጥ ገባሁ። ስልኳን ስደውል በጭራሽ አታነሳም። በሰው ስልክ ስደውል ስልኩን ታነሳና ድምጼን ሰምታ ስልኩን በጆሮዬ ላይ ትዘጋዋለች። በቃ በእርሷ ላይም ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ።

በዚህ ሁኔታ ላይ ሳለሁ ከሀደሮ ወንድሜ ወደ እኔ ደውሎ "ወደ ሆሳዕና እየመጣን ነው፤ በድጋሚ በጣም ታማለች" ብሎ ለእኔ ነገረኝ። "ወደ አዲስ አበባ ስለምሄድ፣ ልብስ ቀይረህ በመናኸሪያው ውስጥ ጠብቀኝ" አለኝ። ህፃንዋን ይዘው እና ወደ ሆሳዕና ደረሱ። በሰዓቱ ከእነርሱ ጋር አንድ ላይ እንዳልሄድ ልብሴን አልቀየርኩም ነበር። እነርሱን በአዲስ አበባ መኪና፣ በትልቁ ኤፍኤስአር ቅጥቅጥ መኪና ውስጥ አስገብቼ፣ በሞተር ወደ ቤት ሄጄ ልብሴን ቀይሬ፣ እነርሱ ከወጡ ከ ሰላሳ ደቂቃ በኋላ በሌላ መኪና፣ ወደ አዲስ አበባ በሀይሩፍ መኪና ተሳፈርኩኝ። ምሳ ለመብላት ስላልተመቸኝ የመቶ ብር ጭማቂ ገዝቼ ጉዞ ጀመርኩ። የምጓዝበት መኪና ሀይሩፍ ስለሆነ የእነርሱን መኪና ቀደምኩት። ህጻኗን ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ልንወስዳት ወሰንን። በዚህ መሀል ደግሞ በአዲስ አበባ የሚያገለግል በጣም ጥሩ አገልጋይ ፓስተር ከታላቃችን ጋር ስለሚተዋወቅ በድንገት ወደ ቤት መጥቶ ህጻኗን አይቷት በጣም አዘነላትና ይጸልይላት ጀመር። ውሃም በብርጭቆ አድርጎ ከጸለየ በኋላ ለህጻኗ አጠጣት።

ህጻኗ ከታላቃችን ልጆች ጋር መጫወት ጀመረች። በጣም ተገረምን። ሙሉ በሙሉ ዳነች። በዚህ መሀል ደግሞ ለእኛም ፀሎት አደረገልን። ለእኔም ብዙ መልእክት ነገረኝ። እኔ በቤታችን ላይ ከሁሉም እንደምበልጥ፣ ደግሞ ፈጣሪ በልዩ በረከት እንደሚባርከኝ ተናገረኝ። ጭራሽ በቃ ፎቅ እንደምሰራ፤ ከዘራችን ውስጥ በጣም በሀብት እንደምባረክ ተናገረኝ። እንደዚህ አይነት ነገር በጣም እንቃለሁ፣ በውስጤ ያሰብኩትን ሳይቀር በጣም ብዙ ያደረግኩትን መጥፎ ነገር ሁሉ ተናገረኝ፣ በፈጣሪ ፊትም ንስሃ አስገባኝ። የአንተ ነገር አታስብ ይስተካከላል ብሎ በጣም መልእክት ተነገረኝ።

ለህጻኗ ልብስ ገዛንላት፣ ለእኛም ልብስ ገዝተን በአዲስ አበባ ትንሽ ቀናቶችን ካሳለፍን በኋላ ወደ ሆሳዕና ተመለስን። እኔም ወደ ስራዬ ተመለስኩ። ከአዲስ አበባ ከተመለስኩ በኋላም ላገኛት ስፈልግ፣ ናፍቆቷን መቋቋም ስላልቻልኩ፣ ስልኳን በየቀኑ እቀጠቅጣለሁ፣ ግን በጭራሽ አታነሳም። ለጓደኞቿ ስደውልም ሁለተኛ አታገኛትም ብለው በእኔ ላይ አፌዙብኝ። በቃ ተስፋ ቆርጬ ነገሩን ተውኩት። ያ ሁሉ ቃል መግባት፣ ያ ሁሉ ደስታ፣ ያ ሁሉ በፍቅር ያሳለፍነው ውብ ቀናቶች በትንሽ ነገር ፈረሰ።

በቃ ቀን ጨለመብኝ፤ የምሆነውን አጣሁ። ጓደኞቼን ሳዋራቸው አትተዋት ይሉኛል፤ የምሆነውን አጣሁ። ቀን ማታ ጭንቀት ብቻ ሆንኩኝ። ግራ ተጋባሁኝ። ለእራሴ ሰርቼ መኖር ተሳነኝ፣ ብቻዬን ማውራት ሆነብኝ። ጓደኞቼ አስጠሉኝ፣ ከሰው ጋር ማውራት ሁሉ አስጠላኝ፣ በቃ ብቸኝነት ነው የሚሰማኝ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ስራ እንደድሮ መስራት በጣም ደበረኝ። በቃ አስጠላኝ። እንደምንም ጓደኞቼ እኔን እራስህን አትጣል ብለው በጣም መከሩኝ። መጀመሪያ ቀኑን ሙሉ ከቤት መውጣት እራሱ ተውኩኝ፣ በኋላ ጓደኞቼ ብዙ ነገር ከመከሩኝ በኋላ በጠዋት ተነስቼ ወደ ስራ መሄድ ጀመርኩ። እንደድሮ በስራዬ ላይ ተመለስኩ፣ ጭንቀቴ ቀለለልኝ፤ ዝም ብዬ ከጓደኞቼ ጋር መሆን ጀመርኩ። ጓደኞቼም በጣም እኔን ማፅናናት ጀመሩ፣ በተለይ የምለው ጓደኛዬ ስለ ልጅቷና ስለ እኔ በጣም ስለሚያውቅ በጣም አፅናናኝ። ወደ መዝናኛ ይወስደኛል፣ ያዝናናኛል። ስራም አብረን ስለምንሰራ እኔን በጣም እረዳኝ።

## ክፍል ሀያ አንድ

በሁለት ሺህ አስር፣ ሰኔ ሰባት፣ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት አካባቢ በሞተር ላይ ሳለሁ ከደቡብ አፍሪካ ተደወለልኝ:: ቀኑም ሀሙስ ቀን ነበር፣ ልጁ ደውሎልኝ "ዮኒ ሰላም ነክ? እንዴት አለህ?" አለኝ። እኔም ደህንነቴን ነገርኩት። መጀመሪያ ከአስር ዓመት በፊት ወደ ደቡብ አፍሪካ የሄደው ወንድሜ ነው። እንዲህም አለኝ፤ "ሁለት አማራጭ ሰጥቼሃለሁ፣ በደንብ አዳምጠኝ" አለ። እኔ "እሺ" ብዬ ነገሩን ማዳመጥ ጀመርኩ። ቀጥሎም "ዮኒ አሁን ወደ ሀዋሳ ተሳፍረህ ከዚያም ወደ ደቡብ አፍሪካ ጉዞ ትቀጥላለህ? ወይስ እስከ ጥቅምት መንገዱን አመቻችቼ በበረራ እንድትሄድ ላድርግ?" ከሁለቱ እንዱን ምረጥ አለኝ።

ጥያቄውም በጣም አልከበደኝም። "አሁን ጉዞ ጀምር ወይም እስከ ጥቅምት ጠብቅ" አለኝ። መጀመሪያ ወደ ደቡብ አፍሪካ እንዲወስደኝ በጣም ስላስቸገርኩት ብዙም ሃፍረት ሳይሰማኝ በእግር ጉዞ ላይ ወሰንኩ:: ውሳኔዬንም ነገርኩት። "በቃ ወደ ሀዋሳ አሁኑኑ ሂድ፣ ለመሄድ የተዘጋጁ ልጆች ስላሉ በእነርሱ ላይ ሄደህ ተጨመር" አለኝ። ለእኔም ጊዜ በጣም አጠረኝ። ቻው ለማለት ወደ አባቴ ቤት በሞተር ሄድኩ። አባቴንና ቤት ውስጥ ያሉትን ሁሉ ቻው ብያቸው ወዲያው ከቤት ወጣሁ። አባቴ ግን ደስተኛ አልሆነም ነበር፤ በጣም አዘነ።

ከዚያም ወደ አክስቴ ልጅ፣ ወደ ማርያም ሰፈር በሞተር ሄድኩኝ። የአክስቴ ልጅም በጣም በጣም አለቀሰች "ዮኒ በጭራሽ አትሂድ" ብላ በጣም ለመነችኝ። እኔ ግን " ምንም ማድረግ አልችልም፤ ነው የጠራኝ" ብዬ በግድ ቻው ብያት ወጣሁ። ቻው ለማለት በጣም ሼም [የሚያሳፍር] የሚሆንብኝ፣ አንድ በጣም የምወደው ጓደኛዬ ነበር። እርሱን ወደ ሆቴል ጠራሁት። ወደ እኔም መጣ። ተገናኝተን አብረን "እኔ ወደ ደቡብ አፍሪካ ልሄድ ነው፣ ቻው ልልህ ነው የጠራሁክ" አልኩት። እርሱም በጣም አዘነ። ፊቱም በጣም ተቀያየረ። ለእኔም እንዲህ አለኝ "ዮኒ በውስጥ መንገድ ከሆነ አንተ በጭራሽ አትችልም፤ በጣም ከባድ ነው። ደግሞም እኔ በመንገድ ላይ ሳልሞት ነው ተርፌ የመጣሁት። መንገዱ ቀላል አይደለም ተው ይቅርብህ፤ በበረራ ከሆነ ሂድ።" ብሎ በጣም ተቆጣኝ፣ እኔ ግን አልሰማም አልኩት። ወደ አንድ ሺህ የሚጠጋ ብር ለመንገድ፣ ለትራንስፖርት ይሆናል ብሎ ሰጠኝ። ቻው ብዬው ተለያየን።

ለእኔም የተነገረኝ በድንገት ስለሆነ፣ በሆሳዕና የምትኖር በጣም የምንዋደድ የምትባል የአክስቴን ልጅ በሞተር እስከምትሰራበት ሱቅ ድረስ ሄጄ " ወደ ደቡብ አፍሪካ በድንገት ወንድሜ ጠርቶኛል፤ ቻው በይኝ" አልኳት። በጣም ደነገጠች፤ ምክንያቱም በጣም ትወደኛለች፤ ደግሞም ሁሌም እንገናኛለን። አንዳንዴ ወደ ከተማ ለሻይ ቡና የስራ ልብስ ቀይረን በጣም ፈታ ብለን እንወጣለን። በእሩቅ ብቻ የሚያውቁኝ ሰዎች እንኳን "የዮኒ ፍቅረኛ ነች" እና "በጣም እኮ ነው የምትወድህ፣ ኸረ በጭራሽ አትተዋት" ይሉኛል። ሰው በእኛ ላይ በጣም ይቀናል፣ ደግሞም የትም ብትሄድ እኔን ሳትጠራኝ ከቤት እራሱ አትወጣም። በቃ ይህን ሁሉ አሰበች "አሁን እኔን ማነው የሚያዝናናኝ? ከማን ጋር ነው የምደበረው?" ብላ "በቃ ሂድ! ቻውም አትበለኝ!" ብላ በጣም አኮረፈች። እምቢ ስላለችኝ ቻው ሳልላት ከእርሷ ተለየሁ። ካገኘሁት ሰው ሁሉ፣ በእኔ መሄድ ላይ የሚስማማ አንድም ሰው አጣሁ። ልቤን እንዲሁ ስላነሳሳው ጉዞዬን ቀጠልኩ። በሆሳዕና ያሉ ጓደኞቼንም ብቻ ቻው ብያቸው፣ ከሆሳዕና ወደ ሀደሮ በሞተር ሳይክል ቤንዚል ሞልቼ ጉዞ ጀመርኩ።

ወደ ማሬ ከተማ ደርሼ ወደ አክስቶቼ ቤት ገባሁ፣ ለአክስቴም ነገርኳት። እርሷም ግን ፈቃደኛ አልሆነችም ነበር። ወደ ሌላኛዋ አክስቴ ቤት ሄጄ ቻው ብያቸው ወደ ደቡብ አፍሪካ እንደምሄድ ነገርኳቸው። እነርሱም አልተስማሙም። በቃ በእኔ መሄድ ላይ የተደሰተ አንድም ሰው አጣሁ። ከማሬም ወደ ሀደሮ ከተማ ጉዞዬን ጀመርኩ። ወደ ሀደሮ በአስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ደረስኩ። ቤቱን ጎዝጉዛ ፈታ አድርጋ ጠበቀችኝ። ወደ ቤት እንደገባሁ በጣም ደነገጠች፤ በመሄዴ አልተደሰተችም ነበር። ምክንያቱም በጣም ስለምትወደኝ፣ ደግሞም በጣም ሰለማዝናናቸው በጣም አዘነች። ቤት ከደርስኩ በኋላ ወንድሜ ከስራ ቦታ እንዳልመጣ ነገረችኝ። እኔም "ወንድሜን

ከባንክ ቤት እስኪመጣ እመለሳለሁ” ብያት ከቤት ወጣሁ። ሞተር ሳይክል ይዤ ከጓደኞዬ ከ ጋር ወደ ፍቅረኛዬ ወደ ቤት ድረስ ከልጁ ጋር ሄድን፤ ቤታቸውም ደረስን።

በድፍረት የግቢውን በር ማንኳኳት ጀመርኩ። ከቤታቸው ፊት ለፊት ሱቅ አላቸው፤ ከሱቅ የሆነች ልጅ ወጥታ በሩን ከፍታ እኔን ማናገር ጀመረች። ልጅቷም “ ቤት ውስጥ የለችም። ወደ ቤተክርስቲያን ሄዳለች” ብላ ነገረችኝ። ወደ ቤተክርስቲያን ሄጄ ልጆቹን ጠየቅኳቸው፤ ልጆቹም እንደሌለች ነገሩኝ። ልጆቹንም ስላለመንኳቸው ወደ ውስጥ በጣም በፍጥነት ገባሁ። ስፈልጋት አልተገኘችም። በቃ አጣኋት። ተመልሼ ወደ ቤታቸው ደጃፍ ያለው ወደ ሱቃቸው ገብቼ እረጅም ሰዓት ጠበቅኳት፣ ግን ወደ ቤት አልተመለሰችም። ወንድሜ በየደቂቃው እየደወለልኝ በጣም ጨቀጨቀኝ። ተሰፋ ቆርጬ ለባለ-ሱቋ መልእክት ፅፌላት እንድትሰጣት አስቀምጬ ወደ ቤት ተመለስኩ።

ወደ ቤት ስመለስ በጣም ተናደዋል። ቡና ጠብቀው ጠብቀው ስለቆየሁ በጣም ተቆጡኝ። እኔም “ጓደኞቼን ቻው ልላቸው ሄጄ ነው” ብዬ ወንድሜን ይቅርታ ጠየቅኩት። ከዚያም ቡና ጠጥተን፣ እራትም በልተን፣ ለጉዞ የሚሆኑ እቃዎችን ማዘጋጀት ጀመርን። ለመንገዴ የሚሆን ልብስ፣ ጫማ፣ ሁሉንም ነገር ጨርሰን እንቅልፋችንን ተኛን። እኔ ግን እንቅልፍ የሚባል ነገር ከየት ይምጣልኝ? ሳላገኛት መሄዴ በጣም አስጨነቀኝ ያለ እንቅልፍ አደርኩኝ።

## ክፍል ሃያ ሁለት

ሰኔ ስምንት፣ ሁለት ሺህ አስር፣ ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ሁሉንም ነገር እረስቼ ጉዞዬን ለመጀመር ወሰንኩ። ከሀደሮ ጉዞ ወደ ሀዋሳ ከጠዋቱ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ በሀዋሳ መኪና ተሳፈርኩ። የትራንስፖርት መኪና እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመረ፣ እና እጃቸውን በማንሳት ተሰናበቱኝ። ወደ ሀላባ ከተማ፣ ሶስት ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ ለቁርስ መኪናው ቆመ። በሀዋሳም በጣም አስከፊ እረብሻ እንዳለ ሰማን:: ከሀላባም ጉዞ ጀመርን። ወደ ሀዋሳ ስንደርስ ከተማውን የኢትዮጵያ ሀገር መከላከያ ሰራዊት ምንም አይነት ግርግር እንዳይኖር ተቆጣጥሮታል።

ወደ ስድስት ሰዓት ተኩል ላይ ሀዋሳ መናኸሪያ ደረስን። የከተማው ሁኔታ ጥሩ ስላልነበር እኔ ወደ አንድ ሆቴል ሔጄ፣ አልጋ ይዤ ነገሩ እስከሚረጋጋ እዚያው አልጋ ቤት ተቀመጥኩኝ:: ወደ ውጭ ለመውጣት እራሱ በጣም ከባድ ሆነብኝ። ከተማው ውስጥ አስለቃሽ ጭስ ተለቆ ምንም ወደ መንገድ መውጣት አልተቻለም ነበር። ሁሉንም ነገር፣ ምግብም ከሆቴል መጠቀም ብቻ ሆነብኝ። ወደ አክስቴ ስደውል እርሷም “ወጥቼ ልውሰድህ” ስትለኝ እኔ እምቢ አልኩ። ምክንያቱም የአክስቴ ቤት ከመናኸሪያው በጣም እሩቅ ነው።

ወደ አክስቴ ጋር ደውዬላት ምንም የትራንስፖርት ታክሲ አለመስራቱን ነገርኳት እና እዚያው ሆቴል ውስጥ ነገሩ እስኪረጋጋ ተቀመጥኩኝ። እርሷም ደጋግማ በመደወል “በዚህ በሁከት ላይ ለምን መጣህ?” ብላ ጠየቀችኝ። እኔም ሁሉንም ነገር ነገርኳት። ወንድሞቼ ወደ ደቡብ አፍሪካ እንደጠሩኝ፣ ደግሞም ቻው ብያት ልሄድ እንደፈለግኩ ነገርኳት። እርሷ ግን ፈቃደኛ አልሆነችም ነበር። እኔም “አክስቴ በቃ ምንም ማድረግ አልችልም፤ ቻው ደና ሁኚ! መጥቼ በአካል ቻው ብልሽ በጣም ደስ ይለኝ ነበር። በቃ ምንም ማድረግ አልችልም፤ ደና ሁኝ!” ብያት በስልክ ብቻ ተሰናበትኳት። እርሷም መልሳ “በቃ አንተም እንደወንድሞችህ መራቅ ፈለግክ? ተው ልጄ አትሂድ!” ብላ ለመምከር ሞከረች። እኔም ነገሩን እንደወሰንኩ ነገርኳት። እርሷም ተስፋ ቆርጣ “ቻው” አለችኝ። ጋደም ብዬ በስልኬ መዝሙር እየሰማሁ ሳለሁ፣ ደላላው ደውሎልኝ “ነገ በጠዋቱ ወደ ዲላ መሳፈር አለብህ” አለኝ። እኔም በሀዋሳ ሁከት እንዳለ ለማስረዳት ስሞክር “እንደምንም በነዚህ በሁለት ቀኖች ወደ ሞያሌ መድረስ ይኖርብሃል። ካልሆነ የተዘጋጁ ልጆች ጉዞ ላስጀምር ነው” ብሎ በጣም ጨቀጨቀኝ። ከዚያም ወደ ሆቴል ገብቼ ምግብ በልቼ ተመልሼ ገብቼ በጣም ስለደከመኝ እንቅልፌን ተኛሁ።

በየደቂቃው ስልኬ ላይ እየደወሉ ጓደኞቼ እንቅልፍ ከለከሉኝ። በዚህ መሀል በማላውቀው ስልክ፥ ማለቴም ሴቭድ ባልሆነ [ባልመዘገብኩት] ቁጥር ተደወለልኝ። ስልኩንም አንስቼ ማውራት ጀመርኩ። “ ነኝ” ብላ ነገረችኝ። በጣም ደነገጥኩ። “እንዴት አሰብሽኝ? እንዴት ደወልሽልኝ?” ስላት “ልጅቷ ነግራኛች፤ ለምን ሳታገኘኝ ሄድክ? ይህን ያህል ትጨክናለህ ብዬ አላሰብኩም ነበር፤ ለምን እንዲህ አደረግክ?” ብላ በጣም ማልቀስ ጀመረች። እኔም “ሳላገኝሽ አልሄድም ብዬ ወዳንቺ መጥቼ ነበር፤ ምንም ብንጣላ፣ ምንም ብንኮራረፍ፣ ሳላይሽ፣ ቻው ሳልልሽ አልሄድም ብዬ ወደ አንቺ መጥቼ ነበር፣ ግን አልሆነልኝም። ቤተክርስቲያን ሄደሻል ስላሉ ወደዚያም ሄጄ ላገኝሽ በጣም ሞክሬ ነበር፤ ግን አልተሳካም። ቤተክርስቲያን ስለሆነ ምንም ማድረግ አልቻልኩም። በቃ ሁሉን እርሺው ማማዬ። ባለማግኘት ውስጥ ሆኜ አፈቅርሻለሁ። ቻው ማርዬ! አግኝቼሽ ቻው ብልሽ በጣም ደስ ይለኝ ነበር” አልኳት። እርሷም መልሳ “ድሮም የእኔን መጎዳት ነው የምትፈልገው፤ በቃ እኔን መጉዳት ነው ያንተ ምኞት” ብላ በጣም አለቀሰች። በጣም ስታለቅስ አንጀቴ አልቻም ነበር። ላባብላትም ሞከርኩ፣ እርሷ ግን “በቃ ከእንግዲህ መኖር አልፈልግም!” ብላ በጣም አለቀሰች። “በቃ ባልኖር ይሻለኛል” አለችኝ።

እኔም እምባዬን መቆጣጠር አቅቶኝ እምባዬን አረገፍኩ። ከዛም እረጅም ሰዓት ተነጋገርን። ያለፈውንም ነገር አንስተን ተነጋግረን ይቅርታ ተደራረግን። ያለፈው አልፏል በማለት ሁሉንም ነገር እረስተን እንደድሮ አንድ ልብ ሆነን ለመቀጠል ወሰንን። ከታረቅን በኋላ እኔ አንድ ጥያቄ ጠየቅኳት፤ ጥያቄውም እንዲህ ይላል “ማርዬ ግን እንደድሮ

ታፈቅሪኛለሽ?” ስላት እርሷም “ማርዬ ከድሮ በላይ፣ ከዚያም በላይ ነው የማፈቅርህ፤ ሁሌም አፈቅርሃለሁ!” አለችኝ። ለእኔም በጣም ደስ አለኝ። በቃ እንደገና የተወለድኩ ያህል በጣም የደስታ ስሜት ተሰማኝ። እርሷም “ወደ ሀዋሳ ነገ ጠዋት እመጣለሁ” ብላ ተናገረች። “በጣም ቢዚ ስለሆንኩኝ፣ ደግሞም በሞያሌ ልጆች እየጠበቁኝ ስለሆነ እንዳትመጪ! ብቻ በቻልሽው ያህል ወደ ፈጣሪ ጸልዬ” አልኳት። እርሷም “እጸልያለሁ” ብላ ተናገረችኝ። በቃ እኔም በጣም ደስ አለኝ፤ ኢትዮጵያ ጥያት እስከምውጣ በየደቂቃው በስልክ ስናወራ ነበር።

በማግስቱ ወደ ዲላ የሆነ ዶልፊን መኪና አግኝቼ ተሳፈርኩኝ። ከዲላም ወዴት እንደምሳፈር ደላላውን ጠየቅኩት። እርሱም የት የት እንደምሳፈር ሁሉንም ነገረኝ። በዚህ በድል ጉዞ ላይ ሳለሁ የወንድሜ ሚስት ደውላ እንዲህ አለችኝ “ዮኒ ሕጻንዋ ጠዋቱኑ ተነስታ ዮኒ የት አለ ብላ በጣም አስቸገረችኝ” ብላ በጣም አለቀሰች። ከዚያ ስልኩን ለህጻኗ ሰጠቻት፣ ብዙ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ ስሜን ተጣራች “ናናዬ... ናና...” ትላለች። በጣም እንዳስብ አደረገችኝ፤ በጣም አለቀስኩ። ስልኩንም ማውራት ስላልቻልኩ አቋረጥኩት።

ወደ ዲላ ስንደርስ ቁርስ መብላት በጣም አስጠላኝና ዝም ብዬ ወደ ሀገረ ማርያም ተሳፈርኩኝ። ማርዬ ግን በየሰዓቱ እየደወለች ያለሁበትን ሁኔታ ትጠይቀኝ ነበር። ሀገረ ማርያም እንደገባሁ ወደ ያቤሎ ተሳፈርኩኝ። ያቤሎ ወደ ስምንት ሰዓት ተኩል ደረስኩ። ልክ ያቤሎ ደርሼ ከመኪና እንደወረድኩ ወደ እኔ ደወለችልኝ። “ምሳ በላህ?” ብላ ጠየቀችን እኔም እንዳልበላሁ ነገርኳት። በጣም ተቆጣችኝና “ማርዬ እንዳልበላህ አውቄ ስትበላ አንድ ላይ እንበላለን ብዬ አልበላሁም” አለችኝ። እኔም ከሀገረ ማርያም ወደ ያቤሎ ጉዞ ላይ ከሆነ ልጅ ጋር ተዋውቀን ነበር። ከልጁም ጋር ወደ አንድ ሆቴል ሄደን ምግብ አዘን ያዘዝነው ምግብ እስኪመጣ ብዬ ወደ እርሷ ደወልኩኝ። እርሷም ስልኩን አንስታ “እስከአሁን አልበላክም አይደል? በጣም እየራበኝ ነው፤ ግን በቃ አልበላም” አለችኝ።

እኔም “እየበላሁ ነኝ” ብያት ልሸውዳትም ስሞክር እምቢ አለችኝ። በኋላ ምግብ ከመጣ በኋላ ደወልኩላት። እርሷም “እስቲ ጉረስ” ስትለኝ ጎርሼ በመዋጥ አስረዳኋት። ከዚያም “እሺ በቃ አሁን አምናለሁ፣ በቃ ከበላህ በኋላ ደውልልኝ፣ እኔም ምሳዬን ልብላ በጣም እየራበኝ ነው” አለች። ይህን ሁሉ ሳወራት ልጁ በጥሞና ነበር የሚሰማኝ፤ ልጁም በፍቅራችን በጣም ተገርሞ “በጣም ታስቀናላችሁ” ብሎ ተናገረኝ። የተጠቀምነውን ሁሉ ክፍያ ያልጅ ሸፈነ። ከልጁ ጋር በጣም ጓደኛሞች ሆንን። ወደ ሞያሌ ለመሔድ መኪና ለመያዝ ወደ መናኸሪያ ገባን። ወደ ደወልኩላት፤ እርሷም ስለመንገዱ ጠየቀችኝ።

መንገዱ በጣም የሚያስፈራ መሆኑን ነገርኳት። ምክንያቱም ከሀዋሳ አንስቶ እስከ ያቤሎ ድረስ መንገድ ዳር ያሉ ቤቶች ላይ ያልደረሰ አደጋ የለም፤ ያልተቀጣጠለ እና ያልፈረሰ አንድም ቤት የለም፤ በቃ ለነፍሴ እየፈራሁ ነበር ያለፍኩት። ይህን ሁሉ ስነግራት በጣም ፈራች። በኋላ ላይ “ከዚህ ከያቤሎ ወደ ሞያሌ ባለው ጉዞ ላይ ምንም ችግር ቢገጥመኝ ከእኔ ጋር ያለው የተዋወቅኩት ልጅ፣ የሞያሌ ልጅ ስለሆነ ቋንቋውን ስለሚችል ችግር የለም” ብዬ ነገርኳት።

## ክፍል ሃያ ሶስት

ከያቤሎ ወደ ሞያሌ ጉዞአችን ላይ ገና ወደ ሞያሌ ሳንደርስ በመንገድ ላይ በጣም መሸብን። ቤተሰቦቼም ጋር ስደውል፣ ስልክ በየደቂቃው ሳወራ ነበር። ፍቅረኛዬም ደውላ ስትጠይቀኝ ገና እንዳልደረስኩ ነገርኳት:: በቃ ያልተረበሸ ሰው የለም። ምክንያቱም በሰዓቱ በሱማሌና በኦሮሞ መካከል ጥል ነበር። በየመገናኛ ብዙሃን የሚወራው ስለዚህ ጦርነት ብቻ ነበር። ገና ከሀገሬ ሳልወጣ ህይወቴን ላጣት ነው ብዬ እጅግ መፍራት ጀመርኩ።

በየደቂቃው ስልኬን ሳወራ ተሳፋሪ ሁሉም እኔን ይመለከተኛል፤ በቃ ልቤ በጣም ፈራ። ወንድሜም በየደቂቃው ደውሎ ሲያስቸግረኝ በቃ “ፈጣሪ ያለው ይሆናል” ብዬ ቁርጡን ነገርኩት። እርሱም ተስፋ በመቁረጥ “ቻው ወንድሜ ፈጣሪ ይጠብቅህ!” ብሎ ስልኩን ዘጋ። በዚህ ሁኔታ ውስጥም ጉዞዬን ቀጠልኩ፤ ተሳፋሪ ሰው በሙሉ ግን እኔን መመልከት አላቆመም። በአጠገቤ ተቀምጦ የነበረው እረዘም ያለ ወጣት ልጅም ትኩር ብሎ ይመለከተኛል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳለሁ እህቴ ከጎፋ ዞን ሳውላ ደወለችልኝ። እርሷም በመማረር ሃዘን ውስጥ ሆና መናገር ጀመረች፤ ሐሳቤንም ለማስቀየር በጣም ለመነችኝ:: ግማሽ ልቤ የእርሷን ሀሳብ ተቀበለ፣ ግማሽ ልቤ ደግሞ አንዴውኑ ወጥተሀል ይለኛል።

እህቴም ይህን ሁሉ ስታወራኝ የነበረው በሀድይኛ ቋንቋ ነበር። ከእህቴም ጋር ተነጋግሬ እንደጨረስኩ አጠገቤ የተቀመጠው ልጅ በጣም ፈገግ በማለት “የሆሳዕና ልጅ ነክ? እኔም የሆሳዕና ልጅ ነኝ” ብሎ “ እባላለሁ” አለኝ። እኔም “ዮኒ” እባላለሁ ብዬ ተዋወቅኩት። ስለ እርሱ ታሪክ ነገረኝ፤ በሞያው በ ውስጥ ሆኖ እንደሚሰራ ነገረኝ። እኔም በጣም ደስ አለኝ። መጀመሪያ በጣም ፈርቼ ነበር፣ ስጋቴ ትንሽ ቀነሰ። ከልጁም ጋር በደንብ ተዋወቅን የየራሳችንን እያወራን ጉዞአችንን ቀጠልን:: እርሱም የት እንምሄድ ጠየቀኝ ወደ ደበቡ አፍሪካ እንደምሄድ ነገርኩት በጣም አዘነና ብዙ ነገርም መጫዎት ጀመረ።

"ወንድሜ የኛ የሀድያ እና የከምባታ ብዙ ልጆች በዚህ በደቡብ አፍሪካ መንገድ ላይ ህይወታቸውን አጥተዋል፤ በኬንያ ጫካ ብዙዎች በአንበሳ እና በአውሬ ተበልተዋል፤ ግን አንተን ጌታ ይርዳህ" ብሎ በጣም ሀዘን ውስጥ ሆኖ ተናገረኝ። እኔም "አሁን እዚህ ደርሻለሁ፤ አይሆንም! ቆርጫለሁ" ብዬ ነገርኩት። እየተጫወትንም ወደ ሞያሌ ከተማ ገባን። ወደ ሞያሌ ስንደርስ ሰዓት በጣም ሄዶ ነበር። በዚያ ላይ ደግሞ በጣም ከባድ እረብሻ ስለነበረ ሆቴሎች ሁሉም ተዘግተው ነበር። ም "ዮኒ አሁን አልጋ ቤት አታገኝም፤ በሶማሌ እና በኦሮሞ መካከል ትልቅ ጦርነት ሰሞኑን ስለነበረ ሆቴሎች በጊዜ ነው የሚዘጉት" አለኝ። ከዚያም ምን እንደሚሻለኝ እራሱን ጠየቅኩት። በቃ መላ ጠፋብኝ። እርሱም "ከእኔ ጋር አድረህ ጠዋት ትሄዳለህ" ብሎ ወደ ሀገር መከላከያ ካምፕ፣ ወደ  እንደሚወስደኝ ነገረኝ።

ወደ  ግቢም ደርሰን እዚያ ውስጥ ሰራተኛ እንደሆንኩ አድርጎ አስገባኝ፤ ከእርሱም ጋር አብረን አደርን።  በቃ በጣም ይንከባከበኝ ጀመረ፤ ከዚያም ጠዋቱኑ ተነስተን አብረን ደላላውን ለማግኘት ወጣን። በግጭቱ ምክንያት ለካ ኔትወርክ ጠፍቷል፤ በቃ ኔትወርክ እስኪመጣ ብለን የሆነ ሆቴል ላይ ተቀመጥን። ኔትወርክም ሳይመለስ ምሳ ሰዓት ደረሰ። በቃ እንግዲህ ካልሆነ እዛው ሆቴል ላይ አልጋ መያዝ አለብኝ ብዬ  አማከርኩት። እርሱም እሺ ብሎኝ እዚያው ሆቴል ውስጥ የአልጋ ቤት ከፍሎ አምስት ቁጥር ያዘልኝ። እዚያው ሆቴል ተቀመጥኩኝ፤  ወደ  ደርሼ እመጣለሁ ብሎ ወደ ግቢ ተመለሰ። ኔትዎርክም መጣ። ኔትዎርክ እንደመጣ ወዲያው ደላላው ደወለልኝ። እኔም ወደ  ደውዬ "ቶሎ ና ደላላው ደውሎልኛል" ብዬ ነገርኩት። ም ወደ እኔ መጣ። ከዚያም ሻይ ቡና እያልን ደላላውን ጠበቅን። ያለንበትንም ሆቴል ነገርኩት። "ከማን ጋር ነክ?" ብሎም ጠየቀኝ። እኔም የሚደሰት መስሎኝ " ከሚባል ልጅ ጋር ነኝ። ጥሩ ልጅ ነው፤ እዚያው ነው የሚሰራው፤  ውስጥ ነው የሚሰራው" ብዬ ስነግረው "እርሱን ሸኘው፣ ካልሆነ አንገናኝም" ብሎ ተናገረኝ።

ለ ይህን ሚስጥር ነገርኩት፣ እርሱም እሺ ብሎ ስልኬን ተቀብሎ "ትንሽ ችግር እንኳን ካለ ደውልልኝ" ብሎ "ቻው!" ብሎ ተለየኝ። ደላላውም መልሶ ደውሎልኝ "ሸኘኸው?" አለኝ፤ እኔም እንደሸኘሁት ነገርኩት። እርሱም "በል እሺ የት ሆቴል እንዳለህ እና የአልጋ ቤት ቁጥርህን ንገረኝ" አለኝ። እኔም "ፋሲል ሆቴል፣ አልጋ ቁጥር አምስት ነው ያለሁት" ብዬ ነገርኩት። ከዚያም ወደ ሆቴል መጣና የአልጋ ቤቱን በር አንኳኳ፤ ወደ ሌላ ዶርም፣ ልጆች ወደተሰበሰቡበት እንደሚወስደኝ ነገረኝ። እኔም እሺ ብዬ ሔድኩ። ልጆች ወዳሉበት ዶርም ደረስን። ከዚያ ከልጆቹ ጋር ተዋወቅኩ። ሁሉም ተራ በተራ ስለራሳቸው ነገሩኝ። እኔም ስለኔ፣ ከየት ሰፈር እንደሄድኩ ነገርኳቸው። እነርሱም "ነገ ወደ ኬንያ ትሻገራላችሁ ብሎናል" ብለው ነገሩኝ።

በቃ እረሀብም፣ ጭንቀትም፣ ከራስ ሀገር፣ ከራስ ወገን የመራቅ ያህል ከባድ እንደሆነ ገና ከሀገራችን ሳንወጣ፣ ከሞያሌ ችግር፣ እረሀብ እና ስቃይ ጀመረ። ከዚያም ደላላው ጠዋቱኑ መጣና "በቃ ዛሬ ትወጣላችሁ፤ ልክ ስምንት ሰዓት ላይ ከኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ትሻገራላችሁ፤ አሁን ተነሱ እና ወደ ኢትዮጵያ ኢሚግሬሽን ገብታችሁ የኬንያ ቪዛ ታስመታላችሁ" ብሎ ተናገረን። እኛም ተራ በተራ እየሄድን በኢትዮጵያ ኢሚግሬሽን ቪዛ አስመታን። ሰዓቱም ቀረበ፤ በእጃችን ላይ ያለውንም ገንዘብ ወደ ዶላርና ወደ ኬንያ ሽልንግ አስቀየርን። የኢትዮጵያን ስልክ ጥለን፣ የኬንያ ስልክ (SIM card) ከሳፋሪኮም አውጥተን ተዘጋጀን። ሰዓቱ ወደ ሰባት ሰዓት ደረሰ። ምሳ በልተን ለመውጣት የሚያስፈልገውን ሁሉንም ነገር አዘጋጀን። ቆሎ፣ ውሃ በፌስታል ቋጥረን ኢትዮጵያን ጥለናት ልንወጣ በቃ ጥቂት ሰዓታት ብቻ ቀሩን።

## ክፍል ሃያ አራት

ሰኔ አስራ አንድ፣ ሰኞ ቀን፣ ሁለት ሺህ አስር ዓመተ ምህረት፣ በስምንት ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ላይ ከኢትዮጵያ ወደ ኬንያ ተሻገርኩ። ከተሻገርኩ በኋላ ወደ ኬንያ ኤምባሲ በመግባት ቪዛ አስመታሁ። ከዚያም ደላላው ተቀብሎኝ ልጆች ወደ ተከማቹበት፣ ወደ ዶርም ወሰደኝ። እዚያው አካባቢ ነበር። ቦታው ገምቦ ከተማ ይባላል፤ የኬንያ ቦርደር [የድንበር] ከተማ ነው። እዚያው ቦታ ላይ፣ የቦታው ጥበት እንዲሁም እረሃብም ጀመረኝ። ልጆቹ ከቁጥር በላይ ናቸው፤ እንኳን ለመተኛት ይቅርና ለመቆም በታው፣ ዶርሙ ጠበበን።

በዚያው ስቃይ መሃል የሆነ ነገር ትዝ አለኝ፤ ቀኑን ሙሉ ሳላስታውሰው ለካ ሰኔ አስራ አንድ የፍቅረኛዬ የልደቷ ቀን ነበር። በጣም አለቀስኩ፤ በጣም ተሰማኝ። የሚመልሰኝ ሰው ባገኝ ደስታዬን አልችለውም ነበር፤ በቃ ተቃጠልኩ፣ አረርኩ። የምሆነውን አጥቼ መቶ ሽልንግ በሳፋሪኮም ሞልቼ ወደ አባቷ ስልክ ደወልኩ። አባቷም ስልኩን አነሳ፥ "ጋሼ ከ ጋር አንድ ክፍል ተማርዎች ነን፤ ለልደቷ እንኳን አደረሰሽ ልላት ነው የደወልኩት። ይቅርታ ጋሼ! ስልኳ ስላልሰራ ነው" አልኩት። አባቷም ፈቅዶልኝ አገኘኋት፣ በጣም ተደብራለች። በዚያ ላይ በፊት ስጦታ እየሰጠኋት የሚያስደስታትን ነገር እየነገረችኝ በጣም አለቀሰች። በቃ እኔም እምባዬን መቆጣጠር አቃተኝ። ብቻ "በቃ ከእንግዲህ አይመቸኝም፣ ልደውልልሽ አልችልም ውዴ። እንኳን ተወለድሽ፣ መልካም ጊዜ! ወደ ደቡብ አፍሪካ ገብቼ ብቻ ነው መደወል የምችለው" ብያት በትልቅ ሀዘን ተሰናበትኳት።

ሰኔ አስራ አንድ ሁለት ሺህ አስር ዓመተ ምህረት ከሌሊቱ አስር ሰዓት ላይ ከገምቦ ከተማ ወደ ናይሮቢ ጉዞ ጀመርኩ። ቀኑን ሙሉ ሳንበላ እና ሳንጠጣ ጉዞ አደረግን። ወደ ስምንት ሰዓት አካባቢ ላይ የሆነ ቦታ ላይ መኪና አቁመው ዉሃ፣ ቆሎ ግዙ ብለው ተናገሩን። በታውም ሴሎ ከተማ ይባላል። እዚያም ትንሽ ጊዜ አርፈን ውሃ እና ቆሎ ገዝተን ገባን።

ከሌሊቱ አስር ሰዓት መጓዝ የጀመረ መኪና ወደ ማታ ስምንት ሰዓት ከመኪና አወረደን። ወደ አንድ ቤትም ደላላው ወሰደን። ሲወስደን በዚያ ቦታ ላይ ብዙ ኢትዮጵያውያን ውስጥ ነበሩ። ሁሉንም ልጆች ሰላም ብያቸው ሁሉንም ነገር መጠየቅ ጀመርኩ። “ነገ እንወጣለን? መቼ ነው ወደ ሌላ ሀገር የምንሻገረው?” ብያቸው ጠየቅኳቸው። እነርሱም በኔ ላይ ሳቃቸውን ለቀቁ። በጣም ደነገጥኩ።

በኋላ ላይ ሁሉንም ነገር አንድ በአንድ ነገሩኝ። “በዚህ ዶርም ውስጥ ሶስት ወር የተቀመጡ ልጆች አሉ፤ ለዚያውም ጠዋትና ማታ፣ ሁለት ዳቦ እና አንድ ሻይ ብቻ እየተመገቡ” ብለው በጣም አስፈራሩኝ። በቃ ቀን ጨለመብኝ፤ ወደ ኋላ ለመመለስ አይቻልም። ፖሊስ ከያዘኝ ያስረኛል፤ በቃ ምን ልሁን? የምሆነውን አጣሁኝ። በቃ ቀስ በቀስ እኔንም እዚያው አቆዩኝ። እዚያው ሶስት ቀን እንደቆየሁኝ ከተቀመጥኩበት ስነሳ እራሴን ማዞር ጀመረኝ፤ በቃ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ። እንዲህም እየሆንኩ አምስት ቀን ቆየሁኝ። ደላላው መጥቶ “አሁን ተነስ” ብሎ ተናገረኝ። ከእኔ ጋርም አራት ልጆች ቆጥሮ ወሰደ እና በቤት መኪና ጭነውን ጉዞ ጀመርን።

ናይሮቢ ከተማ ጨርሰን ወደ ሌላ መኪና ላይ፣ ወደ ትልቅ ኮንቴይነር ውስጥ ተዘዋወርን። ግማሾቹን ልጆች ወደ ኮንቴይነሩ ውስጥ ወረወራቸው እና እኔና ሁለት ሌሎች ጓደኞቼ በተሳቢው ውስጥ ወዳለ ጋቢና ገባን። አልጋ ላይ ከመጋረጃ ውስጥ አስቀመጠን። ከምሽቱ አንድ ሰዓት አካባቢ ጉዞ የጀመርን ወደ ሌሊቱ አስር ሰዓት ላይ ወደ ሞምባሳ ደረስን። ከመኪናም አውርዶን ወደ ጫካ አስገባን። በጣም በሚያስፈራ ጫካ ላይ በሆነ መጋዘን ውስጥ አስቀመጠን።

እዚያው ወደ አስራ ሶስት ቀን ተቀመጥን። በቀን አንዴ ብቻ ነው የምንመገበው። በቃ ነፍሴ መውጣት ብቻ አምቢ አለኝ። በዚህ አስራ ሶስት ቀን ውስጥ ከውሃ ሽንት በስተቀር፣ የምግብ ሽንት ሽንቴ አላውቅም ነበር። በቀን አንዴ የሚሰጠው እሩዝ ሆዴን አደረቀው። ሞት መለመን ጀመርኩ። በቃ ከረሀብ የተነሳ በጣም ታመምኩኝ፤ መቆም ሁሉ አቅቶኝም ነበር። በኋላ ላይ እዚያው ሞምባሳ ከደላላው ጋር ትንሽ ተግባብተን ነበር። ለዋናው ደላላ ደውሎልኝ ልጁ ሊሞት ነው ብሎ ተናግሮት እንድወጣ አደረገኝ።

በሁለት ዶርም ውስጥ ሙሉ ልጆች እንደተቀመጡ፣ እኔን ብቻ ከበረሃ፣ ከሞምባሳ ከተማ ወደ ታንዛኒያ በሞተር ወደ አስር ሰዓት ያክል አስጓዘኝ። በኋላም ይህ የሚባለው የሞምባሳ ደላላ ለታንዛኒያ ደላላ አስረክቦኝ ተመለሰ። ታንዛኒያዊውም በበቆሎ ማሳ ውስጥ በጣም አራመደኝ። ነፍሴ ሊወጣ ደረሰ፤ በቃ ጉዞውን እንዳልቻልኩት ነገርኩት። አንድ ቀን ሙሉ ምንም እንዳልበላሁ ነገርኩት፤ በማልችለው እንግሊዝኛ “I am very hungry” [እርቦኛል] አልኩት። ወደ ከተማ ገባን እና በባስ ውስጥ ተሳፈርን። በባስም

ተሳፍረን ከረጅም ሰዓት ከተጓዝን በኋላ፣ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ወደ እራሱ ቤት ወሰደኝ፣ ምግብም ሰጠኝ። በላሁ። ትንሽ ነፍሴ ተመለሰች። በቃ እዚያው አደርኩ። ጠዋቱኑ ተነሳና "ዛሬም እረጅም ጉዞ አለን፤ ፀጉርህን ትላጫለህ፤ ካልሆነ ትያዛለህ። ያንተ ፀጉር ሉጫ ነው፤ ለስለስ ያለ ነው" አለኝ።

ከዚያም ፀጉሬን ተላጨሁኝ እና ወደ ሌላ ከተማ ጉዞ ጀመርኩኝ። ቀኑን ሙሉ ተሳፍረን ስንጓዝ ውለን ወደ አንድ ከተማ ደረሰን። እዚያው ወደ ሆቴል ወስዶኝ አልጋ ቤት አሳደረኝ። እንደገና ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ተነስተን ጉዞ ጀመርን። በቃ ቀኑን ሙሉ ተሳፍሬ ተጓዝኩኝ እና ወደ ማታ አምስት ሰዓት ከመኪና ወርደን ወደ ሌላ ትንሽ የቤት መኪና አስገብተውኝ ጉዞዬን ቀጠልኩኝ። ጉዞው ሲያበቃ ወደ አንድ ቤት አስገቡኝ። ቤቱን ከፍተው ሲያስገቡኝ የሆሳዕና ሁለት ልጆች እና የሀላባ ከተማ፣ ሌሎች ሁለት ልጆችን አገኘኋቸው።

በቃ በጣም ደስ አለኝ። በቃ የኢትዮጵያ ልጆች በማግኘቴ በጣም ደስ አለኝ። ከዚያም ወደ ሌላ ከተማ ለመሻገር በመኪና እዚያው ማታ አንድ ሰዓት ላይ ወደ እኛ መጥተው ወሰዱን። እንደገና በቤት መኪና ለአምስት አድርገውን ጉዞ ጀመርን። ከከተማው ወጣ አድርገው ጫካ ውስጥ ለቀቁን እና "ሌላ ደላላ ይመጣል፣ 'ኢትዮጵያ' ሲላችሁ ውጡ እና በእርሱ ግቡ" ብለውን፣ ጫካ ውስጥ ጥለውን ሄዱ። ብዙ ብርድ ባለበት፣ በዚህ በኩል ፖሊስ በሌላ በኩል ደግሞ ዝናብ ውስጥ ሆንን። በቃ መላ ጠፋብን።

በጣም ቆይተን፣ ተስፋ ቆርጠን ለፖሊስ እጅ እንሰጣለን እያልን ሳለ፣ እዚያው መኪና መጣና "ኢትዮጵያ" ስላለ ወደ መኪናው ሮጠን ገባን። ከዚያም ሳንበላ፣ ሆዳችን በጣም እንደተራበ ወደ ሌላ ከተማ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ከሰላሳ ላይ ወደ አንድ ቤት ወሰዱን። ቤቱም ጫካ ውስጥ ነው ያለው። ያን ሁሉ ጫካ በእግራችን አንከራተተን። ከዚያም ወደ ቤት ስንገባ፣ ወደ ሃያ ዘጠኝ ልጆች ውስጥ ላይ ነበሩ። ሁለት ሶማሌያውያን ልጆችን ጨምሮ በአጠቃላይ ወደ ሰላሳ አንድ ልጆች በቤት ውስጥ ነበሩ። እዚያ ቤትም ስንገባ በቤቱ ግርግዳ ላይ "የዚህ ቤት ችግር ምግብ በሃያ አራት ሰዓት አንዴ ነው" የሚል በአማርኛ የተፃፈ ጽሑፍ አየን። እዚያም ብዙ ልጆች፣ በሞምባሳ ከተማ ያገኘኋቸው ልጆችን በድጋሚ አገኘኋቸው።

እነርሱም በጣም የሚያሳዝን ነገር ነገሩኝ። ከመሀላቸው ሁለት ልጆች በህንድ ውቅያኖስ [Indian Ocean] ላይ እንደተበሉ ነገሩኝ። ከእነዚህ ሁለት ልጆች ውስጥ ለካ የሰፈሬ ልጅ ነበር። ስማቸውም እና የሚባሉ ልጆች ነበሩ። በቃ እጅግ አዘንን። በዚህ ስቃይ መሃል ደግሞ ይህ ልጅ የሆነውን ነገር ሳስብ ለእራሴ እራሱ ትልቅ ስጋት ሆነብኝ። በዚህ ቤትም በስምንት ላይ ተኝተን ሶስት ቀን እዚያው ታሸን። በቃ ነፍሴ ብቻ ነው እንጂ በጣም ከሳሁኝ። በቃ ቆሜ መራመድ እንኳን እያቃተኝ መጣ።

ደላሎቹ ከዚያ ካለንበት ከቱንዱማ ከተማ [ቱንዱማ ከተማ ማለት ለታንዛኒያ እና ለዛምቢያ የመጨረሻ ቦርደር [ድንበር] ነው] ለመሻገር ፖሊስ በጣም በጥንቃቄ እንደሚፈትሽ ስለሚያውቁ ግማሽ፣ ግማሽ ልጆችን ወደ ጫካ መበተን ጀመሩ። ግማሽ ልጆች ወደ ዛምቢያ አሻገሩ እና ሲመለሱ ለታንዛኒያ ኢሚግሬሽን ሰራተኞች ጥቆማ ደረሳቸው። ደላላውን መጀመሪያ በጣም ሳስቸግረው ነበር። እኔን በጣም እያመመኝ ነበር። ደላላውን በጣም በጥብቅ ስናገረው "በቃ አንተ በቀጣይ ትሄዳለህ፣ ጠብቅ ማታ ሁለት ሰዓት ትሄዳላችሁ" ብሎን ወደ አራት ልጆች ቀጥሮን ነበር። ግማሽ ልጆች ቀንሰው የቀረነው ወደ አስራ ዘጠኝ የምንሆን የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ነበርን። የኢሚግሬሽን ሰራተኞች ጥቆማ ሲደርሳቸው፣ በቃ መሳሪያ ታጥቀው፣ ፖሊስ ይዘው እዚያው ቤቱን ከበቡት። በቃ ተስፋችን ጨለመ። ሁሉም ወደ አምላኩ መጮህ ጀመረ። ምን ይዋጠን? በፖሊስ ተከበብን።

## ክፍል ሃያ አምስት

በቱንዱማ፣ በታንዛኒያ አና በዛምቢያ ቦርደር [ድንበር] ላይ የመጨረሻ እርምጃችን በቃ ተገታ። በቃ ተቋጨ:: ያለንበት ቤት በቱንዱማ ከተማ ፖሊስ እና ልዩ ሃይሎች ተከበበ:: የታንዛኒያ ITV እና TBC ጋዜጠኞች ተጠሩ። አሸባሪዎች ያዝን እያሉ በደረት ወደ መሬት ተኙ ሲሉን ቋንቋቸውን ስለማንሰማ ፈዘን ቆምን። ከዚያም በእርግጫ ወደ መሬት መጣል ጀመሩ፤ ሁላችንም ወደ መሬት ወደቅን። በሁላችንም እጅ ላይ ካቴና ማድረግ ጀመሩ። በሁላችንም እጅ ካቴና አደረጉና ከቤት ተራ በተራ ማውጣት ጀመሩ:: የTBC እና ITV ጋዜጠኞች ሁሉንም አንድ በአንድ መጠየቅ ጀመሩ፤ እኔንም "አንተ ነህ የእነርሱ መሪ" አሉኝ። እኔ ብዙም አልተጎዳሁም፤ በነዚያ ልጆች አይን ስታይ እሻል ነበር:: በበረሃ መንገድ በኩል ነበር ወደዚያ የደረሱት። ጫካ ውስጥ ከአንድ ወር እስከ ሶስት ወር ተቀምጠው፣ በጣም ከስተው መራመድ የማይችሉ ልጆችም ነበሩ። በቃ በጫካ እንደመጡ ነገርኳቸው፣ ጋዜጠኞቹም ሁሉን ነገር ቀርጸው፣ ሁሉንም ቃለመጠየቅ አድርገው ሄዱ።

ፖሊስ እና የቱንዱማ ቦርደር [ድንበር] የኢሚግሬሽን ሰራተኞች በመኪና ጭነው ወደ ቱንዱማ ኢሚግሬሽን ወሰዱን። በባዶ ክፍል አስቀመጡን። ያስቀመጡበት ክፍል በጣም ጠባብ ነበር። በቃ ለአስራ ዘጠኝ ልጆች አልበቃም ነበር፤ በጣም ተጨናነቅን። ማታ እዚያው በቱንዱማ ኢሚግሬሽን ውስጥ አሳደሩን። በሁለተኛ ቀንም ረሀብ ሊገለን ሲደርስ በቃ ወደ ማረሚያ፣ ወደ ትልቅ እስር ቤት እንዲወስዱን መለመን ጀመርኩ፡ ፡ አሰራሩ እንደዚያ አይደለም። "መጀመሪያ ወደ ደረቅ እስር ቤት ትገባላችሁ፤ ከዚያም ስማችሁ ተመዝግቦ ወደ ትልቁ እስር ቤት ትገባላችሁ። እዚያ ነው ምግብ ማግኘት

የምትችሉት” ብለው ነገሩን። ሀላፊዎቹንም በጣም ለመንኳቸው፤ “በረሀብ ልንሞት ነው፣ ወደ ማረሚያ፣ እስር ቤት ውሰዱን” ብዬ በጣም ለመንኩኝ።

ኃላፊውም በጣም በማዘን ለእያንዳንዳችን በፌስታል ትንሽ ትንሽ ሩዝ ተቋጥሮ አስመጣልን። ነፍሳችን እንዳይወጣ ይህችን አንድ እጅ የማትሞላ ሩዝ በምላሳችን ላይ ቀመስን፥ መቼም በላን አይባልም። ብቻ ውሃ ለመጠጣት ቻልን። ከዚያም ከኢሚግሬሽን ሁለት ሰው በአንድ እያደረጉ በካቴና አስረው ወደ ደረቅ እስር ቤት ወሰዱን። በደረቅ እስር ቤት ውስጥ ምንም ያልቀመስን ሰዎች፣ ሁለት ቀን በባዶ ሆዳችን ተቀመጥን። ቦታ በጣም ጠቦን ስለነበረ ግማሽ ልጆች በሽንት ቤት ሴራሚክ ላይ ተኙተዋል። በዚያ ላይ በአንድ ልብስ ብቻ ነው ያስገቡን፤ በቲሸርት ላይ ኮት መደረብ የእስር ቤቱ ህግ አይፈቅድም። በቃ በረሃብ፣ በብርድ፣ ቦታ በማጣት ተንገላታን። ስንቱን ልናገር? በቃ ሞት ቢወስደን በጣም ደስተኞች ነን።

ሐምሌ ስድስት ሁለት ሺ አስር በቃ ስቃይ ሳይሆን ሲኦል በምድር ተጀመረ። በዚህ ደረቅ እስር ቤት ላይም በጣም ተጎዳን፤ በቃ ልጆች ሊሞቱ ደረሱ። አንዳንድ ልጆች፣ በባህር እና በጫካ መንገድ የመጡት፣ ረሀብና ስቃዩን መቋቋም አቃታቸው፤ እራሳቸውን መሳት ጀመሩ፤ “በቃ አይዟችሁ! ወደ ትልቅ እስር ቤት ስንወሰድ እዛ ምግብ እናገኛለን፤ አይዟችሁ!” እያልኩ በዚህ በኩል ለራሴም ስል ልጆቹን አፅናናቸው ነበር። ሰኞ ቀን፣ ሐምሌ ዘጠኝ፣ ሁለት ሺህ አስር ዓመተ ምህረት፣ ከደረቅ እስር ቤት ወደ ትልቅ ማረሚያ ቤት ተወሰድን። ማረሚያ ቤት ከመግባታችን በፊት ፍርድ ቤት መቅረብ አለባችሁ ብለው አማርኛ የሚችል የሚባል ሶማሌያዊ አስመጥተው ወደ ፍርድ ቤት አቀረቡን። ወደ ፍርድ ቤት በፓትሮል መኪና እንደደረስን የቤተክርስቲያን እናቶች በዜና ላይ ስለእኛ ስለሰሙ፣ ወደ ፍርድ ቤት በባልዲ እሩዝ በስጋ ሰርተው አመጡልን።

በቃ ወደ ደረቅ ክፍል አስገብተው እዚያው ቆለፉብን። እናቶች ግን ፖሊሶችን አስፈቅደው በመስኮት ምግቡን መስጠት ጀመሩ። ልጆቹም በጣም ከመራባቸው የተነሳ ምንም ሊረጋጉ አልቻሉም። በግምብ ውስጥም ሰው ሁሉ ይመለከተናል። በቃ በጣም ተገረሙ፤ ምግብ ለማግኘት ስንል በመስኮት ላይ ስንደባደብ ምግብ ያመጡልን እናቶችም በጣም አዝነው ፖሊሶቹን ለምነው በር አስከፍተው ምግቡን መስጠት ጀመሩ። በሩ ተከፍቶ ቢሰጥም ትልቅ ድብድብ ሆነ። ከእናቶች እጅም የሚባል ልጅ እሩዙን ወደ መሬት ወደ ሲሚንቶ ላይ ገልብጦ በመሬት ላይ ተቀምጦ ብቻውን መብላት ጀመረ። በቃ የሰው ስጋ ብቻ ነበር መብላት የቀረባቸው። ይህን ሁሉ ስመለከት ልቤ በጣም ተሰበረ። በአባቴ ቤት ምግብ ይወድቃል እኔ ግን ይህን ሁሉ በህይወት ላይ አየሁ ብዬ በጣም አዘንኩ።

ከዚያም ወደ ፍርድ መስጫ፣ ወደ አዳራሽ አስገቡን። በፍርድ ቤትም በአስተርጓሚው በሶማሌያዊው  አማካኝነት ተራ በተራ ቃለ መጠይቅ አደረጉልን፤ እኛም ሁሉንም ነገር ተናገርን። ከተያዝነው ከአስራ ዘጠኝ ልጆች ውስጥ ግማሾቹ እድሜአቸውን ከፍ አድርገው ነገሯቸው። ወደ ዘጠኝ ልጆች ደግሞ እድሜያችንን ዝቅ አድርገን ተናገርን። ከዚያም ወደ መኪና፣ ወደ ፓትሮል ወሰዱንና ወደ ሌላ ትልቅ ማረሚያ እስር ቤት ጉዞ ጀመርን። ወደ ሶስት ሰዓት ያህል በመኪና ተጉዘን ወደ ትልቅ እስር ቤት ደረስን። ወደ ማረሚያ ቤት፣ ወደ ውስጥ አስገብተው ያለውን ነገር አስመዝግቡ ብለው ተናገሩን። ፍቅረኛዬ  የሰጠችኝን በድብቅ ይዤ የነበረው የእጅ ጌጥና የአንገት ሀብል ደብቄ ወደ ውስጥ ወደ ማረሚያ ግቢ ውስጥ ይዤው ዘለቅኩ።

ወደ ግድግዳ ስር ወስደው ልብሳችንን አስወለቁን። ፖሊሱ አንድ በአንድ ልብስ እየፈተሸ ሳለ፣ በልብሴ ላይ የሰፋሁትን የፍቅረኛዬን ስጦታ፣ የአንገት ሀብል እና የእጅ ጌጡን ከልብሴ ውስጥ በምላጭ ቀዶ አወጣ። በቃ ልቤ ቀለጠ፣ እምባ አነቀኝ፣ የምሆነውን አጣሁኝ። በቃ አልቻልኩም እምባዬን ዘረገፍኩት። ፖሊሱም "ለዚህ ታለቅሳለህ?" ብሎ በጣም አመናጨቀኝ፣ ሰደበኝ፣ በቆሎ አጥተህ ነው የመጣኸው ብሎ በጣም ገፈተረኝ፣ መታኝ። በቃ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ነበር። በቃ ሁሉንም ነገር ይሄ ስደት ወሰደብኝ። በቃ በውስጤ መቃጠል ብቻ ነው። የምወዳቸውን ሰዎች ሁሉ ከአጠገቤ አጣሁ። ፍቅረኛዬን፣ ቤተሰቦቼን፣ ወንድሞቼን፣ የምወዳት አንድ ፍሬ እህቴን አጣሁ። በቃ ተስፋዬ ጨለመ፣ ከእንግዲህ ሰው አልሆንም አልኩኝ። ተስፋ ቆረጥኩ። ከዚያም ልብሳችንን ፈትሸው፣ አንዳንድ ልጆች በልብሳቸው የሰፉትን ቀድደው ዶላሩን ወሰዱት። ከዚያም ወደ ውስጥ ወስደው አቀላቀሉን።

እስር ቤት ውስጡ ከገሃነም አይተናነስም። ጤነኛ፣ እብድ የሌለ የለም። ወዲያውም ፀጉራችንን ላጩን። መኝታም ይሸላል ብለን ነበር ያሰብነው፤ ከደረቅ እስር ቤት የበለጠ ችግር ያለበት ነበር። ወደ ክፍል ውስጥ ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ያስገባሉ። በዚያ ላይ በአንድ ክፍል ወደ መቶ ሀምሳ ሰው ነው የሚያስገቡት። በቃ ጎናችንን ማሳረፍ እንኳን ብርቅ ሆነብን። እንደምንም ሆነን ጎናችንን ስናሳርፍም "ሌሊቱ ነጋ፣ በቃ ቁርስ ሰዓት ደርሷል" ተብሎ በሰልፍ፣ የበቆሎ ዱቄት ተፈልቶ በኮባ ያቀብላሉ። በጣም ተገረምን። የተፈላውን የበቆሎ ዱቄት ነፍሳችን ከሚወጣ ብለን እርሱንም ተሰልፈን ተቀበልን። አፈር አፈር የሚለውን ይህን የተፈላውን የበቆሎ ዱቄት ከመጠጣት እና ከመዳን ውጪ፤ በቃ ነፍሳችን ከሚወጣ ሌላ አማራጭ አልነበረንም። በሀያ አራት ሰዓት ውስጥ ምግብ የምናገኘው ከቀኑ ስምንት ሰዓት ብቻ ነው። በቃ ሌላ አማራጭ የለንም።

በዚህ ሁኔታ ወደ ስምንት ሰዓት ደረስን። በጣም ታመምኩኝ። የሚሰጡት ምግብ በአፈር የተለወሰ ገንፎ ነው፤ ይህም ገንፎ ጥራት የሌለው ነው። ለሁለት ሺህ ታሳሪ እንዴት በጥራት ይሰራል? በቆሎ በጥሩ ሁኔታ አያስፈጩም፤ ከነ ቆሻሻው ነበር የሚያስፈጩት።

በቃ በጣም አመመኝ። ቆሜ መራመድ በጣም እያቃተኝ መጣ። ከቆምኩበት ብድግ ብዬ ስነሳ ሰማይና ምድር ጨለመብኝ፤ እራሴን ስቼ ወደቅሁ። ብዙ ሰው ተሰበሰበ፤ የኢትዮጵያ ልጆችም በጣም አዘኑ፤ ተሸክመውኝም ወደ ታሳሪ መርጃ ቦታ ወሰዱኝ። ኦ አር ኤስ (ORS) የሚባል ሀይል ሰጪ የሆድ በሽታ መድኃኒት በጥብጠው አጠጡኝ። ይህም ምንም መፍትሄ ሊሆንልኝ አልቻለም። “በቃ የእኔ መጨረሻ እዚህ ነው ወይ?” ብዬ በጣም ስጋት ሆነብኝ። በቃ ወደ ፈጣሪ መጮህ ጀመርኩ፤ “ጌታ ሆይ! የእኔ መጨረሻ በዚህ በታንዛኒያ እስር ቤት እንዳይሆን” ብዬ በጣም ተረበሽኩ። ልጆቹም ተሸክመው ወደ ፖሊሶች ሲወስዱኝ “ይሙት ግቡ፤ ውስጥ ታሳሪዎች የሚቀበሩበት ቦታ አለ፤ እዚያ ቦታ ላይ እንቀብረዋለን” ብለው በጣም ተኩራሩብኝ። በቃ ከፈጣሪ በቀር ሌላ ማንም ሊረዳኝ እንደማይችል አወቅኩ “ጌታ ሆይ የእኔ መጨረሻ ከዚህ እስር ቤት እንዳይሆን” የሚል ነበር ፀሎቴ። ብቻ በእነርሱ መድኃኒት ሳይሆን በፈጣሪ ምህረት እየተሻለኝ መጣ።

በጣም ችግር የሆነብን ነገር ደግሞ ውሃ የሚባል ነገር በፍፁም አናገኝም፤ ለመጠጣት እንኳን በሰልፍ ተሰልፈን አንድ ብርጭቆ፣ እርሱም በትግል ጉልበት ያለው ሰው ሌሎችን ገፍትሮ ነው የሚጠጣው። ብር ያለው በብሩ እየገዛ የታሸገ ውሃ ይጠጣል። በቃ በዚህ ሁኔታ መቀጠል በጣም ከበደን። ልጆችም መታመም ጀመሩ። ለገላችን ውሃ በወር አንዴ፣ እርሱም ቧንቧ ላይ ከመጣ፣ ካልመጣ ደግሞ በሶስት ወር ነበር የምንታጠበው። ይህን ሁሉ ችግር ችለንም ጎናችንን አናሳርፍም፤ በአንድ ጎን ብቻ ሌሊቱን ሙሉ እንተኛለን። ቦታ ስለማይበቃ እግር እና ጭንቅላታችን ተገጣጥመን ነው የሚያስተኙን። በቃ በዚያ ላይ እግሩን ያልታጠበ ያጋጥማል፤ ግማቱንም ችለን ጭቃውንም አቅፈን ሌሊቱን እናሳልፋለን።

ሲነጋ ያቺን በሃያ አራት ሰዓት የምትሰጠውን ገንፎ በጉጉት ነበር የምንጠብቀው። በቃ ያቺን ገንፎ በቦሎቄ እስከምናገኝ ሰዓቱን መቶ ጊዜ ነው የምናየው፤ ሰዓቱ ደርሶ እስከምንቀበል በጣም ነው የምንራበው። ሃያ አራት ሰዓት ጠብቀን ስለምንቀበላት ከማር በላይ ጣፍጣን እንበላለን። በዚያ ላይ ደግሞ በጣም ትንሽ ነው። በቃ አማራጭ ታጣና ልመና ጀመርን። የእስር ቤት ገንፎ የማይበሉ ሀብታሞችን መለመን ጀመርን። ተሰልፈው ተቀብለው እንዲሰጡን እንለምናለን፤ ከሰጡን ትራፊ እስከማድረግ ድረስ ባንጠግብም ትንሽ ይሻላል።

ምግብ ከቤት የሚመጣላቸው ሰዎች፣ ማለትም የሀገሪቱ ልጆች፣ አንዳንዴ ካስተረፉ በኋላ እንለምናቸዋለን። በቃ በሀገራችን የሆቴል ትራፊ እንኳን በልቼ የማላውቅ ሰው በዚህ በባዕድ ሀገር የገንፎ ትርፍራፊ መሰብሰብ ጀመርኩ። አንድ አንዴ ሳስበው ስቅስቅ ብዬ አለቅሳለሁ። ከልጆቹ መሀል የሚባል ልጅ ከሁላችንም በጣም ትንሹ ነበር። እኔ ካለቀስኩ አብሮኝ ያለቅሳል፤ በቃ ለእርሱ ስል ማልቀስ ተውኩኝ። በቃ አላስችል ሲለኝ አንዳንዴ አለቅሳለሁኝ። ሆኖም ግን አልቅሼስ ምን አመጣሁ? እችለዋለሁ። በቃ በዚህ

ሁኔታ በልመና፣ በረሀብ፣ በቦታ ማጣት፤ የቱን ችግር ላውራ? የቱንስ ልተው? በጣም በጣም ከባድ ነው። እንደቀልድ እንደቤታችን ስቃዩን ችለን መኖር ጀመርን።

## ክፍል ሃያ ስድስት

እንደቀልድ ወደ ማረሚያ/እስር ቤት ከገባን ወደ አስራ አምስት ቀን ሆነ። ወደ ፍርድ ቤት ልትሄዱ ነው ተዘጋጁ ተባልን። በቃ ወደ ቤት የምንሄድ ያህል በጣም ተደሰትን። በቃ ከፍርድ ቤት፣ ወደ ቤት ነው የምንሄደው ብለን በጣም ተደሰትን፤ ወደ ፍርድ ቤትም ደረስን። በመጀመሪያ ቀን የነበረው የሚባለው ሶማሌያዊ ልጅ ለትርጉም ተጠራ። ቃላችንንም ተቀበሉ። "ለምን ወደ ታንዛኒያ መጣችሁ?" የሚል ጥያቄ ነበር። እኔም ወደ ደቡብ አፍሪካ ለስራ እንደምንሄድ፣ ሰላማዊ ሰዎች እንደሆንን ተናገርኩ። ተርጓሚውም ይህንን ነገራቸው። ከዚያም ተራ በተራ ልጆቹም ተናገሩ። ሁላችንም ተምበርክከን "ወደ ሀገራችን መልሱን፣ እኛ ጤነኞች ነን አሸባሪዎች አይደለንም፤ ልቀቁን" ብለን ለመንናቸው። በቃ አስወጡልን ብለው በፖሊስ አስወጡን። ለቀጣይም አስራ አምስት ቀን ቀጠሩን።

ወደ ማረሚያ/እስር ቤት መለሱን በዚህ ስቃይ ላይ እንደገና ሌላ አስራ አምስት ቀን መጠበቅ ሆነብን። በቃ በትዕግስት ፍርዱን እስከምንሰማ ጠበቅን። በየአስራ አምስት ቀን ወደ ፍርድ ቤት መመላለስ ሆነብን። "ለምን ወደ ሀገራችን ያለ ቪዛ ገባችሁ?" እያሉን፣ ክርክር ብቻ እያደረጉ ወደ ሶስት ወር አለፈ። በየአስራ አምስት ቀኑ ወደ ፍርድ ቤት ይወስዳሉ፤ ግን ምንም ትርጉም የለውም። በዚህ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ስድስት ጊዜ ወደ ፍርድ ቤት ተመላልሰናል፤ ግን ፍርድም ሆነ እንዲህ ትሆናላችሁ የሚል ነገር ተናግረውን አያውቁም። በቃ ከስድስት ጊዜ በላይ ካመላለሱን በኋላ ለመጨረሻ ፍርድ ጳጉሜ ስድስት ቀጠሩን። ልባችን እየመታ "ዛሬ ምን እንሰማ ይሆን? ወደ ሀገራችሁ ግቡ እንባል ይሆን?" እያልን በጣም ትልቅ ፍርሀት ሆነ። ልክ አራት ሰዓት አካባቢ ሁላችንም ተሰብስበን ሐይማኖት ሳንለይ፣ ሙስሊም የሆነም፣ ጴንጤም፣ ኦርቶዶክስም በህብረት በግቢ ውስጥ በጠጠር ላይ ተምበርክከን ጸለይን።

ጠርተውን በሰልፍ አቁመው ከእስር ቤት ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ በመኪና ጫኑን። ወደ ፍርድ ቤትም ደረስን። ወደ ፍርድ መስጫ አዳራሽም አስገብተው ነገሩን ማውራት ጀመሩ። በመጀመሪያም እድሜ ዝቅ አድርገው የተናገሩትን ዘጠኝ ልጆች አስነስተው "እድሜአችሁ ስንት ነው?" እያሉ ተራ በተራ ጠየቁን። ከአስራ ስምንት ዓመት በታች አድርገን የነገርናቸውን "ከፍርድ ነፃ ናችሁ!" ብለው ተራ በተራ "ኑ! እዚህ ጋር ፈርሙ" ብለው ከፍርድ ነፃ በሚለው ወረቀት ላይ በሶስት ቦታ ላይ አስፈረሙን። ዘጠኛችንም ለይተው አስቀመጡና በቀሩት አስር ልጆች ላይ ሶስት፣ ሶስት ዓመት ጽኑ እስራት

ፈረዱባቸው። በቃ ለኛ ለዘጠኝ ልጆች “እናንተ ነጻ ናችሁ፤ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ከመጣ ነገም ቢሆን ትሄዳላችሁ” ብለው “ነፃ” የሚለውን ወረቀት ሰጡን።

በቃ ወደ አገሬ የገባሁ ያህል ተሰማኝ። ደስ አለኝ። በሌላ በኩል ደግሞ በጓደኞቼ ላይ ሶስት ዓመት ተፈርዶባቸዋል። በቃ ግማሽ ልቤ በደስታ፣ ግማሽ ልቤ በሀዘን ሆኖ ወደ ማረሚያ እስር ቤት መልሰው አስገቡን። የተፈረደባቸው አስሩም ልጆች ግን ውስጥ ሲገቡ በቃ ሶስት ዓመት በዚህ ስቃይ ልናሳልፍ ነው ብለው በጣም አለቀሱ። እኛንም በጣም አስለቀሱን። በዚህም ሁኔታ ላይ ወደ አንድ ሳምንት አስቆጠርን። ከዚያም የተፈረደባቸው ልጆች ወደ እስር ቤት ቢሮ ተጠሩ። ወደ ትልቅ ወደ ክልል እስር ቤት፣ ወደ አራት ሺህ፣ አምስት ሺህ ከዚያም በላይ ወደ ሚታሰሩበት እስር ቤት ትሔዳላችሁ፤ እዚያም ትቆፍራላችሁ ብለው አስደነገጧቸው። በቃ በጣም እረብሻና ለቅሶ ሆነ። ለእኛ ለቀረነው ዘጠኝ ልጆችም “ለቤተሰቦቻችን በህይወት እንዳለን ደውላችሁ አሳውቁ” ብለው ተስፋ በመቁረጥ ወደ ትልቁ እስር ቤት ተወሰዱ።

በቦታው ዘጠኝ ልጆች ብቻ ቀረን፤ እኛንም በጣም ከፋን። በድንገት ከትንሽ ቆይታ በኋላ፣ በመስከረም ሀያ አራት፣ ሁለት ሺ አስራ አንድ ወደ ፍርድ ቤት ተጠርታችኋል ብለው ወደ ፍርድ ቤት ወሰዱን። ወደ ፍርድ ቤትም ውስጥ አስገብተውን እረጅም ሰዓት ተከራከሩ። ሴት ዳኛዋ በጣም ስለ እኛ ተከራከረች። “እድሜአቸው በትልቅ እስር ቤት እንዲቀጡ አይፈቅድም” ብላ ወደ ትንሹ ወደ ህፃናት ማቆያ ተብሎ፣ ወደ ዩኒሴፍ (UNICEF) ድርጅት ግቢ እንድንወሰድ ወሰነች። “በቃ እናንተ ወደ ማጌሬዛ (Magereza)፣ ወደ ማረሚያ/እስር ቤት አትሄዱም፤ አይዞአችሁ!” ብላ ጥሩ ተስፋ ሰጠችን። ወደ ጥሩ ቦታም እንደሚወስዱን ተናገሩን። በቃ ፈጣሪ ወደዚያ ብቻ አይመልሰን አልን። ከዚያው ከፍርድ ቤት፣ ካለንበት ከቱንዱማ ከተማ ወደ አራት ሰዓት በፓትሮል ተጉዘን ማታ ላይ ኤምቤያ ከተማ (Mbeya City) ወደሚገኘው UNICEF [ሕፃናት መርጃ ድርጅት] ግቢ ደረስን። በቃ ሸክማችን ቀለለ። የለበስነውን ሙሉ ልብስ አቃጥለው፣ አዲስ ልብስ ሰጥተው፣ ሻወር አስገብተው፣ ለሁላችንም አንድ አንድ አልጋ ሰጥተው፣ ከዚያም ምግብ እንደልብ አቀረቡልን። ሰራተኛ ወደ አስራ አምስት አለ፤ በቃ ፀሎታችን ተሰማ ።

ማታ ከአንድ ሰዓት እስከ ሁለት ሰዓት ፀሎት እና መጽሐፍ ቅዱስ የመማሪያ ጊዜ አገኘን። እንደልባችን መመገብም ቻልን። በቃ በጣም ከቤታችን የበለጠ እንክብካቤ አደረጉልን። ልብስ እንደልባችን አገኘን። ምግብ እንደቤታችን ጠዋት፣ ቀን፣ ማታ መመገብ ጀመርን። እንደአዲስ ነፍስ ዘራን። ሁሉ ነገር ተመቻቸልን። ጠዋት ቁርስ እንደበላን ወደ ክፍል ገብተን ትምህርት እንማራለን። ወደ ሶስት የትምህርት ዓይነት ያስተምራሉ። ስዋሂሊ፣ እንግሊዝኛ እና ሂሳብ ምርጥ መምህራን ተመድበው ያስተምራሉ። በቃ ችግር የሚባል

ነገር ተረሳን። ነገር ግን የእኛ አዕምሯችን ያለው ከእኛ የተለዩት አስር ልጆች ጋር ነው፣ እነርሱ ከበፊቱም የከፋ ችግር ወዳለበት ነበር የሄዱት።

በቃ ከቆይታችን አንፃር ተመችቶን ወደ ሀገራችን የመመለስ ሀሳብ እንኳን ከውስጣችን ጠፍቶ ማሰብ ሁሉ ትተናል። በኋላ ሀላፊዎቹን ማስቸገር እንዳለብን ዘጠኛችንም ተስማማን። ጠዋቱኑ ተነስተን በቃ ቤተሰቦቻችን ናፍቀውናል፣ ወደ ሀገራችን ካልመለሳችሁን ብለን ትልቅ እረብሻ ፈጠርን። ከዚያም የዚህ ድርጅት ሀላፊዋ ወደ ክፍል አስገብታን በጣም መከረችን። "ይህ ነገር በእኛ ውሳኔ ብቻ የሚሆን አይደለም" ብላ በጣም ለመነችን። እኛም ለማሳሰብ ብቻ ስለሆነ ስልክ እንደምንፈልግ ነገርናት። እርሷም ከበታቿ ላለው ሀላፊ በእርሱ ስልክ ላይ የሁላችንንም ቤተሰቦች ስልክ አስመዘገበች። እኔም የወንድሜን ስልክ ሰጠሁኝ። ወንድሜንም አገኘሁት። በቃ በጣም ችግር ውስጥ እንዳሳለፍኩኝ ነገርኩት፤ እርሱም በጣም አዘነ። "አይዞህ! ትወጣህ፣ ጌታ አለ፣ ምንም አትሆንም" ብሎ መከረኝ።

በቃ በየጊዜው ወደ ቤተሰቦቻችን እየደወልን በጣም በጥሩ ሁኔታ ማሳለፍ ጀመርን። በቃ የሚያሰጋን ወደ ሀገራችን ስላልተመለስን ብቻ ነበር። ግን በዚህ ቦታ ሳለሁ ቡጉንጅ ፊቴ ላይ እያበጠ ተቸገርኩ፣ በጣም አሰቃየኝ። ወደ ስድስት ቦታ ላይ ወጣብኝ፤ በቃ በየጊዜው ማፍረጥ ሆነብኝ። አንዴ እግሬ ላይ፣ አንዴ እጄ ላይ፣ ፊቴ ላይ እና ጀርባዬ ላይ፤ በቃ በእየቦታው እየወጣ በጣም አሳመመኝ። በጣም ተጠራጠሩኝ እና ወደ ሆስፒታል ወስደው የደም ምርመራ፣ የኤች አይ ቪ ኤድስ ምርመራ አስደረጉኝ። ነፃም ተባልኩኝ። ከሆስፒታል የሆነ ማስታገሻ ሰጡኝ። ግን እርሱን ስውጥ ምንም መፍትሄ ሊሆንልኝ አልቻለም ነበር።

በቃ ሌላው ቢቀር በዚህ ቦታ ከቤተሰቦቻችን ጋር እንደልባችን እንገናኛለን። ቤተሰቦቼንም ሁሉንም አገኛቸዋለሁ። አባቴን፣ ወንድሞቼን፣ በተለይም እህቴ በጣም ናፍቃኝ ነበር:: አንድ ፍሬ የእናቴ ልጅ፣ የእናቴ ምትክ፣ በቃ በጣም እያወራን በጣም አለቀስን፤ አላመነችም ነበር። በደስታ ለቅሶ ውስጥ ሆና ማቋረጥ አቃታት "ዮኒ አጥቼሃለሁኝ ብዬ ተስፋ ቆርጬ ነበር፤ በህይወት አለህ ወይ?" ብላ በጣም ተደሰተች። ከዚያም በየጊዜው መገናኘት ጀመርን። እኔም ብዙም እንዳያስቡ ብዬ ከበፊቱ የተሻለ በጣም አሪፍ ቦታ እንደሆነ ነገርኳቸው። በቃ ስልክ ተቸግረን አናውቅም፤ እኔም ወደ ኢትዮጵያ ኤምባሲ በፔጃቸው [በኢንተርኔት ገጻቸው] ገብቼ መልእክት እልክላቸው ነበር። በዚህ ሁኔታ፣ በዚህ በ ዩኒሴፍ (UNICEF) ግቢ ውስጥ ብዙ ወራቶችን አሳለፍን።

## ክፍል ሃያ ሰባት

በጣም የምወዳቸው ወንድሞቼ ሁሉም፣ በተለይም ሙሌ የሚባል በአዲስ አበባ የሚኖረው ወንድሜ በየቀኑ ይደውላል። በደቡብ አፍሪካ ያሉትም በቃ ጥሩ ተስፋ ይሰጡ ነበር "አንተ ብቻ ወደ ሀገር ተመለስ፤ በበረራም ቢሆን ወደ እኛ ትመጣለህ፤ ብቻ አትጨነቅ፤ ፈጣሪ ወደ ሀገር እንዲመልስህ ብቻ ፀልይ" ብለው በየጊዜው ያጽናኑኛል። በኢትዮጵያ የሚኖር ከእኔ ሶስተኛ ታላቄ የሆነችው የእህቴ ባል፣ በጣም የምወደው፣ ከእናቴ ሞት በኋላ በጣም በጥሩ ሁኔታ ያሳደገኝ ልጅ ነበር። እርሱም ደወሎልኝ መጀመሪያ ከሚሰራበት ከሀደሮ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በእድገት ወደ ዋቸሞ ቅርንጫፍ እንደተቀየረ ነገረኝ። በቃ በጣም ደስ አለኝ። እርሱም በጣም ጥሩ ተስፋ ሰጠኝ።

ከዚያ የወንድሜን ሚስት አገኘኋት። እርሷም በጣም አወራችኝ፤ በቃ በጣም ደስተኛ ሆነች። ህጻኗ በጣም እንደምታስቸግር፣ ስሜን እየጠራች በጣም እንደምታስታውስ ነገረችኝ። ከዚያም ህፃኗንም አገኘኋት፤ በጣምም አናገርኳት። የዚህ የሕፃናት እስር ቤት ሀላፊም ከህጻኗ ጋር የማወራውን ወሬ ሰምተው "ልጅ ወልደሃል አይደል?" አለኝ፤ እኔም ሌላ ነገር አላወራሁም። "ልጅ እንዴት ልጅ ይወልዳል?" አልኩት። በኋላም ትዝ አላለውም። ተወው። የዚህ የሀላፊው ንግግር፣ ምንም ቢያወራኝ ለመስማት በጣም ደንዝዤ ነበር። ምክንያቱም ህጻኗ በጣም ልብ በሚሰብር ድምጽ "ናናይዬ አትመጣም እንዴ?" ስትለኝ መልስ አጥቼ ነበር። በቃ "ነፍሴ እመጣልሻለሁ!" ብዬ ነገርኳት። "እሺ" አለችኝ። ከዚያ በቃ በጣም ከፋኝ፤ ወደ ክፍሌ ገብቼም ብቻዬን ማልቀስ ጀመርኩ። አልቻልኩም! ህጻኗ የምወዳቸውን ሰዎች ሁሉ እንዳስብ አደረገችኝ። ሁሉ ነገር ተመቻችቶልኝ ሳለ ራሱ በጣም ከፋኝ። ምንስ ማድረግ እችላለሁ? "ቻል ልቤ!" ብዬ ተቀመጥኩ።

## ክፍል ሃያ ስምንት

በነጮች አቆጣጠር በሃያ አምስት፣ አስራ ሁለተኛው ወር፣ ሁለት ሺህ አስራ ስምንት የጌታችንን የእየሱስ ክርስቶስ ልደት በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ በታንዛኒያ ላሳልፍ ነው። ለበዓሉ ልዩ ፕሮግራም ተያዘ። የፕሮግራሙን ሙሉ በሙሉ ወጪ ሸፍነው በጣም የሚያምር ጊዜ እንደምናሳልፍ አሜሪካዊ የሚባል ሰው ሁላችንንም ሰብስቦ ነገረን። እኛም ደስ አለን። በእለቱም በጣም በሚገርም ሁኔታ ከውጪ ብዙ ሰዎች ተጠርተው ነበር። በጣም ደስ የሚል ቀን አሳለፍን፣ ለእኛ ሲል የእየሱስ የልደት በዓል ቪዲዮ አምጥቶ እያሳየን በጣም አሪፍ ቀን አሳለፍን። ከዚያም ከስድስት ቀን በኋላ ደግሞ የዘመን መለወጫ ነው። በዚያ ላይ ደግሞ ከልደት በዓል ቀጥሎ ሁለተኛ

ቀን “Boxing Day” ብለው ያከብራሉ። በቃ ሳምንቱን ሙሉ ስጋ ብቻ መብላት ሆነብን፤ በቃ በጣም አሪፍ ጊዜ ሆነልን። በቃ ከስድስት ቀን በኋላ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ ሊገባ ነው። በቃ በዚህ ሁሉ በዓላት ወቅት ከቤተክርስትያን ብዙ ሰው እየመጣ ይጠይቀን ነበር።

ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ ገባ። በታንዛኒያ ምድር የነጬችን የዘመን መለወጫ፣ የእየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል አከባበርን፣ ምንም እንኳን ሁኔታው መጥፎ ቢሆንም አሪፍ ጊዜ አሳልፈናል። በዚህ መሀል ደግሞ አንድ ነገር ተፈጠረ። ለዘመን መለወጫ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች የአሳማ ስጋ አንበላም ስንል የፍየል ሙክት ተሰጥቶን ነበር። ይሄን ፍየል ያረደው ታንዛኒያዊ ያልተገረዘ ልጅ ነበር፣ በቃ የፍየሉን ስጋ አንበላም ብለን ሁላችን የኢትዮጵያ ልጆች አደምን። የሚሆኑትን ነገር አጡ፤ በጣም ደነገጡ። በኋላ የበሬ ስጋ ከሆቴል አስመጡልን፤ ያንን በላን። ሀላፊው በጣም ይንከባከበናል። የእኛን ልጅ የነካውን ሰው በጣም ይመታል። የራሳቸውን ልጅ ምንም ቢያወሩ አያምኑም። ውስጥ ላይ እኛን ብቻ ነው የሚያምኑት። ሀላፊውን ስልኩን ጠይቄ ወደ ፌስቡክ (Facebook) ገብቼ የሀገር ቤት መረጃ ዜናዎች እከታተላለሁ። ሀላፊው በቃ በጣም ይወደናል፤ የጠየቅነውን ሁሉ ነበር የሚያመቻችልን።

ከእለታት አንድ ቀን ወደ ማታ አንድ ሰዓት አካባቢ ከሃላፊው ስልክ ወስጄ በፌስቡክ (Facebook) ውስጥ ገባሁኝ። ፍቅረኛዬንም ኦን ላይን (online) ውስጥ አገኘኋት። በቃ በጣም ደስተኛ ሆንኩኝ። “ሰላም ነሽ ወይ?” ብዬ ሰላምታ ጠየቅኳት። ከዚያም ብዙ ነገር ጻፍኩላት፤ ግን ምንም መልስ አልመልስ አለችኝ። በቃ ጸጥ አለች። “ምንድነው ችግር አለ ወይ?” ብዬ ጠየቅኳት። ሁለት ቃል ብቻ “ችግር የለም” አለችኝ። በቃ ምንም ብጽፍ ልትመልስልኝ ፈቃደኛ አልሆነችም። በቃ በጣም ከፋኝ፤ ብዙ ነገር ማሰብ ጀመርኩ። “ምን ሆና ይሆን? ሌላ ፍቅረኛ ይዛ ይሆን?” በቃ ብዙ ነገር ማሰብ ሆነብኝ። በቃ ሌላ ሁለት ወረቀት የሚሆን ያህል መልእክት ላክሁላት። “ምን ብበድልሽ ነው ይሄን ያክል ጊዜ ቆይተን? ምነው ዘጋሽኝ? ምን በድዬሽ ነው?” ብዬ ብዙ መልእክት ላክሁላት። ምንም አይነት መልስ መስጠት እምቢ አለችኝ። በቃ በሁለተኛው ቀንም ሆነ፤ በዚህ ሳምንት አስባ መልዕክቱን ትመልሳለች ብዬ በጣም ስጠባበቅ ነበር።

በመሀል ሌላ ችግር ገጠመኝ። የእኛው ወንድሞች፣ ለዓመታት እና ለብዙ ወራት አብረውን የነበሩ፣ የበግ ቆዳ የለበሱ ሁለት ሌቦች ሌላ ችግር ፈጠሩብኝ። የጠባቂያችንን ስልክ ወስደው፣ በአጥር ዘለው፣ ምንም ሳያውቅ በእዚያው ጠፉ። በቀረነው በሰባት ልጆች ላይ ትልቅ መዘዝ መጣብን፣ በቃ ሃላፊውም የእኛን ልጆች በፊት በትልቅ አክብሮት ነበር የሚያየን። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ስልክ፣ ወደ ሜዳ ወጥቶ እንደድሮ ኳስ መጫወት

ተከለከለ። በቃ በላያችን ላይ ቆልፈውብን በቤት ውስጥ ብቻ መዋል ጀመርን። ልጆቹ በራስ ወዳድነት በእኛ ላይ ትልቅ ክህደት ነው የፈጸሙብን። በቃ በቀረነው ልጆች ላይ ትልቅ እርምጃ ተወሰደ። ስልክ ባለማግኘታችን እኔም ፍቅሬን አጣኋት። ችግሯን ሳልረዳ ብዬ በጣም ጭንቀት ውስጥ ወደቅኩኝ። ብዙ ጊዜም በጣም ሳስብ እንቅልፍ እምቢ አለኝ።

አንድ ነገር ትዝ አለኝ፣ ወደ አዕምሮዬ መጣ። በቀን ሃያ አራት አንደኛው ወር፣ ሁለት ሺህ አስራ አንድ፣ ከሁሉም ነገር የወጣንበት ቀን ነበር። በዚህ ቀን ደግሞ ከኢሚግሬሽን ሰራተኛ ስልክ (Smart Phone) ወደ ፌስቡክ (Facebook) ገብቼ ገጼን ስመለከት፣ የእኔ ገጽ ላይ የሴት ፎቶ ተለጥፎ አየሁ። በጣም ደነገጥኩ። “ማነው ያደረገው?” ብዬ በጣም አሰብኩኝ። ሁሉም ነገር ትዝ አለኝ።

በሆሳዕና ከተማ ከስፖርት ሆቴል (Sport Hotel) ፊት ለፊት፣ በሆነ ምግብ በሚሰሩ ሴቶች ስልክ ፌስቡክ (Facebook) ተጠቅሜ ከገጼ ሳልወጣ (“Sign Out”) ሳላደርግ ትቻለሁ። በቃ ፎቶውን እነርሱ እንደለቀቁት ገባኝ። በቃ በዚያ ይሆናል፣ ወደፊት አስረዳታለሁ በሚል ነገሩን ተውኩት። ከልቤ የሌለብኝ ነገር ልታስብ ትችላለች፣ ግን በቃ በምንም እንደማልቀይራት፣ ከእርሷ ሌላ ማፍቀር እንደማልችል ታውቅ ነበር።

ችግር እረሳን ስንል በጭንቀት መዋጥ ጀመርኩ። በቃ በየቀኑ የራስ ምታት ህመም መታመም ብቻ ሆነ። ምክንያቱም ሁለት ልጆች ከእኛ መሀል ጠፍተዋል፤ ነገ ምን እንደሚፈጠር አላውቅም። በቃ ጭንቀት ብቻ ሆነ። በቃ ለእርሷ ያለኝን ክብር በፊትም ስለምታውቅ ብዙም የእርሷ አይደለም እያስጨነቀኝ ያለው። ነገር ግን “ከዚህ በኋላ ምን ይፈጠር ይሆን?” የሚል ጥያቄ ነበር። የዚህ ያለንበት ቦታ ሃላፊዎች እኛን በመጥፎ አይን መመልከት ጀመሩ። ስለዚህ ነገር ከሁሉም ልጆች ይልቅ እኔ በጣም እያሰብኩ ነበር።

## ክፍል ሃያ ዘጠኝ

በነጮች በቀን ዘጠኝ፣ አራተኛው ወር፣ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ፣ ቀኑም ማክሰኞ ቀን ነበር። ድንገተኛ የሆነ ጥሪ ተጠራን። የሰባት ሰዓት ምሳ በልተን አረፍ ብለን ነበር። ሁላችንንም ወደ በር ኑ ብለው ጠሩን። “እንኳን ደስ አላችሁ!” ብለው ነገ ልክ አስራ አንድ ሰዓት ተነሱ፤ ወደ ሀገራችሁ ልትሄዱ ነው አሉን። በቃ በደስታ እራሳችንን መቆጣጠር አቃተን። ለእኛ ይህ ነገር ሰበር ዜና ሆነብን፤ በደስታ ከራሳችን ልጆች ጋር ተሰብስበን ትልቅ ደስታ ውስጥ ስለነበርን እስከ ሁለት ሰዓት መዝሙር ዘመርን፤ ዘለልን።

በቃ የምንለብሰውን መምረጥ፣ ሻወር መግባት፣ በጣም በደስታ ብዛት የምናደርገውን አናውቅም ነበር። ወደ አስር ሰዓት ላይ ለብሰን ተዘጋጅተን ጠበቅናቸው። ወደ አስራ አንድ ሰዓት ሁሉም መጥተው ሸኙን። መልካም መንገድ ብለው ተሰናብተውን ወደ መኪና ውስጥ ገባን። ወዴትም ይውሰዱን ወዴትም አናውቅም ነበር። በቃ ዝም ብለን ተጓዝን። ስንጠይቃቸውም ወደ ቱንዱማ፤ መጀመሪያ ወደተያዝንበት ኢሚግሬሽን እንደሚወስዱን ነገሩን። “ለምንድነው?” ብዬ ስጠይቃቸውም “የእናንተ ወረቀት እዚያው ነው ያለው፤ ወደ ዳሬ ሰላም (Dar es Salaam) ያ ወረቀት ከሌለ መውሰድ አንችልም” ብለው ነገሩኝ።

“በቃ አስጨርሰን ብቻ መመለስ ነው። ከዚያም ጉዞ ትጀምራላችሁ” አሉን። ከጠዋቱ አራት ሰዓት፣ በቀን አስር፣ አራተኛው ወር፣ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ፣ ወደ ሶስት ወር ታስረን እና መጀመሪያ ብዙ ስቃይ አይተን ወደ መጣንበት ወደዚያ እስር ቤት በር ደረስን። በቃ ግራ ተጋባን። ማውራት አልቻልኩም፤ በቆምኩበት ቀለጥኩ፤ ሰውነቴ ተሳሰረ፤ በቃ ቀዘቀዝኩ:; “ወይኔ ለምን ተፈጠርኩ?” አልኩኝ። በቃ መፈጠሬን መርገም ጀመርኩ። ከእስር ቤት ሀላፊውም ጋር በጣም ተከራከሩ። የሀገሪቱ ህግ ፍቃድም እያለ ቢሆን ጠፍተው ሊያልቁ ነው ብለው እረስተነው በሄድነው ችግር ውስጥ፣ ርሀብ ውስጥ ለመተኛት፣ ከዚህ በፊት ያሳለፍነው ሶስት ወር እንኳን እንደሶስት ሺህ ዓመት በቆጠርንበት ቦታ አምጥተው፣ በድጋሚ በዚህ ሲኦል ውስጥ አስገቡን። በቃ ችግርን በድጋሚ በፀጋ ተቀበልን።

መጀመሪያ ከዚህ ከኤሌምቦ እስር ቤት [Elembo prison] ስንወጣ ማንም አልነበረም። የኢትዮጵያ ሰዎች ግን ስንመለስ እስር ቤቱን ሞልተው ጠበቁን። አጠቃላይ ከዘጠኝ ወር በኋላ ስንመለስ የኢትዮጵያ ልጆች ሞልተው ጠብቀውናል። በቃ እኔ ያየሁትን ይህን ስቃይ ሁሉ ለማየት ስለገቡ ሰላምም ልላቸው አልፈለግኩም ነበር። በእኛ ሀገራችን ተሰደበች፣ አሰደብናት። “ቦሎቄ እና በቆሎ አጥታችሁ ነው ወይ የመጣችሁት?” ተባልን:: በቃ በጣም አፈርኩ። በዚያች ሰዓት ብሞት ሁሉ ደስ ይለኝ ነበር። ወደ ሀያ ልጆች በእኛ በሰባታችን ላይ ተጨምረው ወደ ሀያ ሰባት ኢትዮጵያዊያን ሆንን። ልጆቹም በዚህ እስር ቤት ወደ አራት ወር እንደቆዩ ነገሩን። በቃ በዚህ ችግር መቃጠል ሆነ። ሃላፊው ጋር በየጠዋቱ እንሄዳለን ግን ምንም አይነት መፍትሄ አይሰጥም። “በቃ ኤምባሲ የመጣ ቀን ትሔዳላችሁ” ብለው ማውራት ብቻ እንጂ ሌላ የሚያውቁት ነገር የለም።

ኤምባሲው እንዴት ሆኖ ይህ ቦታ ይድረስ? እኛ ያለነው በታንዛኒያ መጨረሻ ቦርደር [ድንበር] ላይ ነን፤ ወደ ከተማ ለመድረስ ከዚህ ቦታ ወደ ሶስት ቀን እና ማታ ያስኬዳል። በቃ ተስፋችን ጨለመ። ከዚያ ከሃያ ሰባት ልጆች ፍርድ ያልተቀበሉ አስራ ሶስት ልጆች

ነበሩ። በቃ ወደ ሀገር ቤት የመመለስ ተስፋ ቀርቶ ወደ ስራ፤ ለማስቆፈር ከእስር ቤት ወደ እሩቅ ቦታ አውጥተው መውሰድ ጀመሩ። ሌሊት አስራ አንድ ሰዓት ወስደዋቸው ማታ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ወደ እስር ቤት ይመለሳሉ። በጣም አፈር ለብሰው ነው የሚመለሱት፤ ስንጠይቃቸውም በጣም ከባድ እንደሆነ፣ ከጠዋት እስከ ማታ ማረፍ እንደማይቻል ነገሩን:: በጣም ብዙ እርሻ እንደሚያስቆፍሩ ነገሩን።

ልጆቹ በጣም ከሱ፣ በጣም ታመሙ። ግቢው ውስጥ በየቦታው መውደቅ ጀመሩ። በቃ እራሱን ስቶ የሚወድቅ በዛ፤ ስቃዩንም መቋቋም አቃተን። የዩኒሴፍ (UNICEF) ሰዎች ወደ እዚህ እስር ቤት ሲያመጡን በ24/04/2019 ላይ ትሄዳላችሁ ብለውን ነበር። እኛም በጉጉት ስንጠብቅ ነበር፤ ቀኑም ደረሰ። ልብሳችንን ለብሰን ለመሄድ ተዘጋጀን። ለካ በእኛ ላይ ቀልደውብናል። ወደ ዋና ሀላፊውም ቢሮ ሄደን ስንጠይቀው “ዛሬ አትሄዱም! ምክንያቱም ኤምባሲ አልመጣም፤ በቃ ከዚህ ሌላ መልስ ከእኔ አትጠብቁ” ብለው ከበር አስወጡን። የእነርሱን ቋንቋ ስለምችል አብዛኛውን ጊዜ ልጆች ሲያስቸግሩ፣ ወደ ቢሮም ገብቼ እጠይቃቸዋለሁ። በዚህ ሁኔታ በቃ ተስፋችን ይመጣል፣ ግን ደግሞ መልሰው ይሸኙናል። “ትሔዳላችሁ በቃ ለሚቀጥለው” ይባላል፤ ግን ነፍሳችን ላይ መጫወት ብቻ ነው። ትሄዳላችሁ ተብለን ደግሞ ወደ ስቃይ፣ ወደ መኻታ ክፍል ሲመልሱን የስቃይ ህይወት ብቻ ሆነብን።

በቃ ተስፋ ለቆረጡ ልጆችም ከእለታት አንድ ቀን መጽሐፍ ቅዱስ ይዤ የተለያዩ ቦታ በመሰብሰብ የሆነ ለየት ያለ ነገር አዘጋጀሁኝ። በእንጨት ክርም ሰበሰብኳቸው። ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከአንደኛ ሳሙኤል ምዕራፍ አንድ፥ ቁጥር አንድ እስከ አስራስምንት [ሳሙ 1፥1-18] ላይ ያለውን የሀናን ታሪክ ነገርኳቸው። ተስፋ በቆረጠችው ነገር ላይ ጌታ በተአምራቱ ያደረገውን ሙሉ ታሪክ አነበብኩላቸው። ልጆቹ ተስፋ እንዳላቸው በማሰብ በጣም ተደሰቱ፤ በጣም ተጽናኑ፤ ለእኔም በጣም ደስ አለኝ። ልጆች ሲጨነቁ ስለሚጨንቀኝ አልችልም ነበር። የእስር ቤት ሃላፊውም አልፎ አልፎ ሁሉንም ታሳሪ ሰብስቦ ችግር ይጠይቃል። የታንዛኒያ ልጆችም ችግራቸውን ያወራሉ፤ ወደ ፍርድ ቤት ሳይወሰዱ ከቆዩም ወደ ፍርድ ቤት እንዲሄዱ ያደርጋል። እኔም እጄን አውጥቼ ችግሬን እና የሌሎች የእኛ ልጆችን ችግር ተወክዬ ማውራት ጀመርኩ።

መጀመሪያ በቱንዱማ ድንበር በኢሚግሬሽን ሰራተኞች እንደተያዝን፣ ወደ ፍርድ ቤት ቀርበንም በግማሾቻችን ሳይፈረድ ነፃ መሆናችንን፣ በግማሽ ልጆች ላይ ደግሞ ተፈርዶባቸው ወደ ሌላ እስር ቤት ለስራ እንደተወሰዱ፣ በዚህ እስር ቤት ደግሞ ከፍርድ ነጻ ሆነን በባዶ በመቆየታችን መፍትሄ ሊሰጠን እንደሚገባ በጣም ስሜታዊ ሆኜ ለሀላፊው አስረዳሁ። ሀላፊውም መጀመሪያ ለያዙን፣ ለቱንዱማ ኢሚግሬሽን ሰራተኞች

ችግራችንን እንደሚነግራቸው መፍትሄም እንደሚፈልጉ ነገረን። እኔም ሀሳቡ ይፈጸማል ብዬ ባልጠብቅም በቃ ትቼው ተቀመጥኩ። ነገር ግን ሃላፊው በጣም ጥሩ ስለሆነ የያዙንን ሰዎች በሁለተኛው ቀን አስመጥቶ አገናኘን። ሀሳባችንንም፣ ሁሉንም ችግር፣ እዚህ ያለ ፍርድ ነጻ ሆነን በስቃይ እንዳሳለፍን፣ ሁሉንም በስዋሂሊ አስረድቼ ሳወራላቸው በጣም ተደነቁ። ምክንያቱም መጀመሪያ ሲይዙን ቋንቋ የሚያውቅ አንድም አልነበረም። ስለሆነም በዚህ በቆይታ እንደለመድኩ አውቀው በጣም ተገረሙ።

ወደ ኤምባሲ እንደሚደውሉ፣ የኤምባሲ ሰዎችም ወዳለንበት ቦታ እንደሚመጡ ጥሩ ተስፋ ሰጥተውን ሄዱ። እኛም ብዙም ያወሩትን አልተቀበልንም ነበር። ምክንያቱም ጥሩ ተስፋ ሁሉ ወደ ሀዘን ተቀይሮ ስለተቸገርን ነበር። ዝም ብለን ከመቀመጥ ይሻላል በማለት ወደ ሀላፊው ጋር ሄደን እንጠይቃቸዋለን። እነርሱም ሳይሰለቹ ተመሳሳይ ነገር ሁሌም ያወራሉ።

## ክፍል ሠላሳ

በዕሮብ ቀን፣ ሳምንቱን ሙሉ ስንጠባበቅ የነበረው ቀን፣ ሁላችንም የኤምባሲ ሰዎቹን ለመቀበል ጥሩ ለብሰን፣ ታጥበን ተዘጋጀን። ወደ በርም አቀርቅረን መመልከት ብቻ ሆነ። ይመጣሉ የተባሉት የኤምባሲ ሰዎች ቀሩ። በቃ ጭንቅላታችንን በጨርቅ አስረን፣ ሳናገኛቸው ወደ ዶርም መግቢያ ሰዓት ዘጠኝ ሰዓት ደረሰ። ልጆቹ ሁሉም "የእኛ መጨረሻችን በቃ እዚያው ነው" ብለው በጣም ተበሳጩ። ከመካከላችንም ሁለት ልጆች በጣም ተናደው ስለነበር፣ ታንዛኒያውያኑ ደብቀው ወደ እስር ቤት የሚያስገቡትን አደገኛ አደንዛዥ እፅ ወሰዱ። በቃ እራሳቸውን ሳቱ። ለእኛ ትልቅ የህይወት ፈተና ሆነብን። በፊት ስፀልይ የነበረው ጠቅሞኛል። እኔም ሁሉንም ሰብስቤ "ለእናንተ የተናገረው ማነው?" አልኳቸው። "ሃላፊው" አሉኝ። "ሃላፊ ምንድነው?" አልኳቸው። እነርሱም "ሰው" አሉኝ። እኔም "አይዞአችሁ፤ ሰው ብሏል፤ ነገርግን እኛን የፈጠረንን ፈጣሪ ብቻ አሁንም ተስፋ እናድርግ፤ ልጆች ተስፋ አንቁረጥ፤ እንፀልይ" አልኳቸው። በቃ ውስጤም እየተቃጠለ እኔም ቻልኩት። በቃ እኛን ሊያጽናናን የሚችል ነገር ጠፋ። መራር ሐዘን ሆነብን። በቃ ይህን መራር ህይወት በግድ እንኖራለን። በቃ ከእንግዲህ ምንም ነገር ባወራ፣ ብናገርም ሁላችንም ተስፋ ቆርጠናል። በቃ የእኛ መጨረሻ እዚያው መሆኑን እራሳችንን ማሳመን ጀመርን። "ጌታ ሆይ ይህ ሁሉ ስቃይ ለምን? ለምን ሆነ?" ብዬ አለቅሳለሁ። ምንስ ማድረግ እችላለሁ።

በኋላ አምባሳደር የሚባሉ ሰው አናገሩን። ለጸጉራችን ምላጭ እንዳጣን፣ አርብ ቀን ሲደርስ በምክንያት እንደሚደበድቡን፣ ልብስ አጥተን በባዶ እንደምናሳልፍ፣ ለመኝታ ፍራሽ እንኳን እንደማናገኝ፣ ደግሞም በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ አንድ ጊዜ

ብቻ እንደምንበላ፤ ለዚያውም ገንፎ እና የቦሎቄ ሾርባ እንደምንበላ ሁሉንም ነገር ነገርኳቸው። እርሳቸውም እንዲህ አሉን “አትጨነቁ፣ በጨለማ ነበራችሁ፣ አሁን ግን ብርሃን አግኝታችኋል። በገዛ እጃችሁ ብር ከፍላችሁ ሲኦል ገብታችሁ ነበር። ነገር ግን ወደ ሀገራችሁ እንደገባችሁ ቁጠሩት” ብለው አሉን። በጣም ተደሰትን። በጣም በጣም ደስተኞች ሆንን። አምባሳደር ደግሞ “ለመሆኑ የት ሀገር ተወላጅ ናችሁ? ትውልዳችሁ የት ነው?” ብለው ጠየቁን። ከሀድያ ብዙ ልጆች ነን፣ ከከምባታ እና ከሀላባ ደግሞ ሶስት ልጆች ብቻ ነበሩ።

እርሳቸውም “ከሀድያ ዞን ምን አጥታችሁ ነው የምትሰደዱት? በጤና ክትፎ ከምትበሉበት ገንፎ ለመብላት ትሰደዳላችሁ? ምን አጥታችሁ ነው? ሀገራችሁ ምርት የሚሰጥ ነው፤ እንዴት እንዲህ አደረጋችሁ?” ብለው በጣም መከሩን። ለኦሮሞ ልጆችም ብዙ ምክር ሰጡ፤ ለሀላባ ልጆችም ብዙ ሰዓት አወሩ። “በቃ በጣም አዝናለሁኝ፤ በእራሳችሁ እጅ ሲኦል እንዴት ትመጣላችሁ?” ብለው በጣም አዘኑ። “ለትራንስፖርት የሚሆን የገቢ ማሰባሰቢያ እያደረግን ነው። ብር ቶሎ ከተገኘ ትሄዳላችሁ፤ እናንተ ብቻ አይደላችሁም። ወደ 1,600 የኢትዮጵያ ልጆች ከዚያው የሀድያና የከምባታ ልጆች ናቸው በብዛት ያሉት” ብለው እስከምንመለስ ብንቆይ ሁለት ወር ከዚያም ብቻ ሊያልፍ እንደሚችል ነገሩን:: “በጀት የለም፣ በልመና ነው እየሰራን ያለነው” አሉን። ፎቶም ተራ በተራ አንስተውን ጊዜያዊ ፖስፖርት ተሰርቶ ለፕሌን አዘጋጁልን:: ለፀጉራችንም ምላጭ መግዣ ብለው ወደ አርባ ሺህ ሺልንግ ሰጥተው ሄዱ። አምባሳደር ብዙ ምክር ነው የሰጡን፤ በቃ ለእኔ ምክራቸው በጣም ተመቸኝ። ከብዙ ጭንቅ እና ስቃይ በኋላ ትልቅ ተስፋ ሰጥተውን ሄዱ።

## ክፍል ሠላሳ አንድ

በቃ ፈጣሪ ጩኸታችንን ሰማን። መቼ እንደምንሄድ ባናውቅም ብቻ የእኛ መረጃ እንኳን ወደ ሀገር ቤት ገባ ብለን በጣም ተደሰትን። ዛሬ ቀን በነጮች ሐምሌ አስራ አንድ ቀን፣ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ ዓመተ ምህረት ነው። በፊት ከኤሌጄ እስር ቤት [Eleje prison] ለስራ ከእኛ ተወስደው፣ ማለትም ኤሌምቦ እስር ቤት [Elembo prison] ፍርድ በተፈረዱ ልጆች ላይ፣ ልብሳቸውን አስቀይረው፣ የእስር ቤት ልብስ አስለብሰው፣ ስራ ለማሰራት እና እርሻ ለማስቆፈር ከእኛ ነጥለው ወደ አስራ ሶስት ልጆችን ወስደው ነበር። ከእነርሱ መካከልም አቶ የሚባሉ ሽማግሌ ነበሩ። እድሜያቸውም በግምት ወደ 55-60 ይሆናሉ። እርሳቸውም ከእኛ ተለይተው ወደዚያ ወደ ሌላ እስር ቤት ተወስደው ነበር። በዚህ በተወሰዱበት እስር ቤት የነበረውን ችግር አንድ በአንድ ለእኛም አጫወቱን:: በጣም ብዙ ችግር እንዳለፉ ነገሩን። በጣም ይከብዳል:: በጆሮ እንኳን ለመስማት ይከብዳል።

ልክ ከሌሊቱ 11 ሰዓት ያስነሱና ወደ እርሻ ቦታ ወስደው ያስቆፍራሉ። በዚህ በእርሻ ማሳ ላይ ደከመኝ ልረፍ የሚል ቃል በፍጹም የማይታሰብ ነው:: እያስቆፈሩ እንኳን ከመስመር ወደ ኋላ ብትቀር ልግምተኛ ነህ ብለው በቱቦ ውስጥ ሽቦ ጨምረው በዚያ በጣም ይመታሉ። ያንን ፈርቶ በፍጥነት እየቆፈሩ ወደ ፊት ሲቀድሙ ማምለጥ ፈልገህ ነው ፊት ፊት የምትሄደው ብለው ግምባራቸውን በዚያ በከባዱ ዱላ ይመታሉ:: በዚህ ስቃይ፣ ይህን ድካም፣ እንግልት፣ መመታት አሳልፈው ወደ እስር ቤት ሲመለሱ ምግብ አያገኙም። በዚያው በአቧራ፣ በዚያው በአፈር ያስተኟቸዋል። ይህም ስቃይ ሳያንሳቸው ቀን የተሰራውን የበቆሎ ገንፎ እና በፍሬ የሚቆጠር ቦሎቄ በኩባያ ላይ ጨምረው በረዶ የሆነውን ይሰጡዋቸዋል። የዚህ ምግብ ስሙ ኡጋሊ ይባላል። ገንፎ ማለት ነው። ቦሎቄውን ደግሞ ማረጌ ይላሉ። ይህን ያልተመጣጠነ ምግብ እየበሉ፣ በዚያ ላይ ደግሞ በ24 ሰዓት አንዴ ብቻ ምግብ እየሰጡ ከባድ ስራ ያሰራሉ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ በጣም ታመው፣ በጣም በከባድ በሽታ ብዙ ልጆች ወደቁ:: ይህን ሁሉ በዚህ በሌለንበት ቦታ ላይ በኤምባሲ ሰዎች ፊት አንድ ላይ ለማስነሳት ነበር የጣሩት።

እነዚህ የተፈረደባቸው ልጆች ከኤሌጂ ለፎቶ ከመጡ በኋላም ብዙም ከእኛ ጋር እንዲቆዩ አላደረጉም። ለስራ ብለው ዳግም ወደ ሶንጌ ማረሚያ [Songwe Prison] ወሰዷቸው። እዚያም ደግሞ ሰፊ እርሻ ስላለ ወደዚያ ወሰዷቸው። በጣም ያሳዝናሉ። ስራ ከጠዋቱ 11 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12፡30 ሰዓት ድረስ እያሳረሱ አንድ አንዴ ውሃ ሰጥተው ገላቸውን ያሳጥባሉ። ሲፈልጉም ይከለክሏቸውና በዚያው ያስተኛሉ። በሰው ልጅ የማይሰራ ግፍ ይሰራሉ። ትዕዛዛቸውን ከማድረግ ውጭ ምንም አማራጭ የለም። በቃ በዚህ ሁኔታ ውስጥ መቆየታችን ግድ ሆነብን። እነዚህን ልጆች ከኛ ሲነጠሉ ለስራ ብለው ሌላ ቦታ ሲወስዷቸው በቃ በጣም ተሰማን። በቦታው ከፍርድ ለይተውን የተወሰንን ልጆች ብቻ ቀረን። ሰውን ተላምዶ፣ ችግር ተካፍሎ ሲሄዱ በቃ በጣም ነበር የሚጎዳን።

በዚህ በሰው ሀገር የስደት ህይወት ይሄ ሀዲያ፣ ይሄ ከምባታ የሚል ነገር በመካከላችን አንድም ቀን አስበን አናውቅም። ሁላችንም እንደአንድ አባት ልጆች ነበር የምንተያየው፤ የምናሳልፈው። በዚህ እስር ቤት ውስጥ በየጊዜው ብዙ አዳዲስ ኢትዮጵያዊያን በፖሊሶች ተይዘው ወደ እስር ቤት ይመጣሉ። በጫካ፣ በባህር፣ እና በበረሀ በጣም ተጎድተው፣ ተርበው፣ ልብሳቸው አልቆ ወደ እስር ቤት ይመጣሉ። በዚህ ጊዜ ከውስጥ ሆነን አቀባበል እናደርጋለን፤ እናድናለን። ያለንን ልብስ አካፍለን እናለብሳቸዋለን። በዚህ በጣም ተጎድተው በሚመጡ ልጆች ምክንያት በእስር ቤት ውስጥ በታንዛኒያውያን እንሰደባለን። በቃ በጣም ነበር የሚሰድቡን፤ “በሀገራችሁ ላይ ምግብ የሚባል ነገር የለም፤ በሀገራችሁ ላይ በቆሎ እና ቦሎቄ በቅሎ አያውቅም” ይሉናል። በዚህ የተነሳ በጣም ያሳፍሩናል። በቃ ለማስረዳት ብንሞክር እንኳን አይሰሙንም ይስቁብናል። በጣም ነበር የምናፍረው፤ የምንሳቀቀው።።

በዚህ እስር ቤት ውስጥ ደስ የሚል ነገር ቢሆን የኛ ልጅ ኢትዮጵያዊ ከተባለ አንዱ ሲገረፍ ሁላችንም እናለቅሳለን። በተለይ በርሃብ ጊዜ ምንም ጥቂት ነገር ቢኖረን ተካፍለን፣ ሽታም ብቻ ቢሆን እንኳን ተካፍለን እንቀምሳለን። እኔ በዚህ መንገድ፣ በዚህ በስደት ህይወት ተጎድቼ መጥፎ ነገር በህይወቴ ቢደርስብኝም ብዙ ነገር ተምሬአለሁ። ከሰው ጋር መተኛት የማልወደው ሰው፣ የሰውን እግር ተሸክሜ መተኛትን ለመድኩ። መጽሐፍ ቅዱስ አንብቤ የማላውቅ ሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ውዬ ማደርን ተለማመድኩ። ስመከር የማልሰማው ሰው መምከር አሰብኩ። በጣም ትህትና ያለው ሰው አድርጎኛል። ችግር ማለት በጣም አስተማሪ ነው። በውስጤ ላይ ድሮ የነበረው ጭካኔ ከውስጤ ጠፋ:: ሰው ናፍቆኝ የማላውቅ ሰው፣ ሰው ናፍቆኝ እምባዬን አፈሳለሁ።

በዚህ በስደት ህይወት ብዙ ነገር አየሁኝ። ግን ቢያስለቅስም፣ ተስፋ ቢያጨልምም፣ ተስፋ ቢያስቆርጥም ብዙ ያስተምራል። እኔ በበኩሌ ተምሬአለሁ። ስቃይ ይመራል፣ ተስፋ ያስቆርጣል፣ ባዶነት ይሰማል። መልሶም ተስፋ ይሰጣል። ብቻ እሩሩህ ልብ እንዲኖረኝ አድርጎኛል። በዚህ በእስር ቤት ውስጥ ለስራ ሳይወሰዱ በፊት ሁላችም አንድ ቦታ ተቀምጠን እረጅም ሰዓት እንፀልያለን። ከእኛ ልጅ ውስጥ ማንም በምንም ሀይማኖት ይኑር፣ ተለይቶ አይጸልይም። ሁላችንም በህብረት እንጸልያለን። ከጸሎት መልስም ሁሉም የየራሱን አመጣጥ ያወራል። እስከ እስር ቤት ያለውን መንገድ ላይ የደረሰበትን ችግር ምንም ሳይዋሽ ያወራል። ለጆሮ የሚከብድ ችግር የደረሱባቸው ልጆችም ሁሉንም ችግር ያወራሉ። ሁላችንም በጫካ የመጣን፣ በውሃ መሃል የመጣን ሁሉም የየራሱን ችግር ያጫውታል። በቃ በጣም ችግር እንደደረሰ ያወራሉ። በጫካ ላይ ወደ ሶስት ወር እንዳሳለፉ አንድ ልጅ አጫወተኝ። በዚያ በጫካ ላይ ወደ 145 ልጆች ቆይተዋል። በዚያ ጫካ ላይ ማንም ምንም ሊደርስለት አይችልም፣ ምክንያቱም ጫካው በባህር የተከበበ ደሴት ነው። በዚህ ቦታ ብትጮህ፣ ምንም ብታደርግ ማንም ሊደርስልህ አይችልም። በዚህ ቦታ ደላሎቹ ስደተኞቹን አስቀምጠው ለራሳቸው ወደ ከተማ ወጣ ብለው ይቀመጣሉ። በዚህ ቦታ ለ145 ልጆች የበቆሎ ዱቄት ብቻ በሁለት ቀን አንዴ 15 ኪሎ፣ 20 ኪሎ ያመጣሉ። በዚህ ቦታ ደግም በአራቱም ማዕዘን ባህር ነው ያጠረው፤ የትም ማምለጥ አትችልም። ከዚህ ከባህር ውሃ ወስደው ምግብ ይሰራሉ። ውሃው ደግሞ በጣም ጨዋማ ነው። በዛ ላይ ደግሞ በጣም ጥቂት ዱቄት ነው የሚሠጠው:: በቃ በዚህ ሁኔታ የሀላባ ልጆች መቋቋም አቃታቸው እና እራሳቸውን መሳት ጀመሩ። ሶስት ልጆች ናቸው፣ በዚያ በርሃብ ምክንያት፣ በዚያ በድብድብ የሚያገኙት ገንፎ ከጉሮሮ የማይወርድ በጣም ትንሽ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ በቃ እራሳቸውን ስተው ወድቀው፤ በተለይ ሁለት ልጆች ሆዳቸውን ታመው በጣም ማስቀመጥ ጀመራቸው። እራሳቸውን ስተው ስለነበር በለበሱት ልብስ መሸናት ጀመሩ። ከዚያም ከዚህ ከጫካ ለመውጣት ደላላው መርከብ ይዞ መጥቶ እነዚያን የሀላባ ልጆች እዚያው ደሴቱ ላይ ጥሎ ወደ




142 ልጆችን ወደ መርከብ ጫናቸው። በመርከብ ላይ ሲወጡ እስከ ባህሩ መሀል ድረስ በእግራቸው ወሰዷቸው። ከዚያም አናታቸውን በዱላ እየቀጠቀጡ ወደ መርከቡ ያስገባሉ።

በዚህ መሃል የሰፈሬ ልጅ ነበር። በጣም በሀይለኛው ጭንቅላቱን ሲመታ መቋቋም አልቻለም ነበር። በቃ እጅ ሰጠ፤ እዚያው በባህር ውስጥ ሰምጦ ቀረ። ሲነግሩኝ በጣም አለቀስኩ፤ በጣም ተረበሽኩ። ምንም ማድረግ ስለማልችል ለእኔ የሰፈሬ ልጅ መሆኑን ማንም አያውቅም ነበር። ስሙን ሲጠሩት ግን እኔ እያወቅኩም ቢሆን ቻልኩት። በጣም አለቀስኩ። ምንም ነገር ማድረግ ስለማልችል አፌን ይዤ ዝም አልኩ። ልጁም የካምፓስ ትምህርቱን ትቶ ነበር ይህን አስቀያሚ ጉዞ የጀመረው። በቃ በዚህ በባእድ ሀገር ህይወቱን አጣ። በመርከብ ላይ ወደ መቶ አርባ ሁለት ልጆች ናቸው የወጡት። ከዚህ ከሰፈሬ ልጅ ሌላ ደግሞ ከጎምቦራ ወረዳ የሔደ የሚባል እርሱም እዚያው በባህር ውስጥ ቀረ። በዚህ በመርከብሶስት ቀን እና ማታ ጉዞ ላይ ሁለት ልጆች ህይወታቸውን አጡ። ለህንድ ውቅያኖስ [Indian Ocean] ስጋቸውን ገበሩ። በቃ ምርር አለኝ። የምሰማው ለጆሮ የሚከብድ ነገር ብቻ ነው። የዚህ ልጅ ትዝታው ሁሌ ይረብሸኛል። የአንዳንዶቹ እስከ እስር ቤት ያለው አመጣጥ ከዚህ የበለጠ ነው።

እድሜያቸው ከአስራ ስምንት በታች የሆኑትን ልጆች አስገድደው ይደፍራሉ። በጣም ጨካኞች ናቸው። ይህንን ነገር እንኳን ምንም ልል አልችልም። ምክንያቱም በዚሁ በእስር ቤት ውስጥ በጣም ቀይ ስለነበርኩ ይህ ጥያቄ ለእኔም ደርሶኝ ነበር። ወደ እስር ቤት ሀ ብዬ የገባሁኝ ሰሞን በጣም እንክብካቤ አበዙብኝ፤ እርስ በራሳቸው በእኛ ልጆች ሲመራረጡ ነበር። በተለይ ይህ ጥያቄ በእኔ ላይ በረታ። ጭራሽ ግቢ ውስጥ አረብ ትመስላለህ ያንተ ስም መረቡ ነው ብለው ስም ሰየሙልኝ። ከእነዚህ ከታንዛኒያውያን ታሳሪዎች መካከል በነፍስ ግድያ ተጠርጥሮ ፍርድ ሳይፈረድበት ወደ አስር አመት በክርክር ፍርድ ቤት የሚመላለስ ልጅ ነበር። ይህም ልጅ ከወር እስከ ወር የታሸገ የሀይላንድ ሚሪንዳ

በፖሊሶች አስመጥቶ ይሰጠናል። እኔ ግን ጥሩ ሰው ነው ብዬ በጣም ወደድኩት፤ ለካ የእርሱ ልብ ሌላ ጋር ነበር።

ከትንሽ ቆይታ በኋላ በእስር ቤት ግቢ ውስጥ ብቻዬን ቁጭ ብዬ ነበር። ሊያናግረኝ ጀመረ፤ ከዚያም በዚህ በእስር ቤት በጣም እንደቆየ ነገረኝ። እኔም አይዞህ እለዋለሁ። እርሱም መልሶ "በቃ ማታ እኔ ጋር ትተኛለህ" ብሎ አወራኝ። በጣም ደነገጥኩ። በቃ መልስ እንኳን መስጠት አልቻልኩም ነበር። እዚያው ትቼው ወደ እኛ ልጆች ወዳሉበት ተቀላቀልኩ። ከእኛ ልጆች መካከልም የሚባል በጣም ብዙ ነገር የሚያማክረኝ ልጅ ነበር። ለእርሱም ታንዛኒያውያዊው ያወራውን ሁሉንም ነገር ነገርኩት፤ እርሱም "አትፍራ!" ብሎ አበረታታኝ። ከዚያም ወደ ዶርማችን ልክ ዘጠኝ ሰዓት ሲደርስ ተሰልፈን ወደ መኝታ ክፍል እንገባለን። ይህም ልጅ ቤት ከገባን በኋላ ደግሞ አወራኝ። እኔም እያፈርኩት "አልመጣም! እዚያው ከእኛ ልጆች ጋር ይሻለኛል" ብዬ ነገርኩት። ያን ማታም ሔዶ ዝም ብሎ ለራሱ ተኛ። በማግስቱም "ለምን መምጣት እምቢ አልክ?" ብሎ ጠየቀኝ። እኔም "አይ እኔ እንደዚህ አይነት ጥያቄ አልወድም ክርስትያን ነኝ" አልኩት። ደግሞም ልመክረውም ለመንኩት "ሶዶማዊነትን ፈጣሪ አይወድም፣ ወንድሜ ነህ ይቅርብህ" ብዬ መከርኩት። ብዙ ጊዜም ለመንኩት፤ በፍጹም እንደማላደርግም አስረግጬ ነገርኩት። ግን ሊሰማኝ አልቻለም። በቃ በዚያው ጉዳይ በዚህ አንድ ልጅ ብቻም ሳይሆን በብዙ ሰው ተቸገርኩ። መወለዴን እስከምረግም ድረስ ደረስኩ። በጣም ተጨነቅኩ። በኋላ ላይ በቃ ለፖሊስ እነግራለሁ ብዬ፣ ልጁንም ሆነ እንደዚህ አይነት ነገር የሚጠይቁትን ፖሊሶች ከሰሙ አስረዋቸው በጣም ይመቱአቸዋል። ለዚህም በጣም ይፈራሉ።

እንደዚያው የሚባል በጣም ቆንጆ ልጅ ነበር፤ በጣም ያስቸግሩት ነበር። ሁላችንም ተሰብስበን እነርሱ የሚሰጡትን ምግብ ላለመብላት ተስማማን። እኔንም ሲያስቸግረኝ የነበረው ልጅ በጣም ተኮሳትሬ "እዚያው እስር ቤት በቆርቆሮ አርድሀለሁ! እገድልሀለሁ" ብዬ አስፈራራሁት። ከዚያም ተወኝ። መጀመርያ ፈርተናቸው ነበር። ከዚያም ቋንቋቸውን ከተለማመድን በኋላ እኩል ማዋራት፣ መደብደብ ጀመርን። ለፖሊሶችም ችግራችንን ለማስረዳት፣ ለመንገር ቻልን። መጀመርያ አካባቢ ምንም ስለማናውቅ በጣም ሲያስፈራሩን ነበር። በኋላ ላይ ቋንቋውን ተለማምደን ችግራችንን በራሳችን ማውራት ጀመርን። ከእንደዚህ አይነት ችግር መከላከል ቻልን። በቃ በጣም ደስ አለን።

ነገር ግን በጫካ፣ በባህር ሲኖሩ ከእስር በፊት በጣም ችግር ነበር። ወደዚህ እስር ቤት ከጫካ ስንገባ ለማናችንም ልብስ አልነበረንም። ምክንያቱም በመንገድ ላይ ልብስ፣ ጫማ እና በእኛ ላይ የሚያምር ነገር በሙሉ ቀይረው፣ የእራሳቸውን የደከመውን ጫማ እና ሱሪ ነው ያለበሱን። ግን በዚህ በእስር ቤት ከቆየን በኋላ ፈጣሪ ብዙ ነገር አድርጎልናል።

በፈጣሪ እርዳታ ሁላችንም ልብስ አግኝተናል። በእስር ቤት ከእነርሱ ጋር እኩል ማውራት ችለናል። ፈጣሪ ይመስገን፤ በትንሹም ቢሆን ከበፊቱ ይሻላል።

## ክፍል ሠላሳ ሁለት

ሁሌም በአዕምሮዬ የማመላልሰው ነገር አለ። “ምን አለ በሀገሬ ሰርቼ መለወጥ ስችል ይህን አስቀያሚ ነገር መረጥኩ? ይህን ለምን አደረግሁ?” እላለሁኝ። ይህ ወደ ደቡብ አፍሪካ የመሄድ ሀሳብ በውስጤ በፍጹም አልነበረም። ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመሄድ ወይንም ለመሰደድ ሀሳቡ የመጣው ከወንድሞቼ ነበር። ከዚህ በፊት እንደጠቀስኩት አራት ወንድሞች እና ሁለት እህቶች አሉኝ፤ በአጠቃላይ ሰባት ነን። በእናቴ በኩል አራት ወንድሞችና አንድ እህት አለች፤ እናቴ ከሞተች በኋላ አባቴ ሌላ ሚስት አግብቶ ነበር። ከአዲሷ ሚስቱ አንድ ልጅ ብቻ ወልዷል፤ ሴት ልጅ ነች። የቤቱ መጨረሻ ልጅ [የእናቴ የመጨረሻ ልጅ] እኔ ነኝ። ከእኔ በኋላ እናቴ ሌላ ልጅ አልወለደችም። የቤታችን የመጀመሪያው ልጅ ኑሮውን በአዲስ አበባ ነው ያደረገው። ስራውም የኤሌክትሪክ እና የብረታ ብረት ስራ ነው። ስሙ ይባላል።

ከ ቀጥሎ ያለው በሆሳዕና ባጃጅ ከሚሰራበት ትቶ፣ በ2007 ዓመተ ምህረት በስደት ወደ ደቡብ አፍሪካ ገባ። አሁን የሱቅ ውስጥ ስራ በመስራት በደቡብ አፍሪካ ይኖራል። ስሙም ይባላል። ከእርሱ ቀጥሎ ያለው ደግሞ በ2001 ዓመተ ምህረት ከቤት ወጥቶ ወደ 2002 ዓመተ ምህረት አካባቢ ወደ ደቡብ አፍሪካ ገብቷል። በጣም ችግር አይቶ ነበር ወደ ደቡብ አፍሪካ የገባው። ዛሬ ላይ በደቡብ አፍሪካ ኑሮውን አድርጎ ይኖራል፤ ስሙም ይባላል። ከ ቀጥሎ ግን ያለው የባንክ ሠራተኛ ነው፤ ስሙም ይባላል። ለትምህርት በጣም ቦታ ይሰጣል፤ አሁን በሆሳዕና ከተማ ባንክ ውስጥ ምክትል ስራ አስኪያጅ ነው። ከእርሱ ቀጣይዋ ሴት ልጅ ነች፤ ስሟም ይባላል። በጣም ታታሪ ሴት ነች፤ በሆሳዕና ኮሌጆች ውስጥ ሰልጥና፣ በዲፕሎማ ተመርቃ፣ በመዋዕለ ህጻናት ትምህርት ቤት አስተማሪ ነች። ትንሿ እህቴ ገና ልጅ ነች፤ ታደሰ ይባላል። እህትነትዋ በአባቴ በኩል ብቻ ነው፤ ግን ምንም ይሁን ምንም በጣም እንዋደዳለን።

በሁለት ሺህ ሰባት ላይ የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ፤ እናቴን በማጣቴ ምክንያት ከእኔ በላይ ያሉ ወንድሞቼ በጣም ነበር የሚንከባከቡኝ። በክፍል ትምህርቴም ጎበዝ ነኝ። ሆኖም ግን ታላላቆቼ በጣም ተስፋ ይሰጡኝ ነበር። “ወደ እኛ ትመጣለህ፤ እዚያ ብቻህን አትሆንም” እያሉኝ በጣም ተስፋ ይሰጡኝ ነበር። በቃ በዚህ ንግግራቸው ቀስ በቀስ ውስጤ ሊሰረቅ ቻለ። እኔን ለማጽናናት ብለው ሁልጊዜም ቃል ይገቡልኝ ነበር። ወደ ደቡብ አፍሪካ ትምህርትህን ከጨረስክ እንወስድሃለን ብለው ያባብሉኝ ነበር። በዚህም

ሀሳባቸውን ሳላውቅም ቢሆን በድፍረት እሺ እላቸው ነበር። ግን እንደዚህ የሚያባብሉኝ ብቻዬን ስለነበርኩ ነው። ግን ቀስ በቀስ የሚያወሩት ነገር በልቤ ውስጥ መቅረት ጀመረ። ከስምንተኛ ክፍል በኋላ ትምህርቴ ላይ ትኩረት እያሳነስኩ መጣሁ፤ ለማባበል ሲሉ የጀመሩት በፊት እኔ አልፈልግም ነበር፤ በኋላ በቃ ትምህርቴን ሳልጨርስም ለመሄድ በጣም ጓጓሁኝ።

በቃ በትምህርቴም መቀለድ ጀመርኩኝ። ወንድሜ ሁሌም "እንደምንም አስረኛ ክፍል ጨርሰህ ትመጣለህ" እያለ ያባብለኝ ነበር። ከእኔ የሚጠበቀው አስረኛ ክፍል መጨረስ ብቻ ሆኖ ይታየኝ ጀመር። በቃ ትምህርቴን እስከ አስረኛ ክፍል ተምሬ ከጨረስኩም በኋላ እራሴን በጣም ለጉዞ ማዘጋጀት ጀመርኩኝ። ወንድሞቼንም በጣም ማስቸገር ጀመርኩኝ። ወንድሜ ለበረራ ስድስት ወር ብቻ ጠብቅ አለኝ። ግን ልቤ ስለተነሳ መጠበቅ አልቻልኩም። በስደት፣ በመኪና መጓጓዣ እና በጫካ ይሻለኛል፣ አሁኑኑ ካልሄድኩ ብዬው ጉዞዬን ጀመርኩ። ግን ቸኮልኩ፤ ለዚህም ለችግር ለስቃይ ለእንግልትና ለመታሰር በቃሁ። በህይወቴ እያለሁ በእራሴ እጅ ጉድጓዴን ቆፈርኩ። ይህን መንገድ ያሰብኩባት ቀን፣ ያቺ ቀን የተረገመች ትሁን! ትሁን! ትሁን እላለሁ።

በዚህ ቦታ በእኔ ህይወት ብቻ ሳይሆን በወንድሞቼ ላይ፣ በሀገሬ ልጆች ላይ የሚደረገው በደል በጣም ለማመን ይከብዳል። ዛሬ ላይ በዚህ ቦታ ላይ ሆኖ የማይጸጸት ማንም የለም። ከሰው የተነገረውን አልሰማንም። ስደት መጥፎ ነው ሲሉን የደረሰበት ሰው ሲመክረን አልሰማንም። አሻፈረን ብለን ግን እኛም ቁጭ አልን። ግን የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ሀገራችንን እንደሲኦል የቆጠርንበትን ያንን ሰሞን ሳስበው፣ ዛሬ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ሳየው፣ በጣም በጣም ይገርመኛል። ለካ ሀገራችን ኢትዮጵያችን ውብ ሀገር ናት። እንደፈለግን የምንኖርባት የምንከብርባት ለካ ሀገራችን ናት። ኢትዮጵያ እናታችን ለዘላለም ትኑር።

በቀን ሁለት፣ አንደኛው ወር፣ ሁለት ሺህ አስራ ሁለት ዓመተ ምህረት ሁለት አትዮጵያውያን እኛ ወዳለንበት እስር ቤት ተጨመሩ። በቃ በየጊዜው አዳዲስ ኢትዮጵያውያን ተይዘው በእኛ ላይ ይመጣሉ፤ በጣም ይከፋል። እነዚህም ልጆች ለአራት ወር ያህል በጫካ ሲጓዙ እንደነበሩ ነገሩን፤ በጣም ብዙ ችግር እንደደረሰባቸው ነገሩን። "በቃ ይህ እስር ቤት ባንደርስ ሞተን ነበር፤ እንኳንም ታሰርን" ብለው ተደሰቱ። ደላላው ጫካ ላይ ጥሏቸው እንደጠፋ ነገሩን። በጣም ያሳዝናሉ፤ በጣም ከስተዋል። ልብሳቸው ከመቆሸሽ አልፎ ገምቷል። በባዶ እግር ነበር ወደዚህ የመጡት። በቃ ምንም ማድረግ አልቻልንም ነበር። ያለውን ቅያሪያችንን አካፍለን አለበስናቸው።

በነዚህም በአዳዲስ በኢትዮጵያ ታሳሪዎች ምክንያት በእስር ቤት ውስጥ በታንዛኒያውያን ብዙ እንሰደባለን። "ርሃብተኞች! በሀገራችሁ በቆሎ አይበቅልም፤ ኢትዮጵያ ላይ ምግብ የለም" ብለው ይሳደባሉ:: አንድ ቀን አንዱ በክፉኛ መሳደብ ጀመረ፤ ስሙም ይባላል። "ዮኒ" ብሎ ጠርቶኝ "በጣም ወፈርክ እኮ! ወደዚህ እስር ቤት ስትገባ በጣም ከስተህ፣ እሬሳ መስለህ ነው የመጣኸው፤ ዛሬ ላይ ግን እድሜ ለታንዛኒያ ወፈርክ" አለኝ:: አይኖቼ ደም ለበሱ፤ እምባ እያነቀኝም ስለ ሀገሬ ስለ ኢትዮጵያ ላስረዳ ሞከርኩ። ግን ሊሰማኝ አልቻለም። በቃ በጣም ስለተናደድኩ በጣም መትቼው ዘረርኩት። ጭራሽ እራሱን ስቶ ወደቀ፤ ለተወሰነ ሰዓትም አልተነሳም ነበር። በኋላ ላይ በጥበቃዎች ብዙ ድብደባ እና ብዙ እንግልት ደረሰብኝ። በቃ አልቻልኩም ነበር። ወደዚህ ወደ እስር ቤት ከገባን ወደ ሁለት አመት እየሆነ መጣ። ግን ወደዚህ እስር ቤት ከገባን በኋላ በገባን በሳምንቱ ነበር ወደ ሀገራችሁ ትሄዳላችሁ ማለት የጀመሩት። ግን ዛሬ ላይም እዚያው እስር ቤት ውስጥ ነን።

ኤምቢያ ከተማ (Mbeya City) ባለው ሩዋንዳ ማረሚያ ቤት [Rwanda Prison] የእኛ ብዙ ልጆች እንዳሉ የታንዛኒያውያን ታሳሪዎች ነግረውን ነበር። አንዴም እኛ ካለንበት ወደዚህ እስር ቤት ደብዳቤ ለእኛ ልጆች ልኬላቸው ነበር። ስንት ልጆች እንዳሉ፣ አዲስ ነገር መኖሩን እንዲነግሩኝ ጽፌላቸው ነበር። እነርሱም መልሰውልን በቀን ሀያ፣ አስረኛው ወር፣ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ ላይ ቀኑም ሰኞ ቀን በሩዋንዳ ማረሚያ ቤት ካሉ ከኢትዮጵያ እስረኞች እጅ ደብዳቤ መጣልን። ደብዳቤውንም በታንዛኒያ ልጆች አማካኝነት ተቀበልን። ደብዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር "ሁላችሁም የኢትዮጵያ ልጆች፣ በሰላም አላችሁ? እኛ እዚህ ያለነው የኢትዮጵያ አንድ መቶ አርባ አምስት ልጆች ሁላችንም ሰላም ነን። እኛ ጋር አዲስ ነገር ቢኖር ከሶስት ወር በፊት የኢትዮጵያ ኤምባሲ ደርሶ ፎቶ አንስቶን ሄዷል። ነገር ግን ከመቶ አርባ አምስት ልጆች ውስጥ መቶ አርባ ሶስታችን አምስት ዓመት ጨርሰን፣ ስራ ከመስራት ተርፈናል። ሌሎች ጓደኞቻችን በሶንጌ እስር ቤት (Songwe Prison) በከባድ ስራ ላይ ይገኛሉ። በእኛ መካከል ፍርድ ያልጨረሱ ሁለት ልጆች ብቻ ናቸው። ሌሎች ብዙ ልጆችም ወደ ኤሌጄ እስር ቤት [Elege Prison] ለስራ ተወስደዋል"። ሌላ እስር ቤትም ብዙ ልጆች አሉ ብለው ደብዳቤ ላኩልን። ለልጆችም ሳነብላቸው በጣም አዘኑ፤ ይበልጥ ከበፊቱም ተስፋ ቆረጡ።

አዝነን ልባችን ቆስሎ ሳምንታትን ካሳለፍን በኋላ በቀን አስራ ዘጠኝ፣ አስራ አንደኛው ወር፣ ሁለት ሺህ አስራ ዘጠኝ ላይ፣ ቀኑም ማክሰኞ ቀን በታንዛኒያ በ ቲ ቢ ሲ ሬድዮ (TBC Radio) እንዲህ የሚል ዜና ሰማን። "Wa Ithiopia Watu Uku Tanzania Mingi Sana

Sari Elfu Moja Na Mia Sith Upo Gerezani” ማለትም “የኢትዮጵያ ልጆች በየእስር ቤቱ፣ ወደ አንድ ሺህ ስድስት መቶ ታሳሪዎች አሉ። እነዚህንም ልጆች ወደ ሀገራቸው የመመለስ ስራ እየተሰራ ነው” ብሎ ዜና ዘገበ። ቋንቋውን በደንብ የምናወራ ልጆች ለእኛ ልጆች ተርጉመን ነገርናቸው። በቃ ሁላችንም ተሰብስበን በደስታ ፈነደቅን። በቃ በጣም ትልቅ የደስታ ምሽት ሆነልን። ወደ ሀገራችን የገባን ያህል ተሰማን። ግን እንደበፊቱ አጉል ተስፋ እንዳይሆን ብለን ከሙሉ ልብ ወደ ግማሽ ልብ ደስታችንን ለወጥነው። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ትሄዳላችሁ ብለው አስደስተውን በነፍሳችን ላይ ተጫውተዋል። ለዚያም ደስታችን ብዙም አልነበረም።

በዚህ እስር ቤት የሚገርመኝ ትንሽ ተደስተን ደስታውን ሳንጨርስ ሌላ ደስታውን የሚያደፈርስ ነገር ይከሰታል። በቃ እንዲህ ነው። አናስታውሰውም እንጂ ተደስተን ቢያንስ ሙሉ ቀን ውለን አናውቅም። ደስታችንን ሳንጨርስ እንከፋለን። ማታ ተደስተን በማግስቱ በሬድዮ ዜና አንድ ነገር ሰማን። ዜናውም “ከታንዛኒያ ወደ ማላዊ ሲጓዙ የነበሩ አስራ ስምንት የኢትዮጵያ ልጆች መኪና ተገልብጦ፣ አስራ ስድስቱ ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው ሁለቱ ልጆች ግን ሞተዋል” ሲል ሰማን። በቃ በጣም ተደናገጥን፤ በጣም አለቀስን። በህይወት የቀሩት አስራ ስድስት ልጆች ግን በከባድ እንደቆሰሉ ተናገሩ። የዚህ እስር ቤት መንፈሱ እራሱ መልካም ዜና ሰምተህ ደቂቃዎች ሳይሞሉ ወዲያው መጥፎ ዜና ትሰማለህ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነን ደግሞ በታንዛኒያውያን ታሳሪዎች መሰደብ መወቀስ ትልቅ ሸክም ሆነብን። በሀገራችን ምግብ የሚባል ነገር እንደሌለ ይቆጥራሉ። ብዙ ጊዜ ይሰድቡናል። ምንም ብናወራላቸው አይሰሙንም፣ አያምኑንም። በጣም ይጸየፉናል። በቃ ምን ልበል? በጣም እናፍራለን። በኛ በሀድያ እና በከምባታ ምክንያት ኢትዮጵያ የተባለች ሀገር፣ ይህች የተባረከች የሆነች የምድር ገነት፣ በእኛ በልጆቿ ተሰደበች።

# ክፍል ሠላሳ ሶስት



ስድብም ቢበዛብን፣ ብንጋፈጥም፣ ብንጸየፍም መኖራችን መች ቀረ? እንኖራለን። ፈጣሪ ከዚህ ጉድ እንዲያስወጣን እንታገላለን። ፎቶም አንስተው የሄዱት የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ድምጻቸው ጠፋ። ከእስር ቤቱ ደጅ አይናችን ተነስቶ አያውቅም። ሁሌም ወደ በር ነው አይናችን። ከአሁን አሁን መጥተው ይወስዱናል እያልን፣ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ፎቶ አንስተውን ትሄዳላችሁ ከተባልን አንስቶ ወደ አራት ወር ያህል በተስፋ ብቻ፣ የእስር ቤቱን በር በመመልከት ብቻ አሳልፈናል። ከዚህ በኋላ ምን ይፈጠር፣ ምን ይሆን? በቃ የእኛ ድርሻ በተስፋ ቀኑን መጠበቅ ብቻ ነው። የእኛ ችግር፣ ጭንቀታችን ሳይቃለል በዚያው ባለንበት የነጩች ዘመን መለወጫ ልናከብር ነው።

የ2020 አዲስ ዘመን ተቀበልን። ከነችግራችን ከነጥያቄአችን ዘመን ተለወጠ። በዚሁ ጊዜ ሁሉ ጥያቄ እናነሳለን። የእስር ቤቱ ሀላፊ፣ ባለ ሶስት ኮከቡ የሚሰጠን መልስ ሁሌም ተመሳሳይ ነው። ከአፉም የማይጠፋ ቃል ቢኖር “በዚህ በሁለት ዓመት ከግማሽ ትወጣላችሁ፤ ትሄዳላችሁ፤ ትንሽ ታገሱ” ብቻ ነው ከአፉ የሚወጣው። በማይሆን ተስፋ፣ በማይሆን ወሬ ስንቴ ተረበሽን? በቃ ከዚህ የተለየ ነገር በፍጹም አይተን አናውቅም። በዚሁ ሁኔታ ልጆች እየታመሙ፣ መኝታ ቦታ በማጣት ለስምንት እየተኙ፣ ብዙ ልጆች በብርድ በሽታ ወደቁ። የምግብ እጥረት አለ፤ የቦታ ችግር አለ፤ የውሃ ችግር አለ። በሁለት ወር ሳንታጠብ ያሳለፍነው ጊዜ ብዙ ነው። በቃ በጋ ሲሆን በጣም ችግር ነው የሚሆነው። ልጆች ሁሉም ውሃ ከማጣታቸው የተነሳ በጣም ችግር ውስጥ ወደቁ። በእስር ቤት ውስጥ ያለው ከግማሽ በላይ ሁሉም እከክ በእከክ ሆኑ። የእስር ቤት ሀላፊውም ተጠራ፤ ችግራችንንም አወራን። ለአንድ ቀን ብቻ ከእሩቅ ቦታ ውሃ በመኪና አስመጣልን። እርሱም አንድ ባልዲ ውሃ ለሁለት ሰው ብቻ ሰጡን። በቃ ውሃ በጣም ናፍቆናል። ውሃው በቃ ከማር በላይ ነበር የምናየው። ሆኖም ግን እከካችንን ሊሻለን አልቻለም። ለሁሉም ታሳሪዎች እንደሽሮፕ ያለ መድሃኒት ተሰጣቸው፤ እርሱም መፍትሄ

አልሆነንም። በቃ በጣም ተቸገርን። ልብሳችን ካለመታጠቡ የተነሳ ቅማል በቅማል ሆነ። አንዳንዴ ተሰብስበን ቅማል ከልብሶቻችን እንለቅማለን። በቃ ቀን አራት ሰዓት የቅማል ለቀማ ፕሮግራም ነው። ሁሉም ሹራቡን እንደጉርድ ልብስ ለብሶ ከሱሪው እና ከፓንቱ ቅማል ይለቅማል።

በቃ ከሲኦል በምንም አይተናነስም። በቁም መቃጠል ነው። ይህም ሳያንስ ያስቆፍራሉ፣ ድንጋይ ያሸክማሉ፣ ያንገላታሉ። በዚያ ላይ ነብስ አድን ብቻ ትንሽ ምግብ ይሰጣሉ። ከዚህ የሚበልጥ ሲኦል አለ ታድያ? እሺ ምን ልበል? በቁማችን ደረቅን። ሳንሞት ሸተትን፤ ሳንቀበር በሰበስን። ከዚህማ ሞቶ መገላገል ይሻላል እንላለን፣ እንመኛለን። በዚህ በችግር መሀል ፈጣሪ ሲረዳኝ በእስር ቤት ውስጥ ሀላፊነት ተሰጥቶኝ ነበር። በዚህ ትንሽ ከልጆች እሻላለሁ፤ ትንሽም ቢሆን ለምግብም መስሪያ የመጣ ውሃ ካለ ከእርሱም ትንሽ ወስጄ እታጠባለሁ። በዚህ በዚህ ትንሽም ቢሆን እሻላለሁ። አንዳንዴ ለእኛ ልጆች ስለማደላ፣ ውሃ ሰርቄም ስሰጣቸው ይወቅሱኛል። ለእራሱ ወገን ብቻ ነው የሚሰጠው ይላሉ፤ በጣም ይናደዳሉ። ሆኖም ግን ሀላፊነት ስላለኝ ብዙም ማውራት ይፈራሉ። ምክንያቱም የእስር ቤቱ ህግ ነው። አንዴ የተመረጠ ሰው ምንም ቢባል አይጥሉም፣ አይቀይሩም። በእስር ቤት የንፅሕና ሀላፊ ነበርኩ። በዚህ ብዙም ባይሆን ትናንሽ ጥቅማጥቅም አገኛለሁ።

## ክፍል ሠላሳ አራት

በ2020 በዚሁ እስር ቤት ማስቆጠር ጀመርን። ከኢትዮጵያ ኤምባሲ የመጡት ሰዎች ነገርም ተረሳ። ችግራችንን ተሸክመን መኖር ሆነብን። በዚሁ ሁኔታ ውስጥ 01-01-2020 ሆኖ ኤምባሲዎች ከመጡ አምስተኛ ወር ሆነ። በቃ ተስፋችን እንደጨለመ ማመን ጀመርን። በቃ ከመካከላችንም ብዙ ልጆች መበላሸት ጀመሩ። ወደ እስር ቤት በታንዛኒያውያን ታሳሪዎች ተደብቆ የሚገባውን አደንዛዥ እፅ መውሰድ ጀመሩ። በቃ የልጆቹ አዕምሮ ከማሰብ ውጪ መሆን ጀመረ። እርስ በራሳችንም እንመካከራለን። አንዳንድ ልጆች በቃ የእኔ መጨረሻ እዚሁ ነው ብለው ስላመኑ ይስቁብኛል። ምክሬንም ይንቃሉ። እውነታቸውን ነው ግን፤ ሁኔታችን እውነትም ተስፋ ያስቆርጣል። በዚሁ ሁኔታ የኤምባሲውም ሰዎች ሳይመለሱ ወደ ስድስት ወር አስቆጠርን።

ከዕለታት አንድ ቀን፣ ከጠዋቱ አራት ሰዓት የማይታመን ተአምር ሆነ። በቀን 17-02-2020 ባለ ሶስት ኮከቡ የእስር ቤቱ ሀላፊ ወደ ቢሮው ጠርቶን ድንገተኛ ስለሆነ ጥሪ አወራልን። ጥሪውም “ዛሬ ከዚህ እስር ቤት ትፈታላችሁ፤ ወደ ሀገራችሁም ትሄዳላችሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ!” ብሎ የምስራች ነገረን። በቃ በደስታ እራሳችንን ስተን፣ በደስታ ብዛት ሁሉም ማልቀስ ጀመረ። በቃ የምናደርገውን አናውቅም ነበር። ወዲያው ትልቅ

መኪና፣ ባስ [bus] ተጠራ። ወደ ኤምቢያ ከተማ (Mbeya City) ወሰዱን። እዚያም የስም ዝርዝር እየጠሩ ለሁሉም መጓጓዣ እንደሚዘጋጅ ነገሩን። በ18-02-2020 የእስር ቤቱን ደጅ እረግጠን ወጣን። በባስ ጉዞ ወደ ዳሬ ሰላም ከተማ (Dar es Salaam) አቀናን። የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ስምንት ባስ ሞልተን፣ ከአንድ እስር ቤት ወደ ሁለት መቶ አርባ አካባቢ ሆነን ጉዞ ጀመርን። ፈጣሪ ፀሎታችንን ሰማን። እስራታችን ተፈታ። በባስ ውስጥ በጩኸት፣ በመጨፈር፣ በመደሰት እንዲሁ በጉዞ ላይ ዋልን። ወደ ዳሬ ሰላም መድረስ ስላልቻልን የሆነች ከተማ ላይ አረፍን። በማግስቱም ጉዞ ጀመርን። ከቱንዱማ ወደ ሩዋንዳ እስር ቤት፣ እስከ ኤምቢያ ከተማ (Mbeya City) ጉዞው አራት ሰዓት ብቻ ነበር። ግን ከኤምቢያ ከተማ እስከ ዳሬ ሰላም ሶስት ቀን ፈጀ። በጣም እሩቅ ነበር። በዚያም ላይ ብርድ ስለሆነ በጣም ነበር መንገድ ላይ ያቆየን።

እንደምንም ወደ ዳሬ ሰላም (Dar es Salaam) በ21-02-2020 ላይ ደረስን። እዛም በአለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ሰራተኞች ብዙ ዝግጅት አዘጋጅተው ነበር። የመክሰስ ፕሮግራምም አደረጉልን:: ከዚያም በመቀጠል ለሁላችንም ተመሳሳይ ልብስና ጫማ ሰጡን። እዚያም ብዙ ጥያቄ ጠየቁን። ችግር ላይ እንዳሳለፍንም ነገርናቸው:: እነርሱም ብዙ ምክር ሰጡን፤ በሀገር ቤት ብዙ ስራ እንዳለ፣ ሰርቶም መለወጥ እንደሚቻል መከሩን። የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሀላፊ አቶ ብዙ ምክር ሰጡን። እርሳቸውም በቦቴ መኪናዎች ብዙ ልጆች ታፍነው ሞተው እሬሳቸውን ወደ ሀገር ቤት እንደላኩ ነገሩን። በጣም ብዙ ልጆች በአውሬ ጫካ ውስጥ እንደተበሉ፣ ብዙዎች ደግሞ በባህር ውስጥ ተገልብጠው እዚያው እንደቀሩ፣ ብዙ ነገር ነገሩን።

ከዚያም በመቀጠል ወደ ሀገር ቤት ስንመለስ በአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) አማካኝነት የመቋቋሚያ እንደሚሰጠን ነገሩን። ከዚያም ምግብ በልተን ልብሶቻችንን ቀይረን ወደ ታንዛኒያ አየር ማረፊያ (Tanzania Airport) ጉዞ ጀመርን። ወደ አየር ማረፊያው ደረስን። ማታውን ሙሉ እዚያ ጠበቅን። ታንዛኒያን ለመጨረሻ ጊዜ ቻው ብለን ለመውጣት ተዘጋጀን። እዚያው አውሮፕላን ስንጠብቅ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆነ። ከንጋቱ አስር ሰዓት ላይ ወደ አውሮፕላን ውስጥ ገባን። ወደ ሁለት መቶ አርባ ልጆች ጉዞ ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጀመርን። በቃ ልባችን ከስቃይ፣ ከቁጣ፣ ከማመንታት፣ ከርሀብ ስንቱን ላውራ? በቃ ልባችን ነፃነቱን አመነ። ተአምር ሆኖ በነጮች 22-02-2020 ቅዳሜ ጠዋት አንድ ሰዓት አውሮፕላኑ በሀገራችን መሬት ላይ አረፈ። ከአውሮፕላኑም እንደወረድን ብዙ ልጆች በደረታቸው ተኝተው መሬቱን ሳሙ። በቃ መሬቱን ስመን ወደ እንግዳ ማረፍያ በአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ሰራተኞች እርዳታ ወደ ማረፊያ ቦታ ተወሰድን።




እዚያም ትልቅ ግብዣ አደረጉልን። ለሁላችንም ለትራንስፖርት አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ብር ሰጥተው አድራሻችንን ፅፈው፣ የቤተሰብ ስልክ ተቀብለው ሸኙን። በታውም አበበ ቢቂላ መታሰቢያስቴድየም ፊት ለፊት ነው። እኔም ሰውን በመለመን መጀመሪያ ለእህቴ ደወልኩላት። እርሷም ለማንሳት አልቻለችም ነበር። የተለያዩ ሰዎችን ስልክ ለምኜ እደውላለሁ። በመቀጠል እኔን ያሳደገኝ ታላቅ ወንድሜ ጋር ደወልኩ። እርሱም ስልኩን ምልክት እንዳደረግኩ ወዲያው ደወለልኝ። በጣም ተደሰትኩኝ፤ ማውራትም ቀጠልኩኝ። በጣም ደነገጠ፤ ሊያምነኝ አልቻለም ነበር። በጣም ከመደሰቱ የተነሳ እኔን ማናገር ትቶ ለጓደኞቹ፣ ለስራ ባልደረቦቹ ባንክ ውስጥ በጩኸት ነገራቸው። እነርሱም ተራ በተራ አዋሩኝ። በጣም በኔ መታሰር እንደተጎዱ ነገሩኝ። የእርሱን ስልክ እንደጨረስኩ የሁላችንም ታላቅ ወደሆነው፣ ወደ ወንድሜ ጋር ደወልኩኝ። በአዲስ አበባ፣ በአየር ጤና ነው የሚኖረው። እርሱም ወደ ቦሌ ካልመጣሁ ብሎ በጣም አስቸገረኝ። እኔም “ለምንም አትቸገር፤ እኔው እራሴ ታክሲ ይዤ እመጣለሁ” ብዬ ነገርኩት። ታክሲም ይዤ ወደ እርሱ አቀናሁ።

ወደ እርሱም ቤት በታክሲ ደረስኩ። አላመነኝም ነበር። በቃ በጣም ተደሰቱ። የወንድሜ ሚስትም ቤት ውስጥ ጥሩ ዝግጅት አዘጋጅታ ነበር። በዚህ በአዲስ አበባ ሆኜ በወንድሜ ስልክ ወደ አባቴ ጋር እና ወደ ጓደኞቼ ጋር ሳይቀር ደውዬላቸው አገኘኋቸው። ሁሉም በጣም ተደሰቱ። በቃ እኔንም በጣም ደስ አለኝ። ነገር ግን ለሳምንት ያህል የፍቅረኛዬን

ስልክ አላገኘሁም ነበር። በድሮ ስልክ ስደውልላትም ስልኳ ጥሪ መቀበል አይችልም ነበር የሚለው። በቃ በጣም ናፍቄያት ነበር። የፌስቡክ አካውንቴን [facebook account] ስላልረሳሁት በወንድሜ ስልክ በፌስቡክ ገብቼ የእርሷን ስም ፈልጌ መልእክት አስቀመጥኩላት። እርሷም በሰዓቱ ኦን ላይን (online) አልነበረችም። በኋላ ገብታ መልዕክቱን እንዳገኘች ደወለችልኝ። በቃ ደስታዬን መቆጣጠር አልቻልኩም ነበር። በቃ ለእረጅም ሰዓት አወራን፤ በጣም አለቀሰች። ሞቼ የማልመጣ ያህል ተሰምቷት ግን በደስታ ብዛት በጣም አለቀሰች። እኔም በጣም አባበልኳት። አሁን ከጎንሽ ነኝ ብያት በብዙ ማባበያ ቃል አፅናናኋት። በቃ በጣም ተደሰተች። እኔም የድሮ ስልኬን አውጥቼ በቃ ቀን በቀን መደዋወል ጀመርን። እርሷም በዩኒቨርሲቲ ካምፓስ እንደገባች፤ በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ እንዳለች ነገረችኝ። እኔም ወደ አንቺ ካልመጣሁ ብዬ አስቸገርኳት። እረፍት እንደደረሰ ወደ ቤተሰቦቿ እንደምትመለስ ነገረችኝ።

ወንድሜ በጣም ተንከባከበኝ። ፍየል ገዝቶ አርዶ አበላኝ። በቃ የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ ገዝቶ ሰጠኝ። የድሮን ሲም ካርድ ስላወጣሁኝ ስልክም ገዛልኝ። እዚያም ብዙም አልቆየሁም፤ ወደ ሆሳዕና ወደ ቤተሰቦቼ ተመለስኩ። በአዲስ አበባ ለአስራ አምስት ቀን ቆየሁኝ። ጓደኞቼም እያለቀሱ ስላስቸገሩ ወደ ሆሳዕና ተመለስኩኝ። በቃ ጓደኞቼ በጣም ናፍቀውኝ ነበር የጠበቁኝ። ወደ ወንድሜ ቤትም ደረስን፤ እዚያም ብዙ መምጣቴን ያወቁ ሰዎች ጠብቀውኝ ነበር። ጥሩ አቀባበል አደረጉልኝ። ለእኔም በጣም ደስ አለኝ። በቃ ወደ ከተማ ወጣ ስል ጓደኞቼ በጣም በመደንገጥ ሞተሃል ተብሎ እኮ በጣም ነው ያዘንነው እያሉ ብዙ አወሩኝ። በጣም ተገረምኩኝ! በቃ የምለውን አጣሁ። ሌላም ደግሞ ስለ መንገዱ ሁኔታ በጣም አጥብቀው ይጠይቁኛል፤ የኔ መልስ ግን እድልህ ከሆነ የነፍስ ፈተና ተፈትነህ ከወደቅክበት ትነሳለህ። ህይወትህን ጥለህ ይህን ፈተና ካለፍክ ወደ ደቡብ አፍሪካ ትገባለህ። ሌላው ደግሞ ከተያዝክ እስር ቤት ትገባለህ፤ እዚያም የምድር ሲኦል ታያለህ፣ ትቀምሳለህ ብዬ እነግራቸው ነበር።

የእኔን ምክር የሰሙ ነበሩ፤ መሄድም ትተው ባጃጅ በመግዛት ስራ የጀመሩ ጓደኞቼ አሉ። አንድ ሰው በራሱ ሲደርስ ይማራል፣ ሌላኛው ደግሞ ከሰው ይማራል። በኔ ላይ በደረሰ በደል፣ ግፍ፣ መገረፍ፣ መመታት፣ የእስር ቅጣት፣ በርሃብ መቀጣትን ብዙዎች ሰምተው ለመሄድ የተዘጋጁት ቀርተው ስራ በመፍጠር ስራ የጀመሩ አሉ። ግን የሰውን ምክር የማይሰሙ ወደ ስደት በመሄድ ዛሬ ላይ በታንዛኒያ ገበሬዎች እጅ፣ እስር ቤትም በትልቅ ችግር ውስጥ የገቡ ልጆች ብዙ ናቸው። ሰው በራሱ ሲደርስ ከራሱ ይማራል። ሰው ላይ የደረሰውን አይተው ከመጥፎ ውሳኔ እራሳቸውን ይቆጥባሉ። የስደትን ታሪክ እንኳን ባልጠየቅ ነው የምለው፤ የሱን ትዝታውን እንኳን ሰው እንዲቀሰቅስብኝ አልፈልግም። በጣም ከባድ ነው። በአፍ እንደምናወራው ቀላል አይደለም።

ሆሳዕና ለሁለት ሳምንት ያህል እንደቆየሁ እህቴ ከባሏ ጋር ከሚኖሩበት ከጂንካ መጥተው፣ እኔንም አይተው፣ አባቴን እንኳን ደስ አለህ ብለው አባቴንም አስፈቅደው ወደ ዲመካ ወሰዱኝ። እዚያም በጣም ዘና፣ ፈታ አልኩ። ተጎድቼ ስለነበር በጣም በመጮህ ከእንቅልፍ እነቃ ነበር፤ በጣም እቸገር ነበር። በኋላ ላይ በአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ድጋፍ ለብቻዬ ዶክተር አመቻቹልኝ። ዶክተር ትባላለች። ብዙ ጊዜ ምክር ሰጠችኝ፤ በየጊዜውም ደውላ ትጠይቀኛለች። በሆሳዕና በንግስት እሌኒ ሆስፒታል የሚገኙትን ዶክተሮች ስልክ ሰጠችኝ፤ እነርሱም በምክር ደረጃ በጣም እረዱኝ። እኔም ብዙም አልተቀመጥኩም። ዲመካ ላይም በጣም ተዝናናሁኝ። ከዚያም ወደ ሀዋሳ መጣሁ፤ እዚያም አሪፍ ጊዜ አሳለፍኩኝ። በኋላ ላይም ነገሩን እየረሳሁ እንቅልፍም በጊዜ መተኛት የሚያስቸግረኝም እየተሻለኝ መጣ።

ከዙረትም ተመልሼ፣ ከእስር መልስ ለመጀመርያ ጊዜ ከቤተሰቦቼ ጋር ፋሲካ በዓልን አሳለፍኩ። ለፋሲካ በዓል የአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ድርጅቶች ደውለው ለያንዳንዳችን አራት ሺህ ብር ለበዓል እንዳይደብራችሁ በማለት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አድራሻችን ላኩልን። ሌላም ተጨማሪ እርዳታ እንደሚያደርጉልኝ በስልክ ነገሩኝ። በቃ ከፈጣሪ በታች በጣም ነው የረዱኝ። ኑሮን እንደገና ሀ ብዬ በሆሳዕና በባዶ እጄ ከቤተሰቦቼ ጋር ማሳለፍ ጀመርኩ። የሚያኖረኝ ወንድሜ በፊት ከሚሰራበት ከሀደሮ ከተማ ወደዚህ ወደ ሆሳዕና መቀየሩ በጣም አሪፍ አጋጣሚ ነበር። እርሱም የመኪና መንጃ ፈቃድ እንዳወጣ አመቻቸልኝ፤ የመንጃ ፈቃድም መማር ጀመርኩ። የመንጃ ፈቃድ ትምህርቴን ጨርሼ ፈቃዴን ተቀበልኩ። ኪያም ወደ ቤተሰቦቿ ተመለሰች። በጣም ተነፋፍቀን ስለነበር እኔ ከሆሳዕና ወደ ሀደሮ ከተማ ሄጄ አገኘኋት። አሪፍ ጊዜም አሳለፍን። ደስ የሚል ቀን አሳልፈን ወደ ሆሳዕና ተመለስኩ። ተመልሳ እንዳትሄድም በኮሮና ምክንያት ሁሉ ነገር ተዘጋ፤ ለእረጅም ጊዜም በሀደሮ ተቀመጠች።

## ክፍል ሠላሳ አምስት

ወደ ኢትዮጵያ ከመጣሁ በኋላ፣ በዚህ በሁለት ወር ውስጥ "ኮሮና የሚባል በሽታ መጥቷል። በአየር፣ በንፋስ የሚተላለፍ ነው" ተብሎ መዷዷዣ ሳይቀር ሁሉ ነገር ተዘጋ። ፈጣሪዬን ነው ያመሰገንኩት። ከትልቅ ፈተና ነበር ያስመለጠኝ። እዚያው እስር ቤት ብንሆን በትንሽ ጠባብ ክፍል መቶ አርባ ልጆች ነበር የሚያስቀምጡት። በጣም ከባድ ይሆንብኝ ነበር። ፈጣሪ ካስመለጠን በኋላ ይህ ነገር ተከሰተ። ለነገሩ ከቻይና ሲነሳ በዜና እስር ቤት ሆነን ስንሰማ ነበር። እንዲህ ይስፋፋል ብለን ግን አልጠበቅንም ነበር። በኋላ ላይ የአለም ደጆችን እያንኳኳ እዚህ ደረሰ። በዚህ ምክንያትም ለማግኘት በጣም

ከባድ ሆነብኝ። ከቤት መውጣት የለም። ወንድሜ ከስራ ቦታ እስኪመጣ መተኛት ብቻ ነበር።

ነገር ግን ያለስራ መቀመጥ በጣም ትልቅ ሸክም መሆን ጀመረ። ወደ ከተማ ስወጣም “ስራ ጀመርክ? አሁን ስራ እየሰራክ ነው?” በማለት በጣም ያሳፍሩኛል። በፊት በጣም የምትወደኝ የወንድሜ ሚስት ፊቷን መንሳት ጀመረች። አንድ ቀን በተኛሁበትም፣ በሌለበት “አንተ ከመጣህ ወዲህ ፀባዩን ቀይሯል” አለችኝ። በጣም አፈርኩ። እንደድሮ ስላልሆነ፣ እድሜዬም ከፍ ስላለ በጣም አፈርኩ። የማወራው ሳጣ “በቃ እኔ እሄዳለሁኝ” አልኳት። ወዴት እንደምሄድ ሳላውቅም ዝም ብዬ እወጣለሁ አልኳት። እርሷም በጣም ደነገጠች፤ እንደዛ አታድርግ እባክህን ባለቤቴ ይገድለኛል ብላ በጣም ለመነችኝ። እኔም መሄጃ ስላልነበረኝ በሀሳቧ እንደገና ተስማማሁኝ። በቃ በጣም በመረበሽም ቢሆን ተቀመጥኩኝ። ይህ ሁሉ ሲሆን በፈጣሪ ፊት ተናግሬው አላቅም። ለሻይ፣ ለቡና እኔን ይዘኝ ሲወጣ እራሱ በጣም ተረብሻ፣ ፀባይዋም ተቀይሮ ትጠብቀኛለች።

በቃ በዚህ ሁኔታ ለመኖር በጣም እየከበደኝ መጣ። ግን የሚሆነውን ሁሉ ለእህቴ ደብቄ እነግራት ነበር። ግን ካሳደገኝ ከወንድሜ ከተጌ የሚበልጥ ምንም የለም። ለአመታት ሲያኖረኝ እንደባለሀብት ልጆች አድርጎ ነው ያሳደገኝ። አንድም ቀን እንዳይደብረኝ፣ በአፍ ደረጃ እንኳን ተቆጥቶኝ አያውቅም። ባጠፋም ይመክረኛል እንጂ አስደንግጦኝ አያውቅም ነበር። ለኔ በቃ አባት ብለው ከአባት በላይ፤ እናት ብለው ከእናትም በላይ ነው። በቃ በህይወቴ ለእርሱ ከምንም ነገር በላይ ትልቅ ቦታ አለኝ። ትክክለኛ የወለደኝ አባቴ ነው። ለእኔ ከአባትም በላይ ነው።

የእህቴ ባል በጣም ጥሩ ሰው ነው። የመኪና መንጃ ፍቃድ ስላለኝ አንድ ሀሳብ አመጣ። “ለምን ባጃጅ ገዝቼልህ አትሰራም?” ብሎ ጠየቀኝ። እኔም እሺ ብዬ ተቀበልኩ፤ ባጃጁንም ገዛልኝ። ባጃጅ መስራት ጀመርኩ። በጣም ደስተኛ ሆኜ ስራዬን መስራት ጀመርኩ። ባጃጅ ለማሳደር የሚመች ግቢ ያለውን ቤት ተከራይቼ ኑሮዬን ጀመርኩኝ። በቃ በጣም ደስተኛ ሆንኩ። ይገርማል! ስራ ኖሮኝም እንኳን ወንድሜ ብር ይሰጠኛል፤ ለዚያም ነው ከአባትም በላይ ነው ያልኩት።

በዚህ ጊዜ ውስጥም የሆነ ነገር ተከሰተ። ድንገት ከንጋቱ ለአስራ ሁለት እሩብ ጉዳይ ሲል በድንገት ከፍቅረኛዬ ስልክ ተደወለልኝ። በጣም ደነገጥኩ። ስልኩንም ሳይ ፍቅር ይላል፣ ሰዓቱንም ሳይ 11:45 ይላል። ምን ተፈጥሮ ይሆን? ብዬ ባንኜ አልጋዬ ላይ ቁጭ ብዬ ማናገር ጀመርኩ። በጣም እያለቀሰች ስሜን እየጠራችኝ “መጥፎ ህልም አየሁ፤ በጣም ይዘገንናል!” ብላ በጣም እያለቀሰች ነገረችኝ። ህልሙንም ስጠይቃት

እንዲህ አለችኝ “የሆነ ቀጥ ያለ መንገድ ላይ ሁለታችን ብቻ እየተራመድን ነበር። ከዚያም በድንገት መንገዳችንን የሆኑ ወጣት ልጆች ዘጉብን። ከዚያም በወንዶቹ መሀል ጥለኸኝ ጠፋህ፤ በቃ ይኸው ነው ያየሁት፤ በቃ እኔን ትክደኛለህ አይደል? በቃ ልንለያይ ነው አይደል?” አለችኝ። ግራ ተጋባሁኝ። የማወራላትን አጣሁኝ። ላባብላት ብዬ “በቃ ቅዠት ሊሆን ይችላል ተኚ፤ ጠዋት እናወራለን” ስላትም “እምቢ አይሆንም! ያየሁት የሚሆን ነገር ነው፤ ህልሜ ደግሞ መሬት ላይ ጠብ አይልም፤ ሁሌም ሳልም በተግባር ደርሶ ነው የማየው” ብላ እያለቀሰች ጆሮዬ ላይ ስልኩን ዘጋችው። መልሼ ስደውልላት እንኳን ለማንሳት እምቢ አለችኝ። በቃ በጣም ተረበሽኩኝ። ብቻዬን ቁጭ ብዬ ማሰብ ጀመርኩኝ። “ምንም ስሌለኝ ይሆን? ከስደት ስተመለስኩ ባዶነቴን ጠልታኝ ይሆን?” ብዬ በቃ ብዙ ነገር ማሰብ ጀመርኩ።

በማግስቱ ስደውልላት በጭራሽ ሀሳቧን ለመቀየር እምቢ አለች፤ በጣም ለመንኳት። ግን ብለምናትም ሀሳቧን ለመቀየር እንደማትችል በጣም አስጠነቀቀችኝ። አንዳንዴ ስልኬንም ለማንሳት እምቢ አለችኝ። በስንት መከራ ደጋግሜ ስደውልላት ታነሳውና “ለምን አታነሽም?” ስላት “ልለማመድ ብዬ ነው፤ ጥለኸኝ ስለምትሄድ” ብላ አለችኝ። ብዙ ጊዜ ስለለመንኳት ግልጹን ነገርኳት። “ድህነቴን ጠልተሽ ነው አይደል? ባይሆን እንደድሮ አሁንም ትወጂኛለሽ አይደል? የኔ ውድ ይህን ብቻ ንገሪኝ እባክሽ?” ብዬ እየጠየቅኳት እምባዬን መቆጣጠር ሲያቅተኝ ዘረገፍኩት።

በተደጋጋሚ ስደውልላት ማንሳት እምቢ አለች። በቃ መታገስ አቃተኝ በመልዕክትም “በጣም አስመሳይ ሴት ነሽ፤ ይህን ያህል ዓመታትን ስታስመስይ ነበር” ብዬ ስሜታዊ ሆኜ መልዕክቱን ላኩት። በጣም ተናዳ ደወለችልኝ። በሰዓቱ ክረምትም ስለገባ ወደ ሀዋሳ ወደ አክስቷ ቤት ሄዳ ነበር። “የወደድኩህን ያህል ጠልቼሃለሁ፤ በቃ የእኔ እና የአንተ ግንኙነት እዚህ ላይ ያበቃል፤ ሁለተኛ እንዳትደውልልኝ” ብላ ስልኬንም ብሎክ አደረገችው። በቃ በጣም ተበሳጨሁኝ፤ የምሆነውንም አጣሁ። አረርኩ፤ በቃ እራሴን መቆጣጠር አቃተኝ። ለብዙ ወራትም ለመንኳት፤ አልፎ ተርፎም በጓደኞቼም አስለመንኳት። በቃ ብዙ ተስፋ የሚያስቆርጡ ቃላቶችን ተናገረችኝ። በቃ የእኔና የእርሷ ነገር እዚህ ጋር ቆመ። ለዓመታት ስጠባበቅ፣ ስናፍቃት የኖርኩት ፍቅረኛዬ የህልም እንጀራ አስበላችኝ።

ከእንግዲህ ሰው አልሆንም ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። እራሴን ጣልኩኝ። ከባእድ ሀገር ያወጣኝን ፈጣሪዬን እረስቼ በአልኮል ጠርሙስ ውስጥ መውደቅ ጀመርኩ። በኋላ ላይም ጓደኛዬ ብዙ መከረኝ፤ ሌላ አማራጭ ሲጠፋ ምክሩንም ተቀበልኩኝ። ግን ህመሙ ከውስጤ መቼም እንደማይጠፋ አምኜ ተቀመጥኩ። በዚያው ሁኔታ ውስጥ የመስቀል በዓል ደረሰ። በዓሉንም ከቤተሰቦቼ ጋር አሳለፍኩኝ። ከትንሽ ቆይታ በኋላ

ትንሽም ቢሆንም ከተዝናናሁ በኋላ በደቡብ አፍሪካ ያለው ወንድሜ በድጋሚ ፓስፖርት እንዳወጣ እና በበረራ ወደ ደቡብ አፍሪካ እንደሚወስደኝ አስጠንቅቆ ነገረኝ። እኔም እሺ ብዬው በሁሉም ነገር ስለተበሳጨሁኝ በውሳኔው ተስማማሁ። ወደ ሀዋሳም ሄጄ ፓስፖርት አወጣሁኝ። ግን ኮቪድ 19 ሁሉንም እንቅስቃሴን አቆመው። በደቡብ አፍሪካ እንቅስቃሴም ሁሉ ተዘጋ። በዚህ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ እንደምቆይ ወንድሜ ነገረኝ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆኜም ባጃጅ እየሰራሁ ቆየሁ። በትንሹም ቢሆን ሲከፋኝ ወጥቼ የምገባበትን ስራ አገኘሁ። ባጃጅም እየሰራሁ ከትራፊክ ፖሊሶች ጋር ሁሌም መጣላት ሆነ። ትራፊክ ፖሊሶቹም በጣም ጠመዱኝ። በየጊዜው በእነርሱ መቀጣት ሆኖብኝ በጣም ተበሳጨሁ። ይህም ሳያንስ በአደባባይ በትራፊክ አደጋ ግጭት ተፈጠረ። በዚህም ምክንያት በጣም ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩኝ። "ለምንድን ነው የሞከርኩት ነገር ሁሉ የሚጠምብኝ?" ብዬ በጣም በህይወቴ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ። በዚህ ጉዳይ ለተወሰነ ጊዜ ስራ ፈታሁ። ባጃጁም ታሰረ። በኋላ ላይ በሰውም በሽምግልና ተይዞ በሀድያ ባህል ነገሩን ሽማግሌዎች ፈቱት። እንደመጀመሪያውም ስራዬን ቀጠልኩ።

በባጃጅም ስራ ለተወሰነ ጊዜ እንደቆየሁ ከአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ድንገተኛ የሆነ ጥሪ ተደረገልኝ። ከቦሌ ስንወጣ አቀባበል ያደረጉልኝ የአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ሠራተኞች ያኔ የወንድሜን ስልክ ነበር የተቀበሉኝ። የራሴ ስልክ ስላልነበረኝ የወንድሜን ስልክ ሰጥቻቸው ነበር፤ በዚያም አድራሻ ወደ ወንድሜ ደውለው እኔን እንደሚፈልጉኝ ነገሩት። ወንድሜም የባንክ ሰራተኛ ስለሆነ ከስራ እንደወጣ ከአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ሠራተኞች ጋር አገናኘኝ። በጣም የሚያስደስት ነገር ነገሩኝ፤ በቃ በደስታ እራሴን መቆጣጠር አቃተኝ። የስራ ዘርፌንም ሲጠይቁኝ ድሮ ባለው እንጨት ቤት ትንሽ ጊዜ እንደሰራሁኝ ነገርኳቸው። በዚህም ዘርፍ ስራ እንደሚከፍቱልኝ ነገሩኝ። በቃ ነገሩ ሆኖ እስከማገኘው በጣም ጓጓሁኝ።

## ክፍል ሠላሳ ስድስት

የአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ሰዎች እስከአለንበት ከተማ ድረስ መጡ። ለእኛም ለእያንዳንዳችን ደውለውልን በሆሳዕና ከተማ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ግቢ ውስጥ ስብሰባ ተደረገ። በዚያም ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ በላይ ልጆች ነበሩ:: እያንዳንዱ ሰው በፍላጎቱ ፋይል ተሞላ፤ ልጆችም የፈለጉትን የሥራ ዘርፍ መረጡ። ብዙ ልጆች ሱቅ ብለው ሞሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ፑል ብለው ሞሉ። ፀጉር ቤት ብለው የመረጡም ነበሩ። ግማሾቹ የእህል መጋዘን፣ ወፍጮ ቤት፣ የወተት ላም ብለው ሞሉ። ሌሎችም የለስላሳ ማከፋፈያ፣ የካፍቴሪያ ስራ፣ የህንፃ መሣርያ ብለው መረጡ። በብዙ ስራ ዘርፍ ተሳተፉ::

እኔ ግን የእንጨት ስራ (furniture) ማሽኖች ብዬ የራሴን ፍላጎት ሞላሁ። ጓደኛዬም ከእኔ ጋር ተመሳሳይ ነገር መረጠ። መረጃ ሰብስበው፣ ለሁላችንም በመረጥነው መሰረት ለመስጠት ከአንድ ወር በኋላ እቃ ይዘው እንደሚመለሱ ነግረውን ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ ሄዱ።

ከአንድ ወር በኋላ ተመልሰውም ለእያንዳንዳችን እንደየፍላጎታችን እቃዎችን ጭነው መጡ። በቃ ታሪክ ተቀየረ። ልባችን ለማመን ከበደው። የፈጣሪ ፈቃድ ሆኖ እቃውን በእጃችን አስገባን። ለእኔም የደረሱኝን የእንጨት ስራ ማሽኖች ወደ ወንድሜ ቤት በመኪና አስጭኜ፣ መኪና ላይ ከእቃው ጋር ፎቶ ተነስቼ፣ ከሀላፊዎቹ ተቀብዬ ወሰድኩ። ወንድሜ ከተቀበልኩት ከእኔ በላይ ተደሰተ። የወንድሜ ሚስትም በጣም ተደሰተች። በቃ አሁን ታሪክ ሊቀየር ነው። ማሽኑንም ተረክቤ ለሶስት ወር ያህል ባጃጄን እየሰራሁኝ ሁኔታውን ማስተካከል ጀመርኩ። በደቡብ አፍሪካ ያሉትንም ወንድሞቼን ስራ ማስጀመሪያ አጥቼ በጣም ሀሳብ ውስጥ እንዳለሁ ነግሬ ለመንኳቸው። በአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) አማካኝነት ማሽን እንዳገኘሁም ነገርኳቸው። ግን የገዛ የእናቴ ልጆች ሊረዱኝ ፈቃደኛ አልሆኑም ነበር። በቃ ይህን ሁሉ ማሽን እንዴት ላድርግ? በማለት በጣም ተጨነኩኝ። የማማክረውም ሰው ሁሉ በቃ ሽጠህ ብሩን ተጠቀም አሉኝ። በቃ የሚረዳኝ ከፈጣሪ በቀር ማንም ሊታየኝ አልቻለም ነበር። በኋላ ላይ እያፈርኩም ቢሆን ባጃጅ የገዛልኝን የእህቴን ባል ነገሩን አማከርኩት። እርሱም አላሳፈረኝም። በሀሳቤ ተስማማ፤ ባጃጄም እንድትሸጥ ወሰነ። ባጃጄን ወደ ስምንት ወር ያህል ከሰራሁበት በኋላ ከገዛንበት አምስት ሺህ ብር ቀንሰን መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር ሸጥነው። ከዚያም ለእኔ ሰባ ሺህ ብር ብቻ እንዲያበድረኝ ጠየቅኩት። ሰባ ሺህ ብሩንም ሰጠኝ። በዚያ ብር እንቅስቃሴ ጀመርኩ። ለመስሪያ ቦታ ሁለት ወር ሙሉ ፈለኩኝ፤ በጣም ስፈልግም ጠፋ። የምሆነውን አጥቼ ተስፋ መቁረጥ ጀመርኩ። በዚህ ትንሽ ዕድሜ ሆኜ ለምን ችግር ብቻ እንደሚፈታተነኝ አላውቅም፤ ፈጣሪዬ ለምን ግን? ለምን አንዱን ሳገኝ አንዱ ይጠፋል? አልኩት። በቃ ይኸው ነው፤ እድል የሚባል ከቶ አይወጣልኝም።

ይህን እቃ ለማግኘት መጀመሪያ የንግድ ፈቃድ አምጡ ተብለን ነበር። የሆሳዕና ከተማ የሴቶች ዱና ቀበሌ ሰራተኞች በነብሴ ላይ ነበር የቀለዱብኝ። በጣም አንገላቱኝ፣ በጣም አስለፉኝ። የሚረዳኝ ድርጅት እንኳን ያልጨቆነኝን ቀበሌዎች ግን በነፍሴ ላይ ተጫወቱብኝ። በቃ ሁሉ ነገር ተስፋ ያስቆርጠኝ ነበር። ያን ሁሉ ችግር መሰናክል ካለፍኩ በኋላ እዚህ ቤት በማጣት ተቸገርኩ። በደላላ ሳይቀር አስፈለግኩኝ። በኋላ ላይ ከተማውን ሙሉ በየቀኑ ዞሬ ዞሬ የሆነች ቦታ አገኘሁ። ያን ቦታም ስጠይቅ አስር ሺህ ብለው ከለከሉኝ። በስንት መከራ እና ፍዳ ቤት ሳገኝ አስር ሺህ ይላሉ፤ በዚያ ላይ የስድስት ወር ኪራይ አስቀድመው ይጠይቃሉ። ተስፋ ባለመቁረጥ እኔ እና ችግሬ ተፋጠጥን።

እዚህ ደረስን። ጌታ ሆይ ከዛሬ በኋላ አንተው ተወጣው ብዬ ቁጭ አልኩ። በቃ መተኛት ብቻ ሆነ። ጠዋት እወጣለሁኝ፣ ማታ እገባለሁ።

በቃ ከባጃጅ ስራም ወጣሁኝ። ከሚረዳኝ ወንድሜ እጅም ወጣሁኝ። በተከራየሁበት ቤት ብቻዬን መቃጠል ሆነብኝ። ወደ ፈጣሪ ብቻ ማልቀስ ሆነብኝ፤ ብሩም ከእጄ መጥፋት ጀመረ። ወይ ላሰብኩት ሀሳብ አላደረኩትም። ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እያልኩኝ ብድር የወሰድኩት ብርም እየቀነሰ መጣ። “አምላኬ ከጉድ አውጣኝ” ማለት ጀመርኩ:: የገዛ ወንድሞቼ ያላገዙኝን ነገር ነው እኔን በማመን ሰባ ሺህ ብር አውጥቶ የረዳኝ። በቃ ለእኔ ትልቅ ፈተና ሆነብኝ። ከአፌ “ጌታ ሆይ አታዋርደኝ” የሚል ቃል ብቻ ነበር የሚወጣው። ጌታም እረዳኝ፤ መፍትሄም ሆነልኝ። ከእለታት አንድ ቀን ዝም ብዬ ወደ ከተማ ከተከራየሁበት ክፍል ወጣ ብዬ ብቻዬን እየተራመድኩ ሳለ “የሚከራይ ቤት” የሚለውን ወረቀት ተመለከትኩ። በድፍረት ስልኩን ወስጄ ደወልኩለት።

ሰውዬው ስልኩን አንስቶ ማናገር ጀመረ። ለምን ስራ እንደሆነም ጠየቀኝ፣ እኔም ለእንጨት ስራ (Furniture Work) መሆኑን ነገርኩት። የብሩን መጠን “ሰባት ሺህ ብር ነበር የበፊቶቹ ተከራይተው የነበሩት” ብሎ ነገረኝ። እኔም በአካል ለመገናኘት ለመንኩት። ሰውዬውንም በአራተኛው ቀን በአካል አገኘሁት። ወጣት ነው፣ የስድስት ወር ክፈለኝ አለኝ። ወጣትም ስለሆነ ተሰድጄ በታንዛኒያ እስር ቤት ሶስት ዓመት ቆይቼ እንደመጣሁ፣ ሁሉንም ነገር በማጫወት እንዲረዳኝ ለመንኩት። ልጁም በጣም መልካም ሰው ነው:: ይባላል። “በቃ ላንተ በተመቸህ ዋጋ ግባ” ብሎኝ የምለምነውን ቃል ነገረኝ:: እኔም የአራት ወር ብዬ ወደ አስራ ስምንት ሺህ ብር ስሰጠው፣ ደግሞ በነፃ ወደ ሃያ አምስት ቀን ጨመረልኝ። በቃ ለማመን አቃተኝ።

ፈጣሪ በብዙ እረዳኝ፤ በድፍረትም ሄጄ ወደ አርባ ሺህ ብር አውጥቼ፣ ለመሥሪያ የሚሆን ኤም ዲ ኤፍ (MDF) አስገባሁኝ። ሠራተኛም በሰው ሰው አገኘሁኝ። በጣም ያገዘኝ ልጅ፣ በባጃጅ ስራም በነበርኩበት ጊዜ “ከዚህ የሚሻለው በማሽን ብትሰራ ነው የሚያዋጣው” ብሎ ሲመክረኝ የነበረው የሚባለው የባህር ዳር ልጅ ነው። እርሱም አንድ አልጋ፣ አንድ ቁም ሳጥን፣ አንድ ኮንትሮል ብፌ በነፃ ሰርቶልኝ ስራ ማስኬጃ ይሆንልሃል ብሎ አገዘኝ። ይህ ልጅም በሰራቸው እቃዎች ጥሩ ብር፣ አረፍ ትርፍ አገኘሁኝ። በቃ ስራው መጣፈጥ ጀመረ። በቃ በአለም ላይ እንደኔ የተደሰተ ሰው እንደሌለ ቆጠርኩኝ።

በሳምንቱም የስራ ቱታዬን ለብሼ ወደ እየሩሳሌም ሰፈር የሞባይል እስክሪን [መስታወት] ለማስቀየር ስሄድ ስልክ ጠጋኙ ሞባይሌን ከሰራልኝ በኋላ "ስራህ ምንድን ነው? የምን ቱታ ነው የለበስከው?" አለኝ። የእንጨት ስራ እንደምሰራም ነገርኩት። የሞባይል ስልክ ቤቱ ልጅም "ይኸው ቤቴን ለማስለካት ወደ እንጨት ቤት ሄጄ የሞባይል ማሳያ እና ትልቅ ሼልፍ፤ ብዛት ያለው ስራ ትዕዛዝ ልሰጥ ነበር፤ እንደዚያ ከሆነ አንተ ጋር ላሰራ?" አለኝ። ወዲያው ወደ ሥራ ቦታ ወስጄው፣ ቤቱንም ለክቼው፣ ወደ ሃምሳ ሺህ ብር ተስማምተን፣ ቀብድም ወደ ሃያ ሺህ ብር ሰጥቶኝ በጣም በመደሰት ወደ ሥራ ቦታ ገብቼ ቀን፣ ማታ፣ ቀን፣ ማታ ሰርተን ወዲያው በሁለት ሳምንት አስረከብን። ልጁም ከተነጋገርነው ውጪ ተደስቻለሁ ብሎ አሪፍ ብር ሰጠኝ። በጣም ደስተኛ ሆኜ፤ ባገኘሁት ትርፍ ብር ወዲያው ቁሳቁስ እየሞላሁ፣ በቃ ቤቱም በጣም እየተስፋፋ መጣ፤ በጣም አደገ።

## ክፍል ሠላሳ ሰባት

ብዙ ደንበኛ በአጭር ጊዜ ውስጥ አተረፍኩኝ። ቤቱም ትልቅ እንጨት ቤት ሆነ። በየሳምንቱ እቃ ሳይወጣ አልፎ አያውቅም። በቃ በቤቱ ላይም ትዕዛዝ እየበዛ መጣ። መተኛት ማረፍ የሚባል ነገር እየረሳን መጣን። የማይታመን ትርፍ ማትረፍ ጀመርን። ማታ፣ ቀን፣ ሁሌም ነበር የምንሰራው። በቃ ለካ ችግርም ሲበዛ ለአንድ ነገር ነው። ፈጣሪ በካሳ መለሰልኝ። ስሜም በትልቁ ታፔላ "ጆን ፈርኒቸር፤ የቤትና የቢሮ እቃዎች ማምረቻና መሸጫ" ተብሎ በትልቁ ይፋ ሆኖ ወጣ። የተረጋጋ ህይወት፣ የተረጋጋ ኑሮ ፈጣሪ ሰጠኝ። ከፈጣሪ በታችም ማመስገን የምፈልገው ሰዎች አሉ። በቃ ለልብስ፣ ለምግብ፣ ለምዝናናው፣ ለምንም ተጨንቄ አላውቅም። ሳልሰለች ለዘጠኝ ወራት ያህል ከዋናው ባለሙያ ተለይቼ አላውቅም። በጣም ያሳየኛል፤ በጣም ያስለምደኛል። በቃ ሁሌም ይመክረኛል "ያኔ እኔ ጥዬህ የሄድኩ ቀን ሰውን መለመን የለብህም፣ እራስህን ችለህ መስራት መቻል አለብህ፣ ከእኔ እጥፍ መስራት አለብህ" ብሎ ይመክረኛል።

ከቆይታ በኋላም ብቻዬን መስራት ጀመርኩኝ። ዛሬ ላይ ፈጣሪ ይመስገን የሚያቅተኝ ዲዛይን የለም፤ ሁሉንም ስራ እራሴን ችዬ እሰራለሁኝ። ስራ ሲበዛ ብቻ ነው ሌሎች ሰራተኞችን የምጠራው። እራሴን ችዬ ፈጣሪ ይመስገን እየሰራሁ እገኛለሁ። የዚህ ሁሉ መነሻ ፈጣሪ ነው። ከፈጣሪ በታች ደግሞ ለአለም አቀፍ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ትልቅ ምስጋና አለኝ። በሀሳብ ደረጃ የረዱኝ ብዙ ሰዎች አሉ። ለእነርሱም ትልቅ ምስጋና አለኝ። በዚህ ቦታ ላይ እንድደርስ የረዱኝ ወንድሞቼን እህቶቼን ከልብ አመሰግናለሁ።

ስለሁሉም ነገር ፈጣሪ ይመስገን። ከፈጣሪ በታች ሰው ለሰው መድሃኒት ነው። መነሻዬ ትንሽ ቢሆንም መጨረሻዬ ትልቅ ይሆናል። ቃሉም “ለነገ ጅማሬህ ትንሽ ቢሆንም ፍፃሜህ እጅግ ይበዛል” ይላል። ዛሬ ላይ ለሰራተኞች መተዳደርያ ሆኛለሁ፤ ለሰባት ሰው የስራ በር መሆን ማለት ለእኔ ትልቅ ነገር ነው። ሰው ስራ ሲያጣ ይሰርቃል፣ አላስፈላጊ ሱስ ውስጥ ይወድቃል። ፈጣሪ የወደፊት ህልሜን ካሳካልኝ፣ በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰራተኞችን የያዘ ትልቅ ድርጅት (Company) ይኖረኛል። ይህን የሰጠ ፈጣሪ ያንንም ይሰጣል። በህይወትህ መቼም ቢሆን ተስፋ አትቁረጥ! ተስፋችን ሲቆም ጉሮሯችን ይደርቃል። ተስፋ ስናደርግ ግን በባዶም ቦታ ልምላሜ ይታየናል። ከፈጣሪ በታች እንቅስቃሴአችንን በራሳችን ላይ እናቁም። የመፍትሄ ሰው ለመሆን መጣር አለብን ብዬ ነው የማምነው። በፍጹም ተስፋ አንቁረጥ።



ይህ መፅሀፍ የሚዳስሰው የዮናስ ታደሰን የህይወት ታሪክ ሲሆን፤ የሚያተኩረው የፍልሰት አጋጣሚዎቹ እና የፍቅር ህይወቱ ላይ ነው። ዮናስ በደቡብ አፍሪካ በሚገኙት ወንድሞቹ ጥሪ መሰረት፣ ከሚኖርበት ሆሳዕና ከተማ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለመፍለስ ኬንያን አልፎ ታንዛንያ ላይ በተያዘበት የሶስት አመት እስር ቆይታው ላይ የፃፈው ማስታወሻ ነው። በዚህ መፅሀፍ የፀሀፊው የህይወት ውጣ እና ውረድ በተለይም በፍልሰት ላይ እና በእስር ቆይታው ያሳለፋቸውን መከራዎች እንዲሁም የፍቅር ትዝታውን በሰፊ ያሳያል። በአሁኑ ጊዜ ዮናስ ወደ ሀገር ቤት ተመልሶ፣ የእንጨት ስራ (furniture) ላይ ተሰማርቶ፣ ለሌሎች ሰዎችም የስራ እድል ፈጥሮ ህይወቱን በሆሳዕና ላይ እየመራ ይገኛል።

This work has been funded by the UKRI Global Challenges Research Fund (GCRF) [Grant Reference: ES/S0074/15/1]